
ኡኡታዬ
በ ብሩክ ማሞ

# ኡኡታዬ



**አዘጋጅ** - ብሩክ ማሞ

**የሽፋን ስዕል እና ግራፊክስ ዲዛይን** - ተመስገን ማሞ

** ማንኛዉም በኩላሊት ህመም ምክንያት ዲያሊስስ የሚያደርግ ታካሚ ወይንም ለኩላሊት ንቅለ ተከላ ገንዘብ የሚያስፈልገዉ ሰዉ የመፅሀፉን አዘጋጅ ፈቃድ በመጠየቅ ይሄንን መፅሀፍ ማሳተም እና የሚያገኘዉን ገቢ ሙሉ ለሙሉ ለሚያስፈልገዉ የህክምና ወጪ መሸፈኛነት መጠቀም ይችላል፡፡ ከዚህ ዉጪ ሲያሳትም እና ሲያከፋፍል የተገኘ ሰዉ ግን በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ የደራሲዉ መብት በህግ የተጠበቀ ነዉ፡፡

© ኡኡታዬ

**የመጀመሪያ እትም 2013 ዓ.ም**

ዌብሳይት - www.uutaye.com ኢሜይል – biruk.bm17@gmail.com ቴሌ-ግራም - @uutaye

# መታሰቢያነቱ

መታሰቢያነቱ ለማከብረህ እና ሁሌም ከህሊናዬ ለማትጠፋዉ ፤ የታናሽ ታላቄ ሶፎኒያስ ደረጀ (ሶፊ) ይሁንልኝ ፡፡ ሶፊ የልብህን ትርታ አውቃለሁ እና በአካል ባትኖርም በመንፈስ ግን ለዘላለም ከእኔ ጋር ትኖራለህ ፡፡

“ ከአክባሪህ ”

# ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ዉድ ፈጣሪ ቅዱስ እግዚዓብሔር ከእነ እናቱ ድንግል ማርያም ክብር እና ምስጋናዬ ይድረሳቸዉ፡፡ በመቀጠልም እዉነትን ላስተማርከኝ ሀቀኛዉ አባቴ መምህር ማሞ ሻረዉ ፣ የእናቶች ምሳሌ የሆንሽዉ ሁሉም የሚወድሽ እናቴ መምህርት አይናለም ገብሬ፣ ጓደኛዬም ወንድሜም የመፅሀፉ ግራፊክስ ዲዛይነርም ለሆንከዉ የዛሬዉ ብላቴና የነገዉ ዶ/ር ተሜ ፣ ታዳጊዉ ቢኒ ፣ ጣፋጯ ሚጣዬ ፣ ወንድሜ አቡ ፣ ታላቅ ወንድሜ ለሆንክልኝ አቤ እና ባለቤትህ ፀዲሻ ሁሌም ከጎኔ ስለሆናችሁ እግዚአብሄር ዉለታችሁን ይክፈልልኝ፡፡

መፅሀፉን በድምፅ ቅጂ ያዘጋጀህልኝ ፤ የተለየ እና የራስህ የሂወት ጎዳና ያለህ ፤ የምኮራብህ ልዩ ጓደኛዬ ድምፀ መረዋዉ ዴቫ (ጋዜጠኛ ዳዊት ተወልደ) ስለቅንነትህ ከልቤ አመሰግንሀለሁ፡፡

ሁሌም ለምትደግፉኝ አብሮአደግ ወንድሞቼ ዳኒ እና ፍቄ እንዲሁም ያለ እድሜያችሁ በሳል የሆናችሁ ፅሁፎቼን ለገመገማችሁልኝ ፤ አስተያየት ለሰጣችሁኝ እና ከአጠገቤ ሆናችሁ ለረዳችሁኝ ኢንጂነር ብሩክ ፈቃደ (ጢቆሻ) ፣ ኢንጂነር እንድሪያስ የሺድንበር (እንድሪ) ፣ ኢንጂነር ሀና በቀለ (ሀኒሻ) ፣ ኢንጂነር ዳዊት ተገኝ (ቢኪ) ፣ ገብረኤላ አለማየሁ (ዶ/ር ጋቢ) ፣ አርክቴክት በረከት ደባይ (ቤክ) ፣ ሌክቸረር እያሱ ሺፈራዉ ፣ ኢንጂነር ብስራተገብርኤል ፍስሀ (ብስሬ) እና ጋዜጠኛ ነፃነት ከበደ (ነፂ) ሁላችሁም የጀርባዬ አጥንት ናችሁ ፤ ይሄ መፅሀፍ የእናንተ መሆኑን እንዳትረሱ፡፡

በአጠቃላይ ለእኔ ሁሉ ነገሬ ለሆናችሁ የእዉቀት እናት እና አባቶቼ ፣ ዘመዶቼ ፣ ጓደኞቼ ፣ የኩራዝ-ቴክ ቤተሰቦች እንዲሁም ለስራዬ መሳካት የበኩላችሁን ለተወጣችሁ ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነዉ፡፡

" ላንተም/ቺም ስላነበብህ/ሽ አመሰግናለሁ ! "

# መግቢያ

በእለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቼ የገጠሙኝን ነገሮች ከእራሴ ጋር ማዉራት እወዳለዉ ፤ ለዚህም ምርጫዬ ሀሳቤን በቅርቤ ላለችዉ ለወረቀቴ በፅሁፍ ሹክ ማለት ነዉ፡፡ የተለያዩ ፅሁፎቼን በተለያዬ ግዜ ያነበቡ ወዳጆቼ ፅሁፎችን ለሌሎችም ባቀርባቸዉ የተሻለ እንደሆነ በጎተጎቱኝ መሰረት እኔም አስተያየታቸዉን ተቀብዬ ይሄዉ ከፈጣሪ ጋር በመሆን ዛሬ ለዚህ አብቅቼያቸዋለሁ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ላይ እኔ የሶፍትዌር ኢንጂኒየር እንጂ ፀሀፊ አይደለሁም፡፡ ነገር ግን በማህበረሰቡ ዉስጥ የማያቸዉን ማህበራዊ ክፈተቶች እና የተለያዩ ነገሮችን እንዳላዩ እና እንዳልሰማ ሆኖ ከማለፍ ይልቅ አዝናኝ እና አስተማሪ በሆነ መንገድ በመጠቆም ክፍተቶቹ እንዲሞሉ የማድረግ ህሊናዊ ጥያቄ ስላለብኝ እግረመንገዴን ይሄንንም ጥያቄ ለመመለስ ነዉ እነዚህን ፅሁፎች ያቀረብኳቸዉ፡፡

አንዳንድ ፅሁፎቼ ሀገራዊ መልዕክት ስለያዙ ፖለቲካዊ ይዘት እንዳላቸዉ አስተያየት የሰጡኝ ሰዎች አሉ፡፡ ሰዉ ሲኖር ያለ አቋም አይኖርምና የራሴ የምለዉ አቋም ይኖረኛል ነገር ግን ፖለቲከኛ የመሆን ፍላጎቱም ሆነ ችሎታዉም የለኝም፡፡ ፅሁፎቹንም የፃፍኩት እንደዜጋ ለሀገሬ ካለኝ ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ምናልባት ያለዉን ልዩነት አጥብቤ ጥቂት ሰዎችን እንኳን ወደ አንድነት ባመጣ በሚል ተስፍ ብቻ እና ብቻ ነዉ፡፡

አብዛኞቹ ፅሁፎች የወቀሳ አይነት ባህሪ ይታይባቸዋል፡፡ ይሄም ካለፍናቸዉ ስህተቶች ተምረን ነገን ብሩህ በማድረግ ራሳችንን ከታሪክ ተጠያቂነት ነፃ እንድናደርግ ቅን ከማሰብ የተነሳ መሆኑን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡

ፅሁፎቼ ጥልቅ ትንታኔ ከመስጠት ይልቅ እንደ ሀገር ፣ ሰነልቦና ፣ ቴክኖሎጂ በመሳሰሉ ጉዳዩች ላይ የወፍ በረር እይታ ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህም እነዚህን ፅሁፎች በመንተራስ ሌሎች መፅሀፍቶችን መቃረም የተሻለ እዉቀት ያስገኛል፡፡

የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ እንዳይሆን የመጀመሪያዬ እንደመሆኑ መጠን ያልበሰለ ጥሬ ካገኛችሁ ከመዋጣችሁ በፊት ወይ ማብሰል ፣ ወይ ማድቀቅ ፣ ካልሆነ ደግሞ መትፋት እንዳትረሱ፡፡

" ለሚያነበንቡ ሳይሆን ለሚያነቡ ብቻ የተፃፈ ! "

# የገፅ ማዉጫ

1. ሀገር ........ 6
1.1 ሎሬት ........ 7
1.2 ኢትዮጵያ (ዩቶጵያ) ........ 12
1.3 ሰሜን ኮርያ vs ኢትዮጵያ ........ 16
1.4 የቦይ ዉሀ ........ 20
1.5 የወንዜ ልጅ ........ 23
1.6 እኛ ስንዋደድ ........ 25
2. ቴክኖሎጂ ........ 27
2.1 አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ........ 28
2.2 የሳይበሩ ሩጫ ........ 32
2.3 የዘንድሮ ቢዝነስ ........ 38
3. ስነ-ልቦና ........ 44
3.1 አስናቀ እና ታየር ........ 45
3.2 መክሊት ........ 48
3.3 ሚስጥረ ስኬት ........ 51
3.4 የስራ ባህላችን ........ 56
3.5 ወንበር ወደ እሾህ ........ 59
4. ከወግ መንደር ........ 63
4.1 ሶፍትዌር መሀንዲሱ ........ 64
4.2 እዚህ እና እዛ ........ 67
4.3 ግርምተ - ስም ........ 70
4.4 ሁላችንም ሌቦች ........ 73
4.5 የፈሪ ፈሪ ........ 76
5. ትኩረት ........ 80
5.1 የቀለም እናት - የቀለም አባት ........ 81
5.2 መንዝ ጓሳ ........ 86
5.3 ነገረ ዩኒቨርሲቲ ........ 89
5.4 ሳይቃጠል በቅጠል ........ 93
6. ግርምት ........ 96
6.1 ባለ 638 ነፍስ ........ 97

6.2 የኮንትራት ኑሮ .......... 100
6.3 ሂወት IN THE አአሳቴዩ .......... 103
7. ቅምሻ .......... 109
7.1 ከራዲዮኔ .......... 110
7.2 ልናገረዉማ .......... 112
7.3 የህልሜ ኑዛዜ .......... 113
7.4 እቱ ተሳስቼ .......... 114
7.5 መች እጠላሻለሁ .......... 115
7.6 ሳናዉቅ አዉቀንልሽ .......... 116
7.7 አየዋለሁኝ .......... 117
7.8 ከመምጣት አልቀርም .......... 118
7.9 ካሽካከምህ .......... 120
7.10 በግማሽ ልደመር .......... 121
7.11 ይድረስ ለአፍሪካ ፖለቲካ .......... 123
7.12 ድግሱ .......... 124
7.13 ድብብቆሽ .......... 125

# 1. ሀገር

“ ዉብ ሀገሬ ፤ ዉብ ሀገሬ ፤ ዉብ ሀገሬ

ባንቺ እኮ ነዉ ፤ መከበሬ መከበሬ

.

.

.

እናት አባት ሲሞት ፤ በሀገር ይለቀሳል

ሀገር የሞተ እንደሁ ፤ ወዴት ይደረሳል፡፡ ”




“ በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! ”

# 1.1 ሎሬት



** ሎሬት በተለይም በስነ-ጥበቡ ዘርፍ ጥቂቶች እንደ ታላቁ የስነ ፅሁፍ ሊቅ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን እና ታላቁ ሰዓሊ የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ አይነት ታላቅ ስራ የሰሩ እና ሀገራቸዉን ያስጠሩ ባሙያዎች የሚያገኙት ፤ እንኳን አግኝተዉት ሲሰሙት እንኳን ለጆሮ ደስ የሚል የማዕረግ መጠሪያ ስም ነዉ፡፡ ብዙ ያልተለመደ እፁብ ማዕረግ ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ ባለዉ ፅሁፍ ዉስጥ እንደ አጠቃላይ የማዕረግ መጠሪያነት ተጠቅሜዋለሁ፡፡

እስኪ ትንሽ ደቂቃዎች ቆም ብለን እንመልከት-

አንዷት ወፍ እንቁላሏን ሰንጥቃ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ መንቆሯ ጠንክሮ ራሷን ችላ እስከምትመገብ ድረስ እናትዋ ናት የምትመግባት ፤ እናትየዋ ምግቡ ያለበት ርቀት ተጉዛ ለእራሷ ሳያጓጓት ምራቋን እየዋጠች ይዛ መጥታ እሷ ባዶ ሆዷን ሆና ለጫጭቷ ትመግባታለች፡፡

ኦራንጉታን የተባለችዉ የዝንጀሮ ዝርያ እናት ሁሉ ነገሯን ትታ ለ9 ዓመታት ያህል ከልጇ ሳትርቅ ራሱን እንዴት መመገብ እንዳለበት በተጨማሪም ከአደጋ ራሱን እንዴት መጠበቅ እንዳለበት ታስተምረዋለች ፡፡ ለአንድ ታዳጊ ኦራንጉታ እናቱ ከእናትነት በተጨማሪ ዓለሙ ፣ ጓደኛዉ ፣ የመዝናኛ ቲቪ ቻናሉ ፣ የትምህርት ቤት መምህርቱ ናት፡፡

ኦክቶፐስ የተባለችዉ የባህር ዉስጥ አሳ ዝርያ አንዷት እናት ልጆችን ለመዉለድ እና ለማሳደግ ከባድ መሰዋዕትነትን ትከፍላለች፡፡ እጅግ ብዙ ምናልባትም በሺዎች የሚቆጠሩ እንቁላሎችን ትጥላለች ከዚያም እንቁላሎች ወደ ኦክቶፐስነት ተቀይረዉ ልጅ እስኪሆኑ ለዓመታት (እስከ 4 ዓመት ሊፈጅ ይችላል) ስትንከባከብ እና ስትጠብቅ ትቆያለች፡፡ በነዚህ ጊዜያት እንቁላሎቿ ከሌላ አጥፊዎች ጥቃት እንዳይደርስባቸዉ ስትል አካባቢያዋን ለቃ አትሄድም ፤ በዚህም ለረጅም ጊዜያት ምግብ እንኳን መመገብ ሳትችል ትቀራለች፡፡

አንዷት ዝሆን ልጇን ለመገላገል 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ማርገዝ ይኖርባታል፡፡ የተለያዩ ጥቃቶች በሚፈፀሙበት ወቅት ዝሆኖች ከራሳቸዉ በላይ ልጆቻቸዉን ይጠብቃሉ፡፡ እናቱን ሳይገድሉ የዝሆንን ልጅ ለማግኘት ማሰብ የዋህነት ነዉ፡፡ ሌላዉ አስገራሚ ነገር አንዳንድ ጊዜ የሌላ መንጋ ዝሆን እናቱ ሳታዉቅ ልጇን ሊሰርቃት ይችላል የዚህን ጊዜ እናቲቱ ያለችበት መንጋ ከሌባዉ መንጋ ጋር አስፈላጊዉን ፍልሚያ አድርጎ ልጇን በእቅፉ ያስገባላታል፡፡

ዶሮ እንቁላሏን የታቀፈች ሰሞን ነገረ ስራዋ ሁሉ ይለዋወጣል፡፡ ለማዳ የነበረችን ዶሮ እጅግ ቁጡ ከመሆነኗ የተነሳ ማንንም አታስጠጋም በአማካይ 21 ቀናት እና ሌሊቶችን ሳትነሳ የተፈጥሮ ሙቀት ከሰጠች በኋላ ጫጩቶቿ እንቁላላቸዉን እየሰነጠቁ ብቅ ይላሉ፡፡ ከተፈለፈሉበት ቀን ጀምሮ ራሳቸዉን ችለዉ እስኪንቀሳቀሱ ምንም እንኳን ቁጥራቸዉ ቢበዛም ከእቅፏ አትለያቸዉም ፤ ማንም ሊነካቸዉም አይችልም፡፡ የመጣዉን ሁሉ በቻለችዉ መጠን በንክሻ እያነቆረች ትመልሰዋለች፡፡ አንዳንዴም ጭልፊት ከሞጨለፋት ልጇን ለማስጣል የቻለችዉን ያህል ስትከንፍ በመጨረሻም መብረር ተስኗት አቅም አጥታ ልጇ የጭልፊት ሲሳይ መሆኑን አይታ ቅስሟ ተሰብሮ ስትቆም ላያት እናትነት ይገለፅለታል፡፡

ዝንጀሮ በተለይ ወንድ ልጅ ከወለደች እናም ካደገ በኋላ አባትዬዉ ለወደፊት ሲያድግ ሚስቶቼን እንዳይሻማኝ በማለት የገዛ ልጁን ለማጥፋት ይሯሯጣል ፤ እሷም ልጇን ከሞት ለማትረፍ በየቁጥቋጦዉ ፤ በየስርቻዉ እና በየገደላ ገደሉ እየተንጠላጠለች ህይወቱን ሽሽጋ ትታደገዋለች ፡፡

ጎሽ የምትኖርበት አካባቢ በአብዛኛዉ ሳር የሚበዛበት እና የተለያዩ ጎሾችን አድነዉ የሚመገቡ እንደ አቦሸማኔ አይነት አደገኛ እና አስፈሪ እንስሶች የሚገኙበት ስፍራ ነዉ፡፡ ኮሽ ባለ ቁጥር ሁሌም የእሷም ቀልብ አብሮ እንደባተተ ነዉ፡፡ ምድረ ጎሽ ነፍሱን ለማትረፍ እግሬ አዉጪኝ ብሎ በሚፈረጥጥበት ጊዜ እናት ጎሽ ግን ለልጇ ስትል የቁም ስቃይን ትከናነባለች ፤ ራሷንም ለሞት ታጋልጣለች፡፡

እናትነት የሰዎች ብቻ ሳይሆን ለእንሰሳትም ከፈጣሪ የተቸራቸዉ እጅግ አስገራሚ ደመ-ነፍሳዊ ስሜት ነዉ፡፡ ዉድ እናታችን ዘጠኝ ወር ሙሉ የበላችዉን አብልታ የጠጣችዉን አጠጥታ ፤ ደሟን አጋርታ ፤ በህፃንነት አደጋ እንዳይደርስብን ተጠንቅቃ ፤ እኛን ለማሳደግ እሳት እየጠበሳት እንጀራ ጋግራ ፤ እጇ እስኪሰነጠቅ ልብስ አጥባ ፤ ቀን ከሌት እንቅልፍ ሳያምራት ፤ ለእኛ ስትል ስትባዝን አማላይ ዉበቷን አርግፋ እሷ እሷነቷን አጥታ እኛ ሰዉ ሆነናል ፡፡ ያለምክንያት እይደለም “ ማን እንደ እናት ” የሚባለዉ ፤ ክብር ለእናቶቻችን ይሁንና፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ የሁላችንም እናት፤ የእናቶቻችንም እናት ዉድ ሀገር ኢትዮጵያ ፤ ማን እንደ እሷ፡፡

ከላይ የጠቀስናቸዉ እንሰሳት የሚያመሳስላቸዉ አንድ ነገር አለ እሱም ልጆቻቸዉ ሁሉ ለእናቶቻቸዉ ዉለታ ቢስ መሆናቸዉ ነዉ፡፡ እናቱ ቁምስቅሏን አይታ ያሳደገችዉ ዝንጀሮ ፣ አዉራ ዶሮ ፣ አራንጉታ ፣ ጎሽ .... ቀኑ ሲደርስ እናቱን ጥሏት ወደ አዲስ ሚስቱ ይኮበልላል፡፡ ከዚህ በኋላ እናቱ ትኑር ትሙት ለእርሱ ጉዳዩ አይደለም ፤ የእናቱን ዉለታ ጊዜያዊ ሁኔታ እና ጥቅም አይኑን ይጋርደዋል፡፡ የእናቱን መስዋዕትነት መገንዘብ ይሳነዋል፡፡ ራሱን ትላንት ሁሉ ነገሩ ከሆነችለት እናቱ በገዛ ፈቃዱ እና ስሜቱ ተገፋፍቶ ለማያዉቃት ዛሬ ወዳገኛት ሚስቱ አሳልፎ ይሸጣል፡፡

የእኛም አብዛኞቹ ሰዉ ልጆች ነገር ከላይ እንዳየናቸዉ እንሰሳት ነዉ፡፡ የሰዉ እጅ እያየች በየአለም መድረኩ ብድር ጠይቃ እየተበደረች ያስተማረችን ይቺ የሀብታም ድሀ ሀገር ዉለታዋን እየከፈልናት ነዉ ወይንስ እንደ ዝንጀሮዉ ቦለዴ ጥለናት እየኮበለልን ነዉ ? ያስተማረችን ሀገር ችግሯ እና መና መቅረቷ ሳይታየን እንደ ቢሮክራሲዎችን ያሉ ሰበቦችን እየቆረጥን ዛሬ ብር ላሳየችን አሜሪካ እንሰግድላታለን ፤ ጭንቅላታችንንም እንመዘብርላታለን፡፡ እናት ምንም ቢሆን እናት ናት ፤ ቢሮክራሲዉ አላፈላፍን ቢል  ማነቆዉ ቢበዛ ፤ አምጣ የወለደችዉ ልጇ ነዉ ገመናዋን ሊሸፍንላት የሚችለዉ፡፡

ምንም እንኳን በአደባባይ ካባ ያጠለቁ እና መጠሪያዉቸም የሆነ ጥቂት ሎሬቶች ቢኖሩንም ፤ እያዳንዳችን በልቦናችን ዉስጥ ለእናት ሀገራችን ባለ ዉለታ የሆኑ በጣም ብዙ ሎሬቶችን ሾመናል፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ የእዉቀት አባቶች እና እናቶች መምህሮቻችን ፣ ሚስጥራዊ አባቶች ፣ ሀገር ገንቢ ኢንጅነሮች ፣ የጥበብ ባለሙያዎች ፣ ፈዋሽ የህክምና ዶክተሮች ፣ ሀገራችዉን

የሚያስጠሩ አትሌቶች ፣ የማንዘነጋቸዉ ሙዚቀኞች ፣ ጀግኖች የሀገር ሰላም አስከባሪዎች ፣ እዉነተኛ ፀሀፊዎች እና ጋዜጠኞች ፣ ጠንካራ መሪዎቻችን ይገኙበታል፡፡

ሎሬቶቻችን የተሾሙበት ሚስጢር ለቆሙበት ዓለማ ስለታገሉ ፤ በተሰማሩበት ዘርፍ ዉጤታማ ስለሆኑ እናታቸዉንም በቀና ስላስጠሩ ፤ በገቡበት ጠባብ ቀዳዳ ተፈትነዉ ወጥተዉ ብርሀን ፈንጥቀዉ አርዓያ ስለሆኑን ፤ ብዙዎች የወደቁበትን ተራራ ስለወጡ ፤ የእናታቸዉንም ገመና ስለሸፈኑ ነዉ፡፡፡ እንደዚህ ሲሆን ነገሩ እናታችንም በእኛ ትደሰትብናለች ፤ አምላክም የልብ ፀሎታችንን ይሰማናል ፤ ሌሎችም የተጋረደባቸዉ ሀቅ ይገለጥላቸዋል፡፡

በእርግጥ እኔ እንደማስበዉ “አንድ ሰዉ ሎሬትነቱን ለማስጠበቅ ወይም ለእናት ሀገሩ ምላሽ ለመስጠት ግዴታ ሀገሩ ዉስጥ ብቻ መሆን አይኖርበትም ፤ በሌላ ባዕድ ሀገር ሊሆን ይችላል ፤ በተጨማሪም እዉቀቱን ለማሳደግ ባህር ማዶ ሊሻገር ይችላል ፤ ነገር ግን መጀመሪያ አለበለዚያም ዘግይቶም ቢሆን ለሀገሬ ለዉለታዋ ምን አበርክቸላታለሁ? የሚለዉን የህሊና ጥያቄ ሊመለስ ይገባዋል” ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ተነባቢ ከሆኑ እና ቁም ነገር ካላቸዉ መፅሀፎች አንዱ በዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ የተፃፈዉ ዝጎራ ነዉ፡ ፤ የሰዉ ፅሁፍ በሰፊዉ ማስቀመጥ ተገቢ ባይሆንም ይሄንን ፅሁፍ ያነበበ ሰዉ ሁሉ ተመልሶ ዝጎራን ተያይዞም ከእሱ በፊት የተፃፈዉን እመጓ እንዲያነበዉ ለመጋበዝ ያህል ነዉ፡፡ እናም ከመፅሀፉ ዉስጥ ልቤ ላይ ተሰንቅረዉ ከቀሩ መልዕክቶች ዉስጥ አንዱ እንዲህ ይላል ፡፡ ዝጎራ ገፅ 73

**ኢትዮጵያ ቁስሏን በጨው አጥቦ ፤ ዘይት ቀብቶ ፤ በንፁህ ሻሽ የሚያስርላት እንጂ ሃገር ማዶ ሆኖ በትዉልዱና በደሙ ብቻ ያዉም ወረቀት ላይ የማይሰፍር ማስተዋወቅ ብዙ ይጠቅማታል ብዬ አላምንም ፡፡ ኢትዮጵያዉያን እና ትዉልደ ኢትጲያዉያን በባዕድ ሀገር ሄደዉ በስኬታቸዉ ለባዕዳን በረከት አምጥተዉ ስማቸዉ ከገነነዉ ይልቅ ኦስትሮ-ጀርመናዊ ካርል ሃይዘን የተደላደለ ኑሮዉን እና ዝናዉን ረግጦ “ መርሀቤቴን ” ቤቴ ብሎ ዘሎ የገባ ፤ የጀማ ወንዝ ላይ የብረት ድልድይ የዘረጋዉ ለኢትዮጵያ የቁም ነገር ልጅ ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ያለ እድሜ ጋብቻ በፈጠረዉ ቀዉስ በወሊድ ተጎድተዉ ሽንታቸዉን መቆጣጠር ተስኗቸዉ “ ከረፋችሁ ” ተብለዉ የተገፉ በሺኅ የሚቆጠሩ ሴቶችን ህይወት ለመቀየር የምዕራቡን ዓለም ትተዉ የቀረዉን ዘመናቸዉን ለዚች ዉብ ሀገር ኢትዮጵያ ያበረከቱት ጥንዶች ዶ/ር ሃምሊንና ባለቤቱ ለኢትዮጵያ የበለጠ ይቀርቧታል፡፡ የጎንደሩ የቀዶ ጥገና ሀኪም ዶ/ር በርናድ አንደርሰንን ታዉቀዉ የለም ኢትዮጵያዊት ሚስቱን “ሀገርሽ ሀገሬ ህዝብሽ ህዝቤ” ብሎ የትዉልድ ሀገሩን ጃማይካን ፤ የእንጀራ ሀገሩን አሜሪካ ትቶ ጎንደር የከተመ ፤ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ህዝቡን ያገለገለ ፤ ብዙ ኢትዮጵያዉያን በሙያ በምግባርም የወለደ እርሱ ነዉ ኢትዮጵያን ከልብ የወደዳት፡፡ በአንድ ወቅት አንዲት እናት ከደዌአቸዉ ስለፈወሳቸዉ ፤ ከስቃይ ስለገላገላቸዉ ተደስተዉ የተባረኩትን የሙያ እጆቹን ስመዉ ሲያበቁ መቀነታቸዉን ፈትተዉ ዐስር ብር አወጡና “ በል በዚህ ምሳህን ብላ ” ይሉታል፡፡ታላቁ ሰዉ ዶ/ር በርናንድ በምሳ ሰዓት ከቤቱ ደዉሎ ለምሳ ቤቱ እንደማይሄድ አስታወቀ፡፡ የዐስር ብር ምሳ ሊገኝበት ከሚችልበት ሰፍራ ከቀን ሰራተኞች ምግብ ቤት ሄዶ ክብሩንና ማዕረጉን ረስቶ የዐስር ብር ምሳ በላ፡፡**

እዉነት ለመናገር ፅሁፉን ሳነበዉ ምን ያህል ከዉስጤ እንደወረረኝ እኔ ነኝ የማዉቀዉ ፤ ይቺ ሀገር በድህነት አቅሟ እሽሩሩ ብላ ታቅፋ ፤ ዉሀዋን አጠጥታ ፤ አየሯን እና አፈሯን መግባ ካስተማረችንን እና ሎሬታችንን ከሰጠችን በኋላ ስንቶቻችንን ነን ዉለታዋን የምንመልስላት ስንቶቻችንስ ነን የበላንበትን ወጪት ሰባሪ ሆነን የምንቀርስ ? ዞር ብለን ልናስብበት ይገባል እየተንከባከበ ያሳደገን እና ሎሬታችንን የሰጠን ይህ ማህበረሰብ አመድ አፋሽ መሆን የለበትም ፤ ጳዉሎስ ህክምና

ተምረን ለሀገራችን ምንም ሳናበረከት የችካንን በሽተኛ የምንፈዉስ ከሆነ ፤ አዲስ አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ተምረን የሀገራችንን ዉለታ ሳንመልስ የማይክሮሶፍት ቅጥረኛ ብንሆን ህይወታችን ትርጉም አልባ ፤ በገንዘብ እንጂ በሀገር ፍቅር ያልተሞላ ልክ እንደ ባዶ ቆርቆሮ የሚንኳኳ ወና ህይወት ነዉ የሚሆንብን፡፡

በአንድ ወቅት ያነበብኩት አንድ አስገራሚ መረጃ እንዲህ ይላል በመላዉ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ኢትዮጵያዉያን የህክምና ስፔሻሊስት ዶክተሮች ይልቅ በአሜሪካ ችካን ስቴት የሚኖሩ ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን የህክምና ስፔሻሊስት ዶክተሮች በቁጥር ይበልጣሉ፡፡ አብዛኞቹ የሄዱት የተሻለ ኑሮ እና እንጀራ ፍለጋ መሆኑ ባያወላዳም ፤ የተሻለ ነገር ካገኙ በኋላ ተመልሰዉ የሀገራቸዉን እከክ የሚያከኩ እንባ አባሽ ሎሬቶች ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸዉ፡፡

በአሁኑ ግዜ በሀገራችን ካለዉ ነባራዊ በተለይ አብዛኞቻችን በድናችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ቢሆንም ልባችን ፤ ቀልባችን እና አመለካከታችን ከባህር ማዶ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ እንዲያም ቢሆን የዛሬ ዓላሚዎች የነገ ሎሬቶች የሆኑ ልባሞች አይጠፉም ፤ አንድ የትምህርት እድል አግኝታ ከባህር ማዶ ትምህርቷን የምትከታተል እጅግ ጎበዝ ጓደኛዬ ጋር እየተጫዋወትን ለምን ባህር ተሻግራ ለመማር ልቧ እንደሸፈተ እና ስለ ነገስ ምን እንደምታስብ ጠይቅኳት፡፡ የሰጠችኝ ምላሽ ከብዙዎች በተቃራኒ እና ያልጠበቅኩት ነበር፡፡ ቃል በቃል “ አየህ እኔ ለሀገሬ ንብ ነኝ ፤ ከሀገሬም ርቄ የወጣሁበት ምክንያት ለማር መስሪያ የሚዉል መልካም አበባ ፈልጌ ለመቅሰም ብቻ እና ብቻ ነዉ ፤ ማሩን መስራት እና መጋገር የምፈልገዉ ግን ለዉድ የሀገሬ ልጆች በሀገሬ ነዉ ፡፡ ” ስትል ነበር የትንሽ ትልቅ በሳል ምላሽ የሰጠችኝ፡፡ አምናለሁ ነገ ለሀገሯ ሎሬቷ ሆና ገመናዋን እንደምትሸፍንላት፡፡

በእኛ ሀገር ደረጃ ሎሬት አሰጣጣችን ላይ ብዙ ጊዜ ክፍተት ይታይብናል ፤ እንደ ሰለጠነዉ አለም ለሎሬቶቻችን በህይወት እያሉ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ፤ ለየት ያሉ ክብሮችን ከማጎናፀፍ እና እነርሱን ከመደገፍ ይልቅ ከሞቱ በኋላ በየሚዲያዉ ማናፈስ ፤ እጅብ ብሎ ወጥቶ መቅበር ፤ በአበባ መቃብራቸዉን ማሽቆጥቆጥ ይቀናናል ፡፡ ይሄንን ነገር ልናርመዉ እና ሎሬቶቻችንን በዚህ ምድር ላይ እያሉ ልናገናቸዉ እና ልናከብራቸዉ ለሌሎቹም ታዳጊዎች ዓርዓያ ልናደርጋቸዉ ይገባል፡፡

በሀገራችን ታሪክ ዉስጥ ብዙ ለሀገራቸዉ ጥሩ የሰሩ ባለዉለታዎቻችንን ሎሬታቸዉን ሰጥተናቸዋል እየሰጠንም እንቀጥላለን ፤ በዛዉ ልክም በስራቸዉ ምክንያት በአንድ ወቅት የነበራቸዉን ሎሬታቸዉን የነፈግናቸዉ እንዳሉም ወደፊትም የምንነፍጋቸዉ እና የታሪክ ተወቃሽ የምናደርጋቸዉ እንደሚኖሩም ሳይታለም የተፈታ ነዉ፡፡ ህዝብ ሎሬታችንን እንደሚሰጠን ሁሉ በስራችን ምክንያት  መል እንደሚነፍገን ግልፅ ነዉ፡፡ ባንድ ወቅት የሀገራችንን ባንዲራ በዓለም አደባባይ ከፍ አድርገዉ የነበሩ አትሌቶቻችንን አሁን ግን ዜግነታቸዉን ቀይረዉ በሌላ መለያ እና ባንዲራ ሲሮጡ ያ ካባቸዉ የነበረዉ ኢትዮጵያዊነት ከነቀልባቸዉ ርቋቸዋል ፤ ይሄ ነዉ እንግዲህ ሎሬትነትን መነፈግ ማለት፡፡ እዚህ ላደረሰን ህዝብ ዉለታዉን መክፈል ከቻልን ፤ ለእናታችን የብረት መዝጊያ ስንሆን ባለ ሎሬት የማንሆንበት ምንም ምክንያት የለም ምክንያቱም የሚያነግሰን እና የሚያወርደን ስራችን ነዉና፡፡

እያንዳንዳችን እንደ ግለሰብ ስለምናስብላት ድንቅ ሀገር እናት ኢትዮጵያ ከማዉራት ባለፈ ጠብ የሚል አሻራ ማሳረፍ ነዉ የተሻለዉ ነገር፡፡ እኔና እናንተ ሀገራችን ለመርዳት ፖለቲከኛ መሆን አይጠበቅብንም ፤ ነገር ግን በእያለንበት የስራ ዘርፍ የሀገራችንን አንገት ቀና ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ ዉጪ ያለዉ ሀገሬ እወድሻለዉ ፤ ያላንቺ ማን አለኝ ለማንም የማይጠቀም ስንኝ አልባ ግጥም ነዉ፡፡

የብዙነሽን ቀደም ያለ ስራ ማን ይዘነጋል ፤ በእሱ እንለያይ -

የእናት ዉለታዋን ፤ ባወሳ እወዳለሁ

ደግነቷ ብዙ ፤ መሆኑን አዉቃለሁ

ወላጅ እናት እኮ ፤ ፍፁም በመንፈሷ

ልጇን ትወዳለች ፤ አብልጣ ከራሷ

.

.

.

" እናት ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ገና ፤ ገና ለዘላለም ትኖራለች !!! "

# 1.2 ኢትዮጵያ (ዩቶጵያ)



የካ አባዶ የሚባለዉ ኮንዶሚኒየም አካባቢ የገጠመኝ አንድ ነገር መቼም ቢሆን ከህሊናዬ ሊጠፋ አይችልም፡፡ ነገሩ እንዲህ ነዉ ሰዉዬዉ ነጭ ሆኖ በተለምዶ ነጭ ራስታ የምንላቸዉ ሰዎች ገፅታ ያለዉ ሰዉ ነዉ፡፡ ይህ ሰዉ ከባለቤቱ እና ከሁለት ልጆቹ ጋር አብሮ እየተጓዘ ነበር፡፡ አራቱም በሀገራችን ሰንደቅ አላማ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ያሸበረቀ እጅግ ዉብ ኢትዮጵያዊ አለባበስ ለብሰዋል፡፡ ነገር ግን እኔን ያስገረመኝ እና ከሌሎች ሰዎች ልዩ ያደረጋቸዉ የእነርሱ ኢትዮጵያዊ አለባበስ አልነበረም ፡፡ የሚገርመዉ አራቱም ጫማ አላደረጉም በባዶ እግራቸዉ ነበር ያንን የሚያቃጥል የቀትር ፀሀይ የለበለበዉ አስፋልትን ተቋቁመዉ የሚንቀሳቀሱት ምክንያታቸዉ ደግሞ ይቺን ሀይማኖታዊ እና ድንቅ ሀገር አፈሯን በጫማችን አንረግጥም የሚለዉ መሆኑን ሳዉቅ ነበር እጅግ የተደነቅኩት፡፡ በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ማለት እንግዲህ ይሄ ነዉ፡፡ ብዙ ኖሯት ነገር ግን እኛ እርቃኗን ስላስቀረናት እናታችን ልፅፍ የወደድኩት፡፡ አዉቃለሁ ስለ ኢትዮጵያችን ባወራ ግማሹ ሊሰማኝ አይደለም ስሟን ሲጠራ ያቃዠዋል ፤ ሌላዉ ደግሞ ሀገር እና ፖለቲካን መነጣጠል ተስኖት እንደ ፖለቲከኛ እና ዘረኛ ይቆጥረኛል ፤ ልብ ያላቸዉ ልጆቿ ግን ልብ ይሉኛል ፤ ልብ ያላቸዉን ልጆቿን እስካገኝ ጆሮሽን እና ቀልብሽን ለማትነፍጊኝ ወረቀቴ የልቤን ትርታ በእስኪርብቶዬ በኩል ሹክ ልበልሽ፡፡

## <u>ዉዳሴ</u>

እዉነት እልሻለሁ እናት ኢትዮጵያ ፍቅርሽን እና እናትነትሽን ጠጋ ብሎ ላየዉ ልብን የሚያርድ እና የሚያንሰፈስፍ ነዉ ፤ ላንቺ ዉለታሽን መመለስ ከቶ አይታሰብም፡፡ ልጆችሽ ሳናዉቅበት አንቺንም ሳናዉቅሽ እየኖርን ነዉ እንጂ ፈጣሪ በስስት የሚያይሽ የአይኑ ብሌን የምድር ገነት ፤ ነፍስ የዘራብሽ የበኩር ልጁ ነሽ፡፡ ተፈጥሮ ያደለችሽ ያለምንም የአየር ማቀዝቀዣ እና ማሞቂያ የተመቻቸ አየር ያለሽ ፤ የዉሀ ጋን የምትባል የአባይ ምንጭ ፤ የሰዉ ዘር መነሻ የእነ አርዲ እና ድንቅነሽ መገኛ ፤ የኤርታሌ እሳተ ገሞራ መናህሪያ ፤ የዘሩትን የሚያፈራ አፈር ባለቤት ፤ በአጭሩ ፈጣሪ አለምን ሲፈጥር አዳልቷል ቢባል በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የምትቀመጪዉ የኛዋ እንቁ ነሽ፡፡

ኢትዮጵያችን በተፈጥሮ ብቻ አይደለም ህዝቦችሽም የሚያኮራ ባህል ፤ እምነት እና ታሪክ ያላቸዉ ፅኑዎች ናቸዉ፡፡ አንቺ ዉብ ሀገር ሆይ እስላም ከክርስቲያን ተዋዶ እና ተዋልዶ የሚኖርብሽ ምድራዊ ገነት ፤ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ለዘመናት ተከባብረዉ ፣ ተጋብተዉ በመቻቻል እና በፍቅር ሲኖሩብሽ የቆዩ ልዩ ቅድስት ሀገር ፤ ለጥቁሮች የነፃነት ፋና ወጊ እና ጎህ ቀዳጅ የሆኑ ዜጎች ባለቤት ነሽ፡፡

እናት ኢትዮጵያ ፍቅርሽ የተበላሸ ታሪክን ማጥፊያ ላጲስ ፣ በደልን መርሻ ካሳ ፣ የፀብን ግድግዳ መደርመሻ ድማሚት፣ ይቅርታን የሚቸር ለጋስ ፣ ሳይበሉት የሚያጠግብ ህብስት ነዉ፡፡ አንቺ ለእኔ ያልተከፈለ የባንክ ቤት እዳ ነሽ፡፡ ቀኑ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ዉለታዋ የሚጨምርብኝ ፡፡ ከቀን ቀን ወለዱ በዝቶ ለመክፈል የሚያዳግተኝ ፤ ማንነቴን አስይዤ ስለተበደርኩሽ ስለ አንቺ ሳላስብ ዉዬ ማደር የማልችል ዉዝፍ እዳዬ ነሽ፡፡ ይሄም ዉለታሽ አዎ ዉለታሽ ያቃዠኛል ፤ እንደ አሉላ አባ ነጋ ተጋደልላት ፣ እንደ እምዬ ሚኒሊክ ቅን ገዢ ሁንላት ፣ እንደ ጋሽ ጥላሁን ጉሮሮህ እስኪነቃ አዚምላት ፣ እንደ የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ዉበቷን በስዕል አድንቅላት ፣ እንደ ክቡር ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ብዕርህ እስኪነጥፍ ፃፍላት ፣ እንደ አበበ ቢቂላ እግርህ እስኪነቃ እሩጥላት … ይለኛል፡፡

አንቺነትሽን ለተረዳዉ ኢትዮጵያዊነት ማንም ድንገት ተነስቶ የሚንደዉ የገለባ ክምር ሳይሆን መቼም ቢሆን ሊከስም እና ሊጠፋ የማይችል በደማችን ዉስጥ ተበርዞ የሚገኝ ዉህድ ነዉ፡፡ ጥበበኛ ነኝ የሚል ባለጥበብ ፣ ፖለቲካ የሰረፀዉ ፖለቲከኛ ፣ በገንዘቡ የሚመካ ቱጃር ብቻ ማንም ይሁን ማንም ኢትዮጵያዊነትን ከደማችን መለየት የሚያስችል አቅም አይኖረዉም ጥረቱም የህልም ሩጫ ፤ የቁም ቅዠት ነዉ የሚሆንበት፡፡

## <u>ትላንት</u>

ፈር ቀዳጅ የስልጣኔ በር መክፈቻ ፣ ያለ ምንም ሲሚንቶ እና ግንባታ እቃዎች ሰማይ ጠቀስ ሀዉልቶች የተተከሉብሽ ፤ ድንጋይ ተፈርፍሮ ዘመናትን ተሻጋሪ ኪነ ህንፃዎች የቆሙልሽ ፣ ያለ ቴሌስኮፕ ስነ ፈለክ የተጠናብሽ ፣ መድሀኒት ያለ ላብራቶሪ የተቀመመብሽ ፣ ከቅጠል ተቀምመዉ በቆዳ ላይ ታትመዉ ሚስጥሮችን ለቃቅመዉ የተሸከሙ ብራናዎች ባለቤት ነሽ፡፡ ትላንትን ለመረዳት ምዕራናዊያን የልጆችሽን ስራዎችን የሚሰርቁሽ እና የሚራኮቱብሽ ባስ ሲልም ለመካድ እና የእነሱ የጥበብ አሻራ እንዳረፈበት አድርገዉ ሲያቀርቡ እና ማጠናከሪያ መረጃ ሲፈልጉ የሚዉሉብሽ ድንቅ ሀገር ነሽ፡፡

ያኔ ለልጆችሽ ያንቺነት ስሜት ልክ በደም ስር እንደተወጋ የሰመመን መርፌ ዉስጣቸዉ የተቀላቀለ ልዩ መግነጢሳዊ ሀይል ነበረ ፡፡ ታላላቅ ልጆችሽ ስለ አንቺ ሲሉ ክብራቸዉን ዝቅ አርገዋል ፣ የሞት ፅዋን ተጎንጭተዋል ፣ እንደ አፄ ቴዎድሮስ ሽጉጣቸዉን ጠጥተዋል ፣ እንደ አፄ ዮሀንስ አንገታቸዉን ተቀልተዋል ፣ በጣልያን የመርዝ ጭስ እንደ ጤዛ ረግፈዋል ፣ ለነፃነት ሲሉ ብዙ ዓመታትን በዱር በገደሉ ከትመዉልሻል፡፡

ዛሬ ቆሜ በነፃነት የምኖርብሽ ትላንትና አባቶቻችን የአንቺን መዋረድ ከሚያዩ የሞት ፅዋን መጎንጨት መርጠዉ ባፈሰሱት ደማቸዉ ነዉ፡፡ የቀድሞ ልጆችሽ ብልህ ነበሩ የአንቺ አንድነት መቀነት ሸብ አድርጎ አንድ ጋር ያሰራቸዉ የበኩር ልጆች ፡፡ ለእኛ ብሎ መላዉ አፍሪካን ከነጮች የባርነት ቀንበር ያላቀቁን ፋና ወጊዎች፡፡

## <u>ዛሬ</u>

ዛሬ ላይ ልጆችሽ ያለንን ብናዉቅ የሚጎድለን አይኖርም ነበር ፤ እኛ ያንቺ ልጆች ሀብታሞች ሆነን ድህነት የዘመረብን ፣ በጥንታዊ ታሪካችን አለምን ያስቀናን ግን በኦክስፎርድ ዲክሽነሪ ሳይቀር የድህነት ምሳሌ የሆንን ፣ ኩሩዎች ሆነን ስማችን በንቀት የሚብጠለጠል ፣ ፍቅር እያለን ፍቅር የጠማን ነን፡፡

ዉዳሴሽን ፅፌ እንኳን ሳልጨርስ ገና እዚሁ ገፅ ላይ እያለሁ ደግሞ በተቃራኒዉ ሌላ መራራ ታሪኮችን እየፃፍንልሽ ነዉ፡፡ የሠዉ ደም የረከሰበት ጊዜ ላይ እንገኛለን ፣ ሰዎች ከማገናዘብ ይልቅ መነዳትን የመረጡበት አስፈሪ ወቅት ላይ ነን፡፡

ኢትዮጵያዬ በሁለት እግሮችሽ ለመቆም እንደ ህፃን ልጅ ዳዴ እየተለማመድሽ ነዉ ፤ ግና ምን ያደርጋል አንዱ ልጅሽ መጥቶ ቀና እያደረገሽ ስትንገዳገጂ ሌላ ሌቡ ያበጠበት ወጠጤ የመንደር ጎረምሳ እየጠለፈ ይጥልሻል ፤ ስትወድቂ እና ስትነሺ እያየሁሽ ነዉ::

ኢትዮጵያዬ አሁንም ጆሮ ባዳ ሆኖብን ብዙ ነገሮች ከፊትለፊታችን አይን አፍጥጠዉ ፤ ግንባራቸዉን አግጥጠዉ እየመጡ እያየን ፤ ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ትኩረት መስጠት ተስኖን በጊዚያዊ ነገር አይናችንን ሰዉረን፤ በአሉባልታ እና በትርኪምርኪ ስንቦጫጨቅ እና ስንነታረክ አንቺ ዉድ እናታችን በኋላ በር እያመለጥሽን ነዉ:: አንቺ ህመምሽን ታዉቂዋለሽ ህመምሽ ግን ድብቅ በመሆኑ ያየልሽ ጥቂት ሰዉ ብቻ ሆኖ ህመምሽ ፀናብሽ ፤ ዉድ ልጆችሽ በጎን እያመለጡሽ ነዉ:: ስለ ዋካንዳ ሲቲ ፕሮጀክት ቅንጣት ያልሰማን ወይንም መስማት ያልፈለግን ፤ ግብረ ሰዶም ወረርሺኝ ሲሆን ጆሮ ዳባ ልበስ ያልን ጉደኞች በዘረኝነት አረንቋ ዉስጥ ተዘፍቀንልሻል ::

መመርመር ተስኖን ፤ አላዋቂዎች አዋቂዎች ተብለዉ ነግሰዉ ፤ ከኋላ የነገ ነገርሽ አሳስቧቸዉ የሚጮሁ ሊህቃኖችሽ ጆሮ ተነፍገዉ ፤ ተስፋችን ከተስፋ እልፍ ሳይል ገና ከጅምሩ ፈተና በፈተና ሆነሻል:: የብዙ ልጆችሽ ደም ያለ ምንም ምክንያት ለሆዳቸዉ በሚያድሩ እና ነገን አርቆ ማየት በተሳናቸዉ ስግብግብ ጡት ነካሽ በሆኑ ካንቺ ማህፀን የወጡ በማይመስሉ ፍሬ ቢስ ልጆችሽ የቁም ስቃይሽን እያየሽ ነዉ:: አባት ያለ እናት ያሳደጋት ጧሪ ልጇን ፤ እናት እንጨት ተሸክማ ጠላ ሸጣ ያሳደገችዉ ልጇን እየተነጠቀች ነዉ::

ተጠምቀዉ የማያምኑ ፤ ታጥበዉ የማይጠሩ ፤ ካለፈዉ ስህተታቸዉ የማይማሩ ዘገምተኞች የአንድነት መንፈስ በሚቃኝበት ዜማ ዉስጥ የተረኝነት እና የእኔ ብቻነት አንጯ ከረዩ ያንቆረቁራሉ:: አንድ ተራ ወፍ ዘራሽ የተናገራትን ቃል እየሰነጠቅን ተቧድነን በትር መማዘዙን ተያይዘነዋል:: ለመግዛትም ሆነ ለመገዛት የማይመች ህብረተሰብ ተፈጥሮልሻል:: ዳኛዉ በዝቶ የሚዳኝ ጠፍቷል :: በዝሆኖቹ ሽኩቻ የዋሁ ሀገሬዉ ያለ ጥፋቱ እና ኩነኔዉ በዘሩ ብቻ ጥቃት እንዳይደርስበት እቃዉን ሸካክፎ ወደየ ስርቻዉ እየተሸጎጠ ነዉ::

እናትነትሽን እና ሀያልነትሽን እያወቅሁ ልጆችሽ ግን ከሰዉ በታች ቀለን መገኘታችን ሲታሰበኝ ጨርቅህን ጥለህ እበድ ፣ የዉስጥህን ጩሀት ሀገር ምድሩ እስኪናወጥ ለፍልፍ ፣ ኡኡታህን አሰማ ይለኛል:: የተስፋ መቁረጥ ወሽመጥ ጎኔን ሲደቋቁሰኝ አንቺ የእኔ እናት እጅግ እፁብ ድንቅ ሚስጥረኛ ነሽ ያለ ምክንያት እስካሁን አልቆየሽም እና ወደፊትም ማንም እንደማያጠፋሽና እንደማላጣሽ ሲሰማኝ ደግሞ ልቤ ከሀሳብ መቁረጥ ባህር ዘሎ ይወጣና በሀሳብ ሰመመን ሰምጦ ይቀራል:: አዎ ኡኡታዬን ማንም ባይሰማኝ እና ከቁብ ባይቆጥረዉም ያንቺ አምላክ እንደሚሰማኝ አልጠራጠርም::

ኢትዮጵያዬ አንቺን የሚያክል ደግ ፣ ሩህሩህ እና ኩሩ እናት እያለኝ :: እኔን ከባርነት ለማዳን የኦሮሞ ፈረሰኞች ፣ የትግራይ ገበሬዎች ፣ የአማራ ጦረኞች ፣ … የሁሉም ብሄር ልጆችሽ እራሳቸዉን ከፍለዉልኛል:: እና እንዴትስ ሆኖ ከወገንተኞች ጋር አብሬ ልንጎድ ? እነሱ ሲያብዱ አብሬ ልበድ ? የአንቺ ልጅ መሆኔን ትቼ ቁልቁል ተንሸራትቼ በአማራነቴ ብቻ ፣ በኦሮሞነቴ ብቻ ፣ በትግሬነቴ ብቻ … መኮፈስ እና መታበይ ለእኔ ቀሎ መገኘት ፤ ዉለታ ቢስነት እና አላዋቂነት ነዉ ፤ እዉነት እልሻለሁ አላደርገዉም ::

## የነገ ተስፋ

ሁላችንም ልጆችሽ መለያ ታርጋችን ኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያዊ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ ማንም ቢሆን በማንነቱ እና በዘሩ ተለይቶ ጥቃት ሊደርስበት ፤ ንብረቱ ሊወድምበት አይገባም ፡፡ ቢገባን ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ያንቺ የአብራክ ክፋይ ስለሆንን በደም የተሳሰርን ነን ማንም ነጠላ ብሄር ይዞ የተፈጠረ የለም ፤ አማራዉ ከኦሮሞዉ ፣ ትግሬዉ ከደቡቡ …እያለ ሁላችንም የዚህ ድብልቅ ዉጤት ነን ፤ ስለዚህ የጋራ መጠሪያ ታርጋችን ኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነዉ፡፡

ማህፀንሽ ግን ሁሌም አይነጥፍም አንቺ የበረከት ምድር እነዛ በላሊበላ እጅ የታነፁ የድንጋይ ቅርፆችሽ አሁንም በዚያዉ ምድር በዳግማዊ ላሊበላ በሆኑት ልጆችሽ ተገንብተዉ እያየን ነዉ፡፡ አንቺ ያለ ስምሽ መጥፎ ስም ያገኘሽ ፤ ያለ ቦታሽ ዝቅ ብለሽ የተቀመጥሽ ፤ ተስፋሽ እይሞትም ህልምም ሆኖ አይቀርም በእኛ ልጆችሽ ዳግም ገናና ፤ ስምሽ ሲጠራ የሚያርበተብት ፤ ሁሉም የሚያመልክሽ አምሳለ ገነት ትሆኛለሽ፡፡

አንቺ ኢትዮጵያችን ምንም እንኳን የበግ ለምድ ለብሰዉ ስምሽን እያቆላመጡ የሚቦጠቡጡሽ ተኩላዎች ቢኖሩም በዚያዉ ልክ በምንም የማይቀይሩሽ ብዙ ዉድ ልጆች ትላንትም ነበሩ ፤ ዛሬም አለን ፤ ወደፊትም ይኖራሉ ፡፡ እመኚኝ ዉድ እናት ሀገሬ ልጆችሽ ላንቺ ለሀገራችን ስንል የማንወጣዉ አቀበት ፣ የማንወርደዉ ቁልቁለት ፣ የማንቆፍረዉ መሬት ፣ የማንዻዘዉ ርቀት ፣ የማንከፍለዉ ሂወት አይኖርም፡፡

እኛ የአሁን ትዉልድ ተተኪዎችሽ ለክብርሽ አዲስ መንገድ ጠራጊዎች እንሆናለን ፡፡ የማይሳሳት የማይሰራ ብቻ ነዉ ፤ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች አሁንም ጨምሮ ያሉትን የተለያዩ ታሪካዊ ስህተቶች ደምስሰን ረስተን ሁላችንም ይቅር ተባብለን ያለፈዉን ጥቀርሻ ጥለን አዲስ ታሪክ እንሰራለን ፡፡

እኛ ልጆችሽ ፍቅር እንጂ ፀብ አያምርብንም ፤ እርስ በእርሳችን ስንቃቃር ለጠላት መሹለኪያ ቀዳዳ መክፈት ነዉ፡፡ ፖለቲካን ፖለቲካ ፤ መሪን መሪን ይተካዋል የእኛ ፍቅር እና መዋደድ ግን ምንም ዳገቱ ቢበዛ ፤ ገመዱ የተበጠሰ ቢመስልም ፤ እሳት አቃጥሎት ቢሰለስልም ጫፍ ላይ ከመድረስ ማንም አያግደንም ፡፡

የአንቺ ተስፋ እያበበ እንዳለ ፅጌሬዳ አበባ ነዉ ፤ ሳይፈካ ሊያዳፍኑት የሚሯሯጡ ከይሲዎች ቢበዙም ፤ እኛ ግን አፍክተን እናፈነዳዋለን፡፡ ኢትዮጵያችን ጊዜዉ ይቆይ እንጂ እመኚኝ በእኛ በልጆችሽ ወደ ነበረሺበት የንግስና ዙፋን ትመለሻለሽ፡፡

ያኔ ሁላችንም ኢትዮጵያዊነትን ያስቀደምን ጊዜ ፤ ማንም ነጭ ጋዜጠኛ አፉን ሞልቶ እኛን ማንኳሰስ አይችልም ፤ ቀደምት እንደ ነበር ቀደምት ሆነን እንቀጥላለን ፤ የክብርን ዙፍን እንቆናጠጣለን ፤ ድህነትን ላይመለስ እስከ ወዲያኛዉ አንሸኘዋለን ፤ የታሪክ ተወቃሽ ሳንሆን የታሪክ ተወዳሽ መሆን እንችላለን፡፡ ያኔ አንቺ እናታችን ለማንኛዉም ሰዉ ዩቶጲያ (አምሳለ ገነት ወይም ለመኖር ምቹ የሆነች ቦታ ትሆኛለሽ) ፡፡

ምንም ማድረግ አይቻልም ተዋጠልንም አልተዋጠልንም ፤ እያቃረንም ቢሆን እንዋጠዉ ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል፡፡ እንዴት ሆኖ እንዴትስ ቢደረግ ከቶ በማንነቴ ፤ በማተቤ እና በአንቺ በዉድ እናት ሀገሬ ድርድር እና ቀመር ዉስጥ ልገባ እችላለሁ፡፡

" እናት ኢትዮጵያዬ … አንቺን ብቻ ! "

# 1.3 ሰሜን ኮርያ vs ኢትዮጵያ



**ቀደም ብሎ የተፃፈ ...**

ብዙዎቻችን የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን የማወቅ እና የማየት እንዲሁም የመጎብኘት ፍላጎት አለን ፡፡ እስኪ ዛሬ ምዕራባዉያንን እኛም የምዕራባዉያን አምላኪዎች እና ተከታዮች የሆንን ህዝቦች ብዙ ስለማናዉቃት እና መጥፎ ነገሯን ብቻ ስለምንሰማላት ሀገረ ሰሜን ኮርያ የተወሰነ ዳሰሳ እና ጉብኝት እናድርግ፡፡ ጉብኝት ስላችሁ እንዳትጨናነቁ ፓስፖርት ፣ ቪዛ ፣ የአዉሮፕላን ትኬት ፣ የሆቴል እና ተያያዥ ወጪዎች ሂሳብ በእኔ ነዉ፡፡ ጉዞ ወደ ሰሜን ኮርያ ፒዮንግ ያንግ ልንጀምር ስለሆን የመቀመጫ ቀበቷችሁን ጠበቅ አድርጉ -

ሰሜን ኮርያ በኤዥያ አህጉር የምትገኝ ሀገር ስትሆን ልክ የኢትዮጵያ እና ኤርትራ ህዝቦች እንደተገነጣጠሉት ሰሜን ኮርያዉያንም ከደቡብ ኮርያዉያን ጋር የደም ግንኙነት ያላቸዉ ቢሆኑም ከሁለተኛዉ የአለም ጦርነት በኋላ በርዕዮተ አለም አለመጣጣም ምክንያት ተገነጣጥለዉ አሁን አይጥ እና ድመት ሆነዉ የሚኖሩ ሀገራት ናቸዉ፡፡ የሁለቱም ሀገራት ህዝቦች ከወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ጋር የተገነጠልን መሆናችን ያመሳስለናል፡፡

አለም ስለተደበቀችዉ እና ስለ ሚስጥራዊቷ ሀገራት ብዙ የማያወቃቸዉ ብዙ አስገራሚ ፣ አስደንጋጭ እና ይበል የሚያስብሉ ነገሮች አሉ፡፡ እስኪ የተወሰኑትን ከሀገራችን አንፃር እያወዳደርን እነመልከታቸዉ -

በሰሜን ኮርያዉያን የራሳቸዉ የዘመን አቆጣጠር አላቸዉ በዚህም መሰረት ዘንድሮ ማለትም እ.ኤ.አ 2017 ዓ.ም ለሰሜን ኮርያዉያን ገና 105 ዓ.ም ነዉ ፡፡ መነሻ ምክንያቱም የእነሱ ካሌንደር የሚጀምረዉ ከኪም ኢል ሱንድ መወለድ አንስቶ ነዉ ፡፡ በእኛም ኢትዮጵያዉያን አቆጣጠር መሰረት 2010 ዓ.ም ላይ እንገኛለን ከ አዉሮፓዉያን አቆጣጠር በ7 ዓመት ዘግይተን መሆኑ ነዉ፡፡

ወደ ስልጣን ሽግግር ስንመጣ ሰሜን ኮርያ ከነፃነት ጀምሮ የምትመራዉ በዉርስ እና የዘር ሀረግ በሚተላፍ የስልጠን እርከን ነዉ፡፡ ነፃ አዉጪዉ ተብለዉ የሚጠሩት ኪም ኢን ሱንግ በሞት ሲለዩ ልጃቸዉ ኪም ጆንግ ኢል ተተኩ ፤ እኝህ ተወዳጅ መሪ እየተባሉ በሰሜን ኮርያዉያን የሚጠሩት ሰዉ ህይወታቸዉ ሲያልፍ ጎረምሳዉ እና ብላቴናዉ ኪም ጆንግ ኡን በ29 ዓመታቸዉ ስላጣናቸዉን ተቆናጠጡ፡፡ በሀገራችን ስልጣን በቀደመዉ ጊዜ ልክ እንደ ሰሜን ኮርያ በዉርስ ይተላለፍ ነበር ፡፡ ከዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ በኋላ ጀምሮ ግን ስልጣን የሚገኘዉ በዉርስ መሆኑ ቀርቶ በፈረጠመ ጡንቻ ሆኗል፡፡ በነገራችን ላይ ሰሜን ኮርያ የምርጫ ስነ-ስርዓት ትከተላለች ነገር ግን እጩ ሆነዉ የሚቀርቡት የኪም ኢን ሱንግ ቤተሰቦች ብቻ ናቸዉ ፡፡ የእኛም ሀገር ከደርግ ዘመነ ጊዜ ጀምሮ በይፋ ምርጫ ታካሂዳለች ምንም እንኳን እስካሁን በምርጫ የስልጣን ዝዉዉር ተካሂዶ ባንመለከትም፡፡

የትምህርት አሰጣጣቸዉ እና ተያያዥ ጉዳዮች በቀጥታ ከኮሪያ ብሄራዊ ቋንቋ ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡ እኛ ሀገር በተለይ አሁን አሁን ከኬጂ ጀምሮ ሙሉ እንግሊዘኛ ነዉ፡፡ በነገራችን ላይ በእንግሊዘኛ መማራችን ጥሩ እና ከተቀረዉ አለም ጋር በቀላሉ እንድንግባባ ስለሚያስችል የሚያስመሰግን ነዉ፡፡ ነገር ግን የእኛ የሆነዉን ቋንቋችንንም እያሳደግን መሆን ይገባዋል፡፡ አለበለዚያ ነገ የራሳችንን አጥተን … ኢትዮጵያዊ ሆነን ግዕዝ ለመማር ጀርመን ፤ ካናዳ ወይም ቻይና መሄዳችን የማይቀር፡፡

የምዕራባዉያን ሚዲያ እና ፊልሞች በሰሜን ኮርያ ምድር የሚታሰቡ አይደለም፡፡ አንድ ወቅት ላይ ደቡብ ኩርያ ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ሰሜን ኮርያዉያን የአዉሮፓ ሰራሽ ፊልሞችን እየኮመኮሙ እንደሆነ መንግስት ሹክሹክታ ይሰማል፡፡ የወሰደዉ ምላሽ አስገራሚ ነበር ፡፡ በዚያ አካባቢ ሙብራት አጠፋ በመቀጠልም በእያንዳንዱ ቤት ዉስጥ እየገባ የዲቪዲ ማጫዎቻዎችን መፍታት ጀመረ፡፡ በመጨረሻም በዲቪዲ ማጫዎቻዎቹ ዉስጥ የአዉሮፓዉያ ሲዲ የተገኘባቸዉን ሰዎች ለሌሎች ትምህርት በሚሆን መልኩ ቀጣቸዉ፡፡ እኛ አገር የተገላቢጦሹ ነዉ … ማንም የፈገዉን ማየት ይችላል፡፡ የኮፒ ራይት እና የዉጪ ፊልሞች ተጋግዘዉ የሀገሯቷን የጥበብ ኢንደስትሪ እየደቆሱት ይገኛሉ፡፡

በሰሜን ኮርያ ምድር የኢንተርኔት እና የቴሌቪዝን አጠቃቀም ገደብ አለዉ፡፡ ማንኛዉም ሰሜንኮርያዊ የምዕራባዉያን ሚዲያን መከታተል አይፈቀድለትም፡፡ የደቡብ ኮርያ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሲከታተል የተገኘ ሰዉ በሞት ይቀጣል፡፡ በሀገሪቱ 3 የቴሌቪዥን ሰርጭት ጣቢያዎች አሉ፡፡በተጨማሪም አለም አቀፍ የስልክ መልዕክት ማድረግ ለሞት ቅጣት ይዳርጋል፡፡ እኛ ሀገር ስንመለስ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ክልከላ የሚተላለፍባቸዉ ጣቢያዎች አሉ እንጂ ሌላ የዉጪ ሀገር ሚዲያ መከታተል አይከለከልም፡፡ በሀገር ዉስጥ የቴሌቪዥን ገበያዉን ለረጅም ጊዜ የድሮዉ ኢቲቪ የአሁኑ ኢቢሲ ብቻዉን በጅምላ ተቆጣጥሮት ቢቆይም አሁን ድንገት ካየት መጡ ሳይባሉ እጅግ ብዙ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንደ ደራሽ ዉሀ ተከስተዉ የኢቢሲን ህልዉና እየተፈታተኑት ይገኛሉ፡፡ ኢንተርኔትም ቢሆን የፀጥታ ችግር ሲከሰት የሀገሪቱ አንድ አይን የሆነዉ ቴሌ ዘግቶ በነካካ እጁ መልሶ ይከፍተዋል እንጂ ያን ያህል የከረረ እገዳ የለም፡፡

በሰሜን ኮርያ ምድር የእነ ማይክል ጃክሰን እና የኬቲ ፔሪ ሙዚቃዎችን መመልከት እና ማድመጥ ቀርቶ ስማቸዉን የሚያዉቀዉ ሰዉ ፈልጎ ማግኘት በጣም ከባድ ነዉ፡፡ የምዕራባዉያን ሙዚቃዎችን ለማዳመጥ አቅርቦቱም አይኖርም ህብረተሰቡም አስቦት አያዉቅም፡፡ እኛ ሀገር አሁን አሁን በተለይ ወጣቱ ዘነጠ የሚባለዉ ቢገባዉም ባይገባዉም የእንግሊዘኛ ሙዚቃ ማዳመጡ አይቀሬ ሲሆን ነዉ ፡፡ እስከሚችለዉ ድረስ የአሜሪካዊ ዘፋኝን ስሙን ቀጥሎም ማንነቱን መሸምደድ ይጀምራል፡፡ በዚህ ከቀጠለ ወደፊት 4 የዜማ ስልቶቻችን ጠፍተዉ ፤ ማህሌተ ያሬድ ተዘንግቶ ፤ ራፕ እና ሂፓፕ የማንከተልበት ምንም አይነት ምንክንያት የለም፡፡

ወደ አለባበስ ስንመጣ ሰሜንኮርያዉያን ለእኛ ኢትዮጵያዉየንም አርአያ ሊሆኑን የሚገቡ ህዝቦች ናቸዉ፡፡ በአለም ላይ ካሉ ያልተበረዘ ማንነት እና ባህል ካላቸዉ ህዝቦች ዉስጥ ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ የሰሜን ኮርያዊት ሆና የቻይና ጅንስ ሱሪ የለበሰች ሴት ማግኘት ሰሜን ኮርያዊ ሆኖ የአዎሮፓዉያንን ጅንስ እና ፋሽን ለብሶ መታየት የማይታሰብ ነዉ፡፡ ሲበዛ ማንነታቸዉን አስጠብቀዉ ግሎባላይዜሽን አለባበሳቸዉ ላይ ጫና ያልደረሰባቸዉ ናቸዉ፡፡ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት የአለባበስ እና ባህል አያያዝ ዉጥንቅጡ የወጣ ነዉ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የቻይናን ቅርፅ አልባ ልብሶች ተጎናፅፈናል፡፡ የቻይና ርካሽ ልብሶች ፣ የአዉሮፓ እና አሜሪካ ልባሾች የሀገራችንን ባህል ልብስ አምራቾች ከገበያ ዉጪ አድርገዉ አሽመድምደዋቸዋል፡፡

ወደ ፀጉር ቁርጥ እና ስታይል ስንመጣ በአጠቃላይ 28 የፀጉር ቁርጥ እና ስታይል አይነቶች ሲኖሩ 10ሩ ለወንዶች ብቻ ሲሆኑ 18ቱ ደግሞ የሴቶች ናቸዉ፡፡ ማንኛዉም ሰሜን ኮርያዊ የሆነ ዜጋ ከነዚህ የፀጉር ቁርጥ አይነት ዉጪ ከተቆረጠ ለቅጣት ይዳረጋል፡፡የፕሬዝዳንቱ ኪም ጆንግ ኡን የፀጉር ቁርጥ የእርሳቸዉ ብቻ ነዉ ሌላ ሰዉ ሊቆረጠዉ አይችልም፡፡ እኛ ጋር የፀጉር ገደብ በቀደመዉ ጊዜ ነበር ያለዉ ፤ በጥንት ጊዜ ፀጉሩን ሹርባ የሚሰራ እና የሚያጎፍር ወንድ እንደ አፄ ቴዎድሮስ እና አፄ ዮሀንስ ያለ ጀግና ወይም ገድሎ የፎከረ አርበኛ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ አሁን የወንድን እና የሴትን ፀጉር ቅርፅ አይነቶች እርስ በእርስ ተቀላቅለዉብን መለየት ተቸግረናል፡፡ የእኛዉ የነበሩት እነ ቁንጮ የመሳሰሉ የፀጉር ቁርጦች እየናቅናቸዉ ነገር ግን በአዲሱ ተሻሽለዉ ባላቶሊ ቁርጥ ተብለዉ እየተከተልናቸዉ ነዉ፡፡ ነገር ግን ይህ ለየቅል እና ትርጉም አልባ የሆነ የፀጉር ቅርፅ ቢያንስ በስራ ቦታዎች እና ትምህርት ተቋማት ህግ ሊበጅለት ይገባል፡፡

ሰሜን ኮርያ ዉስጥ መፅሀፍ ቅዱስ ማንበብ ከባድ እስራት ከፍ ብሎም ሞት ሊያስቀጣ ይችላል ምክንያቱም መፅሀፍ ቅዱስ የምዕራባዉያን ነፀብራቅ ነዉ ተብሎ ስለሚታመን ነዉ ፡፡ለሰሜን ኮርያዉያን ፈጣሪያቸዉ እና አምላካቸዉ ገዢ መንግስታቸዉ ነዉ፡፡ እኛ ሀገር ከሆነ ብቻ ግዜ እና ፍላጎት ይኑረን እንጂ የፈለግንዉን ሀዲስ ኪዳንን ከ ብሉይኪዳን እያቀላቀልን ብንሸመጥጠዉ ዞር ብሎ የሚጠይቀን የለም፡፡ ሀገራችን የእምነት ነፃነትን አስጠብቃለች ብሎ መናገር ይችላል፡፡ማንም ሰዉ የፈለገዉን መከተል ይችላል፡፡

በአስገራሚ ሁኔታ በሀገሪቱ ዉስጥ እድሜዉ ከ15 እና ከዚያ በላይ የሆነ ሰዉ ማንበብ እና መፃፍ ይችላል፡፡ በዚህም 100% የተማረ ሰዉ (litracy rate) አሳክታለች፡፡ እኛ ጋር በደርግ ጊዜ ህብረት በህብረት የሚባል ዘመቻ አሁን ደግሞ የጎልማሶች ትምህርት ተብሎ የተማረ ሰዉ ቁጥር ለመጨመር ጥረት ሲደረግ ይታያል ፤ እንደምንሰማዉ ከሆነ የህብረት በህብረት ዘመቻ የተሳካ ነበር ፤ አሁን ላይ ያለዉ የጎልማሶች ትምህርት እንኳን ከሪፖርት ያለፈ ነገር አይታይበትም፡፡

ሰሜን ኮርያ ለየት ያለ ከትዉልድ ትዉልድ የሚሸጋገር የእስራት አካሄድ ትከተላለች፡፡ አያት ያጠፋዉ ጥፋት መጠን ከበድ ያለ ከሆነ ቅጣቱ ከእሱ አልፎ ለልጆቹ እና ልጅ ልጆቹ ይተርፋል፡፡ ስለዚህ ምንም የማያዉቅ አዲስ ልጅ ምናልባት የአያቱን ቅጣት ሊቀበል ይችላል፡፡ እኛ ሀገር እንኳን አሁን አሁን እንኳን ለልጅ ልጁ ቀርቶ ለወንጀለኛዉም በቂዉን ቅጣት እየተሰጠዉ አይደለም፡፡ የሰዉ ነፍስ አጥፍቶ በ10 ዓመት ፤ እንደዉም አንዴ በቅርቡ የሰማነዉ የ4 ቤተሰብ ሂወት በመርዝ አርግፋ የተፈረደባተት 16 ዓመት ነዉ ፡፡ ያዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ አይቀጡ ቅጣት የምንቀጣዉ ፖለቲከኛ ስንሆን ብቻ ነዉ፡፡ ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊወርጊስ ወንበር ላይ ከተቀመጡበት ጊዜ ጀምሮ በግልፅ ባይደነገግም የአደባባይ የሞት ፍርድ ተቀልብሷል ማለት ይቻላል፡፡ ዉስጥ ዉስጡን ስንት ሰዉ ያለ ፍርድ እየረገፈ ተቸገርን እንጂ፡፡

ሀገሬ ናፈቀኝ የሚሉት ዘፈን ሰሜንኮርያ አይኖርም ምክንያቱም ማንኛዉም ዜጋ በሀገሩ ተወልዶ በሀገሩ ነዉ የሚሞተዉ ወደ ሌላ ሀገር ለስራ ጉዳይ እንኳን ሄዶ እዚያዉ ለመቅረት መሞከር እንኳን ለቅጣት ይዳርጋል፡፡ እኛ ሀገር ከተቻለ አሜሪካ መሄድ ካልተቻለ ደግሞ አረብ አገር መንገድ የአብዛኛዉ ወጣት ህልም ነዉ፡፡

ከአለም ድብቅ እና ሚስጥራዊ የሆነችዉ ሰሜን ኮርያ ምንም እንኳን ትንሽ ሀገር ብትሆንም አሜሪካን የምታክል ሀያል ሀገርን እና የአሜሪካን ወዳጆች ለሆኑ ሀገራት ባጠራቀመቻቸዉ እና በሰራቻቸዉ ጅምላ ገዳይ መሳሪያዎች እና ሳይታሰብ በታጠቀችዉ የኒኩለር አረር በመታገዝ እያሽቆጠቆጠች እና እንቅልፍ እያሳጣች ያለች አልቀመስ ባይ ሀገር ሆናለች ፡፡የሸገር ራዲዮዉ ጋዜጠኛ እሸቴ አሰፋ በአንድ ወቅት የሰሜን ኮርያን አልቀመስ ባይነት ሲገልፅ እንደዚህ ብሎ ነበር **" የሩቅ ምስራቋ ሰሜን ኮርያ ለእነ አሜሪካ እና ጃፓን የማይቆረጠም የብረት ቆሎ የማይጨበጥ የእሳት አሎሎ ሆና ከፉኛ አስቸግራቻዋለች "** ፡፡ ሆሆይ .... እኛ እንኳን ከምዕራባዉያን ጋር የምን እልህ መጋባት ነዉ ሲጠሩን አቤት ሲልኩን ወዴት እያልን ፤ የሰጡንን እየተጋትን ፤ የሰፉልንን እየለበስን ፤ አንዳንዴም እየተበደርን ፤ እነሱን እየመሰልን ራሳችንን እየዘነጋን ይሄዉ እዚህ ደርሰናል፡፡

ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም የተወሰነዉን አዉግተንዋል ፤ ስለዚች ሚስጥራዊት ሀገር ብዙ ጉድ የሚያስብሉ ብዙ እዉነታዎችን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ፈልጉ እና ድረሱበት፡፡

## <u>በቅርቡ የተጨመረ</u> ....

ነገሮች በምንያህል ፍጥነት እንደሚቀያየሩ ስናይ እጅግ ይገርማል :: ታሪክ ፅሁፋችን እስከምናሳትም ድረስ እንኳን መታገስ ተስኖት በቅፅበቶች እየተቀያየረ ነዉ:: እንደዚህ ነዉ እያልን የፃፍነዉ ነገር ሁሉ እንደዚህ ነበር እየሆነ መጣ፡፡ምን ታሪክ ቢቀያየር ፣ ምን ፍቅር ቢፈርስም ፣ ፍቅር ቢነግስም የእኛ እና የኮርያዎች ነገር ግን መመሳሰሉን ማቆም ተስኖታል፡፡ የዘንድሮዉ የፍቅር አዉሎ ነፋስ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ ላይ ብቻ አይደለም ያንዣበበዉ በዚያ ፍጥነቱ ኤሽያንም አዳርሶ ኮርያዎች ላይ የፍቅር ናዳ እና ዉሽንፍር አዝንቦባቸዋል፡፡ በአዉሎ ነፋሱም የብዙ ሰዎች ህይወት ላይ ከፍተኛ የሆነ ለዉጥ እንዲከሰት ፣ የተራራቁ ቤተሰቦች እንዲገናኙ ፣ ታጥረዉ የቆዩ ዜጎች እህቶቻቸዉንና ወንድሞቻቸዉን እንዲያገኙ አድርጓል፡፡

አዲስ አበባ እና አስመራ ላይ አዲመራ እያልን ስናዜመዉ ፤ የኢትዮጵያና ኤርትሪያ መሪዎች የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በጋራ ሲመርቁ ፤ በኮርያ ልሳነ ምድር ላይም ለነገዉ ትዉልድ መሪዎቻቸዉ ዛፍ ሲተክሉላቸዉ ለመመልከት በቅተናል፡፡ በተመሳሳይ አመት ሁለቱም ላይ የሰላም ዝናብ መዝነቡ ፤ አሜን የሚያስብል አስገራሚ ገጠመኝ ነዉ፡፡

***<u>መደምደሚያ</u>***- በፅሁፉ ላይ ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት ሰሜን ኮርያዉያን የራሳቸዉን ነገር ጠብቀዉ ማቆየታቸዉ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ይሄን ያህል ከአለም መነጠል ፤ የግሎባላይዜሽን ጠቃሚ ጎን ማግኘት አለመቻል እና ነገሮች በግዴታ ያለፍቃድ መከወናቸዉ ግን የራሱ የሆነ ታላቅ ጉዳት እና መገለል አለዉ፡፡ እኛ ኢትዮጵያዉያን ደግሞ እንድንመርጥ ተፈቅዶልናል ከፈለግን የራሳችንን ነገር እንድንጠብቅ ካልሆነም ከግሎባላይዜሽኑ እንድንቃርም ፤ ከቻልን ደግሞ እንድናመጣጥናቸዉ፡፡ በተገላቢጦሹ እኛ መምረጡ ተስኖን የራሳችንን እየረሳን መጣንና የግሎባላይዜሽን ሙሉ ለሙሉ ተጠቂ ሆንን፡፡ ጥሩዉንም መጥፎዉንም አግበስብሰን ቃረምን፡፡ ነገሩ የቆጡን ስታወርድ የብብቷን ጣለች እንዳይሆን እንደ ሰሜኖቹም ሳናካርር እንደኛም ሳናላላ ያለንን ነገር አጥብቆ መያዙ ያዋጣል፡፡ ነገሩ ብልጥ ልጅ እየበላ ያለቅሳል ነዉና ...

" አይ የሰሜን ኮርያ እና የኢትዮጵያ ነገር ... "

# 1.4 የቦይ ዉሀ



የቦይ ዉሀ በተገነባለት ቦይ ልክ የሚፈስ ፤ ከቦዩ ዉጪ ዉልፍት የማይል ፤ አቅም አግኝቶ እንኳን ከቦይ ዉጪ መፍሰስ ቢችል ልክ እንደ አዲስ አበባችን አስፋልት ላይ ጎርፍ ያለ ቅርፅ የሚግተለተል ፍሳሽ ዉሀ ነዉ፡፡

ብልጭ ድርግም እያለ ያየነዉ የዴሞክራሲ የሚመስል ጭላንጭል እና ተስፋ ሁላችንም የፈለገንን መተንፈሳችን ፣ የቋጠርነዉን ቁርሾ መዘርገፋችን ፣ ተደብቀን የምናያቸዉ ቲቪ ቻናሎች በሀገራችን በገሀድ መከሰታቸዉ ፣ የተዘጉ መፅሄቶችና ጋዜጦች ነፍስ መዝራታቸዉ ፣ ታክሲ ዉስጥ ፣ ቡና ቤት እንደፈለግነዉ መቦትለካችን ፣ ጥላቻን እንድንፍቅ እና እንድንዋደድ በር ሲከፍትልንም አሁንም ግን ቀላል የማይባል የማህበረሰብ ክፍል ወደ እንደ ቦይ ዉሀ መፍሰሱን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል፡፡

ማህበረሰብ እንደ ቦይ ዉሀ በደፈናዉ ገዢዉን መንግስት ወይንም ሌላ ተቃዋሚ አካል ደጋፊ ሆኖ ፤ መንግስት አለበለዚያም ተቃዋሚ በከፈተዉ ቦይ በደመ-ነፍስ የሚፈስ ከሆነ እድሉን አግኝቶም ከቦዩ ነፃ ሲወጣ እንደ ሸገር አስፋልት ላይ ጎርፍ ያለ ማመዛዘን ሲግተለተል እና በጅምላ ሲጫረስ መታየቱ አይቀርም፡፡

አሁንም እንዳየነዉ አልሸሹም ዞር አሉ ቢሆንም ነገሩ ከለዉጥ በኋላ ብለን በምንጠራዉ ጊዜ መፍሰሳችን ሳናቆም ጊዜያቶች አለፉን፡፡ ዛሬ ላይ ያለፉትን 27 ዓመታት የነበረዉን መንግስት ልማታዊ መንግስት ባልንበት በገዛ አንደበታችን ጥፋታዊ መንግስት እያልን ስንወቅስ ፣ ያሞገስነዉን ስናንኳስስ ፣ ያነገስነዉን ስንሽር ፣ አደባባይ ወጥተን እንባ የረጨንለተን ያላንተ ማን አለ ያልነዉን መሪ በአለቀስንለት አደባባይ ስናለቅስበት ፣ ከቦይ ዉጪ ማሰብ ተስኖን ጥቂቶች ሲጮሁ እና መቀመቅ ሲወርዱ ጆሮ ዳባ ልበስ እያልን ፣ ንፁሀንን ሌሎች ወገኖቻቸዉ ባጠፉት በብሄራቸዉ ያለምንም ጥፋታቸዉ ማግለሉን እና መሸንቆጡን ተያይዘንዋል፡፡ ጥቂቶች ብቻ ናቸዉ ከእዉነት ጋር ቆይተዉ ትላንትም በነበረዉ መንግስት ፤ ዛሬም በሚመራዉ መንግስት ላይ ነፃና ሚዛናዊ አመለካከታቸዉን የሚያንፀባርቁ ፤ በቦዩ ዉስጥ ቢሆኑም እንኳን የተሳሳቱ

አቅጣጫዎችን ሲያዩ ለምን ብለዉ ከቦዩ ወጣ እያሉ የራሳቸዉን ቦይ ይዘዉ የሚቀጥሉ፡፡ ሌላዉ አብዛኛዉ ባለ መንታ ምላስ ትላንት ከነበረዉ ጋር አብሮ የቆመረ ፣ ዛሬ ከመጣዉ ጋር አብሮ የሚደመር ፣ ነገ ከሚመጣዉ ጋር ያነገሰዉን የዛሬን መንግስት የሚሸር ፣ ከተረኛዉ ጋር አብሮ የሚነጉድ የቦይ ዉሀ ነዉ፡፡

ማህበረሰብ ካልመረመረ ተመነጠረ፡፡ እኛ እናዉቅልሀለን ባዮች የሚጋልቡት ፈረስ ሲሆን አስቸጋሪ ነዉ፤ ለመግራትም አይመችም፡፡ አንድ ማህበረሰብ አንዱ ዲዛይነር ሰፍቶ የባህል ልብስህ ነዉ ብሎ ሲሰጠዉ የባህል ልብሴ ይሄ ነዉ ብሎ ከተከናነበ ፣ ታሪኩን ከማንበብ እና ከመመርመር ይልቅ መስማትና ማስተጋባትን ከመረጠ ፣ ተሰብስቦ መፍትሄ መስጠቱን እና ፍሬ ማፍራቱን ትቶ ተሰብስቦ መፎከር እና ዳንኪራ መደንከር ካበዛ ፤ በጎጥ ስም መጠራቱ ሀሴት ከሰጠዉ ፤ ማንነቱን በጥቅም ከቀየረ ፣ የእኔ ሀገር ብቻ ፣ የእኔ ቋንቋ ብቻ ፣ የኔ ብሄር ብቻ ፣ የኔ .... ብቻ ማለት ከጀመረ ፣ የልቡን ትርታ ማድመጥ ተስኖት በአሉባታ እና ሚዲያ ከደነቆረ ፣ የዛሬዉን ብቻ አይቶ የነገን መመልከት ከተሳነዉ ፣ የነገ ተረኛ ታሪክ ተወቃሽ መሆኑ አልገለፅልህ ካለዉ ፣ ሰፊ የሆነች ሀገር ከጠበበችዉ ፣ በቦይ ዉሀ ደዌ መለከፉን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸዉ፡፡

ዛሬ ላይ ህዝብ በተራዉ ከስልጣን መዉረድ አለበት ፤ ከስሜታዊነት መንፃት ይኖርበታል፡፡ ያልተፈጠረ ታሪክ ተፈጠረ ብለን እየተጎነታተልን እኛ ግን በሰዉ ልጆች በታሪክ ተፈጥሮ የማያዉቅ ደማቅ የሀፍረት ታሪክ እየፃፍን እንገኛለን፡፡ ዶሮ እንኳን መዘቅዘቅ ወንጀል ነዉ ተብሎ በተበየነበት ሀገር የሰዉ ልጅ ዘቅዝቀን እየገደልን ያለን የዓለም አሳፋሪ ማፍያዎች ከሆንን ሰነባብተናል፡፡

ወጣት ለአንድ ሀገር አለኝታዋ እደሆነ ሁሉ ማመዛዘን ካልቻለ ደግሞ አፍራሽ መሆኑ አይቀርም፡፡ ባህርዳር ላይ 500 ሜትር የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ሲሰፋ ፤ ወለጋ ላይ 1000 ሜትር የኦነግ መለያ ሰንደቅ ይሰፋል ፤ ቀጣዩ ሰልፍ ላይ ደግሞ መቀሌ ላይ 1500 ሜትር የትግራይ ክልል ሰንደቅ ሲመተር ፤ አዲስ በተራዋ 5000 ሜትር ጨርቅ ስታስቀድድ … የማያስፈልግ እና ከንቱ ፉክክር ዉስጥ እዳክራለን፡፡ በዚህ ፉክክር ዉስጥ ብቸኛዉ አሸናፊ የጨርቁ ነጋዴ እና ሰፊዉ ሆነዉ ጨዋታዉ ይደመደማል፡፡ ዛሬ የገዢዉን ቲሸርት እና ኮፍያ አጥልቆ አሸሸ ገዳዬ ሲል የነበረ ወጣት ፤ ነገ ተቃዋሚ ፓርቲ በሀገር ገባ ሲባል የተቃዋሚዉን ጃኬት እና ሱሪ ደርቦበት ከቸች ይላል፡፡

እመኑኝ ብዙ የማያነብ ፣ ብዙ የማያመዛዝን ፣ የነገሮችን ቀኝ እና ግራ የማያይ ትዉልድ መጨረሻዉ አያምርም ፡፡ ምክንያቱም ለወገንተኝነት ፣ ለብሄርኝነት ፣ ለስሜታዊነት እና ለደመነፍሳዊነት የተጋለጠ ስለሆነ የፈለገዉ መሪ ነኝ የሚል እየመጣ እንደፈለገዉ ስለሚቀዝፍበት እና ማርሽ እየቀየረ ስለሚሾፍረዉ ነዉ፡፡

ብዙ ነገሮችን አይቶ የራስን አመለካከት እና የራስን አቋም መያዙ ሀጢያቱ ምን ላይ እንደሆነ አይገባኝም፡፡ የመንግስት ካድሬ የሆነ ሰዉ ተጠምቆ የተገዘተ ይመስል ከመንግስት በተቃራኒ የሆኑ ሚዲያዎችን ለማደመጥ በፍፁም ፈቃደኛ አይደለም ገና ሳይሰማቸዉ ፣ ሳያነባቸዉ እነዛ ዉሸታሞች ብሎ ይጀምርልሀል፡፡ በተቃራኒዉ ተቃዋሚ ነኝ ብሎ እራሱን የሰየመዉ ደግሞ የመንግስት ሚዲያዎችን ከቻናል ሊስት ላይ ከማጥፋት ይጀምራል፡፡ ይሄንን አስታርቆ ገለልተኛ ሆነን እንድንሰማ የሚያደርገን ነፃ ሚዲያ እንዴት ይናፍቃል፡፡

የደጋፊነት እና አለማመዛዘን አደጋን ለማየት በቅርቡ የነበሩትን የሊቢያን የሶርያን እንዲሁም የየመን ትዝታ መቃኘት ተገቢ ነዉ፡፡ ሊቢያዉያን ሳይሰሩባት የዜግነት እየተከፈላቸዉ የሚንቀባረሩባት ያቺ ሊቢያ ዛሬ በምዕራባዊያን ሴራ የአሸባሪዎች መናሀሪያ የኢትዮጵያኖች መታረጃ ህግ አልባ ምድር ሆናለች፡፡ ሶርያዉያን ስምንት አመታትን መቶሺዎችን ከጨረሰ እልቂት ሚሊዮኖችን ካፈናቀለ ድርጊት ፤ መቶ ቢሊዮን ዶላሮችን ዋጥ ስልቅጥ ካደረገ እኩይ የእርስ በርስ ጦርነት በኋላ ያለምንም

ለዉጥ ፤ መሪ እንኳን ሳይቀየር እዚህ ላይ ደርሰዋል፡፡ ሶማሊያም ቢሆን ከራሷ አልፋ ለእኛም ጠንቅ ሆና ሚስኪን ኢትዮጵያዉያን ወታደሮችን ያለህጢያታቸዉ ለአልሸባብ እና ደም ለማይጠግበዉ የሶማልያ አሸዋ ገብራለች፡፡ የመኖችም ቢሆኑ የአረቦች ድንቅ ሴራ እና የአዉሮፓዉያን ድብቅ የጦርነት መፋለሚያ ሜዳ ከሆኑ ሰነባብታዋል፡፡ የዚህ ሁሉ መነሻ እና መድረሻ ምክንያት የማህበረሰቡ እንደ ቦይ ዉሀ መፍሰስና ግልብ ስሜታዊነት ነዉ፡፡

ብልህ ከሰዎች ስህተት ሲማር ሞኝ ደግሞ ከራሱ ስህተት ይማራል ፡፡ እኛ ካለፉት ስህቶታችን መማር ተስኖን በእኔነት ጥያቄ ዉጥንቅጥ ዉስጥ እንገኛለን፡፡ እኛም ብልጦች ከሆነ ከእነዚህ አገራት በድጋሜ እንማር ፤ አሁን በምንከተለዉ በድፍን ዘረኝነት ከቀጠልን ደግሞ ያዉ ከራሳችን ስህተት በቅርብ ጊዜያት ለመማር የድቅድቁን ጨለማ ዋሻ በር ማንኳኳታችን አይቀሬ ነዉ ፡፡

የማናመዛዝን ከንቱዎች ከሆንን ከትላንት ወዲያ አባቶቻችሁ እንዲህ አደረጉ ስንል ትላንት ንፁህንን አማራዎችን ብለን ፈርጀን ስናወግዝ የጥላቻ መርዝ ስንረጭ ፤ ትላንት ገዢ በነበረዉ ህዉሀት ስም ዛሬ ላይ ፍቅር የሆኑ ዉድ የትግራይ እህት እና ወንድሞችን ያለህጢያታችዉ ስናሳድድ ፤ ነገ ዛሬ ላይ በሚገዛዉ መንግስት ሀጢያት የኦሮሞ ልጆችን ለፀብ ስንፈልግ ተረኛ ሆነን እንዳችን በአንዳችን ስንስቅ በችግር ተከበን ጀምበር ትጠልቃለች፡፡ ገና ጌጤ እንደዚህ አድርጋኛለች ብሎ ምንም የማያዉቀዉ ካሱን የምንገዳዉ ከሆነ አንዱ ሲንደምር እና ሌላዉን ስንቀንስ እርስ በርሱ እየተጣጣ ከዛሬ አስር አመት በኋላም አሁን አለንበት የአዘቅጠት ቦታ ላይ መገኘታችን የማይቀር ነዉ፡፡

ፖለቲካ ኳስ አይደለም ዘለን የምንገባበት እና እንደፈለግን የምንደግፈዉ፡፡ ኳስ እንኳን ለመግባት ትጥቅ ያስፈልገዋል ፤ አብዛኞቻችን ግን ፖለቲካ ዉጥ የምደነቀረዉ ስሜታዊነት እና ጥቅምን ታጥቀን ነዉ፡፡ ከዚህ ይልቅ ፖለቲካ ከስሜታዊነት በፀዳ ምክንያት ካላየነዉ አንድ ያለምክንያት የምንነዳለት ሰዉ ያወጣት አንዲት ቃል ከጣሊያን ከበተነዉ መርዝ ይልቅ የብዙዎችን ነፍስ ልታጠፋ ትጥላለች፡፡

አዉቀንም ይሁን ሳናዉቅ አጨብጫቢ እና አለቅላቂ ሆነን እስከመቼ ፤ የራሳችንን ጥግ ልንይዝ ይገባል፡፡ የፖለቲካ ፣ የዘር ፣ የሀይማኖት ፣ የጥቅም ሸኩቻ በመጣ ቁጥር የምንጋለብ ተራ ፈረስ ሆነን እስከ መቼ ? ድንገተኛ ደራሽ ጎርፍ ጠራርጎት የሚሄድ ቁስ አንሁን፡፡ ከጊዜያት በፊት የመሪዬ ግድያ ሙከራ ዉጤት ካልተነገረኝ ፣ የኢንጂነራችን ቅኔ ካልተፈታ ፣ ማናባቱ ነዉ ጀነራሌን የገደላቸዉ ፣ የታገቱ እህቶቼ ካልተለቀቁ እንቅልፍ በአይኔ አይዞርም ሲል የነበረ ማህበረሰብ ቀናት ቀናትን ሲወልዱ እንኳንስ ዉጤቱን የሚጠይቅ ቀርቶ የክስተቱን መፈጠሩንም የሚያስታዉሰዉ ከቀልቡ የሆነ ብቻ ሆኗል ፤ ሌላዉ የሆይ ሆይታዉ አጃቢ እና በስሜት የሚነዳ ነበር ማለት ነዉ፡፡

የፍትህ አሰራራችንም ልክ እንደ ህብረተሰቡ የቦይ ዉሀ ሆኖ እምባ ማበስ ተስኖታል፡፡ እንጅነሮች ሞቱ ፣ የቡራዬ ድሀ ደም በከንቱ ተንደቀደቀ ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ግድያ ሙከራ ፣ የባለስልጣኖች ግድያዎች ፣ የክቡር ጀኔራሎች ህልፈት ፣ በማግስቱ በሚዲያ ብቅ ብሎ አለንላችሁ ፤ በቁጥጥር ስር አዋልን ከሚል ድንፋታ ዉጪ ጠብ የሚል ነገር አለመኖሩ ህብረተሰቡን እምነት ያሳጣዉ እና እንደ ቦይ ዉሀ ወንጀል ሲከሰት ብቅ ብሎ መግለጫ ከመስጠት ያለፈ ነገር እንዳንጠብቅ ሆነናል፡፡ ወቅቱ ካለፈ በኋላ የሚጠይቅም ሆነ ዉሳኔ የሚሰጥ አካል እምብዛም አለመኖሩ ያሳዝናል ፤ ከዚህ በላይ ምን የቦይ ዉሀነት አለ ?

" አባይን ብቻ ሳይሆን ራሳችንንም እንገድብ ! "

# 1.5 የወንዜ ልጅ



ጓደኛዬ ያወጋኝ ትንሽ ቆየት ያለ ገጠመኙ ሀሳቤ ወደ ብዙ ቦታ እንዲሰራጭ እና ስለ ብዙ ነገሮች እንዳስታዉስ አደረገኝ ፤ እኔን ያስገረመኝ ገጠመኙ እናንተንም ያስገርማችሁ፡፡

ነገሩ እንዲህ ነዉ ፤ ልጁ የሚኖርበት ወረዳ ከሌላ ወረዳ ጋር የእግር ኳስ ግጥሚያ ይዘጋጃል፡፡ ለግጥሚያዉም ተጨዋቾች ይመለመላሉ በዚህ ጊዜ የልጁ ጓደኞች ሁሉ በጣም ጎበዞች ነበሩ እና ሁሉም ተመርጠዉ እሱ ብቻ ቀረ፡፡ ጓደኞቹም የእሱን መቅረት እና የሚከፈለዉን የአበል ክፍያ ማጣቱን ሲያስቡት አልዋጥ አላቸዉ ስለሆነም ልጁ በግብ ጠባቂነት እንኳን ቢሆን እንዲገባ መከረዉ ተስማሙ፡፡ ለአሰልጣኛቸዉንም ሄደዉ ጥሩ ግብ ጠባቂ እንዳለ እና ቡድኑን ቢቀላቀል የተሻለ እንደሆነ ሀሳብ አቀረቡ፡፡

በአሰልጣኛቸዉ ሀሳባቸዉ ተቀይባነት አግኝቶ የፍፁም ቅጣት ምት የግብ ጠባቂዎች መምረጫ መለያ መስፈርት ሆኖ ልጁ ለዉድድር ቀረበ ፤ ልጆቹም ኳሱን ወደ ጓደኛቸዉ ከመምታቸዉ በፊት ለግብ ጠባቂዉ ጓደኛቸዉ በጣታቸዉ አቅጣጫ ይጠቁሙት እና በአየር ላይ ከፍ አድርገዉ ይሰጡታል ... እሱም ስራዉ አየቀለበጠ ዋጥ ማድረግ ሆነ ፡፡ ሌሎቹ ግብ ጠባቂዎች ሲሆኑ ግን የተጨዋቾቹን ምት መቋቋም አቅቷቸዉ ከጨዋታ ዉጪ ሆኑ፡፡ አሰልጣኙም ድምጹን ለልጁ ሰጠ እና ተመረጠ፡፡

የጨዋታዉ ቀን ደረሰና ኮከቡ ግብ ጠባቂ ቋሚ አሰላለፍ ዉስጥ ገባ፡፡ ይህ ኮከብ ጠባቂ ግን ጨዋታዉ እንደተጀመረ ብሱ ሳይቆይ ቀልቡ ራቀዉ ፣ ወኔዉ ከዳዉ ፣ ያ መቅለብ የለመደ እጁ ተስለመለመ ፣ ግብ መጠበቅ አቅቶት የተቃራኒ ቡድን ተጨዋቾች መረቡን ወንፊት ሲያደርጉት ዉለዉ ቡድኑ 8 ለ 0 ተረታ ፡፡ የወንዜ ልጅ ብለዉ ይዘዉት የመጡት ጓደኛቸዉ ደራሽ የወንዝ ጎርፍ ሆኖ በጎል ዝናብ አጥለቅልቋቸዉ አረፈ፡፡

ስንቶች በወንዜ ልጅ ሰበብ ኦሎምፒክ ለዋና ሄደዉ ተንቦጫርቀዉ መጥተዋል ፣ የስንቶችን የትምህርት እድልን ሳይገባቸዉ ሞጭልፈዋል ፣ ስንት ጨረታዎችን በዝግ ድራማ ተጫዉተዋቸዋል ፣ ስንቶች መርከብ ተሳፍረዉ ሳያዉቁ የመርከብ ጥገና እና እድሳት ተቆጣጣሪ ሆነዋል ፣ ስንቶች … ኧረ ስንቶች …

ብዙ ምሩቅ ወጣቶች የሚገርም ብቃት እና ዉጤት ይዘዉ የወንዜ ልጅ በቃለ-ምልልስ (ኢንተርቪዉ) ረትቷቸዉ ከቤት ቁጭ ብለዋል ፡፡ አንድ ቀልድ ትዝ አለኝ ነፍሱን ይማረዉ እና ኮሜዲያን ሀብቴ እና ደረጀ ነበሩ ፤ ጠያቂዉ ከነበሩት ወንድ እና ሴት ተወዳዳሪዎች መካከል ሴቷ እንድታልፍ ይፈልግና ጥያቄዉን ይጀምራል፡፡ ያዉ ነገሩ ቃለምልልስ ነዉ እና ለእርሷ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ስንት ይሆናል ብሎ ጠየቃት ይሆናል ብላ የገመተቸዉን ተናገረች እንዲወድቅ የወንዜ ልጅ ዱላ ያረፈበት ተጠያቂ ደግሞ የደረሰዉ ጥያቄ የእያንዳንዳቸዉን ስም ጥቀስ የሚል ነበር፡፡

ብዙ ኳሶች ከሜዳ ዉጪ አልቀዉ ፤ ብዙ ዉሳኔዎች ከችሎት በፊት ተበይነዉ ፤ የችሎታ መወዳደሪያ መድረኮች ከመድረክ በፊት ተከዉነዉ ፤ሹመቶች ከፓርላማ በፊት ተሾመዉ እና የወንዜ ልጅ ሰለባ ሆነዉ ካለቁ በኋላ አብዛኛዉን ሰዉ የትዕይንቱ ተሳታፊ በማድረግ አዉቀንም ሆነ ሳናዉቅ የትዕይንቱ ተዋናይ ሆነን እንተዉናለን፡፡

አስፍተን ካየንዉ የወንዜ ልጅ ከባድ እና ማህበረሰቡን ያስመረረ ነቀርሳ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በወንዜ ልጅነት አዲስ አበባን ረግጦ ሳያዉቅ ኮንዶሚኒየም ደርሶት ቁልፍ ሊረከብ ሲመጣ ታገኙታላችሁ ፤ ሀይ ባይ ሳይኖረዉ ኮንትሮባንዱን ሲያጧጡፈዉ ትመለከታላችሁ ፤ ገቢዎች የማያቀዉ ንግድ ቤት መሀል መገናኛ ላይ ንገዱን ሲያጧጡፍ ትኮመኩማላችሁ፡፡

አንዳንዱ መስሪያ ቤት እማ ትልልቅ ሀገራዊ መስሪያ ቤቶችን ጨምሮ ሙሉ ለሙሉ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የአንድ ትንሽ ወንዝ ልጅ ይሆኑ እና ተሳስቶ የገባ የሌላ ገባር ወንዝ ልጅ ቢኖር እንኳን መፈናፈኛ እና መተንፈሻ አጥቶ ተፈትልኮ ሲወጣ ትመለከቱታላችሁ፡፡

አንድ ወዳጄ የመከረኝ ትዝ አልኝ አሁን ባለዉ ሁኔታ ያለህ ክህሎት ብቻ ለስኬታማነት በቂ አይደለም ገንዘብ ወይንም ልበ ደንዳና የወንዝህ ልጅ ያስፈልገሀል ነበር ያለኝ፡፡ መቼም ይህ ሰዉ የወንዜ ልጅ መኸርገር ቆንጥጦ ያደማዉ ስለመሆኑ ብዙ መጠራጠር አያስፈልገዉም፡፡

ግራም ነፈሰ ቀኝ ወንዜ ልጅ አባዜ ማስወገድ የሚከብድ ነገር ነዉ ፤ የሚሻለዉ ነገር ግን ወንዛችን እዛ በየጎጣችን ቡልቅ ቡልቅ አያለች የምትፈሰዉ ምንጭ ሳትሆን ወንዛችን ሁላችንንም ያስተሳሰረን አባይ ከሆነ ነዉ ያን ጊዜ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የወንዜ ልጅ ይሆናል ፍትሀዊነትም ይነግሳል፡፡

“ ወንዛችን ታላቁ አባይ ይሁን ! ”

# 1.6 እኛ ስንዋደድ



ታላቁ መፅሐፍ እንዲህ ይላል “ **ፍቅር የሌለው ፈጣሪን አያውቅም ”** ። በሌላ ክፍል ደግሞ እንደዚህ ይላል “ ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አፅንታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ ”።

ወንድሜ ትላንት ጠላት ሲመጣ አጥንታችንን መግረን (ማገር አድርገን) ፣ ደማችንን አፍሰን ፣ ስንቁን አልፈን ድልን ተጎናፅፈን አርበድብደን ጥለነው ነበር። ያንን አረመኔ ነጭ አንተ አንገቱን እኔ ባቱን ስንሰይፈው ፣ በሽለላ በቀረርቶው ስንሞጋገስ ፣ ልባችን በወኔ ሲመታ ፣ ለሰንደቅ ዓላማችን ብለን እንባችን በዓይናችን ሲፈስ ፣ የሞተው ጓዳችንን አልቅሰን በክብር ስንሸኘው ፣ ቆላው ሀገሬ በሽታ ሲያንገላታኝ “ና” ብለህ ጠርተሀኝ ፤ እኔም ከደጋው ምድርህ ድርቅ ሲከሰትብህ አስጠልዬህ የነበረው ወንድሜ ምነው ዛሬ እንደዚህ ተጨካከንን ? ስንት ታሪክ አንድ ላይ እንዳልሰራን ? ከፍቅር ማዕድ አብረን እንዳልበላን ከፍቅር ውሃ አብረን እንዳልጠጣን ምነው ዛሬ እንደዚህ አይንህን ላፈር ተባባልን ?

አንቺስ ብትሆኚ እኅቴ በረሃ ወርጄ ጥሜን በዉሃሽ ያረካሽልኝ ፣ ፈርቼ እንዳልመለስ “አይዞህ ጀግናዬ ፣ አንበሳዬ” ብለሽ ያሞካሽሺኝ ምነው ዛሬ እንደዚህ ፊትሽን አዞርሽብኝ ? ገፅሽንስ ስለምን አጠቆርሽብኝ ?

አባቴ ካንተ ዘር ተከፍሎ የተገኘሁ አይደለሁምን ? ምን ተገኝቶ ነው ታዲያ ዛሬ ላይ አላውቅህም ያልከኝ ? እናቴ አንቺስ አምጠሽ ወልደሽኝ የለ እንዴ ? ከኋላዬስ እየተከተልሽ መግበሽኝ የለም ? እኔ አንቺን ፤ አንቺም እኔን አይደለንም እንዴ ? ምነዋ ታዲያ ውዴ ዛሬ ላይ በቃህኝ አልሺኝ ?

“ የኔ አባት ቶሎሳ ያንተ አባት ሰንደቁ ” እንዴት ወንድሜ ትለኛለህ እንዳትለኝ ፤ ረገረረ “ እናቴ ሽዊት ናት ያንተ ደግሞ ሲዲሱ ” እንዴትስ እኅቴ ትለኛለህ እንዳትይኝ። አባቴ ያልኩህ እናቴም ያልኩሽ “ መቼ ወለድንህና! አናውቅህም ” እንዳትሉኝ። ምክንያቱም ታውቁኛላችሁ። እኔን አለማወቅ መብት አይደለም። ፊታችሁን ብታዞሩ ፣ ጆሯችሁን ብትደፍኑ ፣ አይናችሁን ብትጨፍኑ ፣ ከኔ ብዙ ብትርቁም ታውቁኛላችሁ። ለምን? ምክንያቱም እኔ ብዙ ነኝ ፣ እኔ በመካከላችሁ ነኝ ፣ እኔ ሁለመናችሁ ነኝ ፣ እኔ የአዳም ልጅ ነኝ ፣ እኔ የሄዋን ፍሬ ነኝ ፣ እኔ ወንድማችሁ ፣ አኅታችሁ ፣ አባታችሁ ፣ እናታችሁ ነኝ ፣ እኔ ሀገራችሁ ነኝ ፣ እኔ ኢትዮጵያ ነኝ።

እኔን ስትገፋኝ የምትገፋዉ እኔን አይደለም ፈጣሪህን ነው የምትገፋው። አንቺንም ስጠላ ፈጣሪዬን ነው የጠላሁት። ለምን ? የእርሱ (የአምላክ) መልክና ምሳሌ የሆነውን ሰው መጥላት ፈጣሪን መጥላት ነውና።

እናም ውዶቼ ኑ እንዋደድ ፣ በአንድነት እንዘምር ፣ እኔን ገለህ አታሸንፍም ፣ አንተን ወግቼ ልቤን ደስ አይለውም ፣ ቤቴን ከልክዬህ ብቻዬን አይደላኝም ፣ ብቻዬን ተጉዤ ብዙም አልርቅም ፣ ፈጣሪን ሰድቤ መቼም ከፍ አልልም።

<u>**ወንድሜ**</u>

ብፎክር ባባትህ ፤ ብትኮራ ባባቴ

እናትህ እናቴ ፤ ሚስትህ ናት እኅቴ

ሀገርህ ሀገሬ ፤ መክበርህም ክብሬ

መሞትህ ሞቴ ነው ፤ ውርደትህ ውርደቴ

ናና እንዋደድ ፤ አባክህ በሞቴ።

እኛ ስንዋደድ ገበታችን ሞልቶ ይተርፋል ፣ የጠላታችን ጉልበት ይርዳል ፣ እንደ ንጋት ፀሀይ ተሙቀን አንጠገብም ፣ እንደ ሮማን አበባ መዓዛችን ያውዳል ፣ እንደ ቅዱሳንም መንደር ህያውነት ይነግሳል ፣ እንደ ድር እንበሳን እናስራለን ፣ ከችግራችን እኛ እንበልጣለን፣ ከሚያስጨካክኑን የሚያሳተባብሩን ይበልጣሉ ፣ ጸሎታችን ይሰምርልናል ፣ ከፈጣሪያችን ጋር እንኖራለን ፣ እናወራዋለን ፣ እናወቀዋለን ፤ የልቦናችን አይቶ ሀጢያታችንን ያስተሰረይልናል፡፡

ውዶቼ ፍቅር ያድለን! አሜን!

“ ትልቅ ነበርን ፤ ልብ የገዛን ቀን ፤ ትልቅ እንሆናለን !”

ምስጋና ለኢንጂነር ብሩክ ፈቃደ

# 2. ቴክኖሎጂ

" አሁን ላይ ወደድንም ጠላንም የቴክኖሎጂ ጥገኛ ሆነናል፡፡ በትንሹ እንኳን ፌስቡክ ሳንገባ ፤ ጎግል ሳንጎግል አንዉልም፡፡

.

.

.

ዶክተር ትምኒት አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ለዓለም እጅግ ብዙ ቱሩፋቶችን እንደሚያበረክት ታስረዳለች ነገር ግን ጥቁሮች በተለይ አፍሪካዉያን ከዚህ ቴክኖሎጂ ጋር እኩል መራመድ አለመቻላቸዉ ስጋት እንሚፈጥርባት ትናገራለች፡፡ "




" በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! "

# 2.1 አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ



አሁን 21ኛዉ ክፍለዘመን የቴክኖሎጂ ዘመን ነዉ፡፡ በዚህ ዘመን ነገሮች በዝግመታዊ ሳይሆን በቅፅበታዊ ለዉጥ ላይ ናቸዉ፡፡ አሁን ላይ ወደድንም ጠላንም እዉነታዉ የቴክኖሎጂ ጥገኛ ከሆንን ሰነባብተናል፡፡ በትንሹ እንኳን ፌስቡክ ሳንገባ ፤ ጎግል ሳንጎግል አንዉልም፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜያት ለዓለም አስፈሪ የነበረዉ የኒኩለር አለበለዚያም የተለያዩ ጁምላ ጨራሽ መሳሪያዎች ነበር አሁን ግን አስፈሪዉ እና ቢሊዮን ዶላሮችን እያንቀሳቀሰ የሚገኘዉ ይህ ሳይሆን ያለምንም መሳሪያ በጭንቅላታችን እና በኮምፒዉተሮቻችን የምንገጥመዉ የሳይበር ጦርነት እና የአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ እሽቅድምድሞሽ ነዉ፡፡

በእንግሊዘኛዉ አጠራር አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ (Artificial Intelligence) እየተባለ የሚጠራዉ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ዘርፍ የ5ተኛዉ ትዉልድ የኮምፒዉተር መገለጫ ባህሪ ሲሆን አላማዉም ኮምፒዉተሮች ልክ እንደ ሰዉ ልጆች የማገናዘብ እና ድርጊቶችን የመከወን ችሎታ እንዲኖራቸዉ ማድረግ ነዉ፡፡

ኮምፒዉተሮች ብዙ መረጃዎችን በመስጠት እንዲማሩ ይደረጋል ፤ በአስገራሚ ሁኔታ ለሰዉ ልጆች ለመለየት እና ለማታወስ እጅግ አዳጋች የሆኑ ነገሮችን ኮምፒዉተሮች ከሰዉ ልጆች ጋር በማይነፃፀር ሁኔታ ያለምንም ስህተት ሲለዩ እያየን ነዉ፡፡

አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ከተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ጋር በመጣመር ለአለም የተለያዩ ጥቅሞችን የሚሰጡ ዉጤቶች አሉት፡፡ የተነሳበት ዋና ዓላማዉም የሰዉ ልጆችን ሂወት ቀላል እና ምቹ ማድረግ ነዉ፡፡ ነገር ግን መድሀኒት እንኳን ሲዉጡት የጎንዮሽ ጉዳት እንዳለዉ ሁሉ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ጉዳቱ ቀላል አይደለም እያሉ የሚከራከሩ ወገኖችም አሉ፡፡

## የአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ጥቅሞች (ዉጤቶች) ተብለዉ ከሚነሱት መካከል

❖ የሰዉ ልጅ እንኳን ሊከዉናቸዉ ቀርቶ ከቶ ሊያስባቸዉ የማይችሉ ረጅም ጊዜ የሚፈጁ ስራዎችን ያቀላጥፋሉ፡፡

❖ ለግብርና እና ለምርምር ሳይቀር ከአየር ላይ ዉሀን ማመንጨት የሚችሉ ስራዎችን ሳይቀር እየከወነ ነዉ፡፡

❖ ሴንሰር ያላቸዉ ያለ ምንም አሽከርካሪ የሚከንፉ ተሽከርካሪዎች ፡፡ በየጉራንጉሩ ገብተዉ ግዳጅ ፈፅመዉ የሚመለሱ ሰዉ አልባ አዉሮፕላኖች ፣ የተለያዩ እጅግ ብዙ እና ዉስብስብ ምስሎችን የሚለዩ ማሽኖች ፣ ከኮምፒዉተር ጋር በተፈጥሮአዊ ቋንቋ መግባባት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ፣ የሰዎችን የእጅ ፅሁፍ ፣ ምስል እና ድምፆችን በቀላሉ መለየት የሚችሉ ኮፒዉተሮች ፣ ሰዉ ፈፅሞ ሊደርስበት የማይችለዉ ቦታ ሁሉ እየገቡ ምስል ይዘዉ የሚወጡ ድሮኖች እና ጌሞች ይገኙበታል ፡፡

❖ ብዙ ቋንቋዎችን መተርጎም መቻሉ፡፡ በአለም ላይ ያሉ ቋንቋዎችን ወደ ፈለግነዉ ቋንቋ የሚቀይርን ጎግል፡፡

❖ ዋትሰን (IBM) - በካንሰር ምርምር ላይ ሳይቀር በጤና ላይ እና ብዙ ነገሮች ላይ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ፡፡

❖ ሶፊያ - ኢትጲያዉያን የተሳተፉበት እንደ ሰዎች መረዳት ብሎም የፊት እንቅስቃሴ መስጠት የምትችል ፤ የሳዉዲ ዜግነት ያገኘች የመጀመሪያዋ ግዑዝ አካል፡፡

❖ ካፐቻ(CAPTCHA) - ኮምፒዎተሮች ከሮቦቶች የሚደርስባቸዉን ጥቃት የደህንነት ጥቃት ለመከላል የሚያገለግል፡፡

❖ ፅሁፍን ወደ ንግግር መለወጥ የሚያስችል (Text to Speech)

❖ የፈለግንበትን መረጃ መፈለጊያ (Google Search Engine)

❖ ጎግል ካርታ (Google Maps) በአለም ላይ የፈለገንን ቦታ በቅፅበት ባለንበት ሆነን የምናይበት

❖ የምንወደዉን ሙዚቃ እየገመተ የሚያመጣልን ዩ -ትዩብ

❖ የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም ልናዉቃቸዉ የምንችላቸዉን ሰዎች የሚያመጣልን ፌስቡክ

❖ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ በአንዳንድ መመዘኛዎች ከሰዎችም እጅግ ልቆ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ - ሰዎች ለመከወን የሚከብዳቸዉን ስራ በቀላሉ መከወኑ ፣ ጊዜ ቆጣቢነቱ ፣ አስተማማኝነቱ ፣ ያለምንም እረፍት እና ተጨማሪ ወጪ ስራዎችን መከወን መቻሉ ፣ ሰዎች ሊደርሱባቸዉ የማይችሉ ቦታዎች ስራዎችን መከወኑ ፣ የተሰጠዉን ትዕዛዝ ያለ ስህተት መከወን መቻሉ ፡፡

## የአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ጉዳቶች ተብለዉ ከሚነሱት መካከል

❖ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ከፍተኛ ወጪ እና እዉቀት ስለሚጠይቅ ድሀዎችን ያገላል ተብሎ ይወቀሳል፡፡

❖ ብዙ ዉሃ ባያነሳም የሰዉ ልጅ በተፈጥሮ የተሰጠዉን ፀጋ ለአንድ ግዑዝ አካል መስጠት ከተፈጥሮ ጋር የሚቃረን ነዉ የሚል ሀሳብ ያስነሳሉ፡፡

❖ ኮምፒዉተሮች ፕሮግራም ከተደረጉት ዉጪ እንደ ሰዉ ልጅ ነባረዊ ሁነቶችን በብልሀት ማገናዘብ እና መከወን ይሣናቸዋል ፡፡

- ❖ የሰዉ ልጅ አስፈላጊነት ላይ ጥያቄ ምልክት ያስቀምጣል - ማለትም የሰዉ ልጆችን ከስራ ገበታ ያፈናቅላል ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደ አሜሪካ ያሉ ሀገራት ምናልባትም ቴክኖሎጂ የሰዉ ሀይላቸዉን ከተካላቸዉ የሰዉ ልጅ ሰርቶ የመኖር ህልዉና አደጋ ሊጋረጥበት ይችላል፡፡
- ❖ የሀይል ሚዛን እንዲያጋድል ያደርጋል፡፡
- ❖ ምናልባትም ለጦር መሳሪያነት ከተጠቀምንበት ካየናቸዉ ነገሮች ይበልጥ እጅግ አዉዳሚ ሊሆን ይችላል የሚሉ ይገኙበታል፡፡

በተለያየ አጋጣሚዎች ስለ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ግንዛቤዉ ያላቸዉ ወይንም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ሰዎችን አግኝቼ ነበር፡፡ እስኪ የ 2ቱን ሀሳብ ለማስቀመጥ ልሞክር ፡-

ዶክተር አያልነሽ በለጠ መኖሪያዋን በአሜሪካ ያደረገች በ LAC + USC Medical Center Los Angeles , California ክሊኒካል ፋርማሲስት ስትሆን በ University of South California ደግሞ በረዳት ፕሮፌሰርነት ሙያ የምትሰራ ትዉልደ ኢትዮጵያዊት ናት፡፡ ምንም እንኳን በስራዋ እና በአገልግሎቷ አንቱ ብትባለም እኔ ካለኝ አክብሮት እና ቅርበት አንፃር ሁሌ እንደምላት አንቺ ብዬ ልቀጥል፡፡ ዶ/ር ደቦ የእርዳታ ድርጅት የሚባል ግብረ ሰናይ ተቋም ከአጋሮቿ ጋር አቋቁማ ለሀገሯ ልጆች ነፃ የትምህርት እድል ፤ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድጋፍ ከዚም በተጨማሪ እጅግ ሰፊ የማህበረሰብ አቀፍ ስራዎችን ትሰራለች፡፡

ዶ/ር አያልነሽ ከሰራቻቸዉ ስራዎች አንዱ በሆነዉ ደቦ የትምህርት ማዕከል ዉስጥ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ በተለይም ሮቦቲክስ ላይ ትኩረት አድርጋ የሮቦቲክስ ማዕከል በከፍተኛ ወጪ አቋቁማ ታዳጊ ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ በነፃ ከልጅነታቸዉ ጀምሮ ከቴክኖሎጂዉ ጋር አብረዉ እንዲያድጉ እያደረገች ትገኛለች፡፡ እኔም በተደጋጋሚ ተገኝቼ እንዳየሁት በዚህ ቤት ዉስጥ ብዙ ተስፋ ያላቸዉ ገና 7ኛ እና 8ኛ የክፍል ደረጃ ያላቸዉ ህፃናት እጅግ ብዙ ፈጠራዎችን ሲከዉኑ ፣ ራሳቸዉን ቻይና እና አሜሪካ ብለዉ ከፍለዉ በቴክኖሎጂ ሲሽቀዳደሙ እና ሲፎካከሩ ፤ የዲዛይን ስርቆት እርስ በእርሳቸዉ እንዳይደረግባቸዉ ሲጠነቀቁ ፣ ባስ ሲልም ተሰረቅን ብለዉ ማስረጃቸዉን ሲያቀርቡ ፣ የዓለምን እዉነት በአንድ ቤት ዉስጥ ሲከዉኑ አይቻለሁ እንደዚህም አለ ብዬ ለራሴ ተደንቄያለሁ፡፡ በዚህ ቤት ዉስጥ በአስገራሚ ሁኔታ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ተማሪዎች ጭምር በተቋማቱ የማያገኙዋቸዉን በስያሜ ብቻ የሚያዉቋቸዉ መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች እነዚህ ህፃናት ገና በለጋነታቸዉ ጠንቅቀዉ አዉቀዉ ይባስ ብለዉ አሻሽለዉ ሰርተዉባቸዋል፡፡

ለዶ/ር አያልነሽ ይሄን የሮቦቲክስ ማዕከል ለማቋቋም ምን እንዳነሳሳት ለጠየኳት ጥያቄ የሰጠችኝ ምላሽም ፤ ይህ ቴክኖሎጂ ዓለምን በቅፅበት እየለወጠ የሚገኝ ቴክኖሎጂ ቢሆንም እንኳን ሀገራችን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ግን የግንዛቤዉ ደረጃ ገና ስለሆነ ይሄንንም ክፍተት በመሙላት ወደፊት የሚመጡ ታዳጊ ህፃናት በዘርፉ የተሻለ ክህሎት ይዘዉ እንዲያድጉ እና የተሻለ ነገር በመፍጠር ተዕፅኖ እንዲፈጥሩ ለማስቻል በማሰብ እንደሆነ አስረድታኛለች፡፡ በምትኖርበት በሀገረ አሜሪካ ባለችበት የህክምና ሙያ ዉስጥ እንኳን ሳይቀር የአርቲፊሻል ኢንተሊጅንስ ሮቦቶች እጅግ ከባድ እና ጥንቃቄ የሚጠይቁ ህክምናዎችን ሳይቀር ከሰዎች በላቀ መልኩ እንደሚከዉን አብራርታልኛለች፡፡

በመጨረሻ ዶክተር አያልነሽ ሶፍያን የሚያክል አለምን የሚያስደንቅ ትልቅ ስራ ላይ ኢትዮጲዉያን አመርቂ ዉጤት ማስገኘታቸዉ በሀገሪቷ ያለዉን የዘርፉን መነቃቃት የሚያሳይ እንደሆነ እሷንም እጅግ እንዳስደሰታት እና የበለጠ ተስፋ እንድታደርግ እንዳደረጋት ገልፃልኛለች ፡፡

ዶክተር ትምኒት ገብሩ ባለ ብሩህ አዕምሮ ወጣት ስትሆን ገና በዚህ በወጣትነት ጊዜዋ እንደ አፕል እና ማይክሮሶፍት ያሉ የዓለም ቁንጮ የሆኑ ካምፓኒዎች መስራት የቻለች አሁንም በማይክሮሶፍት በአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ሪሰርቸርነት እሰራች ያለች የአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ቴክኖሎጂስት ናት፡፡ ዶክተር ትምኒትም ልክ እንደ ዶክተር አያልነሽ ሁሉ ለሀገሯ የተለያዩ ስራዎችን ትሰራለች ከነዚህም ዉስጥ ኢትዮጵያዉያን ሴቶች ቴክኖሎጂ ፈጣሪ እንዲሆኑ የምትሰራበት እና እንደ ዶክተር ጄላኒ ኔልስን ( ኢትዮ-አሜሪካዊ ወጣቱ የሀርቫርድ ተባባሪ ፕሮፌሰር ኮምፒዉተር ሳይንቲስት) ካሉ ኢትዮጵያዉያን እና የሌሎች ሀገራት ዜጎች ጋር በመሆን የሚሰሩበት አዲስ ኮደር ፕሮግራም ይገኝበታል፡፡

ይቺን ለኢትዮጵያዉያን የዘመኑ ምሳሌ የሆነች ቴክኖሎጂስት የማግኘት እድል ገጥሞኝ ነበር፡፡ ዶክተር ትምኒት አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ለዓለም እጅግ ብዙ ቱሩፋቶችን እንደሚያበረክት ታስረዳለች ነገር ግን ጥቁሮች በተለይ አፍሪካዉያን ከዚህ ቴክኖሎጂ ጋር እኩል መራመድ አለመቻላቸዉ ስጋት እንሚፈጥርባት ትናገራለች፡፡ የእኛ ከአለም ጋር እኩል አለመጓዝ እንደ አሜሪካ እና ሌሎች የአለም ታላላቅ ሀገራት በሌሎች ሀገራት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዲኖራቸዉ ያስችላቸዋል በማለት ፍርሀቷን ታንፀባርቃለች፡፡ እሷም ይሄንን በማሰብ ለሀገሯ የቻለችዉን አስተዋፅኦ ለማበርከት ቀና ደፋ እያለች ትገኛለች፡፡

አሁን ላይ ማሽኖች እንደ ሰዉ ማሰብ ጀምረዋል ፡፡ በፍጥነት በመከወን ፤ ብዙ መረጃ በመሸከም እና ነገሮችን ያለ ስህተት በመለየት ደግሞ እንዲያዉም ከሰዉ ልጆች የበለጠ ርቀዉ ሄደዋል፡፡ የሰዉ ልጆችን መተዳደሪያ የሆነዉን እና የሰዉ ልጅ እድሜዉን ሠዉቶ እና ተምሮ ያገኘዉን ስራ ሊቀሙት ከደጃፉ እያነፈነፉ ይገኛል፡፡ በአለም ላይ አሁን አሁን እጅግ ጥንቃቄ የሚጠይቁ ስራዎችን የነርቭ ቀዶ ህክምናዎችን ጭምር ሮቦቶች ያለምንም ስህተት ሲያጠናቅቁ እየተመለከትን ነዉ፡፡ ለሰዉ ልጅ የሚያዳግተዉን እና መቋቋም የማይችለዉን የዐየር ፀባይና አስቸጋሪ ስራ በሚያስደንቅ ሁኔታ እና እጅግ በፈጠነ መልኩ እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

አሁን ከዓለም ጋር እኩል ለመራመድ ሁለት አማራጭ ነዉ ያለን የመጀመሪያዉ እና ዘላቂ መፍትሄ የሚሆነዉ ዜጎቻችን ከሮቦት እና ማሽኖ የበለጠ ብሩህ አእምሮ ያላቸዉ ናቸዉ እና አዕምሮአቸዉን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ማድረግ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ያለ የሌለንን አቅማችንን ተጠቅመን አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ቅንጦት ያለመሆኑን ተረድተን ትኩረት ሰጥተን ከኋላ መከተል፡፡ ይህ ካለሆነ ግን የሚመጣዉ ጊዜ እጅግ አስፈሪ እና ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እጃችንን ተጠምዝዘን የምንረታበት ጊዜ መሆኑ አይቀሬ ነዉ፡፡

“ በሰመመን ዉስጥ ነን ፤ የነገን ህልዉናችንን ለማስቀጠል ዛሬ ላይ አይናችንን እንግለጥ፡፡ ”

# 2.2 የሳይበሩ ሩጫ



ኮምፒዉተርን መሰረት ያደረገ ኑሮ መኖር ካደረግን ሰንበትበት ብለናል፡፡ ወደንም ይሁን ሳንወድ ጥገኞች እየሆንን እንገኛለን ፤ ብዙ ኮምፒተሮች አንድ ጋር ተጣምረዉ ደግሞ በኢንተርኔት አማካኝነት ግንኙነት በማድረግ ህይወትን ቀላል እያደረጉልን ይገኛሉ ፤ ይሄንን ስብስብ ሲስተም ሰንል እንጠራዋን፡፡ እነዚህ የኮምፒዉተር ሲስተሞች ዉጪ ሀገር ካሉ ቤተሰቦቻችን ጋር ፊት ለፊት ለማዉራት ከማስቻል ጀምሮ እስከ ገንዘባችንን በፈለግንበት ቦታ ሰዓት ማንቀሳቀስ እንድንችል አድርገዉናል፡፡ በተገቢዉ አገልግሎት ካሰጡን ደግሞ ህይወታችን ሲስተጓጎል ይታያል፡፡ ለምሳሌ አብዛኛዉ ሰዉ ከሚጠላቸዉ ቃል አንዱ የሆነዉ ሲስተም ጠፍቷል የሚለዉን እየሆነ መጥቷል ፣ ባንክ ላይ ሄደን ሲስተም ከሌለ ብራችንን መጠቀም አንችልም ፣ ቀበሌ ሄደን ሲስተም ከተቋረጠ ጉዳያችንን ሳንጨርስ አራዝመን እንመለሳለን ፣ ከዚህም ከፍ እያለ ደግሞ የጤና መረጃዎቻችን ሲስተም ላይ ሲቀመጡ ድንገተኛ እንኳን ታመን ሄደን ሲስተም ሲቋረጥ የበፊት መረጃችንን ማግኘት ይሳነናል ፣ ፈተና ልንፈተን ሄደን ሲስተም የለም ተብለን እንመለሳለን፡፡ ስለ ጊዜያዊ ትንሹ የሲስተም መቋረጥ ምን ያህል አደጋ እንዳለዉ ለማንሳት የሞከርኩት አለምን እየተፈታተናት ስላለዉ የሳይበር ጥቃት ለማዉጋት እያኩበኩብኩኝ ስለሆነ ነዉ፡፡

በ1988 ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የሳይበር ደህንነት የሚለዉ ቃል ጥቅም ላይ የዋለዉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በአሜሪካ 60 000 ኮምፒዉተሮችን በአንድ ጊዜ ከጥቅም ዉጪ ለማድረግ ያጠቃዉ ወርም ነበር፡፡ የሳይበር ደህንነት ትርጉሙም በኢንተርኔት አማካኝነት የተያያዙ የክፍያ ስርዓቶችን ፣ ዌብሳይቶችን ፣ የግለሰብ መጠቀሚያ አካዉንቶችን ፣ የመሰረተ ልማቶችን ኢላማ ያደረገ ጥቃትን መከላከል መቻል ነዉ፡፡

የሳይበር ጥቃት ህገወጥ በሆነ መንገድ ኢንተርኔትን እና ኮፒዉተሮችን አጣምሮ እዉቀትን በመጠቀም ያለ ፈቃድ መረጃ መመዝበር ከዚህም ሲያልፍ ከጥቅም ዉጪ ማድረግ ነዉ፡፡ በየአመቱ ከ 1 ዜታባይት በላይ የዲጂታል መረጃዎች ይዘዋወራሉ፡፡ አብዛኞቹ ጥቃቶችም እነዚህ መረጃዎችን ማግኘት ላይ ትኩረቶቻቸዉን ያደርጋሉ፡፡

ለሳይበር ጥቃት እንደ መሳሪያነት የሚያገለግሉ ለዚህ ድርጊት ታልመዉ የሚዘጋጁ የኢንተርኔት ቫይረሶች እና ወርሞች ሲሆኑ ከሚተላለፉባቸዉ መንገዶ ዉስጥም እንደ ፍላሽ ያሉ መጠቀሚያዎች ፣ ፋይል ከኢንተርኔት ዳዉንሎድ በሚደረግበት ጊዜ እና የኢሜይል አታችመንት ፋይል ሲላክ አብረዉ በመቀላቀል ዋናዎቹ መንገዶች ናቸዉ፡፡

## የሳይበር ደህንነት ጥቃት አይነቶች

የሳይበር ጥቃት እዉቀቱ እና ችሎታዉ ያላቸዉ ኤክስፐርቶች የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም የሚያደርጉት የዘመኑ ፍልሚያ ነዉ፡፡ እነዚህም የተለያየ አይነት ስያሜ እና ቅርፅ ሊኖራቸዉ ይችላል -

1. **ዲኒያል ኦፍ ሰርቪስ** (Denial of Service) - አንድ ትልቅ ሰርቨር ኮምፒዉተርን የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም እጅግ ብዙ መረጃዎችን በመለከ ማጨናነቅ እና ኢላማ ዉስጥ ያለዉንም ኮምፒዉተር ከአቅም በላይ ሲሆንበት ስራ እንዲያቆም በዚያም ምክንያት ከጥቅም ዉጪ ማድረግ ነዉ፡፡
2. **ዲትሪቢዉትድ ዲኒያል ኦፍ ሰርቪስ** (Distributed Denial of Service) - ይሄም በተመሳሳይ እጅግ ብዙ መረጃዎችን በመላክ ኢላማ ውስጥ የገባዉን ኮምፒዉተር ድምጥማጡን ማጥፋት ሲሆን ልዩነቱ ጥቃቱ እና መረጃዎች የሚመጡት ከተወሰኑ ኮመፒዉተሮች ሳይሆን ብዙ ቀድመዉ በተጠቁ ዞምቢ ኮምፒዉተሮች በመታገዝ ነዉ፡፡ በየቀኑ ከ150 000 በላይ ኮምፒዉተሮች ምናልባትም የእኛን የግል ኮምፒዉተር ጨምሮ የዞምቢይ ጥቃት ሰለባ ይሆናሉ፡፡ እኛም ኮምፒዉተራችን ሰለባ ይሁን አይሁን ሳናዉቅ ሀከሮች ግን ኢንተርኔት ላይ ስንሆን የኛን ኮምፒዉተር ሌሎች አገልግሎቶችን ለማጥቃት ይጠቀሙባቸዋል፡፡
3. **በቫይረስ** (Virus) - ከተለያዩ ፋይሎች እና ፕሮግራሞች ጋር ራሱን በመቀላቀል ከአንዱ ኮምፒዉተር ወደ ሌላ ኮምፒዉተር እንዲተላለፍ በማድረግ ጥቃትም እንዲፈፅም የሚያደርግ ነዉ፡፡
4. **ዎርም** (Worm) - ከቫይረስ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ልዩነቱ ወርም ራሱን ቶሎ ቶሎ በማባዛት ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርስ በተጨማሪም ከአንድ ወደ አንድ ኮምፒዉተር ያለ ቀጥተኛ ሰዉ ንክኪ መተላለፍ ይችላል፡፡
5. **ስፓም** (Spam) - በጣም ብዙ ኢሜይሎችን እና መረጃዎችን በዉስጣቸዉ ድብቅ አደጋ በመያዝ የብዙዎችን ኢሜይሎች እና ኮምፒዉተሮች ሰለባ እያደረገ የሚገኝ የጥቃት አይነት ነዉ፡፡
6. **ትሮጃን ሆርስ** (Trojan Horse) - በጣም ጠቃሚ የሆኑ አፕሊኬሽናች ዉስጥ ራሱን እንዲደብቅ ተደርጎ ሰዎች አፕሊኬሽኑን ጭነን ስንጠቀም ትሮጀን ሆርስም አብሮ ጥቃቱን ይጀምራል፡፡
7. **ኪይ ሎገር** (Key logger) - ይሄኛዉ ደግሞ ከላይ ካሉት ጥቃት ለየት የሚያደርገዉ ቀጥተኛ ጉዳት ከማድረስ ይልቅ ልክ እንደ ሰላይ ያለ እኛ እዉቅና እያንዳንዷን እንቅስቃሴዎቻችንን ከኮምፒዉተር ላይ እየመዘገበ የሚያስተላልፍ አደገኛ ሶፍትዌር ነዉ፡፡

## ሳይበር ምን ያህል ያሳስባል ?

እኛ ጎግልን መረጃዎችን ለመፈለግ እንደምንጠቀምበት ሁሉ ሾዳን የተባለዉ ብሮዉዘር በዓለም ላይ ያሉ ተጋላጭ የሆኑ ኔቶርክ እና ሲስተሞችን ቁልጭ አድርጎ ለሀከሮች የሚያሳይ ነዉ፡፡ በዚህም ብሮዎዘር ላይ እንደሚታየዉ አብዛኛዉ የአለም ኔቶርክ ለጥቃት ተጋላጭ ነዉ፡፡

እኛ ገና በአግባቡ ወደ ሰለጠነዉ ዓለም ስላልተቀላቀልን ያን ያህል ሀሳብ አልሆነብንም እንጂ ዓለም እንቅልፍ ካጣች ሰነባብታለች፡፡ ነገሮች ሁሉ ወደ ሲስተምነት እየተቀየሩ በመጡባት ዓለም መረጃዎችን ከጥቃት መከላከል ትልቁ ፈተና እየሆነ መጥቷል፡፡ የአለም ትልልቅ የደህንነት እና የስለላ ቢሮዎች ትኩረታቸዉን ወደ ሳይበር ካዞሩ ሰነባብተዋል፡፡ እንደ የአሜሪካዉ ሲአይኤ ፣ የእስራኤሉ ሞሳድ የራሺያዉ ኬጂቢ በተጨማሪም የቻይና ፣ ሰሜን ኮርያ እና እንግሊዝ የመሰሉ የአለም ቁንጮ ሀገራት የስለላ ድርጅቶች አንዱ የአንዱን ድክመት በመጠቀም ሀያልነታቸዉን ለማስከበር ደፋ ቀና እያሉ ናቸዉ፡፡ በኛም ሀገር ምንም አንኳን ኢትዮጵያ ሳታላይት ልታመጥቅ መሆኑን ስንሰማ ብዙዎቻችን ሆዳችን ሳይሞላ ብለን የጮህንባት ሀገር ብትሆንም ኢንሳ ብቀጥንም ጠጅ ነኝ ፣ ብዙ ጥቃቶችን መልሻለሁ እያለን ይገኛል፡፡ እንደዚህም ቢሆን ገና በብዙ ርቀት ሀገራችን ዉስጥ ግንዛቤዉ እና ትኩረቱ ይቀራል፡፡ የታለመ ከባድ ጥቃት ቢፈፀምብን የመከላከል አቅሙ ይኖረናል ብሎ ማሰብ ከባድ ነዉ፡፡

አሜሪካ በየአመቱ ከምታወጣቸዉ በጀቶች ዉስጥ ከፍተኛዉን ጉርሻ ሳይበር ይወስዳል፡፡ በዚህ በሰለጠነ ዘመን መረጃን መደበቅ የማይቻልበት ዘመን ሆኗል፡፡ አንድ ሀገር የሌላዉን ሀገር መረጃ በመመንተፍ መረጃ ጠላፊዉ ከተጠቂዉ ሀገር በላይ ስለ ሀገሪቱ ግንዛቤ እንዲኖረዉ ይጥራል፡፡ አሁን ማን ያምናል አስፈሪዉ እና ታላቁ ሞሳድ ከኢትዮጵያዉያን በላይ ስለ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ ፤ በተጨማሪም ክስተቶች የተተነተነ እና በቂ መረጃ አለዉ ቢባል፡፡በዘመነ ኢንተርኔት ምንም የሚደበቅ ነገር አይኖርም ፤ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎቻችን እንደ አሜሪካ ያሉ ባለ ፈርጣማ ጡንቻ ሀገራት ባስወነጨፏቸዉ ሳቴላይቶች ቁጥጥር ስር ከዋለ ሰነባባቷል፡፡

## የሳይበሩ አስፈሪ ንጉሶች

የ24 ዓመቱ አልጀሪያዊ ሀምዛ ቤንዴላጂ እጅግ አስፈሪ ግለሰብ ነበር ፤ ከ217 በላይ የዓለም ባንኮችን ብቻዉን ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ የመዘበረ ሰዉ ነዉ፡፡ እጅግ ብዙ አየር መንገዶች ሳይከፍል በፓስፖርት የተጓዘ መረጃ ጠላፊ፡፡ ይሄ ሰዉ የመዘበረዉን ብር ሙሉ ለሙሉ ለአፍሪቃዉያን እና ለፍልሰጤሞች በእርዳታ ለግሷል፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳን ብዙዎች ቢከራከሩለትም አሜሪካ ጥፋተኛ ነህ አልምርህም ብላ በሞት ስቅላት እንደቀጣችዉ የሚሳይ ምስል አስተላልፋለች ፤ ሀከሩም ሲሰቀል ፊቱ ላይ ከፍተኛ ፈገግታ የሚታይበት ምስል ይፋ ተደርጓል፡፡ አሁንም ቢሆን ምስሉን የሚጠራጠሩ ሀምዛ እንዳልሞተ እና አሜሪካ በድብቅ እያሰራችዉ እንደሆነ የሚከራከሩ ሰዎች አሉ፡፡

አኖነይመስ የተባለዉ ማንነታቸዉ በግልፅ የማይታወቁ በተለያዩ ዓለማችን ክፍሎች የሚገኙ የሀከሮች ስብስብ ሲሆን እስካሁን ድረስ በብዙዎች በመፈራት እና ብዙ መረጃዎችን በመመዝበር የሚስተካከለዉ የለም፡፡ ይህ ቡድን መንግስታዊ እና የኮርፖሬት ድርጅቶችን እንቅልፍ ከነሳቸዉ ሰነባብቷል፡፡

ጆናትን ጀምስ የ15 ዓመት ታዳጊ እያለ የናሳ እና የአሜሪካ መከላከያ ዲፓርትመንትን ሀክ አድርጓል፡፡ይሄም ጆናታንን በእድሜ ትንሹ ትልቅ ድርጅቶችን ያጠቃ ሀከር አድርጎታል፡፡ ጆናታን ከናሳ 13 ኮምፒዉተሮችን መጠቀም ሲችል ከ 2 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመቱ ሶፍትዌሮችን እና መረጃዎችን መዝብሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ሲስተሙ ለ21 ቀናት ሲቋረጥ ይሄንንም ለመመለስ ከ40 000 ዶላር በላይ ወጪ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጆናታን የአሜሪካን መከላከያ ዲፓርትመንት በተለይም የመከላከያ አደጋ መቀነስ ኤጀንሲን በመስበር የመጀመሪያዉ ሀከር ሲሆን ይሄም አሜሪካ ሊገጥሟት የሚችሉ አደጋዎች የሚመዘገብበት እንደመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ እየተደረገበት ሾልኮ መረጃ መዝረፉ አስደናቂ አድርጎታል፡፡ ጆናታን ምንም እንኳን ህፃን ስለነበር በአሜሪካ ህግ ከ6 ወር ከኮምፒዉተር መራቅ ያለፈ ከባድ እርምጃ ባይወሰድበትም ከ 10 ዓመት በኋላ በ25 ዓመቱ ራሱን ከዚህ ድርጊት ማቀብ ባለመቻሉ ራሱን በራሱ ሊያጠፋ ችሏል፡፡

## የመረጃ ምዝበራዎች እና የካምፓኒዎች ዉድመት እዉነታዎች

በ2010 እና በ2015 መካከል ያለዉን ልዩነት ብንመለከት የሀኪንግ እና መረጃ ምዝበራ እዳ በ176 በመቶ ጭማሬ አሳይቷል፡፡ በ2018 ብቻ ደግሞ ዲስትሪቢዉትድ ዲኒያል ሰረቪስ በ500 ፐረሰንት ጨምሮ ታይቷል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የኮምፒዉተር ወርም የተፈጠረዉ እኤአ በ1979 ሲሆን የኮምፒዉተር ቫይረስ ደግሞ 1983 ነዉ፡፡ አይ ላቭ ዩ የተሰኘዉ ቫይረስ በ2000 እኤአ ዓ.ም በ 2 ቀን ብቻ ከ45 ሚሊዮን በላይ ኮምፒዉተሮችን በማጥቃት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ በዚሁ ቫይረስ አማካኝነት በ ጃንዋሪ 25 2003 የዓለም መገናኛ ኢንተርኔት ተቋርጦ ነበር፡፡

በ2009 በዩኤስኤ ብቻ ከ222 ሚሊዮን በላይ መረጃዎች ድምጥማጣቸዉ ጠፍቷል ፤ ይሄም የኦባማን መንግስት ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ወደ ጠንካራ እርምጃ እንዲገባ አስገድዶታል፡፡ በአንድ ጊዜ ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ በአንድ ጥቃት ብቻ ከኤትኤም መዘረፉም የቅርብ ጊዜ ትዉስታችን ነዉ፡፡

ታዋቂ የኢሜይል አገልግሎት ሰጪ የሆነዉ ያሁ ከቢሊዮን በላይ ተጠቃሚዎች አካዉንት ተመዝብሯል ወይንም ሀክ ተደርጓል፡፡ ይሄም ሀያልነቱን ለጂሜይል እንዲያስረክብ አስገድዶታል፡፡

ከስራ ጋር ተያያዥ የሆነዉ ሁላችንም የምንጠቀምበት የሊንክድ ኢን የሶሻል ሚዲያ ከ167 ሚሊዮን በላይ አካዉንቶች መረጃ በጠላፊዎች ተመዝብሮበታል፡፡

ሁላችንም በምንጠቀምበት በዓለም ላይ ከ2 ቢሊዮን በላይ ተጠቃሚ ባሉት ፌስቡክ እንኳን በየቀኑ ከ160 000 በላይ አካዉንቶ ሀክ ይደረጋሉ፡፡

ድሮፕ ቦክስ መረጃዎቻችንን ክላዉድ ላይ እንድናስቀምጥ የሚያስችለን ፕላትፎርም ሲሆን፡፡ የ68 ሚሊዮን ድሮፕ ቦክስ አካዉንቶች ከነመረጃዎቻቸዉ የጥቃት ሰለባ ሆነዋል፡፡

በ2011 የሶኒ የጌም ኔቶርክ በደረሰበት ጥቃት ከ77 ሚሊዮን በላይ ደንበኞቹን መስተጓጎላቸዉ እና ከፍተኛ ዉድመት መድረሱ በተጨማሪም በዚሁ ዓመት የሲአይኤ ዌብሳይት እና ሲስተም አገልግሎት ለማቆም ተገደዉ ነበር፡፡

የታዋቂዉ ድርጅት አፕል አይክላዉድ መረጃ ማከማቻ በ2014 በደረሰት ጥቃት ብዙ መረጃዎች ተመዝበረዋል፡፡ ከ200 በላይ እዉቅ አሜሪካዉያን ያልተፈለጉ ምስሎች እና ፎቶዎችን ጨምሮ በአደባባይ ከስልኮቻቸዉ ተሰርቀዉ ለህዝብ ይፋ ተደርገዉባቸዋል፡፡

የሳይበር ጥቃቶች ከመረጃ ምዝበራ በተጨማሪ አሁን ላይ ትኩረታቸዉን ወደ ዉሀ ፤ ባቡር ፤ ጋዝ እና ኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶች ላይ አነጣጥረዋል፡፡በአሜሪካ የኢነርጂ ዲፓርትመንት ላይ በተለይም ከቻይና ፤ ሰሜንኮርያ እና ራሺያ ያነጣጠሩ በየቀኑ ከ10 ሚሊዩን በላይ ጥቃቶች ይሰነዘራሉ፡፡

በ2009 ተደረገ ሌላ ጥናት ከ60 በመቶ በላይ ተቀጣሪ ድርጅቶቻቸዉን ሲለቁ የመረጃ ስርቆት ይፈፅማሉ፡፡ ይሄም ተጋላጭነቱን ይጨምረዋል፡፡ በአማካይ አንድን ሀክ የተደረገ ነገር መፍትሄ ለመስጠት 170 የስራ ቀናተን ይፈጃል፡፡

በጁሊያን አሳንጅ የተመሰረተዉ ዊኪ ሊክስ የተመዘበሩ መረጃዎ የሚለቀቁበት ሳይት ሲሆን ጁሊያን ምንም አይነት የግል የሚባል መረጃ የለም ሁሉም ለጥቃት የተጋለጠ እና በሀከሮች እጅ ስር የሆነ ነዉ ይላል፡፡

## እንዴት ራሳችንን ከሳይበር እንከላከል?

ሀከሮች በግለሰብ ደረጃ የሚያደርጉት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ኢሜይል ፤ የክፍያ ፓስዎርዶች አይነት መረጃዎችን ከሞጨለፉን በኋላ ይደብቁብናል ፤ በመቀጠልም በምንያህል ዋጋ ሊመልሱልን እንደሚችሉ ይደራደራሉ ፤ በመጨረሻም በገዛ ንብረታችን ክፍያ ስንፈፅምላቸዉ መልሰዉ ንብረታችንን ይልኩልናል፡፡ ይህ በብዙ ሀገራት የተለመደ ሲሆን በኢትዮጵያም በጥቂት ዓመት ዉስጥ ወረረሽኝ እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም እያንዳንዳችን ራሳችን ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል የሚከተሉት አርምጃዎች መዉሰድ አለብን -

- ❖ ፓስዎርድ ስንጠቀም ፊደላትን ፣ ቁጥሮችን ምልክቶችን አቀላቅሎ በጣም ጠንካራ ፓስወርድ እንዲኖረን ያስችለናል፡፡
- ❖ ለተለያዩ አካዉንቶች የተለያዩ ፓስወርዶችን መጠቀም አንዱ ሀክ ቢደረግ የሌላዉን ያድንንልናል፡፡
- ❖ የማይገመቱ ረዘም ያሉ ፓስዎርዶችን መጠቀም ፤ ባለ 6 ሆሄ ብቻ ሲሆን በ10 ደቂቃ ዉስጥ ሀክ ሊደረግ ሲችል ፤ ሁለት ፊደል እና ቁጥሮችን ብንጨምር ግን ሀኪንጉ እስከ 3 አመት ሊፈጅ ይችላል፡፡
- ❖ እንደ ዌብ ካም ፣ ቴሌቪዥኖቻችን እና የኮምፒዉተሮቻችን ካሜራዎች ከኔትርክ ጋር ሲያያዙ በጥንቃቄ እና አስፈላጊ በሆኑ ሰዓታት ብቻ መጠቀም ፤ አለበለዚያ የተደበቁ ድርጊቶቻችን በሌሎች እይታዎች ስር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- ❖ በተለይ እንደ ቻይና ያሉ ሀገራት በሚያመርቷዉ ምርቶች ላየ ደግሞ ሰፕላይ ቼይን የሚባል የጥቃት አይነት አለ ይሄ ጥቃት የሚሰነዘረዉ እንደ ሞባይል ስልክ ፣ ካሜራ እና ሰርቨር የመሳሉትን እቃዎች ስንገዛ አምራቾች ለስረቆት የሚያገለግላቸዉን በጣም ትንንሽ ችፖች አብረዉ ይቀብራሉ ስለዚህ የኛ የምንለዉ ስልክ ያለ እኛ እዉቅና በአንድ ጊዜ ሌሎች ሰዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ስለዚህም የምንገዛቸዉ ስልኮች ከታወቁ እና አስተማማኝ ካምፓኒዎች ቢሆን ይመረጣል ፡፡
- ❖ በአካዉንታችን እንደ 2 ስቴፕ ቬሪፊኬሽን ያሉ መንገዶችን መጠቀም አካዉንታችን ፓስዎርድ ከመቀየሩ በፊት እዉቅና እንዲኖረን ያስችለናል፡፡

- ዋይፋይ ኔትዎርክ ኮኔክት ከማድረጋችን በፊት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አላስፈላጊ የሆኑ ምስሎችን እና መልዕክቶችን አለመላላክ ፤ ምክንያቱም መልዕክቶቹ ከላክንለት ሰዉ ዉጪ በኔቶርክ ላይ እያሉ ሌሎች ሰዎች ጋር በቀላሉ ሊገቡ ስለሚችሉ፡፡
- አፕሊኬሽኖቻችን አፕዴት ማድረግ ፤ እንዲሁም ከአምራቾቻቸዉ በቀጥታ ዳዉንሎድ ማድረግ ተያይዘዉ ከሚመጡ ጥቃቶች ይሰዉሩናል፡፡
- የኢሚይል መልዕክቶችን ከመከፈታችን በፊት የላኪዉን አድራሻዉ ማረጋገጥ፡፡
- ሰራተኞቻችን ከድርጅቶቻችን ሲለቁ አካዉንታቸቸዉን ወዲያዉኑ ማስወገድ፡፡
- እንደ ኬይ ሎገር ያሉ ሶፍትዌሮች ሰዎች እንዳይጭኑብን ኮምፒዉተራችንን አሳልፈን አለመስጠት፡፡
- በተቻለ መጠን ብሮዉዘራችን ላይ ፓስዎርድ ሴቭ አለማድረግ ምክንያቱም የኮምፒዉተሩን ፓስዎርድ የሚያዉቅ ሰዉ ሁሉ ፓስዎርዶቻችንነ ሊያገኛቸዉ ስለሚችል፡፡
- ለቴክኒካል ሰዎች ደግሞ ኔቶርካችንን በፋየር ዋል መገደብ ይኖርብናል፡፡

የሳይበር ስፔሻሊስቱ የሂልኮ ባለቤት እና መስራች ዶ/ር አህመድ ሰይድ በአንድ ወቅት በቴክ-ቶክ ሰለሞን ሾዉ ላይ ቀርበዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ምንም እንኳን ከፍተኛ የአይቲ ሲስተም ዝርጋታ መስፋፋት ቢኖርም በደህነቱ ላይ በቂ የሆነ ስራ እየተሰራ እየደለም፡፡ ግንዛቤዉ በጣም ገና ነዉ ግንዛቤዉም ያለበት ቦታ ወደ ትግበራ ለመሄድ እጅግ መዘግየት ይታይል፡፡ ኤትኤም ፣ ፔይመንት ካርዶች ፣ ተጋላጭነታቸዉ ይጨምረዋል፡፡ ጥቃት ደርሶብናል አልደረሰም የሚለዉን እንኳን ማወቅ የሚቻልበት ሁኔታ ዉስጥ አይደለንም ፤ ሲሉ ተደምጠዋል ስለዚህ ነገ ከማዘን ዛሬ ደህንነታችን እንጠብቅ፡፡

" ቅስማችን ሳይሰበር ፤ ትኩረት ለሳይበር ! "

# 2.3 የዘንድሮ ቢዝነስ




ዉሎ እንዴት ነዉ ፤ አንዴትስ እያለፈ ነዉ በእኔ በኩል የስራ ቀን እንደመሆኑ ደፋ ቀና እያልኩኝ ነዉ፡፡ በእኔ በኩል ዛሬ ከማከብራቸዉ እና ብዙ ከተማርኩባቸዉ ጓደኞቼ ጋር ተስፋ የሰነቅንበትን እና ለኢትዮጵያዉን ያለምንም ክፍያ የቴክኖሎጂን ትምህርት በነፃ ለማድረስ ያቋቋምነዉን የኩራዝ-ቴክ (www.kuraztech.com) ፐላትፎርም የተሻለ ለማድረግ እየሰራን እንገኛለን፡፡ እናም በዚህ ምክንያት ዛሬ ብዙዎቻችን ተዕፅኖዉን ስላልተረዳነዉ ነገር ግን ዓለምን እየሾፈራት ስለሚገኘዉ የፐላትፎርም ቢዝነስ ምንነት ትንሽ ልፅፍ ወደድኩኝ፡፡

ከ 100 ዓመት በፊት ዓለም ትኩረቷ ሁሉ ወደ ኢንደስትሪ መር እንቅስቃሴ ነበር፡፡ እጅግ ብዙ ነገሮች በተለይ ከመካኒካል ጋር የተያየዙ ዓለም እስካሁን የምትጠቀምባቸዉ ነገሮች ሁሉ የተፈጠሩበት ድንቅ ጊዜ፡፡ አሁን ባለንበት ጊዜ ደግሞ በተለይም የክፍለዘመኑ ምርጥ ፈጠራ ብዬ አፌን ሞልቼ የምናገርለት ኢንተርኔት ከመጣ ጀምሮ አለም ከመንደርም ቀርባ ጎረቤት እንድትሆን ሲያስችላት ፣ ፈጠራዎች ደግሞ ከመካኒካልነት ወደ የማይነካ እና የማይዳሰስ ሶፍትዌርነት እንዲያተኩሩ ሆኗል፡፡

ዛሬ ላይ አዲስ አበባ ላይ ያለ አንድ ባለሙያ ቤቱ ቁጭ ብሎ አሜሪካ ዉስጥ የሚገኝ ትልቅ ካምፓኒ ሰራተኛ ሆኖ እየሰራ ክፍያዉን የሚቀበልበት ፣ ቂርቆስ ላይ አሲድ የደፋ በኢንተርፖል ከአዉሮፓ ተቀፍድዶ ተመልሶ ቂርቆስ የሚታሰርበት ዘመን ነዉ፡፡ ስልካችንን ብቻ ተጠቅመን ሶማሌ ተራ ሳንሄድ ያማረንን መኪና ፣ ቀልባችንን የሳበዉን ቤት የምንገበያይበት ፣ ጥበቃ ሳይኖረን አዲስ አበባ ላይ ሆነን የሐዋሳ ንብረታችንን ደህንነት በስልካችን የምንከታተልበት ፣ ምድር ላይ የተደበቀ ነገር አለ ለማለት የሚያስቸግርበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡

ቴክኖሎጂ ትልቅ አሻራ እና ተፅፅኖ ካሳደረባቸዉ ዘርፎች ዉስጥ አንዱ እና ዋነኛዉ ቢዝነስ ነዉ፡፡ ቴክኖሎጂ ከሚዳሰሱ በፈብሪካ ዉስጥ ግብዓቶችን ተጠቅመን ከምናመርታቸዉ ምርቶች ይልቅ በኮምፒዉተሮች አማካይነት የሚሰሩ እና የሚተገበሩ ሶፍትዌሮች ገበያዉ ላይ ፈርጣማ ጡንቻቸዉን እንዲያሳርፉ አድርጓቸዋል፡፡

ፕላትፎርም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን አንድ ጋር አጣምሮ የሚይዝ ሲሆን በስሩም የተለያዩ መተግበሪያዎች እና የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን የያዘ ባለ ብዙ አማራጭ (MULTISIDED) ቢዝነስ ስትራቴጂ ነዉ፡፡

የፕላትፎርም ቢዝነስ ገቢ ለማስገኘት ሁለት አይነት ገፅታዎች ዓሉት የመጀመሪያዉ ምርት (PRODUCT) ሲሆን ሁለተኛዉ አገልግሎት (SERVICE) ነዉ፡፡ ምርት የምንለዉ ለምሳሌ የተሰሩ የተለያዩ እንደ ማይክሮሶፍት ዊንዶዉስ ያሉ ሶፍትዌሮችን በመሸጥ እና በማከራየት የሚገኝ ገቢ ሲሆን አገልግሎት የምንለዉ ደግሞ እንደ ማህበራዊ ሚዲያዎች ያሉ አገልግሎቶችን በማቅረብ ገቢ የማግኛ መንገድ ነዉ፡፡

ብዙ የቢዝነስ ኢንዱስትሪዎች እና ድርጅቶች እጅ ሰጥተዉ የነበራቸዉን ክብር ለቀዉ ከገበያ ሲርቁ ፤ ከዚህም አልፈዉ ለሌሎች ድርጅቶ ለሽያጭ ሲዳረጉ ሲብስም ከስረዉ ሲዘጉ ፤ ሌሎች ከራዕይ ዉጪ ምንም ገንዘብ ያልነበራቸዉ ደግሞ አንፀባርቀዉ ሲወጡ እና በገፍ ሲያተርፉ አይተናል፡፡ ለእነዚህ ስኬታማ ድርጅቶች የጀርባ አጥንታቸዉ ቴክኖሎጂን በተለይም ማህበራዊ ሚዲያን የተጠቀሙበት መንገድ መሆኑ አያወላዳም፡፡ ቀደም ብሎ ቢዝነስ ፤ ቢዝነስ ለመባል 2 ነገሮች መያዝ ይጠበቅበት ነበር እነሱም የሰዉ ሐይል እና ጥሬ እቃ (RESOURCE) ነበሩ አሁን ግን 3ኛ ነገር ማለትም ቴክኖሎጂን ያልያዘ ቢዝነስ ተወዳዳሪ መሆን እና ራሱን ችሎ መቆም አይችልም፡፡

በፕላትፎርም ቢዝነስ ላይ ንጉስ ሆኖ መቅረት እጅግ ከባድ ነዉ፡፡ ምንጊዜም የተሻለ አማራጭ እና ብዙ ደንበኞች ያሉት ፕላትፎርም አሸናፊ ነዉ፡፡ ዛሬ ላይ ያለ የማይነካ ግዙፍ ፕላትፎርም ነገ በሚመጣ ቤሳቤስቲን በሌለዉ ነገር ግን እጅግ ጥሩ በሆነ ፕላትፎርም ሊገረሰስ ይችላል፡፡

በእኛ ሀገር ጥቂት የማይባሉ ፕላትፎርሞች ቢኖሩም የመረጃ ልዉዉጡ ደካማ ስለሆነ ለማነፃፀር ስለሚያስቸግር ጥቂት ቴክኖሎጂ የደቆሳቸዉ እና ቴክኖሎጂ ያነነሳቸዉ ዘመናዊ ዓለም ዓቀፍ የቢዝነስ ዘርፎች እና ፕላትፎርሞችን እንይ -

## ፌስቡክ vs ማይ ስፔስ

በአለማችን ላይ ከ 2 ቢሊዮን በላይ ተጠቃሚ ያለዉ ትልቁ ፕላትፎርም ፌስቡክ ነዉ፡፡ በዚህ ዓለም ላይ እንደ ፌስቡክ ያህል ብዛት ተከታይ ያለዉ ሀይማኖት እንኳን የለም፡፡ ፌስቡክ ይሄንን ድል ለመቀናጀት የወሰደበት 15 ዓመታትን ብቻ ነዉ፡፡ ፌስቡክ የሚያስገባዉን ገቢ እነ ቦይንግ እና ኤይርባስ የመሳሰሉ ካምፓኒዎች እንኳን ዉድ አዉሮፕላኖችን እየሸጡ ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ ፌስቡክ ፕላትፎርም ነዉ ፣ ብዙ ነገሮችን አንድ ጋር የሚገናኙበት ፣ እኛ ፌስቡክ ስንጠቀም ምንም የምንከፍለዉ ነገር የለም ፣ ለፌስቡክ ግን እኛ የገቢ ምንጮቹ ነን ምክንያቱም ሌሎች አካለት የእነሱን ማታወቂያዎች እንድናይላቸዉ ለፌስቡክ ስለሚከፍሉ ፤ ፌስቡክ መስራቹ ማርክ ዙከን በርግን በዓለም ካሉ ወጣቶች የመጀመሪያዉ ባለሀብት ሊዳርገዉ ችሏል፡፡

ፌስ ቡክ ምንም እንኳን ዛሬ ላይ ሀያል ቢሆንም በተጀመረበት ወቅት እንደ ማይ ስፔስ አይነት እጅግ የገዘፉ ብዙ ተጠቃሚዎች ከነመረጃቸዉ የነበራቸዉ እና ለረጅም ጊዜ ዙፋኑን የተቆናጠጡ ካምፓኒዎችን ይበልጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነበር፡፡ ዛሬ ላይ ማይ ስፔስ የደረሰበትን የተለያዩ ጥቃቶች መቋቋም ተስኖት ተደቋቁሷል፡፡

## ኔትፊሊክስ vs ዩቱዩብ vs ብሎክ በስተር

በእኔ እድሜ ያለ አብዛኛዉ ሰዉ ዴክ ፤ ከፍም ሲል ሲዲ ተከራይቶ ፊልምን ኮምኩሟል አለበለዚያም ካሴት ገዝቶ ክሩን አጠንጥኖ ሲበጠስም ቀጥሎ በቴፑ ሙዚቃን አጣጥሟል፡፡ ብሎክ በስተር በዓለም ላይ ታዋቂዉ የቪዲዮ ሲዲዎች ማከራያ ድርጅት ነበር ነገር ግን ኔትፊሊክስ የተሰኘዉ ፕላትፎርም በኢንተርኔት አማካኝነት ቪዲዮችን ማከራየት (ማሳየት) ሲጀመር ፤ ብሎክ በስተር የኔት ፊሊክስን ጡጫ መቋቋም ተስኖት ከገበያ በበቃኝ ወጥቷል፡፡ በነገራችን ላይ ብሎክ በስተር ብቻ ሳይሆን በእኛም ሀገር ያሉ አብዛኞቹ በየሰፈሩ የነበሩ የቪዲዮ አከራዮች ስራቸዉን ለማቋረጥ ተገደዋል፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት በሀገራችን እንደ ኤሌክትራ ፤ ናሆም ሪከርድስ እና ማስተር ሳዉንድ እይነት ካምፓኒዎች የሙዚቃ ገበያዉን እና ሽያጩን ተቆጣጥረዉት ነበር፡፡ ነገር ግን የዩቱዩብ መስፋፋት በተለይም በሙዚቃዉ ኢንደስትሪ እንደ ሆፕ ሚዉዚክ ፣ ምንዉ ሸዋ እና አድማስ ያሉ ገፆች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ ጊዜ ለአንድ ሙዚቃ እስከ 1.5 ሚሊዮን በመክፈል ከፍተኛ ተፅፅኖ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡ ቀድመዉ ፕላትፎርሙን ስለተረዱት በዚያም እጅግ ብዙ ተመልካቾች ስላሏቸዉ ዝነኞች እና ሙዚቀኞች የእነርሱ ገፅ ጥገኛ ለመሆን ተገደዋል፡፡ ይሄም የሲዲ ሽያጭ ገበያን እጅግ አጣብቂኝ ዉስጥ አስገብቶታል፡፡

ዛሬ ላይ አብዛኞቹ በተለይም ወጣት ሙዚቀኞች የዩቱዩብ ፕላትፎርም ግንዛቤ ስላላቸዉ ስራዎቻቸዉን ለሌሎች ከመሸጥ ይልቅ ለግዜዉ ከሽያጭ ብዙ ገቢ እንዲሁም እይታ ቢያሳጣቸዉም የነገን ተስፋ አድርገዉ የየራሳቸዉን የዩቱዩብ ፕላትፎርም ገፆችን መጠቀም ጀምረዋል፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ ቴዲ አፍሮ ፣ ወንዲ ማክ ፣ አስቴር አወቀ ፣ ሳያት ደምሴ ፣ ናቲ ማን ፣ ሀመልማል አባተ እና አቡሽ ዘለቀ ይገኙበታል፡፡

## አሊባባ vs አማዞን vs ኢቤይ

አለም የኦንላይን ግብይትን የሚሳልጠዉ አማዞን በዓመት ብቻ በአጠቃላይ የሚያተርፈዉ ትርፍ ኢትዮጵያ ለ110 ሚሊዮን ዜጎቿ ለአመት ከምትመድበዉ 14 ቢሊዮን ዶላር ገንዘብ ከእጥፍ በላይ የበለጠ ነዉ፡፡ በዚህ የፕላትፎርም ዘርፍ አማዞን ብዙ ጊዜ ቢጠራም አሁን ላይ ሌላኛዉ ከኤሽያ ቻይና መቀመጫዉን ያደረገዉ አሊባባ በማይታመን ፍጥነት እየገሰገሰ ይገኛል፡፡

ለሁላችንም አርዓያ በሆነዉ የአሊባባ መስራች ጃክ ማ እና ጓደኞቹ ስለ ኢንተርኔት እንኳን በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸዉ የኦንላይን ግብይትን ሀሳብ ሲጠነስሱ በወቅቱ የማይነካ የሚመስለዉ ኢቤይ ጠንካራ እጆቹን በቻይና ላይ አንሰራፍቶ ነበር፡፡ ኢቤይን ሌላ ድርጅት ብልጫ ይወስድበታል ብሎ ማሰብ ከንቱነት ነበር፡፡ ይሄዉ ጊዜን ጊዜ ተካዉና የማይሆነዉ ሆነ ከተስፋ ዉጪ ምንም ያልነበረዉ አሊባባ ታላቁ ኢቤይን በዝረራ ከቻይና ገበያ ዉጪ አድርጎታል፡፡ የዛን ጊዜ ስራ አጡ ፣ ተፈላጊነት ያለነበረዉ ሰዉ ጃክ ማ ዛሬ ላይ ከአለም ቱጃር ቢሊዬነሮች አንዱ ለመሆን በቅቷል፡፡ ሀገራችን ለዜጎቿ ጥቅም ሲባል በኦንላይን ግብይት ለዉጪ ሀገር ካምፓኒዎች ዘግታዉ የነበረዉን በር ገርበብ ማድረጓን ተከትሎ አሊባባ እያነፈነፈ ይገኛል፡፡ በቅርቡም በሀገራችን እንደሚገባ ይጠበቃል ፣ ነገር ግን ብዙዎች የአሊባባን ጠቃሚና ጎጂ ተፅፅኖዎችን ስላልተረዳንዉ ከአንዳንድ ኢኮኖሚስቶች እና ቴክኖሎጂስቶች ዉጪ ያን ያህል ትኩረት የሰጠዉ አካል የለም፡፡ የአሊባባ መግባት ለብዙዎች በተለይም በቴክኖሎጂ ዙሪያ ላሉ እና ዘመናዊ ነጋዴዎች የስራ ዕድልን ቢፈጥርም በልማድ ለሚሰሩ ለአብዛኞቹ ነጋዴዎች ፈተና

እንደሚሆን እና የመኖር ህልዉናቸዉን እንደሚፈታተናቸዉ ግልፅ ነዉ፡፡ ቻይኒቲ እስካሁን ዘረፈችን እያለን ከምናሚርተዉ ይልቅ አሊባባ ከመጣ እጅግ ብዙ የሀገሪቷን ሀብት አጥቦና ጠራርጎ ለሀገሩ ቻይና እንደሚገብር ምንም አያጠራጥርም፡፡

## ቴሌግራም vs ዋትሳፕ vs ቫይቨር

ኢትዮጵያዉያን በብዛት ከሚጠቀሙባቸዉ የማህበራዊ ሚዲያዎች አንዱ ቴሌግራም ነዉ፡፡ ቴሌግራም ለአጠቃቀም ምቹ መሆኑ እና በደካማ ኢንተርኔት ዴታ በፍጥነት መስራቱ ጭምር ተመራጭ አድርገዉታል፡ ይሄ ገፅታዉም አብዛኞቻችን እንደ ቫይበር እና ዋትሳፕ ካሉ ተመሳሳይ መተግበሪያዎች እንድንርቅ እየደረገን ይገኛል ፡፡ ምንም እንኳን በዓለም ደረጃ ዋትሳፕ የተሻለ ተቀባይነት ቢኖረዉም ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን ሙሉ በሙሉ በቴሌግራም የበላይነት ተወስዶበታል፡፡ ይሄም አልበቃ ብሎት ብዙዎችን ከፌስቡክ መንደር እያስቀረን ይገኛል፡፡ ቴሌግራም ገና ቅርብ ጊዜዉ ቢሆንም በብዙ ሚሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ እያግበሰበሰ ይገኛል፡፡

በነገራችን ላይ ፕላትፎርምን መስራት ብቻ ሳይሆን ፕላትፎርምን በአግባቡ መጠቀም የስኬት ሚስጢር ነዉ፡፡ ዛሬ ላይ እጅግ ብዙ ሚሊዮን ብር ከሚመደብላቸዉ እና እጅግ ብዙ ሰራተኞች ካሏቸዉ የሚዲያ ተቋማት ይልቅ በአንድ እና ሁለት ግለሰብ የሚንቀሳቀሱት ቲክቫህ ኢትዮጵያ ፤ ጌጡ ተመስገን እና ኤልያስ መሰረት ተፅፅኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

## ኮዳክ vs ኢንስታግራም

በእኛ እድሜ እንኳን በየፎቱ ቤቱ እየሄድን የምንነሳዉ በባለ ፊልሙ በተለይም በኮዳክ ሰራሽ የፎቶ ፊልሞች ካሜራዎች ነበር ፡፡ የተነሳነዉን ፎቶ ይበላሽ ወይንም ልክ ይሁን እንኳን የምናዉቀዉ ታጥቦ ከመጣ በኋላ ነበር፡፡ ይሄ ከትንሽ ዓመት በፊት የነበረ ድርጊት ዛሬ ላይ ነበር ሆኗል፡፡

ዛሬ ላይ የፎቶ ክንዉኑ ብቻ ሳይሆን ከዋኙ ኮዳክ በየቀኑ በሰልፊ ካሜራ የሚነሱ እና አንደ ኢንስታግራም ያሉ ፕላትፎርሞችን ያጨናነቁ ፎቶዎችን ጫና መቋቋም ስላለቻል ቁልፉን ከርችሞ ከገበያ ለመጥፋት ተገዷል፡፡ ዛሬ ከዲቂቃ በፊት የተነሳነዉ ፎቶ ወዲያዉኑ እኛ ብቻ ሳንሆን በኢንስታግራማችን ላይ የሚገኙ ሚሊዮኖች ያዩታል፡፡

## ኖኪያ vs ሳምሰንግ vs ሁዋዊ

ስኔክ ጌም የተጫዉትንባቸዉ ፣ ወድቀዉ ንክች የማይሉት ፣ በ2ጂ ኔቶርክ የተነጋገርንባቸዉ የኖኪያ ስልኮች የቅርብ ጊዜ ትዉስታዎቻችና ናቸዉ፡፡ የፊንላንዱ ኖኪያ የአንድሮይድ ኦፕሮቲንግ ሲስተም ሲመጣ ከመቀበል ይልቅ የራሱን ለመስራት ጉድጉድ ማለት ቢጀምርም ከስኬት ይልቅ ወደ ዉድቀት ጉድጓድ ዉስጥ ራሱን በመክተቱ ከገበያ ከራቀ ሰነባብቷል ፤ ንግስናዉንም ለሳምሰንግ አስረክቧል፡፡ አሁን ላይ ኖኪያ ከስህተቱ ተምሮ የተሻሉ ስልኮችን ለገበያ በማቅረብ የነበረ ስሙን ለመመለስ እየተጋ ነዉ፡፡

ነገ ምን እንደሚፈጠር አይታወቅም ፤ አንድሮይድን ይጠቀም የነበረዉ ሁዋዌ እንዳይጠቀም በተጣለበት እገዳ ምክንያት በሚያስገርም ሁኔታ እጅግ ጥሩ የራሱን መተግበሪያ አዘጋጅቶ ለገበያ አቅርቧል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ጎግል ፉቺሳ የተባለ ኦፐሬቲንግ ሲስተም እያዘጋጀ ሲገኝ ለዚያም እንዲረዳዉ ፍለተር የተባለ ሞባይል መተግበሪያ ማዘጋጃ ለጥቅም አዉሏል ፡፡ ጦርነቱ እና ሀያልነቱ በፕላትፎርም ነዉ ምክንያቱም የወደፊቷ ዓለም ሙሉ ለሙሉ የፕላትፎርም ዓለም ናትና፡፡ የነገ ተዕፅኖ ፈጣሪ ዛሬ ላይ ገንዘብ ያለዉ ሳይሆን ዛሬ ላይ ፕላትፎርም ያለዉ እና መረጃን ያከማቸ ሰዉ ነዉ፡፡

## ኢክሳይት vs ጎግል

ከዓመታት በፊት አክሳይት ዶት ኮም ልክ እንደ ዛሬዉ ጎግል ስሙ የገዘፈ የመረጃ መፈለጊያ ቦታ ነበር፡፡ የዛሬዉ ጉግል ባለቤቶችም የሰሩት ፈጠራ የኤክሳይት ባለቤቶች እንዲገዟቸዉ ብዙ ጊዜ ተማፅነዋቸዉ ነበር፡፡ የዛን ጊዜ ጎግል እንዲሸጥበት ለኤክሳይት የቀረበዉ እዚህም ግባ የማይባል በጣም ትንሽ ብር ነበረ፡፡ ነገር ግን ጊዜን ጊዜ ወለደዉና የዛን ጊዜ ጎግልን የናቀዉ ኤክሳይት የናቁት ያዋርዳል ነዉ እና በጎግል ከገበያ ወጪ ሆኖ ከህይወት ወደ ሞት ጫፍ ተሸጋግሯል፡፡

ሁላችንም የጎግል ጥገኛ ሆነናል፡፡ ኑሮ ያለ ጎግል የማይታሰብ እየሆነ መጥቷል ፡፡ ከግል መረጃችን እስከ የትኛዉም የዓለም መረጃ የምናገላብጥበት እና የምንፈልግበት መሳሪያችን ጎግል ነዉ፡፡

## ኤች ፒ vs ሊኖቮ vs ቶሺባ

አንድ ቢዝነስ ሲፈካ ሌላዉ ጫናዉን መቋቋም ያልቻል እየጠወለገ መምጣቱ አይቀሬ ነዉ፡፡ አንዴ ክንፋቸዉን የተመቱ ቢዝነሶች ደግሞ የመመለሳቸዉ ነገር የማይመስል ነዉ፡፡ ሁላችንም እየተጠቀምንበት የምንገኘዉ ቶሺባ ኮምፒዉተር አንዱ ነዉ፡፡ ቶሺባ ዛሬ እንጠቀምበት እንጂ ነገ ከነገወዲያ ቅርስ ሆኖ የመምጣቱ ነገር እዉን እየሆነ መጥቷል፡፡ ምክንያቱም በባንክ እዳ እና ተያያዝ ጉዳዮች ቶሺባ ኪሳራ ዉስጥ ከገባ ሰነባብቷል፡፡ እንደ ሌኖቮ እና ኤችፒ ያሉ ካምፓኒዎች ደግሞ በተቃራኒዉ በገበያዉ ዉስጥ ድርሻቸዉ የበለጠ እያሻቀበ ፤ ትርፋማነታቸዉ እየተመነደገ ይገኛል፡፡

## ጂሜይል -- ያሁ

ከጥቂት ዓመታት በፊት በእኛም ሆነ በሌላዉ ሀገር ኢሜይል ሲባል ጭንቅላታችን ዉስጥ የሚመጣዉ ያሁ ነበረ፡፡ ያሁ በደረሰበት ተደጋጋሚ የሳይበር ጥቃት በቢሊዩን የሚቆጠሩ ደንበኞቹን መረጃ ተመዝብሮ ታላቅነቱንም ለተረኛዉ ጂሜይል ለማስረከብ ተገዷል፡፡ በዚህ ጊዜ ጂሜይል የሚሰጠዉ የማጠራቀሚያ ቦታ እስከ 15 ጊጋ ባይት ብቻ ሲሆን በተቃራኒዉ ያሁ ግን በብዙ እጥፍ እስከ 1000 ጊጋ ባይት ወይንም 1 ቴራ ባይት ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ያሁ ይሄን ያህል አድርጎ እንኳን ደንበኞችን ሊያስቀር እና የጂሜይልን ጫና ሊቋቋም አልቻለም፡፡ ጂሜይል በዓለማችን ትልቁ የኢሜይል መረጃ መለዋወጫ ሆኖ ህይወታችንን ቀላል እያደረገልን ይገኛል፡፡

በ2019 የፎርብስ መፅሄት በሚያሳዉቀዉ የአለም የቱጃሮች ሰንጠረዥ መሰረት ካሉት ባለሀብቶች መጀመሪያ ላይ የሚገኙት ባህብቶች የገቢ ምንጫቸዉ ፕላትፎርም እና ፕላትፎርም ነዉ፡

1. ጆሴፍ ቤዞስ - ከ110 ቢሊዮን በላይ የአሜሪካን ዶላር ከአማዞን

2. ቢል ጌት - 95.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከማይክሮሶፍት

5. ካርሎስ ስሊም - 64 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከቴሌኮም ኢንደስትሪ

7. ላሪ ኢሊሰን - 63 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከኦራክል

8. ማርክ ዙከንበርግ - 62.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከፌስቡክ

9. ሚካኤል ብሎምበርግ - 55.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከብሎምበርግ

10. ላሪ ፔጅ - 50.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከጎግል

የፕላትፎርም ቢዝነሶች በኢትዮጵያ ላይ ቢስፋፉ በ 2 ምክንያቶች ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጭምር የተሻለ ገቢ የሚያስገኝ ይሆናል የመጀመሪያዉ ምክንያት ሀገሪቷ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣት የስልክ ተጠቃሚዎች ሲኖሯት ሁለተኛዉ ደግሞ ገና ያልዳበረ ኢንደስትሪ ስለሆነ ከባድ የቢዝነስ ፉክክር የለዉም፡፡ ለዚያም ይመስላል እንደ አሊባባ ፤ ሳፋሪ እና ሾዳፎን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ተቋማት ገበያዉን ለመቀራመት አይናቸዉን የሚያማትሩት፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ከመግባታቸዉ በፊት ነገሩ በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት እንዳይሆን የሀገራችንን ስታርት አፖች እና የቴክኖሎጂ ካምፓኒዎችን ማበረታታት ይገባናል፡፡

ለዛሬዉ በዚህ ይበቃኛል ምናልባት ወደፊት ደግሞ በሀገራችን ስላሉት እና ተስፋ ስለጣልንባቸዉ የፕላትፎርም ዉጤቶች እናወጋለን፡፡ ሠናይ ዘመነ ፕላትፎርም ይሁንልን ...

“ የዘንድሮ ቢዝነስ ቀመር ፕላትፎርም ነዉ ! ”

# 3. ስነ-ልቦና

“ራስህን የምትፈትሽ ከሆንክ ለሽንፈት አትዳረግም ፤ አንተ የሂወትህ ሾፌር ነህ የሚያስፈልግህን ነዳጅ እና ጎማ በበቂ ሁኔታ መያዘህን ካረጋገጥክ ጉዞዉ አያሳስብህም ፤ ጎማህ በቂ አየር የለዉም ስለዚህ አስነፋዉ የሚልህ ጓደኛ ካገኘህ ጎማዉን ከእንደገና አረጋግጠህ በቂ አየር ከሌለዉ ለአስተያየቱ አመስግነህ ጎማህን አየር አስሞልተህ ትጓዛለህ ፤ ጎማዉ በቂ አየር ካለዉ ደግሞ ጓደኛዬ ተሳስቶ ነበር ብለህ መንገድህን ትቀጥላለህ፡፡ አለበለዚያ የጓደኛህን ምክር ካልሰማህ እና ራስህን ካልፈተሽክ ግን መጥፎ ቦታ ላይ ትቆምና መመለሻ አጥተህ እንደወጣህ ትቀራለህ፡፡

.

.

.

ጓደኞችሽ ግን አብረዉሽ ሲያዘግሙ ወደፊት እንጂ ወደኋላ የሚስቡሽ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ወደኋላ የሚጎትትሽ ጓደኛ ካለ በመንገድሽ ላይ የቆመ ጋሬጣ ነዉና ከመራመድሽ በፊት መንጥሪዉ ፡፡ ”





“ በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! ”

# 3.1 አስናቀ እና ታየር



በኢቲቪ ይተላለፍ የነበረዉ ሰዉ ለሰዉ ድራማ መሪ ተዋናይ አስናቀ እና በቃና ቲቪ ይተላለፍ የነበረዉ የጥቁር ፍቅሩ ገፀ-ባህሪይ አለቃ ታየር ዱንዳር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸዉ፡፡ እነዚህን ሁለት ሰዎች ብዙ የሚያመሳስሏቸዉ ገፅታዎች አሉ ከእነርሱም መካከል አስመሳይነታቸዉ ፣ ተንኮለኝነታቸዉ ፣ አጭበርባሪነታቸዉ ፣ ድፍረታቸዉ ፣ ቆራጥነታቸዉ ፣ መሰሪነታቸዉ ፣ የገንዘብ ሱሳቸዉ ፣ ወንጀል ለመፈፀም ከሚሳኤል የፈጠኑ መሆናቸዉ ፣ የእጃቸዉ ረዥም መሆን( በገንዘብ የፈለጉትን ማሳካታቸዉ ) ፣ ቅቤ አንጓችነታቸዉ ፣ አርቆ አሳቢነታቸዉ ፣ እጅግ የረቀቁ እና የበሰሉ መንታፊዎች መሆናቸዉ ፣ ብልህነታቸዉ (እንኳን ስኬት ጫፍ ላይ ለመድረስ ለወንጀልም ቢሆንም ብልህነትን ጥበበኝነት አስፈላጊ ነዉና) ፣ እነዚህ ሁሉ ባህሪያት ሁለቱን ገፀባህሪያት ወደ አንድ ማንነት ያመጧቸዋል፡፡

አስኔን እና ታየር መጥቀስ ያስፈለገኝ የድራማ ዘገባ ልተርክላችሁ ሳይሆን ዙሪያችንን በአስናቆች እና በታየሮች የተከበብን ስለሆንን ዞር ብሎ ለማየት እንዲያስችለን ብዬ ነዉ፡፡ እንደ እነ አስኔ አይነት ሰዎች ክንዳቸዉ ከመፈርጠሙ ፣ አፋቸዉ ጤፍ ከመቁላቱ ፣ ልባቸዉ ከመደንደኑ ፣ አይናቸዉ በገንዘብ ሱስ በመታወሩ የተነሳ ከእነርሱ በተቃራኒ የቆመን ሰዉ በቀላሉ እንደሸቀጥ በገንዘብ ሊገዙት ይደራደራሉ ፤ ይህ ካልተሳካ እና ሰዉየዉ ለህሊናዉ የቆመ ከሆነ ግን ሀይላቸዉን ተጠቅመዉ አከርካሬዉን ሊያደቁት ፣ አፉን ሊለጉሙት ፣ ልቡን ሊሰብሩት ፣ አይኑን ጨለማ እግሩን ቁጠማ ሊያደርጉት እቅድ ነድፈዉ ፣ መሳሪያ ታጥቀዉ ፣ በጦር ታጅበዉ ቆርጠዉ ይነሳሉ፡፡

በነገራችን ይህ የአስናቀና እና ታየር ባህሪ በሰዉ ደረጃ ሳይሆን በሀገራትም ደረጃ ይታያል ለዛም ነዉ ምዕራቡ ዓለም ፣ ምስራቁ ዓለም ብሎ የዓለም ህዝብ ራሱን ሁለት ከፍሎ እንደ አይጥ እና ድመት ተፋጦ ያለዉ ፤ ግማሹ መሬትን ለቆ ህዋ ላይ ላለ ቦታ ሲፎካከር ግማሹ ደግሞ ለዳቦ ሽሚያ ይፎካከራል ፤ ይህ የአስኔ እና የታየር ባህሪ ነዉ አለምን አሁን ላለችበት ሁኔታ የዳረጋት ፣ የጥቅም ጉዳይ ፣ የስልጣን የበላይነት ፣ የሀይል ሚዛን ..... እና የመሳሰሉት፡፡ በአንድ አለም ላይ እየኖርን ግማሹ አምላኩን የእለት ጉርሱን ይለምናል የተቀረዉ ደግሞ እነ አስኔ ባመጡት ጣጣ የኒኩለር እና የአየር ለዉጥ ሰለባ እንዳይሆን አምላኩን ይማፀናል ፡፡

ስንቶች ናቸዉ የጀርባህን እከክ ልከክል በሚል ሰበብ ከኋላ የማንወጣዉን ትልቁን ጉድጓዳችንን የሚምሱልን እና በሁለት እግራችን ቆመን ከመሄድ ይልቅ ባዘጋጁልን ተሽከርካሪ ወንበር (ዊልቸር) እየገፉ እንደ መዥገር የእነርሱ ጥገኛ ሆነን ከስር ከስራቸዉ ስንከተል ልባቸዉ ጮቤ የምትረግጠዉ፡፡ አንድ ወቅት ላይ ያጋጠመኝን ልንገራችሁ ወቅቱ እርሻ ታርሶ የሚዘራበት ነበር ግን አንድ አካባቢ ላይ ብዙ ገበሬዎች ተሰብስበዉ ይጨቃጨቃሉ ፤ እኔም ጭቅጭቁ ቀልቤን ስለሳበኝ ጠጋ ብየ ሁኔታዉን ታዘብኩ ፤ ያሁሉ ሰዉ ስራ ፈቶ የመጣዉ እና ቀኑን ሙሉ ተሰልፎ የዋለዉ ከዉጪ የሚመጣ የእርዳታ ስንዴ ለመከፋፈል ነበር ፤ አስገራሚ የሚያደርገዉ ለአንድ ቤተሰብ የሚደርሰዉ 1 ማዳበሪያ ወይም 50 ኪሎ እንኳን አይሞላም ነበር ፤ የፀቡ ምክንያትም ይህ ነበር ከአንዱ ወደ አንዱ የማቀናነስ ሂደቱ ፤ እኔን የገረመኝ ይህ አልነበረም የእነ አስናቀ ስራ ቁልጭ ብሎ የታየኝ ከመካከላቸዉ አንዱን አርሶ አደር እያወራሁት አያለ ነበር ፤ እርሻ ስራ ጀምሮ እርዳታ እንዳለ ሲሰማ እንዳያመልጠዉ አቋርጦ እንደመጣ ነገረኝ ፤ እናም እርሻዉን ትቶ የመጣዉ አሁን የወሰደዉን ስንዴ ለዘር ፈልጎት ይሆን ብየ ጠየኩት ፤ ከት ብሎ ስቆ ... አይ ልጄ ይሄ እኮ ለምግብ ካልሆነ ለዘር እኮ አይሆንም ፈረንጆች ሲልኩት ዘርተነዉ እንዳያበቅል በእንፋሎት ቀቅለዉ ነዉ የሚልኩት ብሎኝ አረፈ ፤ አሁን ይህ ምን አይነት እርዳታ ነዉ ? ሰዉ ሰርቶ እንዲበላ ከማድረግ ይልቅ ጥገኛ እንዲሆን እና የሰዉ እጅ እንዲጠብቅ ማድረግ ፤ ተስፋ የሌለዉ እና ከመስራት ይልቅ መለመን ፤ ከማጥናት ይልቅ መኮረጅ ፤ ላቡን ጠፍ አድርጎ ከመስራት ይልቅ ቀማኛ ፤ ባህሉን እና ወጉን ከመጠበቅ ይልቅ ብልሹ እና ግብረ ሰዶም ፤ ከህሊናዉ ይልቅ ለገንዘቡ እና ለስሜቱ የሚገዛ ትዉልድን መፍጠር ነዉ፡፡ ይህም የእነ አስናቀ እና ታየር አይነት ስዉር ዓላማቸዉን ማሳካት የሚፈልጉ ሰዎች ስራ ነዉ፡፡

በሌላ ቀን ኤፍ ኤም 102.1 እየተከታተልኩ ነበር እና ዜናዉ ሩዋንዳ ከአግዋ ስምምነት ልትሰናበት እንደምትችል ከአሜሪካ መንግስት ማስጠንቀቂያ ደረሳት ይላል፡፡ የገረመኝ የሩዋንዳ መንግስት ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ምክንያት ነበር፡፡ አግዋ በአፍሪካ ላሉ ኢትዮጵያን ጨምሮ ላሉ ታዳጊ የህብረቱ አባል ሀገራት በአሜሪካ ካለ ታክስ ምርቶቻቸዉን እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ስምምነት አንደሆነ በሚዲዎቻችን ሲደሰኮር እንሰማለን፡፡ ነገሩን ጠጋ ብሎ ላየዉ ከኋላዉ አስፈሪ ስምምነት አለዉ፡፡ ከስምምነቶቹም መካከል አንዱ ሩዋንዳን ማስጠንቀቂያ ያሰጣት ምክንያት ነበር፡፡ በዚህ ስምምነት ዉስጥ አባል ሀገራት ከታላቋ ሀገር አሜሪካ የሚመጡ ልባሽ ጨርቆችን ወይንም ሰልቫጆችን የመቀበል ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ሩዋንዳም አሻፈረኝ በማለቷ ነበር ማስጠንቀቂያ የተሳጣት ከዚህ በፊት ኡጋንዳ እና ታንዛንያ ተመሳሳይ ህግ አዉጥተዉ ቢሆንም ቅጣቱን በመፍራት ተግባራዊ ሳያደርጉት ቀርተዋል፡፡ ይህ በተለይ ለታዳጊ ሀገራት ትልቅ አደጋ ነዉ፡፡ የተለያዩ ሀገር በቀል አልባሳት አምራች ድርጅቶችን አቅማቸዉን በመደቆሽ ከገበያ ጠራርጎ በማስወጣት ራሳቸዉን እንዳይችሉ እና ህብረተሰቡን ከዉጪ በተመጣጣኝ ዋጋ በኮንቴነር ታጭቀዉ ህጋዊ ሆነዉ ለሚመጡ ልባሽ ልብሶች ጥገኛ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ሀገራትን ትንሽ ታክስ ቀነስኩ ብሎ አላስፈለጊ የሆነ ምርትን ማስወገጃ ማድረግ እርዳታ ሳይሆን በእርዳታ ሰበብ የሚመጣ ስልታዊ የእነ አስኔ እና ታየር የዝርፊያ ሴራ ነዉ፡፡

አስኔ እና ታየር ገፅታቸዉ በዚህ ብቻ አይወሰንም ፤ ቁጭ ብየ ቴሌቪዥን እያየሁ ነበር ፤ በአሁኑ ጊዜ መቼም ኢትዮጵያ ዉስጥ የቲቪ ቻናሎች እንደ ችግኝ እየበዙ ነዉ እና ለመምረጥ ብቸገርም ENN የሚባለዉ ቻናል ላይ ጊዜያዊ ማረፊያየን አድርጌ ሳለሁ አንድ አስገራሚ ዜና ሰማሁ ፤ ዜናዉ የሚገልፀዉ በተለምዶ አቃቂ ቱሉዲምቱ በሚባለዉ ኮንዶሚኒየም አካባቢ ከ 2 ኪሎሜትር አስፋልት በላይ መጥፋቱን እና አንድ ህንፃ ገና ነዋሪ ተመድቦ ሳይገባበት ከዚህ አለም መሰናበቱን ነበር የሚገልፀዉ ፡፡ አስገራሚ እኮ ነዉ ! አስፋልት ልክ እንደ ተሰረቀ ሞባይል ጠፍቶ ቀረ ሲባል ፤ አሄሄ መች ጠፉን ... ይች የእነ አስኔ እና ታየር ስራ ናት ገንዘቧን በባሌም በቦሌም ብለዉ ከቦጠቦጧት በኋላ አስፋልት የነበረችዉን በስምምነት ወደ ኮብልስቶን ፤ ኮብልስቶን የነበረችዉን ወደ ፒስታ ይቀይሯታል ፤ G+12 የነበችዉን ህንፃ ወደ G+8 ያሳጥሯታል

፤ እነርሱ ጥበባቸዉ ብዙ ነዉ ብቻ የሚያሳዝነዉ እነርሱ በአካፋ ዝቀዉ ካዝናቸዉን በብር ካጨቁ በኋላ ሌላዉን በማንኪያ አልሰዉ ማነካካታቸዉ እና ወደ ከርቸሌ ይዘዉ መንሸራታቸዉ ነዉ፡፡ ለእኔ ይህ ብዙ አላስደነገጠኝም ምክንያቱም የዚህ አይነት ወሬ እነ አስኔ ባሉበት ቦታ የተለመደ ነዉ ፡፡ አስደንጋጩ ሁለተኛዉ ዜና ነበር ምንም እንኳን ኮንዶሚኒየም ህንፃዉ የተደረመሰዉ ሰዉ ሳይገባበት ሆኖ ጥሩ ሆነ እንጂ ሰዉ ገብቶበት ቢሆን ኖር በአስኔ እና በታየር አይነት ሰዎች ምክንያት የሚፈፀመዉ ወንጀል አስከፊ ነበር እነ ሂትለር ፤ ሙሶሎኒ እና ግራዚያኒ ካካሄዱት ጭፍጨፋ ለይቶ ማቅረብ ይከብዳል ፤ ምክንያቱም በኮንዶሚኒየም ዉስጥ አብዛኛዉ የሚኖረዉ ቤተሰብ ስለሆነ የዘር ማጥፋት ነበር የሚከሰተዉ ፤ ስለዚህ እንደ ኮንዶሚኒየም አይነት ትልቅ ስራ ሲሰራ በተቻለ መጠን በጥንቃቄ መስራት እና እንደ አስኔ እና ታየር አይነት ስግብግቦችን ማጥፋት ባይቻልም እንኳን ለህዝብ ሲባል ማራቅ ይገባል፡፡

በእኛም ዙሪያ ቢሆን በአካባቢያችን ፤ በትምህርትቤታችን ፤ በጓደኞቻችንን አንዳንዴም በቤተሰቦቻችን መካከል እነ አስኔን እና ታየርን በአካል እናገኛቸዋለን ፤ ከእዉነተኛ ጓደኛ ይልቅ ሀብትህን/ሽን ፤ እዉቀትህን/ሽን ፤ መልክህን/ሽን … ፈልጎ ወይም የራሱን ጥቅም አስቀድሞ የሚመጣን ጓደኛ ከእነ አስናቀ እና ታየር ለይቶ ማየት ከባድ ነዉ፡፡

“ ከአስኔ እና ከታዬር አይነት ሰዎች ይሰዉረን ! ”

# 3.2 መክሊት

..........የአፋልጉን ማስታወቂያ.........

.................... ........................................

ተፈላጊ አቶ ሥራ ልዩ ሥሙ work በመባል ይታወቃል እንደጠፋ አልገኘም የተሰወረበት ቀን እንደተመረቅን ሀምሌ1,2009 ተፈላጊውን ያያችሁ ወይም ያለበትን የምታውቁ በታውን ብቻ እንድታሳውቁን።

ፈላጊ: ክቡር ተመራቂ

ፌስቡክ ላይ እየተጠቀምኩኝ ሳለሁ አንድ ፈገግም ፣ ፈልሰፍም ያደረገኝን የሚከተለዉን ፎቶ ተመለከትኩኝ። እንደ እኔ እይታ ይህ ፎቶ ቀልድን ብቻ ሳይሆን በዉስጡ ብዙ ነገሮችን አቅፎ ይዟል ፡፡ እስከመቼ ስራ ፈልገን ? 17 ዓመታት በትምህርት ዓለም ላይ ያጠፋ ሰዉ ስራ አጥቶ ኮብልስቶን ለማንጠፍ ሲሯሯጥ ማየት የተለመደ ነዉ ፤ ኮብልስቶን ማንጠፍ ዝቅተኛ ስራ ነዉ እያልኩ አይደለም ግን ያ ሰዉ 17 ዓመት የደከመበት ነገር ፍሬ ቢስ መሆኑ እና ለሰዉዬዉ የሞራል ዉድቀት ለሀገሪቷ ደግሞ ክስረት መሆኑ ነዉ የሚያስቆጨዉ ፡፡ይህ የስራ መጥፋት የተለያዩ መንስኤዎች አሉት ፡፡ ከነዚያም ዉስጥ መክሊትን አለማወቅ ፤ ዓላማ-ቢስ መሆን ፤ ደካማ የስራ ባህል እና የስራ ፈጠራ አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ ፡፡

ጥለፈኝ የሚል ፊልም ላይ የማስታዉሰዉ አንድ አብርሀም የሚባል ገፀ ባህሪ የሚናገራት እና የምወድለት አንድ አባባል አለች ፤ እንደዚህ ትላለች “የሰዉ ልጅ የመጀመሪያ ስህተቱ መክሊቱን አለማወቁ ነዉ ፤ ጥሩ ግንበኛ መሆን እየቻለ ዶክተር ካልሆንኩ ፤ ጥሩ ፖሊስ መሆን እየቻለ ፓይለት ካልሆንኩ ፤ ጥሩ ነጋዴ መሆን እየቻለ ዘፋኝ ካለሆንኩ እያለ ስንቱ ነዉ ላልተፈጠረለት ዓላማ እየኖረ ሳይሳካለት የሰዉ ሸክም ሆኖ የሚሞተዉ ” ትላለች፡፡ ቤት ይቁጠረዉ ስንቶቻችን ነን የምንኖርበት ዓለማ እና መነሻ መድረሻችንን የምናዉቀዉ ? ኢንጅነሮች መሆን እየፈለግን ለእናት አባታችን ብለን ዶክተሮች የሆንነዉ ፤ ስንቶቻችንስ ነን ጥሩ ኢንጅነሮች መሆንን እየቻልን ሰዉ ሲገባ ስላየን ብቻ ዶክተር ካልሆንን ብለን ያለ መክሊታችን የተሰነቀርንዉ ፤ የሰዉ ልጅ ምንም እንኳን የሆነ ነገር ላይ ቢሰማራም የተሰማራበት ነገር መክሊቱ ካልሆነ ስኬታማ የመሆን እድሉ ኢምንት ነዉ፡፡

ይሄ መክሊትን ፍለጋ ላይ የቤተሰብ ተፅዕኖም አለበት ለምሳሌ አንዳንድ ቤተሰቦች ልጃቸዉ ጥሩ የንግድ ችሎታ እያለዉ እነርሱ ግን ልጃቸዉን ያለ መክሊቱ ዶክተር ካልሆንክ ብለዉ ማለቂያ የሌለዉ አረንቋ ዉስጥ የሚጨምሩ ፤ ሌሎች አይነት ወላጆች ደግሞ ልጃቸዉ ትምህርት መክሊቱ እንዳልሆነ ተረድተዉ ግን ልጃቸዉ ኮርጆም ቢሆን ትምህርቱን

እንዲጨርስላቸዉ የሚፈልጉ አሉ ፤ ብቻ ይሄ መክሊትን ፍለጋ ብዙ ሰዎች ያልተረዱት ነገር ግን የህይወትን ጓጉንቸር መፍቻ ቁልፍ ነዉ፡፡

የሰዉ ልጅ ዓላማዬ ብሎ በያዘዉ ነገር ላይ ከፀና እና ከተጋ ብሎም መክሊቱን አዉቆ ከታገለ በተሰማራበት ዘርፍ ምንም እንኳን ቢከብደዉ የማይወጣዉ ደረጃ እና የማይቆናጠጠዉ መቀመጫ የለም፡፡ እኔ በሂወቴ ብዙ ልጆች ኢጋጥመዉኛል እስከ 12ኛ ክፍል ከተማሩ በኋላ የዩኒቨርሲቲ ዉጤት አምጥተዉ የሚመርጡትን ዲፓርትመንት ለመምረጥ እና ለመወሰን የተቸገሩ፡፡ መድረሻቸዉን እና ፍጎታቸዉን ሳያዉቁ ነበር የትምህርት መሪያቸዉን ዝም ብለዉ የሚያሾሩት፡፡ እነዚህ ልጆች 12 አመት ሙሉ ሲማሩ ግባቸዉን እና መክሊታቸዉን ገና ያልተረዱ ወይንም በተለያየ ምክንያት መክሊታቸዉን መከተል ያልቻሉ መሆናቸዉ ግልፅ ነዉ ፡፡

ለአንድ ሀገር ትልቁ መሳሪያዉ የታጠቀዉ ሚሳዔል ወይም የኒኩለር ማብለያዎቹ አይደለም ይልቁንስ እነዚህን የፈጠረዉ ልዐለ ሀያሉ የሰዉ ልጅ አእምሮ ነዉ፡፡ ዉዱ ሀብት አልማዝ ሊመስለን ይችላል እዉነታዉ ግን እሱ አይደለም ዉዱ ሀብት አልማዝን ካለበት ፈልፍሎ እና ቆፍሮ የሚያወጣዉ ብሎም አልማዝን አልማዝ ሆኖ እንዲያምርበት ያስቻለዉ ጥበበኛዉ የሰዉ ልጅ አእምሮ ነዉ፡፡ ይሄ አዕምሮ ግን ፍሬያማ ሊሆን የሚችለዉ መክሊቱን ሲያገኝ ነዉ፡፡ አለበለዚያ በሰዉ መክሊት ዉስጥ ገብቶ ሲባዝቅ ይቀራል፡፡

ችግኝ ከማልማታችን እና ከመትከላችን በፊት ፤ ለችግኙ የሚቆረቆርለት ማህበረሰብ ልናለማ ይገባል ፤ አለበለዚያ ያ ችግኝ በአመቱ ደርቆ ሌላ ችግኝ እዛዉ ቦታ ላይ መትከላችን የማይቀር ነገር ነዉና፡፡ የሰዉ ልጅ አስተሳሰቡ ከሰለጠነ ለማደግ መንገዱም ጨርቅ ፤ እዳዉም በገብስ ነዉ፡፡ የሰዉ ልጅ ከሰለጠነ በሰዉ መክሊት ገብቶ አይዳክርም የራሱን ለመክሊት ለመፈለግ ይጣጣራል፡፡ ከአለም ሰባቱ ሰዉ አንዱ ቻይናዊ ነዉ ፤ እንግዲህ ይቺ ሀገር ናት ይሄንን ሁሉ ህዝብ ይዛ አሜሪካን የመሰለች የሰለጠነ የዓለም ህዝብ ተዉጣጥቶ የተከማቸባትን ሀገር ደረስኩብሽ እያለች በቁሟ የምታቃዣት፡፡ የቻይና ጉልበቷ ሌላ ሳይሆን ዜጎቿ በመክሊታቸዉ ሀገራቸዉን ስለሚያገለግሉ እና ስለሚተጉ ብቻ ነዉ፡፡

የሰዉ ልጅ መክሊቱን ከሳደደ የማይወጣዉ አቀበት የማይወርደዉ ቁልቁለት አይኖርም፡፡ የፅናትን ድማሚት ይታጠቃል ያገኛቸዉን መሰናክሎች ሁሉ በያዘዉ ደማሚት ወደ ዶግ አመድነት እየቀየረ ያከስማቸዋል፡፡ ፅኑ ፍላጎት ወደ ስኬት ይጎትተዋል፡፡ ዘፈኝነት ፣ ኳስ ተጫዋችነት ፣ መምህርነት ፣ ኢንጂነርነት ፣ ዶክተርነት ፣ ነጋዴነት ፣ ሹፌርነት … የእሱ የሆነዉ መክሊቱ እሱነቱን ያነግሰለታል፡፡

መጀመሪያ መክሊታችንን ካወቅን እንደ ፌስቡኩ ፖስት ስራ ስናፈላልግ አንገኝም፡፡ መክሊታችን ወደ ፍላጎት ይገፋናል ፤ ዉስጣዊ ፍላጎት ካለን ደግሞ ችግር በበዛባት ሀገር ዉስጥ እንደመኖራችን ችግሮችን ለመፍታት እንሞክራለን ፤ በተግባር ሲታገዝ ደግሞ መክሊታችን እዉን ሆኖ ስራ ሲፈጥርልን እና የኔ የምንለዉን ነገር ሲያሳቅፈን እናየዋለን፡፡

የሰዉ ልጅ ግንባሩን የሚቋጥርለት ፣ ሽንጡን የሚገትርለት ፣ መስዋዐትነት የሚከፍልለት ፣ የህይወቱን ጣዕም የሚያጣጥምበት መክሊት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

ቆየት ያለች ጥዑም ዜማ -

ሰዉ ከተሰማራ

እንደ እየ ስሜቱ

በዋለበት ፤ ባደረበት

አይቀርም ማፍራቱ …

.

.

.

አዎን … አይቀርም ማፍራቱ ፡፡

“ መከሊትህን ተከትለሀል ? ወይስ እሱ እየተከተለህ ነዉ ? ”

# 3.3 ሚስጥረ ስኬት



አንተ እኔ አንቺ ስኬታማነትን እያለምን ፣ የስኬታማነት መንገዶች እየተሰወሩብን ፣ አንዳንዴም በእድለኝነት እያሳበብን ፣ ስኬታማነት ሲቀናን ቀመስ እያደረግንዉ ሳይቀናን ደግሞ እያለምነዉ በሀሳብ ጎዳና ላይ እንገኛለን፡፡ ብዙ ሰዎች እንደሚስማሙበት ስኬታማነታችን የሚወሰነዉ በገንዘባችን እና በእዉቀታችን ሳይሆን በአሸናፊነት አስተሳሰባችን እና በማይበገር ስነ-ልቦናችን ነዉ፡፡ እስኪ በዚህ ፅሁፍ ዉስጥ ከተመከርኩት ፣ ከተዘከርኩት ፣ ከቃረምኩት እና ከቀሰምኩት የስኬትን ሚስጥር ሹክ ልበልህ/ሽ፡፡

ለማሰብ የሚከብድ አቅም ተሸክመህ እንደምትኳዝ ታዉቃለህ ? ካወቅክ አቅምህ እንቅልፍህን ይነሳሀል ፤ አላማህን አንድታሳካ ቀን ከሌት ያተጋሀል ፤ ሁሉንም ነገር ማሳካት ትችላለህ፡፡ አንድ የሚከብድህ ነገር ቢኖር ሁሉንም ማስደሰት መቻል ነዉ እሱን እንዳትሞክረዉ አትችለዉምና ። እንኳን የአንተ ስራ የፈጣሪ ቅንነት እና በጎ ስራ ሁሉንም አያስደስትም እና ፤ ያንተ ማደግ የሚያስደስታቸዉ እንዳሉ የሚቀነቅናቸዉም እንዳሉ ተረዳ ፤ ሁሉንም ለማስደሰት መሞከር የሽንፈትህ መጀመሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ እምነት እና ፅናት ካለህ ድል ሁሌም ያንተ ናት ታዉቃለህ አይደል ያ ትንሽ ልጅ ዳዊት ያንን ግድንግድ እና ግዙፍ ጎልያድን በአንድ ጠጠር እንደረታዉ፡፡ የአንተም የዉስጥ አቅም እንደዚህ ነዉ ብዙዎችን መርታት እና መማረክ ትችላለህ ሚስጢሩ ያለህን አቅም መረዳቱ ላይ ነዉ፡፡ አንተ ያለህ አቅም ከተጠቀምክበት ትንታግ የሆነ ሀይል አለህ ፤ ካንተ አልፎ አለምን መቀየር የሚያስችል፡፡ ልብ በል ይቺ ዓለም የተቀየረችዉ በጣም ጥቂት በሆኑ ደመ ሞቃት ትንታጎች ነዉ፡፡ ሌላዉ አብዛኛዉ ማህበረሰብ አጃቢ እና ጊዜዉ ሲደርስ ወደማይቀርበት ዓለም ተመልሶ ሂያጅ ነዉ፡፡ አቅማቸዉን ቀድመዉ የተረዱ ስኬታማዎች ብቻ ናቸዉ ላይሞቱ ለዘላለም የሚኖሩት፡፡

ቅን ሁኚ ቅን ለመሆን ምንም መስፈርት አይስፈልገዉም ፤ ቅንነትሽን ለሰዉ ለማሳየት ብለሽ እንዳታረጊዉ ፡፡ ይቺ ዓለም በብዙ አህዞች የሚቆጠሩ አመታትን ኖራለች ፤ ብዙዎችን ተቀብላ ብዙዎችን ሸኝታለች ፤ ከእነዚህ የትየለሌ አመታት ዉስጥ ያንቺ ድርሻ በአማካኝ 60 አመት ነዉ፡፡ ይቺን ኢምንት የሆነች የህይወት ቆይታሽን በቅንነት እና ከልብ በመነጨ ደስታ ብታሳልፊያት ነፍስሽ ምን ያህል ሀሴት የተሞላች ስኬታማ ነፍስ ትሆናለች፡፡ በፈጣሪሽም ዘንድ የከበረ ቦታ ያስገኝልሻል፡፡ አንድ አባባል ታክሲ ላይ አንብቤ ነበር ለሰዉ ቅን እንጂ ቅንቅን አትሁን ይላል፡፡ እዉነት ነዉ በህይወትሽ ከትንሽ እስከ ትልቅ ነገር ለሁሉም ቅን ሁኚ ያን ጊዜ አንቺነትሽ ለዘላለም በሰዎች ዘንድ ታትሞ ይኖራል፡፡ አንቺነትሽን ሞት አይንደዉም ስምሽ ከመቃብር በላይ ገንኖ ይወጣል፡፡ አንቺ ቅን ሆንሽ ማለት ብዙ ወጪ ሳታወጪ ብዙ ትርፍ አገኘሽ ማለት ነዉ፡፡ ቅን ያደረግሽላቸዉ ሰዎች ለአንቺ በምንም አይነት ክፍያ ልታገኚዉ የማትችይዉን በልባቸዉ ዉስጥ የሚገኝ የይዞታ ካርታ በቁጥጥርሽ ስር አዋልሽ ማለት ነዉ ለራስሽ ደግሞ በየትኛዉም ገበያ ላይ አሳደሽ የማትገዢዉን ዉድ ዉስጣዊ ደስታ በርካሽ አገኘሽ ማለት ነዉ፡፡

አላማ እና መድረሻ ይኑርህ ፤ መድረሻህ ካላወቅህ ግን ሁሉም መንገዶች ወደተለያየ አቅጣጫ ይወስዱሀል ፤ አንዳንዶችቹም ከገደል ጫፍ ላይ ያደርሱሀልና፡፡ ህልም እና ራዕይ ካለህ ደግሞ ሁሉም እንደተጓዘዉ መጓዝ አይጠበቅብህም ምክንያቱም የአንተ መንገድ እንደ መንጋዉ ሳይሆን የተለየ እና እጅግ ስኬታማ ነዉ፡፡ ታዉቃለህ አይደል 99 በመቶ የአለም ህዝብ በትንሾቹ 1 በመቶ የሚሆኑት እንደሚመራ እነሱ የተለዩ ሰዎች ሆነዉ አይደለም ፡፡ ነገር ግን ነገሮችን የሚያዩበት እና የሚጓዙበት መንገድ እጅግ የተለየ ነዉ፡፡ ስኬታማ ሰዎችም የተለዩ ነገሮችን የሚሰሩ ሳይሆኑ ነገሮችን በተለየ መንገድ የሚሰሩት መሆናቸዉን ልብ ልትል ይገባል፡፡ አላማ ካለህ ፤ የፅናትን አክሊል ከደፋህ ከፊት ለፊትህ የሚገጥም ጋሬጣ ሁሉ እዳዉ ገብስ ነዉ፡፡ አንተን ሳያከስምህ አንተ ታከስመዋለህ ፡፡ አላማህን ካወቅህ መድረሻህን ታዉቃለህ ፤ መድረሻህ ካወቅህ ደግሞ ዛሬ ያልጠረግከዉ መንገድ ለነገ ከየትም ስለማይመጣ መንገድህን አሁኑኑ መጥረግ ትጀምራለህ፡፡

መልካም አስቢ ፤ አመለካከትሽ የሚወሰነዉ በምርጫሽ ነዉ ፡፡ አንድን ሰዉ ከወደድሽዉ  አእምሮሽ ከእሱ ከሚወጡ ቃላቶች ጥሩ ጥሩዎቹን ይወስዳል ሰዉየን ከጠላሽዉ ደግሞ ምን ቁም ነገር ቢያወራ አእምሮሽ መጥፎ መጥፎዉን ይነቅሳል፡፡ ነገሮችን በቀና መልኩ መተርጎም እንደሚቻለዉ በአሉታዊ ጎናቸዉ ማየትም ይቻላል ፤ ይህ የሚወሰነዉ ለአእምሮሽ በምትሰጪዉ መልዕክት ነዉ፡፡ አዕምሮሽ የአንቺ ሎሌ ነዉ ፤ አንቺ የመገብሽዉን እና ያወረስሽዉን ብቻና ብቻ ነዉ ህሊናሽ ይዞ የሚቆየዉ፡፡ መልካም ማሰብ የሚገርም አእምሮአዊ ብቻ ሳይሆን አካለዊም ለዉጥ አለዉ ፡፡ ብዙ ግዜ የታማሚዎች ጤንነት ከአስተሳሰብ ጋር ይያያዛል፡፡ እድናለሁ የሚል ቀና ተስፋ ያለዉ ታማሚ ቶሎ የመዳን እድሉ የሰፋ ሲሆን ሞትን የሚያስብ ደግሞ ያዉ የመዳን እድሉ ይቀነሳል ምክንያቱም የአእምሮአችን ተግባር የአስተሳሰባችን ነፀብራቅ ነዉና፡፡ መልካም ካሰብሽ በቁምሽ አትሞቺም ፤ ስኬታማነትሽ በመልካምነትሽ ታጅቦ አንድ ቀን መምጣቱ አይቀርምና፡፡

ድክመትህን ለመስማት ፈቃደኛ ሁን ፤ እዉነተኛ ድክመቶችህን ሊነግሩ ለመጡ ወዳጆችህ ጆሮህን ስጣቸዉ ምስጋናም ቸራቸዉ ፤ ምክንያቱም የእነሱ ምክር እና ተግሳፅ ነዉ ለአንተ አርማታ ሆኖ ሙሉ ሰዉ እንድትሆን እና ቆመህ እንድትሄድ የሚያደርግህ ፡፡ እንደዚህ ስል ደግሞ ለእነዚያ ሀሜተኞች ጆሮ ስጣቸዉ እያልኩህ አይደለም ፤ ሀሜት አንድ ደስ የሚል ገፅታ አለዉ እሱም ዉጪ ዉጪዉን እንጂ አንተ ጋር አይመጣም ስለዚህ ትኩረት ንፈገዉ፡፡ ራስህን የምትፈትሽ ከሆንክ ለሽንፈት አትዳረግም ፤ አንተ የሂወትህ ሾፌር ነህ የሚያስፈልግህን ነዳጅ እና ጎማ በበቂ ሁኔታ መያዘህን ካረጋገጥክ ጉዞዉ አያሳስብህም ፤ ጎማህ በቂ አየር የለዉም ስለዚህ አስነፋዉ የሚልህ ጓደኛ ካገኘህ ጎማዉን ከእንደገና አረጋግጠህ በቂ አየር ከሌለዉ ለአስተያየቱ አመስግነህ ጎማህን አየር አስሞልተህ ትጓዛለህ ፤ ጎማዉ በቂ አየር ካለዉ ደግሞ ጓደኛዬ ተሳስቶ ነበር ብለህ

መንገድህን ትቀጥላለህ፡፡ አለበለዚያ የጓደኛህን ምክር ካልሰማህ እና ራስህን ካልፈተሸክ ግን መጥፎ ቦታ ላይ ትቆምና መመለሻ አጥተህ እንደወጣህ ትቀራለህ፡፡ ችግርህን ተቀባይ ልትሆን ይገባል ፤ የእናቴ ቀሚስ አወላከፈኝ አታብዛ ፡፡ አንተ ግን የእናቴ ቀሚስ አወላከፎኝ ሳይሆን መዝለል አቅቶኝ ነዉ የወደቅኩት ካልክ ራስህን ታዉቃለህ ማለት ነዉ፡፡ ሀላፊነትን መሸከም ስትችል ነዉ ስኬታማ እና የማይበገር የምትሆነዉ አለበለዚያ የራስክን እከክ ለሌላዉ ስታሸጋግር መፍትሄ አልባ የሆነ ኑሮ መኖርህ አይቀሬ ነዉ፡፡ ግሬድ A ስታገኝ ጎጆ ሰራሁ F ስታገኝ ደግሞ እከሌ ጫረኝ ካልክ ለመለወጥ እና ድክመትህን ለመለየት ፈቃደኛ አይደለህም ማለት ነዉ፡፡ ለምትሰራቸዉ እያንዳንዶቹ እንቅስቃሴዎች ካጠፋህ በበላይነት ተጠያቂዉ አንተዉ ፤ ጥሩ ከሰራህም ተወዳሹ አንተዉ ልትሆን ይገባል፡፡

እዉቀትን ብቻዉን መልቀሙን ትተሽ ከጥበብ ጋር ሰብስቢ ፤ እዉቀት ያለ ጥበብ እና ተግባር ከንቱ ነዉ፡፡ ብዙ መፅሀፍ ማንበቡ ፣ ቅኔ መቃኘቱ ፣ ክራር መደርደሩ ፣ ድግሪ በድግሪ ላይ መደራረቡ ስኬታማ አያደርግሽም ምክንያቱም ማንም ሊከዉነዉ የሚችለዉ ነገር ነዉና የሰራሽዉ፡፡ ከላይ ያሉትን ነገሮች ተጠቅመሽ ግን ያንቺን ዉስጠት እዉን ካደረግሽ እና ጥበበኝነትሽን እዉን ካደረግሽ አሁን ስኬታማ ነሽ፡፡ መቋጠሪያ ጆንያ ዉስጡ ካልተሞላ መቆም እንደማይችለዉ ሁሉ አንቺም ስኬትን ሳታስቢዉ ብታገኚ እንኳን እዉቀትን እና ጥበብን ዉስጥሽን ካልሞላሽዉ እንደ ባዶ ጆንያ መቆም ይሳንሻል፡፡ ስኬቱም አንቺን ለቆ ሞልቶ ወደ ሚጠብቀዉ ተረኛ ስኬታማ ይነጉዳል፡፡ እዉቀት ያለ ጥበብ እና ትምህርት ያለ ተግባር አንድ አይነት ናቸዉ፡፡ ሁለቱም አእምሮን ከመሙላት እና ራስን ጠቅሞ ከማኖር ያለፈ ለሌሎች አይተርፉምና፡፡

ዉድቀትን አትጥላ ፤ ዉድቀት የስኬት መንደርደሪያ መሆኑን ልትረዳ ይገባል ፤ ማንኛዉም የስኬት ጫፍ ላይ የተቆናጠጠ ሰዉ ጠጋ ብለህ ብታወጋዉ ያለፋቸዉን ፈታኝ ችግሮች እና ያጋጠሙትን አሜኬላዎች ያስወገደበትን ሚስጥር ሹክ ይልህል ፡፡ አየህ ወርቅ ወርቅ ለመሆን በእሳት ሊፈተን ግድ ይለዋል አለበለዚያ ወርቅ መሆን እንዳማረዉ ይቀራል እንጂ ከሌሎች ድንጋዮች የተሻለ አይሆንም፡፡ አንተም ችግሮች ሲገጥሙህ የምትወስዳቸዉ እና የምታልፍባቸዉ መንገዶች ናቸዉ ስኬታማም ፣ ተሸናፊም የሚያደርጉህ፡፡ ዉድቀት እንዳይመጣ የምትፀልይ ከሆነ አንተ ቀድመህ እጂህን ለዉድቀት ካቴና አስረክበህል እግርህንም በዉድቀት እግረ ሙቅ ተይዟል ማለት ነዉ፡፡ መዶሻ ብረትን ቀጥቅጦ ቅርፅ ሲያሲዘዉ መስተዋትን ግን አድቅቆ ይሰባብረዋል፡፡ አንተም የምትፈተንበትን መዶሻ ተቋቁመህ ዉድቀትን ድል ካደረክ ስኬታማ ትሆናለህ፡፡ እንደ መስተዋቱ ተሰባብረህ ተስፋ ከቆረጥክ እዚያዉ ከስመህ ስኬትን ስትመኝ ትኖራለህ፡፡

እድሎችሽን ተጠቀሚ ፤ ብዙዎች በእድል እና በጥረት መካከል ከፍተኛ ክርክር ያነሳሉ ፡፡ እድል ከጥረት የተሻለ ነዉ አይ ጥረት ያለ እድል ከንቱ ነዉ ይላሉ ፡፡ አሸናፊ የሚያደርግሽ እድል ብቻዉን ሳይሆን እድሎችን እንዴት ተጠቅመሻል የሚለዉ ነዉ፡፡ አንቺ ሎተሪ ደረሰሽ ቢባል ፤ አንቺ እድለኛ ሳትሆኚ እድልሽን የተጠቀምሽ ነሽና ምክንያቱም እኔም ሎተሪዉን ለመቁረጥ እና እድሌን ለመጠቀም ስላለሞከርኩኝ፡፡ በሂወትሽ ላይ የሚመጣ እድል በአግባቡ ከተጠቀምሺዉ አንቺ ስኬታማ ትሆኛለሽ ብዙዎቻችን እድሎች ወደ እኛ ሲመጡ አናዉቃቸዉም አንዳንዴ ምናልባት ካለፉ በኋላ ሊገለፁልን ይችላሉ፡፡ ስኬታማ ሰዎች ግን እድሎችን አነፍንፈዉ የተጠቀሙት እንደሆኑ ልብ ልትይ ይገባል፡፡ ንቅ ሁኚ እድል የት እንዳለች አታዉቂም ፤ እዚህ የምታነቢዉ ፅሁፍ ጋር ልትሆን ትችላለች አለበለዚያም ታክሲ ላይ ስትጓዢ እና ዙሪያሽን በደንብ ቃኚ፡፡ የእድል ትልቅ እና ትንሽ የለዉም ፤ ምክንያቱም ትንሽ እድል ወደ ትልቅ ጎዳና ታደርስናለችና፡፡ እያንዳንዶቿን እድሎችሽ አንጠፍጥፈሽ ተጠቀሚያቸዉ፡፡

ተግባሪ እንጂ ተናጋሪ አትሁን ፤ የአብዛኞቻችን ችግር አንደበታችን እና አስተሳሰባችን ፍየል ወዲያ ቅዝምዝ ወዲህ ሆኖ ነዉ የተቸገርነዉ፡፡ ህይወታችንን እንኖረዋለን ወይስ እሱ ይኖርብናል ፡፡ ቃል አባይ የሆነን ሰዉ ማንም አይወደዉም ፤

ማህበረሰባችን ያሉት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ ይላል ይሄም ምን ያህል ለቃሉ እምነት እንዳለዉ ያስረዳሀል፡፡ ድርጊቶችህ ከቃላት የበለጠ መናገር እና ማስተጋባት ይችላሉ ፤ ስለዚህ አንተነትህን እና ማንነትህን አንተ ሳትሆን ተግባሮችህ እንዲናገሩልህ ፍቀድላቸዉ፡፡ አንድ ሰባኪ ስለ አብርሀም ሲደሰኩር ዉሎ ተግባሩ ግን የቃየል ከሆነ ለሌሎች ብርሀን እየገለጠ እሱ ግን በጨለማ ዉስጥ እየኖረ ነዉ፡፡ የሚፀድቀዉ ደግሞ ያወራዉና የሰበከዉ ሳይሆን የኖረዉ እና የኖረዉ ብቻ ነዉ፡፡ ስለዚህ በቃ ሰርተህ አሳይ እንጂ በቃላት አትሽንግል አለቀ፡፡

የሚጠቅምሽን ብቻ መርጠሽ ስሚ ፤ መርጠሽ አዉሪ ፤ አንዳንዴ ጭንቅላታችን በፈጣሪ ሲሰራ ድንቅ ተደርጎ ነዉ የተሰራዉ ብየ አስባለሁ ፤ የሰማንዉን ሁሉ እንደ ካሴት የምንቀዳ ቢሆን ኖሮ የጭንቅላታችን ቦታ ሞልቶ አሁን ለማሰብ አንኳን የምትተርፍ ቦታ ማግኘት ከባድ ይሆን ነበር ፤ የትላንቱን ጥላሸት መርሳት ተስኖን ዛሬ መኖር ይከብደን ነበር፡፡ አምላክ መለኛ ነዉ እና መርሳት የሚባል ትልቅ ጥበብ አደለን፡፡ ቡና ላይ ቁጭ ብለሽ ጎረቤትሽን አትቦጭቂ መጀመሪያ የራስሽን ቀዳዳዎች ለመሸፈን እና ጥሩ ሰዉ ለመሆን ሞክሪ፡፡ ጆሮሽም ማጥለያ ሊኖረዉ ይገባል ፤ ካልጠቀመሽ አትስሚዉ ፡፡ ስትናገሪም ለከት ይኑርሽ ከአንደበትሽ የወጣ መጥፎን ቃል በምንም አይነት መንገድ መመለስ አትችይም፡፡ ለጥሩ ሰዎች ብቻ አንደበትሽን እና ጆሮሽን ለግሻቸዉ ያን ጊዜ አንደበትሽም መልካም ያወጣል ጆሮሽም መልካም መልካሙን መርጦ ይሰማል፡፡

አሜን ባይ አትሁን ፤ ሰዉ ስላደረገ ብቻ የምታደርግ ከሆነ በተሳሳተ እይታ ዉስጥ ነህ ማለት ነዉ፡፡ ለአንተ የማይስማማህ ከሆነ መሞገት እና አለመቀበል ይኖርብሀል፡፡ አለበለዚያ ያመጡልህን ሁሉ አሜን እያልክ የምትቀበል ከሆነ ማንም እየመጣ የፈለገዉን እዳ አንተ ላይ እያራገፈብህ ቆይቶ ራስህን ስትፈልገዉ ታጣዋለህ፡፡ ለምን ባይ ከሆንክ ግን የምትፈልገዉን ብቻ እየመረጥክ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ግትር ሳይሆን ፈታኝ ልትሆን ይገባል ፤ ያን ጊዜ ሰዎች አንተነትህን ይቀምሱታል፡፡ ሰዉ ቃሪያ የሚበላዉ እኮ የሚያቃጥል ስለሆነ እኮ ነዉ ፤ ጨዉ ጨዉ የሆነዉ በጨዋማነቱ ነዉ ፤ ሎሚ ሎሚነቱ የሚታወቀዉ ስለሚኮማጠጥ ነዉ ፤ ኮሶ በሽታን የሚነቅለዉ እጅግ መራር ስለሆነ እኮ ነዉ ፤ አንተም ፈታኝ እና አመዛዛኝ ከሆንክ እሙን ነዉ ፈተናዎችህ ይከብዳሉ ፤ ብዙዎች አይረዱህም ነገር ግን እመነኝ አሸናፊነት ግን ያንተ ነዉ፡፡ የጓደኞችህ ጫና የአንተን ህይወት ሊቀይረዉ አይገባም ፤ ከባድ ፈተናዎችን አልፈህ አንተነትህን ልታሳያቸዉ ይገባል፡፡

በራስሽ ተማመኚ ፤ ለራስሽ ክብር ስጪ እና ተማመኚበት፡፡ አንቺ ያልተማመንሽበት እና ያልተቀበልሺዉን ማንነትን ሌላ ማንም ሊተማመንበትና ሊቀበለዉ አይችልምና፡፡ አሸናፊዎች እና ስኬታማዎች በራሳቸዉ ይተማመናሉ፤ ነገሮችን ሁሉ በጥረታቸዉ ድል እንደሚያደርጉ ያምናሉ፡፡ ለእያንዳንዷ ድርጊታቸዉ ምክንያታዊነትንና ሀላፊነት መዉሰድን የያዘ ስለሆነ የሚመጣዉን ለመቀበል ራሳቸዉን አሳልፈዉ ይሰጣሉ፡፡ የአንቺ በራስ መተማመን ከአንቺ አልፎ ለሌሎች ተስፋ እና ብርሀንን ይፈነጥቃል ፤ ሰዎች እምነት እንዲጥሉብሽ ያደርጋል ፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የስኬታማነትሽ ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ ወዳለሽበት አይኑን አፍጥጦ እንዲመጣ ያደርገዋል፡፡

ጊዜ አጠቃቀምህ የአንተን ሂወት ከሚወስኑ ነገሮች እጅግ ጠቃሚዉ ነዉ፡፡ ለተረዳዉ ዓለማዊ ንጉስ ገንዘብ እና ንዋይ ሳይሆን ዓለማዊ ንጉስ ጊዜ ነዉ፡፡ ህፃናትን አዋቂ ፤ ድሀን ሀብታም ፤ ተመፅዋችን መፅዋች ፤ ምዕመንን ካህን ፤ ተማሪን መምህር ፤ ወታደርን ሀገር መሪ ማድረግ የሚቻለዉ ቢኖር ጊዜ እና ጊዜ ብቻ ነዉ፡፡ ጊዜን ተጠቅሞ ባህሩን የተሻገረ የስኬትን ደሴት ሲቆናጠጥ ፤ ጊዜዉን ያልተጠቀመ ገና ከጊዜ ደሴት ሳይደርስ ረጅሙ ባህሩ ዉጦ ያስቀረዋል፡፡ ስለዚህ የአንተም ምርጫ ጊዜን ተጠቅመህ ከስኬት ደጃፍ መድረስ አለበለዚያም በባህሩ ሰምጠህ በዚያዉ መቅረት ነዉ፡፡ ከስኬት ደጃፍ መድረስ ከሆነ ፍላጎትህ ከአሁን ጀምሮ ለጊዜህ ክብር ስጥ እና አንግሰዉ ፤ ለነገ ማሳደሩን ትተህ የዛሬን ዛሬ ላይ ጨርሰዉ ፤ የነገን ደግሞ ነገ ላይ ትከዉነዋለህና፡፡

ጓደኞችሽን ንገሪኝና ማንነትሽን እነግርሻለሁ ነዉና አባባሉ የጓደኞችሽ አስተሳሰብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያንቺ አስተሳሰብ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ይቺን አለም ለብቻ መግፋት ተራራን ገፍቶ እንደማንቀሳቀስ እጅግ ከባድ ነዉ ፤ ስለዚህም አብረዉሽ የሚያዘግሙ ጓደኞች ያስፈልጉሻል፡፡ ጓደኞችሽ ግን አብረዉሽ ሲያዘግሙ ወደፊት እንጂ ወደኋላ የሚስቡሽ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ወደኋላ የሚጎትትሽ ጓደኛ ካለ በመንገድሽ ላይ የቆመ ጋሬጣ ነዉና ከመራመድሽ በፊት መንጥሪዉ ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ከኋላ ከኋላ እየተከተለ እየወጋሽ ከስኬታማነት ጎዳና በገዛ ፈቃድሽ ያስወጣሻል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት አብዛኞቹን የምትተገብር/ሪ ከሆነ እርግጠኛ ሆኜ ልንገርህ /ሽ ስኬት ያንተ/ቺ ናት ማንም ከዙፋንህ/ሽ ንቅንቅ አያደርግህም/ሽም አሸናፊነት እና ድል ያንተ እና ያንቺ ነዉ ምክንያቱም ጦርነቱ የጭንቅላት ጥበብ ጦርነት ነዉና፡፡

" ግን ስኬት ምንድን ነዉ ? ስኬታማስ ማነዉ ? "

# 3.4 የስራ ባህላችን



ቆየት ያለ አንድ ተረት ወደ አዕምሮዬ መጣ ፤ በጥንት ጊዜ አንድ ሰዉ ነበር ይሄ ሰዉዬ ዘወትር እህል በገዛ ቁጥር ወይም እህል ከአዉድማ ባስገባ ጊዜ በቅርብ የነበሩት አጎቱ ጋር እየሄደ የፍየል ስልቻ ይለምናል። አጎትዬዉም በሰዉዬዉ ድርጊት ሁሌ ይደነቁ ነበር እናም ይሄ ስንት ፍየል ከነ መቅኔዉ ቀርጥፎ የመጠጠ ሰዉ አለማሰብ ነዉ እንጂ እንዴት የራሱ አንድ እንኳን ስልቻ ያጣል ብለዉ አሰቡ ፤ ያልማደኛ ሰዉ ከተወሰነ ቀናት በኋላ ያመረተዉን ሰብል ከአዉድማ ወደ ቤት ለማስገባት ብሎ መቋጠሪያ ስለቸገረዉ እንደተለመደዉ አጎቱ ጋር ሩጫዉን ጀመረ ፤ አጎቴ አስኪ እባክዎት አንድ ሁለት ስልቻ አበድሩኝ እህሉን ካስገባሁ በኋላ እመልሳለሁ ብሎ ጠየቃቸዉ ፤ የአጎትዬዉ ምላሽ ግን አስገራሚ ነበር ፤ እየዉልህ ልጄ በር ላይ የቆሙት የፍየል ወጠጤዎች ይታዩሀል አሉት ፤ ሰዉዬዉም እነርሱ አካባቢ አለ ሊሉት መስሎት ቸኮል ብሎ አዎን አለ ፤ አጎትዬዉም በል ደስ ያለህን ሙክት መርጠህ ይዘህ ሂድ አሉ ፤ ሰዉዬዉም ተደናግጦ አጎቴ ፍየል እኮ አላኩዎትም የፍየሉን ስልቻ እንጂ አለ ፤ አየህ ልጄ አንተ ካሁን በኋላ የራስህ ነገር ሊኖርህ ይገባ ሁሌ የእኔን እጅ ማየት የለብህም ስለዚህ ከፍየሉ ስልቻ አዉጥተህ ተጠቀም ብለዉ ሸኙት፡፡ ነጮቹ እንደዚህ ይላሉ ለጓደኛህ እዉነተኛ ወዳጁ ከሆንክ አሳዉን እያጠመድክ ከመስጠት ይልቅ ፤ ማጥመጃ ገዝተህ ስጠዉ ቀጥሎም አጠማመዱንም አሳዬዉ ይላሉ፡፡

በሀገራችን ልክ እንደ አጎትዬዉ ሰዉ በራሱ ጥረት ራስን እንዲችል ከማድረግ ይልቅ ስልቻ የማበደሩ ባህል የተለመደ ነዉ ፡፡ አንድ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ የወጣ ልጅ የራሱን እቅድ ነድፎ የሚንቀሳቀስበት ገንዘብ ከምንደጉመዉ ይልቅ ያለንን ጥሪት ለቃቅመን ለክብራችን ስንል ላንድ ቀን በሬ ጥለን ከሀገሬዉ ጋር ፍሪዳ በሚጥሚጣ ስንቆርጥ መዋል ይቀናናል፡፡ ያልጅ ወደ 17 ዓመት ሲማር እንኳን ስልክ ሊደዉልለት ቀርቶ መማሩ እንኳን ያላወቀ ሁሉ የምርቃቱን ስነ-ስርዓት ቀን አበባዉን ተሸክሞ ይግተለተላል፡፡ በሁለተኛዉም ቀን ሀገሬዉም ወደ እያለበት ልጁም ወደ የማያባራዉ እና እልህ አስጨራሹ የሥራ ፍለጋ ይሰማራል፡፡

ልጆቻችንን እንዴት ነዉ የስራ ባህል የምናስለምዳቸዉ ? አስታዉሳለሁ ህፃን እያለን አባታችን እኔና ወንድሞቼ ስራ ስንሰራ እየተፎካከርን አስቸገርን ፤ ትንንሽ እንደ ካልሲ የመሰሉ ልብሶች የሚያጥባቸዉ ጠፋ ፤ ጫማ አፅድቶ የሚቀባዉ አጣ ፤ እናታችን ካለሆነች ቤት የሚወለዉል ልጅ ጠፋ በመጨረሻም ያደረገዉ ነገር እስካሁን ያስደንቀኛል እኔ እና ሁለት ወንድሞቼን ጠራን እና እየዉላችሁ ልጆች ከዛሬ ጀምሮ ካልሲ ለሚያጥብ በአንድ ካልሲ 20 ሳንቲም ፤ ጫማ ለሚቀባ (

ቀለሙን እና ብሩሽ ተችሎለት) አንዱን 50 ሳንቲም ፤ ቤት ለሚወለዉል እና እቃ ለሚያፀዳ 2 ብር አለዉ ብሎ ተመን አወጣ ፤ መጨረሻም አብረን እንድንሰራ ብሎ ብር በየግል አይሰጣችሁም ፤ የእለቱን ደምራችሁ ወር ላይ ደሞዝ ሲወጣ ጠይቁ ገንዘቡን እዚህ የምታዩት የቁጠባ ሳጥን ዉስጥ ይቀመጣል ከዚያ ስትፈልጉት ትጠቀሙታላችሁ አለን ፤ እኛም ሳናቅማማ ወዲዉኑ ስራ ጀመርን፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ የታጠበ ካልሲ ድጋሜ ይታጠብ ጀመረ ፤ ጫማ ሁሉ አቧራ በነካዉ ቁጥር መወልወል ሳይሆን መቀባት ጀመረ ፤ ያ በሳምንቱ የሚወለወል ቤት ቶሎ ቶሎ መፀዳት ጀመረ ፤ በዚህ ሁኔታ አራት ወራት አለፉ እና እኛም ብሩን ስለምንፈልገዉ ይዉጣልን ብለን ለበላይ አካል ጥያቄ አቀረብን ፡፡ ከበላይ አካል አዎንታ እንዳገኘን ሳጥኗ ተከፈተች ፤ አላመንንም ሳንጠብቃት ካቅሟ በላይ ነበር የያዘቸዉ 220 ብር ፤ ዘመኑ አሁን የማንገለገልባት አምስት ሳንቲም እንኳን ከረሜላ የመግዛት አቅም ነበራት ፤ በ 1 ብር ከረሜላ ሳይሆን 4 እንቁላል ይገዛበት ነበር ፤ 30 ብር እንዳሁኑ የሽሮ ሳይሆን የዶሮ መግዣ ነበር ፤ ባጭሩ በወቅቱ 220 የአንድ አነስተኛ ገቢ ያለዉ ሰራተኛ የወር ደሞዝ ነበር እናም ይሄ ብር ለእኛ የማይታመን ነበር ፤ ልብ በሉ እዚህ ጋር አባቴ ሁለት ወፍ በአንድ ድንጋይ ነዉ የመታዉ የመጀመሪያዉ ልጆቹን የሥራ ጥቅም እንድንረዳ ሲያደርገን ሁለተኛዉ ደግሞ የቁጠባ ሳጥን በማዘጋጀት የቁጠባ ባህልን እና ጥቅም አስተምሮናል፡፡

እዉነት ለመናገር በስራ ፈጠራ እና በስራ ባህላችን ዙሪያ ያለን ግንዛቤ ገና ብዙ ይቀረናል ፤ ከቤታችን ቀጥሎ ሱቅ ከተከፈተ እኛም ሱቅ እንከፍታለን ፤ ስጋቤት ከሆነ ደግሞ ስጋቤት፡፡ ለነገሩ ሙሉ ለሙሉ በእኛ አይፈረድም የትምህርት ፖሊሲያችን ዉስጥ ኢንተርፕረነርሽፕ የሚል ነገር ዘሎታል ይሄም የተማርነዉን ሳይንስ እንደ ዉሀ ጠጥተን ከማንበልበል ፤ ምንም ሳንሰራበት በድግሪ ላይ ድግሪ ከመደረብ ፤ ወረቀት ከመለቃቀም ዉጪ በተግባር ጠብ የሚል ነገር ለህብረተሰባችን ብሎም ለእኛ ፋይዳ ያለዉ ነገር እንዳንሰራ አድርጎናል፡፡ ቤተሰቦቻችንም ትምህርት ቤት ሄደን ፊደል ቆጥረን እንድንመጣ ከማድረግ ዉጪ የቢዝነስ ፣ የስራ ፈጠራ ፣ መክሊታችንን የመከተል ፣ ራስን የመምራት ፣ ችግሮችን በብልሀት የመፍታት ጥበብ የመሳሰሉትን ነገሮች የማዉረስ እና በልጆቻቸዉ የማስረፅ ነገር አልተለመደም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት እና በተለያዩ ተጨማሪ ምክንያቶች የስራ ባህላችን የወረደ ነዉ፡፡ ለአብዛኞቻችን ስራችን አለቃችን አይደለም ፤ ለክፍያ ወይም ለበላይ አለቆቻችን ስንል ብቻ ነዉ የምንፈፅመዉ፡፡ የተወሰነ ጊዜያትን ተቸግረን የራሳችንን ነገር ይዘን ከመቆም ይልቅ የሰዉ ተቀጣሪ ሆነን ብዙ ሳንለፋ እየተሹለከለክን ገቢ ማግኘትን እንመርጣለን ፡፡

የሀበሻ ጀብዱ በአዶልፍ ፓርለሳክ ተፅፎ በተጫኔ ጆብሬ መኮንን የተተረጎመ ድንቅ ኢትዮጵያዊ መፅሀፍ ነዉ፡፡ አዶልፍ ፓርለሳክ ለኢትዮጵያ ፍቅር ህይወታቸዉን ለመሰዋት ዝግጁ ከነበሩ እና ኢትዮጵያን ልባቸዉ እስኪጠፋ ከሚወዱ ነጮች አንዱ ሲሆን በዘመነ ሀይለስላሴ ጣልያንን የተዋጋ ኢትዮጵያዊ ደመ ነፍስ ያለዉ ሰዉ ነው፡፡

አዶልፍ ፓርለሳክ ገና በዚያን ግዜ ኢትዮጵያን **"እንቅልፍ ላይ ያለች ሀገር"** ብሎ ነበር የሚገልፃት፡፡ የዜጎቿ ደካማ የሥራ ባህል ሁል ጊዜ ያበሳጨዉ ነበር፡፡ በመፅሀፉ ላይ ገፅ 30 የሚከተለዉን አገላለፅ ተጠቅሞ ምን ያህል ደካማ የሥራ ባህል እንደነበረን ትዝብቱን ያወጋናል፡፡

**"ከዛሬ አምስት አመት በፊት ማለት በመጀመሪያዉ በኢትዮጵያ ጉብኘቴ እነዚህ ወዶ ገባ ባሮች በስራ ላይ እንዳሉ የማየት እድሉ ገጥሞኝ ነበር፡፡ አዎ እነዚህ ባሮች ለጌታቸዉ የድንጋይ ቤት ለመስራት ድንጋይ እየለቀሙ ነበር፡፡ አስራ አራት ቀን ሙሉ ለቤት መስሪያ የሚሆን ድንጋይ ከአካባቢዉ እየፈለጉና እያመጡ ቤት ሊሰራበት ከታሰበዉ ቦታ ላይ ይከምራሉ፡፡ የነዚህን ባሮች አስራ አራት ቀን ስራ የአዉሮፓ ሁለት ወዛደሮች በአንድ ቀን ይሰሩት ነበር፡፡**

**ብቻ እነዚህ 20 የሚሆኑ ባሮች አስራ አራት ቀን ሙሉ እያንዳንዱ ባሪያ አንድ ሰዓት ሙሉ ድንጋይ ሲፈልግ ይቆይና በጣም አነስ ያለች ድንጋይ ሲያገኝ እሷኑ ያንጠለጥልና አምጥቶ ከዚች የድንጋይ ክምር ላይ ይወረዉራትና ከጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ ሁለት ሰዓት ያወራል፡፡”**

አዶልፍ ፓርለሳክ ገና በዚያን ጊዜ የነበረን ደካማ የሥራ ባህል ምን ያህል ከዘመኑ ወደ ኋላ እንሚያስቀረን ለመገመት አላደገተዉም፡፡ አሁንም በመንግስት ደረጃ እንኳን የአንድ ሰዉ አማካይ የሥራ ሰዓት 8፡00 ሰዓት በቀን ፤ በሳምንት ደግሞ ካሉት 168 ሰዓታት ዉስጥ 44 ሰዓታትን ብቻ እየተሰራ ፤ ከዚሁ ላይ በስብሰባና በግል ጉዳይ እየተቀናነሰ እንዴት ሆኖ ነዉ ከሌሎች የአዉሮፓ እና ኤዥያ ሀገራት ጋር በእድገት መፎካከር የምንችለዉ ?

የስራ ባህላችን በጣም ደካማ ነዉ ፤ በ1990ዎቹ ነዉ ፡፡ ጊዜዉ ቻይና በኢትዮጵያ አሁን እግሯን እና እጇን በሰፊዉ አንፈራጣ እንደ እንቦጭ አረም ለመስፋፋት ጠብ እርግፍ የምትልበት ነበር እና በኢትዮጵያ ላይ የተለያዩ መንገድ ፕሮጀክቶች ላይ ተሰማርታ የነበረበት ወቅት ነዉ፡፡ እናም በዚያም ወቅት የተለያዩ ኢትጲያዉያን በእነዛ የቻይና ካምፓኒዎች ስር ተቀጥረዉ ይሰሩ ነበር ፤ ነገር ግን የቻይኒቲን የስራ ጫና መቋቋም ያልቻሉት የኛዉ ሀገር የቀን ሰራተኞች የያዙትን አካፋ ከመዛቂያነት ይልቅ ብብታቸዉ ስር እየሸጎጡ መመርኮዣ ብሎም ማንቀላፊያ አደረጉት በዚህም ድርጊት የተበሳጩት መላ የማያጡት ቻይናዉያን አካፋዉ የሰራተኞቻቸዉ ብብት ጋር እንዳይደርስ አሳጥረዉ ቆርጠዉ መጨረሻ ላይ ለመያዝ እንዲያመች መያዣ ያለዉ ድንክዬ አካፋ አዘጋጁላቸዉ ፤ ሰዉ አስተሳሰቡ ካተለወጠ ብሎም ለስራ ተነሳሽነት እና ልምድ ከሌለዉ ከባድ ነዉ፡፡ ምንም እንኳን አካፋዉ ቢያጥርም እነዛ የቀን ሰራተኞችም እንደ ቻይኖቹ የአፀፋ ምላሽ አላጡም ፤ ያቺን አጭር አካፋ መሬት ላይ ይሰኳት እና መያዣዋ ላይ ቁጭ እያሉ ይዉሉ ጀመር ፤ በመጨረሻም ቻይኖቹ በጣም ተበሳጭተዉ የአካፋዋን መያዣ በመንቀል ጫፏን ለመቀመጥ የማይመች ሹል አድርገዉ አዘጋጁት፡፡ ከዚህም ይባስ ብሎ ለግንባታ የተዘጋጁ የተለያዩ እቃዎችን ለግል ጥቅማቸዉ ያሸሹ ነበር በዚህም ምክንያት ነበር ቻይናዊያን እነዚህ ሰዎች ሌላ ሀገር አላቸዉ እንዴ ብለዉ እስከ ማማት ያደረሳቸዉ፡፡ ይሄም ለስራችን እና ለህሊናችን ሳይሆን ለአለቆቻችን እና ለጥቅማችን ባሪያ እንደሆንን ማሳያ ነዉ ፡፡

እኛ ኢትዮጵያዉያን የምንታወቀዉ በደካማ ስራ ባህላችን ነዉ፡፡ ነገር ግን አሜሪካ ሀገር ቆይቶ የመጣ የማዉቀዉ ሰዉ ያወጋኝ የተገላቢጦሹን ነዉ፡፡ እኛ ኢትጲያዉያን አሜሪካን ሀገር የምንታወቀዉ ስራ ባለመናቅ እና በጠንካራ የስራ ባህላችን ነዉ ፡፡ በተለይ በዲቪ የተጓዘን ኢትዮጵያዉያን ኑሮን ለመቋቋም ስንል የማንሰራዉ ስራ የለም ፤ ቀን ከሌት ስራ ነዉ እንቅልፍ አጥተን ነዉ የምንኖረዉ ፤ ነጮቹ የሚጠሉትን ሽንትቤት ማፅዳት እና የጃጁ ሽማግሌዎችን መንባከብ እንኳን አይቀረንም ፤ በዚህ ምክንያት የስራ ቀጣሪዎች ለሀበሻ ሰራተኞች ቅድሚያ ይሰጣሉ ብሎኝ አረፈ፡፡ ሀገራችን ላይ ሀሞታችንን ምን አፈሰሰዉ ? ወኔያችንን የበላዉ ጅብ ምነዉ በዚያዉ ወጥቶ ድምጥማጡ ጠፋ ?

ብቻ ግራም ነፈሰ ቀኝ የስራ ባህላችን ደካማነት ላይ የማይስማማ አይኖርም፡፡ ቀጣዩ ነገር እንዴት ሆኖ ነዉ ይሄን ነቀርሳ ከአብዛኛዉ ማህበረሰብ ላይ መንቀል የሚቻለዉ የሚሆነዉ ጥያቄ ነዉ፡፡ ጥያቄዉን መመለስ ከተሳነን አለም በሮኬት ፍጥነት ስትምዘገዘግ እኛ በፈረስ እየገሰገስን እጅግ ተራርቀን የዛሬ 50 ዓመት ልክ እኔ አዶልፍ ፓርለሳክ በአፄ ሀይለስላሴ ጊዜ የፃፈዉን ፅሁፍ እንደጠቀስኩት ሌላዉ ተረኛ ደግሞ ይሄንን ፅሁፍ ይጠቅስ ይሆናል፡፡

“ ስራችን አለቃችን ፤ ስራችን ንጉሳችን ሊሆን ይገባል፡፡ ”

# 3.5 ወንበር ወደ እሾህ



ረዥሙን ሰልፍ ተሰልፌ ተራዬ ሲደርሰኝ ከመገናኛ ወደ የካ አባዶ G7 በአዲሱ እና ካሉን የከተማ አዉቶብሶች ዘመናዊ በሆነዉ የሸገር ትራንስፖርት ባስ ቲኬት ቆረጥኩ … ለትኬት ቆራጯ 5 ብር ሠጥቼያት የትኬቱ ዋጋ 3.50 ነበር እና 1 ብር መለሰችልኝ ፤ 50 ሳንቲም መልስ የለኝም ሳትይዝ ትመጣለህ አለችኝ ፤ ምን አለበት በስርዓት አንኳን ብታናግረኝ እያገለገለችኝ እስከሆነ ድረስ ሸገሮችም እንደ ታክሲዎች መመለስ ተዉ እንዴ ? ብየ ታዝቤያት ቀድሜ ስለገባሁ ካሉት መቀመጫዎች አንዱን መርጬ ተቀመጥኩ ፡፡ ሰዉ ገብቶ ከተቀመጠ በኋላ ከአጎነበስኩበት ቀና ስል አንድ በእድሜ ጠና ያሉ ሴትዮ ወንበር አጥተዉ ቆመዋል ፤ ኢትዮጵያዊነቴ ብሎም ያደኩበት ማህበረሰብ ባህል አስገድዶኝ ነዉ መሰለኝ ብድግ ብየ መቀመጫ ለቅቄላቸዉ እኔ በተራዬ ቆምኩ ፤ እሳቸዉም አልተግደረደሩም አመስግነዉኝ እና መርቀዉኝ ቁጭ አሉ፡፡

ከተወሰነ ጉዞ በኋላ ልጄ የሚል ድምፅ ከገበሁበት የሀሳብ ማዕበል ጎትቶ ካወጣኝ በኋላ ዞር ስል ሴትየዋ እግዜር ይስጥልኝ ባትለቅልኝ ኖሮ ቤት መድረሴ ራሱ ያጠራጥር ነበረ ብለዉ ወሬ ቆሰቆሱ ፤ እኔም እንዴት ? ብየ አቀጣጠልኩት ብታይ እስካሁን ሰዓት ድረስ ከጠዋት ጀምሮ ጉዳይ ለማስፈፀም እዚህ የካ አባዶ ኮንዶሚኒየም ከመኖሬ በፊት የነበርኩበት ቀበሌ ሄጄ ተገትሬ ነዉ የዋልኩት ፤ በእሮጊት አቅሜ ሲያጉላሉኝ ይሄዉ ሳምንት አለፋቸዉ ፤ ግፍ የማይፈሩ ፍጡሮች አሉኝ ፡፡ ስንቶቻችን ይሆን በየቀኑ በአግልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ የተማረርን ?

በሀገራችን አብዛኛዉ ሰዉ እኔን ጨምሮ መሔድ የማይፈልግበት ቦታ ቢጠየቅ ቁጥር አንድ መልሱ ቀበሌ መሆኑን አልጠራጠርም ፡፡ ቀበሌን እንድንጠላዉ ያረገን ምንድን ነዉ ? መቼም ቀበሌ ስንሄድ ለራሳችን ጥቅም ሲባል መሆኑ ሀቅ ነዉ ፤ ነገር ግን እዛ ከሄድን በኋላ የሚገጥሙን ወንበራቸዉ ላይ አቀማመጡን ሳይችሉበት ተንጋደዉ እና ወንበሩ ያላቅማቸዉ ረዝሞባቸዉ ተንጠላጥለዉ የተቀመጡ አመራሮችን እና የተለመደ ቢሮክራሲያቸዉን ጥላቻ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ሁል ጊዜ አንድ ጥያቄ አለኝ እነዚህ ሰዎች ለምንድን ነዉ እንደዚህ አይነት የተለመደ ባህሪ እና ቢሮክራሲ የሚያሳዩት መቀመጫዉ እሾህ ሆኖ እየወጋቸዉ ይሆን ? ወይስ ደልቷቸዉ ሁሉን ነገር አስረስቷቸዉ ? አለበለዚያም ከፊት ካለፉት ሀላፊዎቻቸዉ የወረሱትን ነገር እንደወረደ ለማስቀጠል ቆርጠዉ ተነስተዉ ? ምላሹን ለእነርሱ …

በዉጪዉ ሀገር እደምንሰማዉ እና በፊልም እንደምናየዉ መጀመሪያ ተስተናጋጅ ሲመጣ እንኳን ደህና መጡ … እባክዎን ምን ልርዳዎት ? ተብሎ ነዉ ከአቀባበሉ እንኳን ፤ እኛስ ሀገር … እሺ … ምን ፈልገህ/ሽ መጣሽ ተብሎ ገና ከመግባታችን

ያሸማቅቁናል፡፡ ቢገባቸዉ የተቀመጡት እኮ እኛን ለማገልገል ፤ የሚኖሩበት እና የሚተዳደሩትም ምክንያት እኛ ስላለን ለእኛ አገልጋይነት ተሾመዉ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ፡፡

አንዳንዴ ሳስበዉ ግራ የሚገባኝ ነገር ለምን ይሆን በምርጫ ጊዜ የአካባቢያዎቻችንን ተዋካዮች የምንመርጠዉ ? የዉጪዎቹ ሲያደረጉ ስላየን ይሆን ወይንስ ? አንድ የዉጪ ሀገር ሴናተር ከአካባቢዉን ተመርጦ ዉክልና ከተቀበለ በኋላ ከወከሉት ህዝቦች ጥያቄዎቻቸዉን በተለያየ መንገድ ይቀበላል ፤ ወካዮችም ፕላትፎርሞችን በመጠቀም ጥያቄዎቻቸዉን በቀጥታ ለሴናተራቸዉ ያቀርባሉ ፤ እሱም ያወያያቸል መጨረሻም መፍትሄ እንዲሰጥለት ለመንግስት ያስተጋባል፡፡ በእኛ ሀገር ግን ለየት ይላል ተወካዮቻችንን የምናዉቃቸዉ የምርጫ እለት በመምረጫ ወረቀት ላይ ፎቶአቸዉን የሆነ ፓርቲ ወክለዉ ተለጥፎ ሲሆን እነርሱ ግን እኛን አያዉቁንም፡፡ ይባስ ብለዉ ከመረጥናቸዉ በኋላ መኖሪያቸዉን ለቀዉ ኑሮአቸዉን በመዲናዋ ያደላድሉና ያዉ የፈረደበትን የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የተወከሉበትን መቀመጫ በጭብጨባ እያደናገሩ ያሟሙቁታል፡፡ ታዲያ ለምን ይሆን ተወካይ የምንመርጠዉ ... ያዉ ለደንቡ ይሆናል፡፡ ኧረረ ... ለመቀመጫዉ ነዉ ፤ መቀመጫዉ ባዶ እንዳይሆን ... እነሱስ ከሌሉ እጅስ ማን ያወጣል ? ማንስ የብሄር ትወና ይተዉናል ? ያልታደለ ወንበር ....

ልጅ ዳዴ ብሎ መራመድ እንደሚጀምረዉ ሁሉ ስልጣን እና ሀላፊነትም የሚጀምረዉ ከቤተሰብ ብሎም ከቀበሌ ነዉ ፤ ለቀበሌዉ ነዋሪ የቅርብ መንግስቱ የቀበሌዉ አስተዳደሩ ነዉ ፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን ከላይ ማለትም ከክልል እና ፌደራል የተሻለ አስተዳደር ቢኖርም ቀበሌዉ ብሎም ወረዳዉ ላይ የተቀመጡ ሰዎች ቅርባቸዉ ያለዉን የወከላቸዉን ህዝብ ማስደሰት እና ማገልገል ካልቻሉ ፤ ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለዉን ዓመኔታ እያሳጡት እነርሱም ወንበራቸዉን እያሟሸሹት ፤ እያደር ይሄ ወንበር እየሳሳ ፣ ቆዳዉ እየተላጠ ፤ እስፖንጁ እየሰመጠ ፤ ለማያያዣነት የተጠቀምንበት ሚስማር ከወንበሩ መሳሳት የተነሳ አግጥጦ እና አቅም አዉጥቶ የተቀመጠበትን ሰዉ ከስር ከስር ፋታ አሳጥቶ መጨረሻ ላይ ወይ አስነስቶ ራሱን ያስከብራል አለበለዚያም አዲስ ወንበር እንዲገዛ እና እንዲቀየር ያስገድዳል፡፡ የቀበሌ አመራርን ለምሳሌ ወሰድን እንጂ ችግር ያለባቸዉ አመራሮች ሁሉ ራሳቸዉን አስተካክለዉ ወንበራቸዉን ከእሾህነት ሊታደጉት ይገባል፡፡ እኛም ቢሮክራሲ የሚባለዉ ነቀርሳን ለማስወገድ ለዉጡን ከራሳችን መጀመር ይገባናል፡፡

አንድ አመራር ወንበር ላይ ተቀምጦ ሲጎረብጠዉ ከተቀመጠበት ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን ዞር ብሎ የወንበሩን ዙሪያ ቃኝቶ ችግሩን በጊዜ መለየት እና መፍታት ካልቻለ ፤ ቀኖች እየጨመሩ በመጡ ቁጥር ወንበሩ ከጎርባጣናት ወደ ሹል መርፌነት ተሸጋግሮ ድጋሜ መቀመጥ እንኳን እንዳይችል አድርጎ አስፈንጥሮ ያሰነሳዋል፡፡

ብዙ ጊዜ ሰዎች በቃችሁ የተንጠላጠላችሁበት ወንበር ለሌላ ልቀቁ ሲባሉ አሻፈረኝ ብለዉ የሞት ሽረት ትግል ሲያደርጉ ይታያል፡፡ እዉነት እነዚህ ሰዎች ይህ አባዜ የተጠናወታቸዉ የተቀመጡበት ወንበር ተመችቷቸዉ ነዉ ወይንስ በተቀመጡበት ጊዜ ያደረጓቸዉ ነገሮች ከወንበራቸዉ ሲነሱ እሾህ ሆነዉ መቆሚያ መቀመጫ እንዳያሳጧቸዉ ሰግተዉ ነዉ የሚለዉ ግላዊ ምላሽ የሚፈልግ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የዳኝነት እና የስልጣን ዙፋን ላይ ከነመዶሻዉ ቁጭ ካለ በኋላ የተሰጠዉንም ሀላፊነት ይሁን ስያሚ ዘንግቶ ህሊናዉን ሽጦ የያዘዉ ወንበር እንኳን ሳይቆረቁረዉ ለጊዜያዊ ጥቅሙ እና ለስጋዉ የሀሰትን ፍትህን ሲያሰምር እና የዉሸትን ነጋሪት በያዘዉ መዶሻ እየደጋገመ ሲደልቀዉ ይታያል፡፡ ይህ ሰዉ የራሱ መዳኘት እንጂ የእሱ በሌሎች መዳኘት (ጠብቆ ይነበብ) ማየት እንደተሳነዉ ቀኖች ቀኖችን ይተኩና ፣ ሰማይ ጎህ ሲቀድ ፣ ፀሀይ ደመናዉን ስትበታትነዉ ፣ ጊዜ ጊዜን ሲቀይረዉ ፣ ወንበሩን ሌላ ሲቀመጥበት ... ፍትህን በጎመደለበት እና በደበደበበት መዶሻ ፍርዱን ይቀበላል፡፡

ከየት መጣ የማንለዉ ሰዉ መስፈርቱን ብቻ ስላሟላ ከማይገባዉ ዙፍን ላይ መጥቶ ሲደነቀር ብዙ ግዜ አይተናል፡፡ በተለይ በመስሪያቤቶች የዉስጥ ሰራተኞች እድገት ላይ ብዙ ነገር ተመልክተናል፡፡ የግዝ ሰራተኛ የነበረ ሰዉ እድገት አግኝቶ የቴክኖሎጂ እና መረጃ ባለሙያ ሀላፊ ሆኖ ካሜራ ሲጨብጥ ፤ የጥበቃ ሰራተኛ የነበረ ሰዉ ፋይናንስ ገብቶ ሲያደናግረን ፤ ከምግብ ቤት ተራ ሰራተኝነት ዲግሪ ብቻ በመገኘቱ የአስተዳደር ስራተኛ ሆኖ የሰዎችን ችግር ሰምቶ ሊፈታ ከወንበሩ መጥቶ ግጥም ሲል .... ኧረ ብቻ ብዙ ብዙ ነዉ ብሶታችን ከተዘረዘረማ፡፡ ሰዉ የሚያድግበት መስፈርት ችሎታ እና ትክለለኛ የስራ ዉጤት መሆኑ ቀርቶ ወረቀት መልቀሙ ብቻ የሆነ ጊዜ ወንበርም የማይገባዉ ሰዉ መቀመጫ ሆኖ ይቀራል፡፡ ተቀማጩም በቂ ክህሎት እና ልምድ ሳይኖረዉ ስለተቀመጠ ፤ ራሱም ተጨንቆ ሰዉም አስጨንቆ ለችግሮች መፍትሔ መስጠት ተስኖት ፤ ባለጉዳዮችን በቅንነት ማገልገል አቅቶት ፤ ዉሳኔዎችን እና ድርጊቶችን ወደ ሌላ ሲገፋ ፤ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ላለመዉረድ የሙጥኝ ብሎ ይጣበቃል፡፡

ሌላዉ እና ትልቁ ስለ ስልጣን ያለዉ የአመለካከት ችግር ፤ ብዙ ጊዜ ወደ ስልጣን የሚያመሩት ብቃት ያላቸዉ እና የስኬት ጫፍ ላይ የተቆናጠጡ ሰዎች ሳይሆኑ ወንበራቸዉን ተጠቅመዉ የስኬትን ጥም መቁረጥ የሚፈልጉ ተስፈኞች መሆናቸዉ ነዉ፡፡ የራሳቸዉን ስራ መፍጠር የተሳናቸዉ ሰዎች ለሌሎች ስራ እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ሊያስተምሩ ከዙፋኑ ይሰየማሉ ፤ የራሱን ርዕዮተ አለም እና ድምፀት ማሰማት ያቀተዉ ፖለቲከኛ የገዢዉ ፓርቲ አባል ሆኖ ከፓርላማዉ ወንበር አንዷቷን የግሉ ያደርጋል ፤ ስፖርት በዘረበት ዞሮ የማያዉቅ ፖለቲከኛ የራሱን ቦርጭ እና ጤና ማስጠበቅ ሳይችል ለሌሎች ሊያስጠብቅ የስፖርት ሚኒስቴር ሆኖ ቦርጩን ታቅፎ ወንበሩ ላይ ይንጋለላል ... ታዲያ እንዴት ሆኖ ነዉ እነዚህ ሰዎች ራሳቸዉን ሳይለዉጡ ሾልከዉ ስልጣን ላይ ተቀምጠዉ ፤ የሌሎችን ህይወት መለወጥ የሚችሉት ? ያልተማሩትን ለሌሎች የሚያስተምሩት ?

አመራሮቻችን ላይ የምንመለከተዉ ችግር ይሄ ብቻ አይደለም ከፍተኛ የሆነ የራስ መተማመን እና ዉሳኔ የመስጠት ችግር ይታይባቸዋል ፤ ሁሉም ሳይሆኑ አብዛኞቹ አመራሮች የዚህ ቫይረስ ሰለባ ናቸዉ ፤ ራሳቸዉን ከላይ ላሉ አለቆች እንደ ሎሌ እንጂ እንደ ውሳኔ ሰጪ ቆጥረዉ በሚያገባቸዉ ሁኔታ ላይ እንኳን ዉሳኔ ከመስጠት ይልቅ በአለቆቻቸዉን ትዕዛዝ መነዳት ይቀላቸዋል፡፡ ከአለቆቻቸዉ የሚቀበሉትን ትዕዛዝ ደግሞ ተዋጠላቸዉም አልተዋጠላቸዉም ከመሞገትና የራሳቸዉን ሀሳብ ከማራመድ ይልቅ ልክ ባይሆንም ሳያምኑበት እንደወረደ መጋት ይቀናቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በወከላቸዉ ኅብረተሰብ ዘንድ አመኔታ አሳጥቶ ወንበራቸወን አሜኬላ በአሜኬላ ያደርግባቸዋል፡፡ መንግስት ይሄንን ለመፍታት እና በቂ አመራሮችን ለማፍራት መጣር ይኖርበታል፡፡

በጣም የሚያስገርመዉ በተለይ በመንግስት መስሪያቤቶች ላይ ከታች ከቀበሌ እስከ ፓርላማ ፤ ከፅዳት እስከ ፀሀፊ ፤ ከዘበኛ እስከ ስራ ሀላፊ ቢሮክራሲ ራሱን እንደ ወረርሽን አስፋፍቷል፡፡ በዚህ ምክንያት ጉዳይ በቶሎ ለማስፈፀም ዝምድና አለበለዚያም የሞቀ ብር ወይም ደግሞ የሞቀ ወንበር ያለዉ ሰዉ ይዘን መዞር እንደ ግዴታ እየታየ መጥቷል፡፡ አሁን አሁንማ ልምድ እየሆነ ከመምጣቱ የተነሳ ምርቃት እና መልካም ምኞት ላይ ከቢሮክራሲ ይሰዉርህ የሚል ሀረግ መጨመር ሳያስፈልገን አይቀርም ፡፡ አይገርምም እኔ እንዳየሁት በኢትዮጵያ ሙዚቃ ዉስጥ ከአባይ እስከ ባሮ ፣ ከእያነጓለለ እስከ ኮበሌ ፤ ከቤት አከራይ እስከ ቁራሌዉ ፤ ከዳቦ እስከ ሽሮ ያልተዘፈነለት ነገር የለም አሁን ደግሞ እሮሮ በሚል ርዕስ በኮሜዲያን ማርቆስ ፍቅረ ቢሮክራሲን የሚያሳይ ሙዚቃ እየሰማን ነዉ ፤ ይሄንን ነገር መንግስትም ሆነ እኛ ትኩረት ልንነፍገዉ አይገባም፡፡

ምንም እንኳን በሀገራችን ያለቦታቸዉ እና እዉቀታቸዉ የተሰነቀሩ ሀላፊዎች በብዛት ስለሚገኙ እና እኛንም ያስመረረን ጉዳይ ይህ ቢሆንም በቦታቸዉና እዉቀታቸዉ የሚያገለግሉን ቅን እና አገልጋይ የሰራ ሀላፊዎች መኖራቸዉን

መዘንጋት የለንብም ፡፡ እነዚህ ሰዎች የወከላቸዉን የማይረሱ ፤ የወንበራቸዉን ሽፋን በየቀኑ በለሰለሰ ቆዳ እየለበጡ የሚያድሱ ፤ ተቀባይነታቸዉን እየጨመሩ የሚመጡ መሆናቸዉን መረዳት ይኖርብናል፡፡

ወንበር ያኮስሳል ፤ ወንበር ያነግሳል እንዳያያዙ ነዉ፡፡ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል ያለፈበት ብሂል ነዉ ፤ አሁን ሲሾም ያልበላ ሲሻር ፍርድቤት አይሄድም ሆኗል ነገሩ፡፡ ስልጣን ላወቀበት የግልን ፍላጎት ማሚያ ፣ እግርን አንሰራፍቶ ተንደላቆ መገላበጫ ፣ ቁርጥ መቁረጫ ቢራ መገልበጫ የአባት ርስት ሳይሆን ቅንነትን ፣ ለጋስነትን ፣ ፍቅርን ፣ ፍትሀዊነትን … መስበኪያ ፤ የተገልጋይን ልብ ሀሴት መስጫ እና ክብርና ዝናን በወርቅ ጌጥ መለበጫ እንቁ ነዉ፡፡

“ ወንበራችንን ከእሾህማነት እንታደገዉ ! ”

# 4. ከወግ መንደር

" ሀይለኝነት እና የሚንተገተግ የጋለ ስሜት የተቀላቀሉባቸዉ ስሞችም አሉ፡፡ በተለይ እነዚህ ስሞች ፅብ ፅብ የሚሸታቸዉ ሲሆን ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን ያጠቃሉ ፡፡ ከእነዚህም ስሞች ዉስጥ ሀይለኛዉ ፣ ገስጥ ፣ ደባልቄ ፣ ጋርጠዉ ፣ ጥጋቡ ፣ በሀይሉ ፣ እሱ እንዳለ ፣ በግዱ ፣ ቀማቸዉ ፣ አሸብር ፣ አስጨናቂ ፣ እርገጤ ፣ አጋጨዉ አንዳንዶቹም ከዚህ አለፍ ብሎ ያላቸዉን የደም ጥማት ለልጃቸዉ ደመላሽ ብለዉ የብቀላን ዉህድ በስም መርፌ ይከትቡታል፡፡

.

.

.

ቀማቸዉ ተብሎ ጭብጦዉን ተቀምቶ ሲመጣ ፣ አስጨናቂ ስንለዉ ጭንቀት ሲያናዉዘዉ ፣ አጋጨዉ ተብሎ ተገጭቶ ሲመጣ ፣ እርገጤ ተብሎ ፌደራል ፖሊስ ሲረገጥ ... አይተናልና፡፡ "




" በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! "

# 4.1 ሶፍትዌር መሀንዲሱ




ብዙ ጊዜ ብዙዎቻችን የተማርነዉን ወደ ህይወታችን አምጥተን ለመተግበር እና በሌላ እይታ ለማየት ስንሞክር አይታይም፡፡ አንድ የሶፍትዌር ምህንድስና ተማሪ የፃፈዉ ለፍቅር ጓደኛዉ ደብዳቤ ይሄንን የሚመስል ቢሆንስ -

## <u>ስለ ሀርድዌር የተማረ ቀን</u>

ፍቅር በጆሮ በኩል በመሥማት ይገባል ሲባል ብሰማም የአንቺ ፍቅር ግን ለእኔ እንደ MOUSE በአይኔ በኩል ነበር የገባው፡፡ መጀመሪያ ያየሁሽ ቀን የአይኔ CURSOR አይንሽ ላይ CLICK ሲያደረግ የሆነ ነገረ ልክ በ POWER SUPPLY በኩል ገብቶ እንደተሰራጨ የኤሌክትሪክ ሀይል ውስጤን እንደ FAN ቢያንቀጠቅጠኝም ቀላል ነው ብዬ ሥላሠብኩ RAM ላይ አስቀምጬሽ ለማለፍ ወሰንኩኝ ፡፡ ፍቅርሽ ግን ሀያል ሆኖ ራሱን ROM ላይ SAVE AS አደረገ ይህም አልበቃ ብሎት ያለውን MEMORY በሙሉ ላንቺ በመውሠዱ ለሌላ ሰው የሚሆን CACHE MEMORY እንኳን ማስቀመጥ አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት MOTHERBORDE ለሌላ ሠው መግቢያ የሚሆን ምንም አይነት ትርፍ SLOT እንኳን የለውም፡፡

ያንቺ ፍቅር ለኔ መብራት ሲጠፋ አብሮ እንደሚጠፋ DESKTOP COMPUTER_ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ቻርጅ ይዞ እንደሚቆይ LAPTOP COMPUTER ነው ፤ መቼም ቢሆን ሊዘነጋኝ አይችልም፡፡ ላንቺ ያለኝ ፍቅር ልክ እንደ COMPUTER CHIPS ተቆጥሮ አያልቅም ፡፡ የልቤ CPU አንቺን REGISTERU ላይ STORE ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሥላንቺ ሣያስብ ውሎ አያድርም፡፡ የኔ ALU (Arthimetic Logic Unit) ሁል ጊዜ ሥላንቺ ሲደምር ፣ ሲቀንስ እና ሲቀምር ነው የሚውለው ስለዚህም የልቤ CMOS BATTERY ቢነቀልም እንኳን መቼም ቢሆን አንቺን ልረሳሽ አልችልም፡፡

የእኔ OUTPUT DIVICE ፍቅሬን እንደ MONITOR ፊትለፊት ቀርቤ ልነግርሽ ቢገፋፋኝም አንቺ ጋር ስደርስ ግን ድፍረቴ VIRUS እንዳጠቃው FILE CORRUPT ያደርጋል ፡፡

## ስለ ፕሮግራሚንግ ቋንቋ የተማረ ቀን

የሚገርመዉ ነገር ሰላንቺ ዉበት ሳስብ ፈጣሪ አንቺ ላይ ምን ያህል የ CSS ኮዶችን እንዳባከነ ይገርመኛል ፤ ከእናትሽ ወይም ከአባትሽ በ INHERITANCE ያገኘሽዉ መሆን አለበት፡፡

ይሄንን የፃፍኩልሽን ABSTRACT የሆነ ደብዳቤ ENCAPSULATE አድርገሽ ተጠቃሚዉ ማንም እንዲያየዉ አልፈልግም፡፡ የፃፍኳቸዉ ቃላት ADD AND DROP የሆኑ ሳይሆኑ ከዉስጤ የታመቁ SCRIPTS እንደሆኑ ተረጂልኝ፡፡

የጊዜዉን ሁኔታ እያየሽዉ ነዉ ሰዉ በየቀኑ እንደ PROGRAMMING LANGUAGE እየተለዋወጠ እና እየተቀያየረ አንድ ቦታ ላይ መቀመጥ አልቻለም፡፡ እኔ ግን የእኔ እና የአንቺ ግንኙነት በ WORDPRESS እንደተሰራ ዌብሳይት በቶሎ እንዲቋጭ አልፈልግም ፡፡ NORMALIZED የሆነ ጠንካራ BACKEND ያለዉ SECURED የሆነ የዘላለም ግንኙነት እንዲኖረን ምኞቴ ነዉ፡፡

ፍሬም ወርክ ስመርጥ ከ LARAVEL እና SPRING የቱን መምረጥ እንዳለብኝ ተቸግሬ ነበር፡፡ አንቺን ስመርጥ ግን ያን ያህል አልተቸገርኩም ምክንቱያም ስብዕናሽ ልክ እንደ GITHUB የገዘፈ ስለሆነ ነዉ፡፡

## ስለ ሶፍትዌር ኡደት (SOFTWARE LIFE CYCLE) የተማረ ቀን

ስላንቺ ብዙ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስቤ FEASIBILITY STUDY አድርጌ ነበር እና ባገኘሁት REQUIREMENT ANALYSIS መሰረት እንደ ሌሎቹ ሴቶች ጥቅም ፈላጊ (OBJECT ORIENTED) አለመሆንሽን ተረድቻለሁ፡፡ ከታች ከልጅነት ጀምሮ ቤተሰቦችሽ እነደ ህንፃ ARCTITECTURE ተጠንቅቀዉ PLAN አድርገዉ እንደቀረፁሽ ግልፅ ነዉ፡፡

እኔም በማንነትሽ ተማርኬ ካንቺ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረን ይሄዉ ደብዳቤ CODE በማድረግ ላይ ነኝ፡፡ የፃፍኩትን ነገር ከራስሽ ጋር UNIT TEST አድርገሽ ግንኙነታችንን IMPLEMENT ብናደርግ ደስ ይለኛል፡፡ ይህ ካለሆን ግን የፃፍኩትን MAINTAIN እንዳደርገዉ ያለሽን አስተያየት መልሰሽ DOCUMENT_ላኪልኝ፡፡፡

ግልፅ እንዲሆንልሽ ከምፈልገዉ ነገር አንዱ ጊዜ ልክ እንደ WATER FALL MODEL ናት ፤ አንዴ ካለፈችን ፍፁም ተመልሰን ልናገኛት አንችልም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን ስህተት እና ጉድለት ቢኖርብኝ ራሴን VERIFY እና VALIDATE እንዳደርግ ITERATIVE እድል ስጪኝ፡፡

## ስለ ማኅበራዊ ሚዲያ ደህንነት የተማረ ቀን

አንቺን ለማናገር እና ለማግኘት ያልሞከርኩት ነገር የለም ስላንቺ ብዙ ነገሮችን ኢሜል እና ፌስቡክሽን HACK አድርጌ ለማወቅ ጥሬያለሁ ፤ በኋላም ስህተቴን ተረዳሁት ከእነዛ MALWARE ከሆኑ መጥፎ ጓደኞችሽም እንድትርቂ DENIEL OF SERVICE (DOS) በማድረግ እንዳታገኚያቸዉ ሞከረኩ በመቀጠልም ANTI VIRUS UPDATE አድርጌ ያቀረብኩት የፍቅር REQUEST በአንቺ CONFIRMATION አግኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ACCOUNT CREATE አድርጌ LOGIN

እያደረኩ ያገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን ችያለሁ፡፡ ለዚህም ምሥጋና በማቅረብ ቀጣይ ራሴን በአዳዲስ VERSION UPDATE እያደረኩኝ ለመቀጠል ቃል እገባለሁ፡፡

ይሄንን ፅሁፍ ስናነብ የፍቅር ደብዳቤ የምናነብ ነዉ የሚመስለን ነገር ግን የሀገሬ ሰዉ "ልብ ያለዉ ልብ ይበል" እንደሚለዉ እዉነታዉ ከዚህ ለየት ያለ ነዉ፡፡ በአንድ ደብዳቤ በሚመስል ፅሁፍ ስር ብዙ የሀርድዌር እና ሶፍትዌር እዉቀቶች ተሸጉጠዉ ተቀምጠዋል፡፡ ማንኛዉም ከኮምፒዉተር ወይም ሶፍትዌር ጋር የተያያዘ እዉቀት ያለዉ ሰዉ ይሄንን ሲያነብ የተለየ እና የሚያስገርም ስሜት እንደሚሰማዉ አልጠራጠርም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ፅሁፍ ዉስጥ ብዙ ነገሮችን በቀላሉ ማስታወስ እና መረዳት ስለሚችል ነዉ፡፡

የትምህርት ስርዓታችን አንዳንዴ አዝናኝ ከመሆን ይልቅ አሰልቺ ይሆናል ተማሪዎች ነገሮችን በቀላሉ ለመያዝ ስልቹ ሲሆኑ ይታያሉ ፤ ለምሳሌ መጀመሪያ ላይ ያለዉን ፅሁፍ ያነበበ በቀላሉ የሀርድዌር አካል ክፍል እና ጥቅማቸዉን መረዳት ይችላል፡፡ አንድ መምህራችን ያወራን እዉነታ ትዝ አለኝ -

*መምህሩ የሶፍትዌር ዲፓርትመንት ተማሪዎችን ሰብስቦ እያስተማረ ነዉ፡፡ ስለ ሀርድዌር እና ሶፍትዌር ካስተማራቸዉ በኋላ የደስክቶፕ ሲስተም ዩኒት ከፍቶ ሀርድዌር ክፍሎቹን ሙሉ ለሙሉ ፈትቶ ካስረዳቸዉ በኋላ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች የዛሬዉ ክላሳችን ይሄን ይመስል ነበር ጥያቄ ካላችሁ ይላል አንድዋም ፈጠን ብላ እጇን አዉጥታ* ***"እንዴ መምህር ሶፍትዌርን መቼ አየን ?"*** *አለችዉ፡፡* እዚህ ጋር በልጅቷ መፍረድ አልችልም ምክንያቱም ልጅቷ ሶፍትዌር ቃሉን እንድትሸመድደዉ እንጂ በህሊናዋ እንድትስለዉ አልተደረገላትም፡፡ አሜሪካኖች እንደዚህ ይላሉ "ከነገርከኝ አላስታዉሰዉም ፤ ብታሳየኝ ላስታዉሰዉ እችላለሁ ፤ ካሳተፍከኝ ግን ለዘላለም አብሮኝ ይኖራል "፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ነገሮችን ቀላል ወደ ሆነ እና ለእኛ ቅርብ ወደ ሆነ ነገር ማምጣቱ ለእኛ የተሻለ እዉቀት እና ግንዛቤ እንዲኖረን ያስችለናል፡፡

በነገራችን ላይ ይሄ የሚጠቅመዉ ለሚማረዉ እና በሙያዉ ዙሪያ ላለ ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ማንኛዉም ስለ ኮምፒዉተር እና ተያያዥ ጉዳዮች እዉቀቱ የሌለዉ ሰዉ ብዙ አስኮላ ሳይገባ ፣ መፅሀፍ ማገላበጥ ፣ ብዙ ቪዲዮ መመልከት ሳይጠበቅበት በዚህ ፅሁፍ ብቻ ብዙ እዉቀቶችን በቀልድ መልኩ መቅሰም ይችላል፡፡

" ትምህርትን ከኑሮአችን ጋር እናዛምደዉ ! "

# 4.2 እዚህ እና እዛ



አንድ ትልቅ ሆቴል ዉስጥ የሚሰራ ወዳጄ ገንዘብ ያለዉ ነፃ ትኬት አበረከተልኝ እና አሁን በከተማችን ካሉ ትልልቅ ሆቴሎች አንዱ ዉስጥ ነኝ ፤ አዎ... ልክ ነህ ስሙ እንደዛ ነዉ፡፡ ደግሞ ለእሱ ማስታወቂያ ሰራ ብለህ ባልተከፈለኝ ቀብድ ስሜን እንዳታጠፋ፡፡

አሁን ያለሁበት ሆቴል ሁሉ ነገሩ ከተለመዱት ሆቴሎች ለየት ያለ እና በኢትዮጵያ ዉስጥ አሉ ከሚባሉ ዓለም አቀፍ ደረጃ ሆቴሎች አንዱ ነዉ፡፡ በሀገራችን ያሉትን ጥቂት ቱጃሮች ብሎም ዲያስፖራዎች እና አብዛኛዉን ከኢኮኖሚ ወለል በታች የሚኖረዉን የሀገሪቱን ህዝብ ለማነፃፀር ጥሩ ቦታ ስላገኘሁት እንደሚከተለዉ ፅፌዋለሁ፡፡

ከመግቢያዉ በር ይጀምራል ፤ ያዉ እኛ የለመድናቸዉ ምግብ ቤቶች እና ማዘርቤቶች በር ላይ ያለዉ ትራፊ የሚፈልግ ዉሻ አለበለዚያም ቡሌ የሚሰበስቡ ልጆች አጅበዉን የበሩ አግዳሚ እንይመታህ ጎንበስ በል ተብሎ ትገባለህ ፡፡ እዚህ ከመግቢያ በር ላይ ላንተ ሴንሰር ያለዉ ዘመናዊ መፈተሻ ዉስጥ ስታልፍ የያዝከዉ እቃህን ወይም ሻንጣህን ደግሞ ተንሸራታች መፈተሻ ተቀብሎህ በዛኛዉ መዉጫ በኩል ፈትሾ ያስቀምጥልሀል ፤ መቼም ጉድ ነዉ አቤት ስልጣኔ ብለህ ታልፋለህ ፤ እንደ መንግስት መስሪያ ቤት ዘበኞች ማሳጅ ይመስል ዳበስ አርጎ ማለፍ የለም ከነ ምናምንቴህ ነዉ የምትፈተሸዉ ፡፡

ለመታሸግ እንደ ተሰናዳ አበባ እስኪ ጠጋ ጠጋ በሉለት ተብለህ እየተጋፋህ ተጣበህ እንዳልበላህ ፤ እዚህ አንተን ዙሪያህን የሚከብህ አራት ወይም አምስት ሰዉ ሳይሆን አራት ወይም አምስት መቀመጫ ነዉ፡፡

በየአይነት ከፍርፍር ሳፈራርቅ የኖርኩ ሰዉዬ አሁን ረዥም የምግብ ዝርዝር ያለበት ሜኑ ደረቱን ገልብጦ ከፊቴ ግስጥ ብሏል፡፡ አይኔ ቶሎ ከምግቡ ዝርዝር ይልቅ ወደ ዋጋዉ ላይ ሲያነጣጥር ደነገጥኩ ጥቂት ባለ 2 የተቀረዉ ግን ባለ 3 አሀዝ ቁጥር ነዉ፡፡ እራሴን በል ተረጋጋ አንዴ ገብተህበታል ብየ መከሬ የብሩን ዋጋ እንዳላይ በቀኝ እጄ ሸፍኜ የምግቡን ስም ማጥናት ተያያዝኩት ፤ የማዉቀዉ ስም እያገኘሁ አይደለም ፤ በስም የተነሳ አትክልት ፈልጌ አሳማ እንዳይመጣልኝ ፈራሁ ፤ ግራ ገባኝ ምነዉ ይሄ ኢትዮጵያ ዉስጥ አይደለም እንዴ ፤ ነዉ ወይስ ያለ ፈቃድ እና ቪዛ የተሳሳተ ኢምባሲ ገባሁ ፤ ቢሆንም ትንሽ ትንሽ ስማቸዉን የማዉቃቸዉን እንደ ችፕስ ፤ ፒዛ እና ኮካኮላ በመኖራቸዉ ተፅናናሁ ፡፡

ባለ ሙሉ ሱፉ የሆቴሉ ማናጀር ይሁን አስተናጋጅ የማይለይ ሰዉዬ ስርዓት ባለዉ መልኩ እንኳን ደህና መጡ ፤ እባክዎትን ምን ልታዘዝ አለኝ ፤ ተጠራጥሬ ከኋላ ሌላ ትልቅ ሰዉ ይኖር ይሆን ብዬ ዞር አልኩ ፤ ማንም የለም እኔን ነዉ እርስዎ ያለዉ ፤ ይሄ ሰዉ ደንበኛ ንጉስ ነዉ የምንለዉን አባባል በተግባር ያዉቀዋል፡፡ ይሄ ሰዉን ማክበር ባህል የትኛዉም ቦታ ሊዳብር ይገባዋል ፤ ጎንበስ ብሎ ትእዛዜን ተቀብሎ ፤ እስከዚያዉ ዋይፋይ ይጠቀሙ ብሎ ፓስወርድ ሰጥቶኝ ሄደ ፤ ልክ ለመላጣ ሰዉ ሚዶ እንደ መስጠት ነዉ ፤ የእኔ ሞባይል እንኳን ዋይፋይ ልትቀበል ቀርቶ ከ 10 ብር በላይ ካርድ ከተሞላባት ትግላለች፡፡

ግቢዉ ዉስጥ የተንጣለለ እና ዉበቱ የሚያስደንቅ መዋኛ ገንዳ አለ ፤ ሰዓቱ ቀን በመሆኑ እና የሥራ ሰዐት ነዉና ህፃናት ናቸዉ ገንዳዉን በጅምላ የተቆጣጠሩት ፤ በዘመናዊ መዋኛ እቃዎች እቅፍ ተጠቅልለዉ ከዚህ እዚያ ይማስሳሉ ፤ የእኔ ህፃንነት እና የዋና ትዉስታ በአዕምሮዬ ላይ ድቅን አለብኝ ፤ እኔና ጓደኞቼ ቤተሰብ እንዳያየን ተደብቀን እንሄዳለን ፤ የምን ገንዳ ነዉ ፈጣሪ በሰጠን ወንዝ ላይ ገብተን እስኪበቃን እንቦጫረቃለን ፤ የመጀመሪያ ቀን ከሆነ እንዳሁኑ ማለማመጃ መሳሪያ ስለሌለ በጀሪካን እንገባለን፡፡ ጀሪካን ከሌለ ያዉ እስክንችል ድረስ ያንን የወንዝ ዉሀ በአፍም በአፍንጫችንም እየተጋትን ሆዳችንን እንደ ከበሮ ተወጥሮ ተንተተን እንወጣለን፡፡ የሰፈር ልጆች በአፍ እና በአፍንጫ የገባዉን ዉሀ ሆዳችንን እየተጫኑ እያስገነፈሉ በገባበት ይመልሱታል፡፡

አስተናጋጁ የታዘዘዉን ምግብ ይዞ ሲመጣ ከገባሁበት ሰመመን ወጣሁ ፤ አመሰግናለሁ ብዬ ተቀበልኩት፡፡ አይ ችፕስ ፤ መንገድ ላይ ሳልፍ ችፕስ መግዛት ልማዴ ነዉ ፤ እዚህ ችፕስ ስሟን ፍሬንች ችፕስ ብላ ቀይራ እና ተሽሞንሙና መጣች ዋጋዋ ግን ያ መንገድ ላይ ከለመድኳት ችፕስ ጋር አይነፃፀርም ፤ በዚህ ዋጋ ያቺ የመንገድ ዳር ችፕስ ብትሆን ኖሮ እንደዚህ በሳህን ሳይሆን በኩርቱ ፌስታል ነበር ተሸክሜ የምንጎራደደዉ ለዚያዉም ሻጯ ያን ያህል ድንች ካላት ነዉ፡፡ ፍሬንች ችፕስን አንድ ነገር አልክዳትም በጥራትና እና በጣዕም ያቺን የሰፈሬን ችፕስ እጅ ታስከነዳታለች፡፡

ፒዛ አሉሽ ስምሽን ቀይረዉ ለነገሩ ቂጣ ማለት እኮ ነሽ ፤ አይገርምም መመሳሰሉ ፒዛም ቂጣም አሰራራቸዉ ፣ መልካቸዉ ፣ ቅርፃቸዉ ፣ ባለ ሁለት ሆሄ መሆናቸዉ ያመሳስላቸዋል ፡፡ ልዮነታቸዉ ፒዛ እንደ ስሟ ቄንጠኛ እና ቅምጥል ናት እንደየ አይነቷ ከላይ አትክልት እና የተለያዩ ነገሮችን ትሸፈናለች ፤ በዚያ ላይ ቂጣ እንደ ሽንት ቤት ወረቀት ያለስርዓት ስንበጭቃት ኖረናል ፒዛ ግን በስርዓት በቢላዋ ነዉ የምትሰነጠቀዉ፡፡ ለነገሩ የሰዉም ልጅም ስም እኮ እንደ ቂጣ እና ፒዛ ከሀብት ጋር አብሮ ይቀየራል እየሩስ ወደ ጄሪ ፣ ቶማስ ወደ ቶሚ ፤ አለማየሁ ወደ አሌክስ ፤ ሶስና ወደ ሱዚ ፤ መኮንን ወደ ማይክ ሲቀየር አይተናል ፡፡ ይሄንን ሳሰላስል ስላነቀኝ ኮካ ጎንጨት አልኩኝ፡፡

ኮካዉ ራሱ ልዩ ጣዕም ዓለዉ እንዴ ፤ ወይንስ ለካ ምንም ይሁን ምንም የበለጠ ወጪ ያወጣንበት ነገር ጥሩ እና የተለየ ስለሚመስለን ነዉ፡፡ አንድ ወዳጄ የከፈሉበት እና የወደዱት ነገር ይጣፍጣል ይል ነበር ፡፡ ጠርሙሷን እጄ እስኪዝል ነበር ዘቅዝቄ ያንጠፈጠፍኳት ፡፡

ሆዴ ሆይ ይሄ ያንተ አይደለም በል የምን ፍሬንች ችፕስ ፤ የምን ፒዛ ፤ የምን ኮካኮላ ነዉ ያንን የለመድከዉን ቆሎህን አድቅቅ ፤ ያንን ትኩስ ቂጣህን ግመጥ ፤ የማይከፈልበትን የእግዜር ዉሀህንን አንደቅድቅ ፤ አንተ አይኔ ደግሞ እረፍ ያየሀዉን ሁሉ አትመኝ ፤ ስማ የሚጠቅምህን እና የማይጠቅምህን አመዛዝን ፤ ለነገሩ ይሄ እንኳን የአንተ ስራ ሳይሆን የጭንቅላቴ ነዉ ፡፡ ሆሆይ ይሄ እንደ ዳሽን ተራራ የተቆለለ ሂሳብ እራሴ ላይ ወጥቶ ያስቀባዥረኝ ጀመር ፤ የምከፍለዉ እኔ ብሆን እማ ኖሮ ቀድሜ አልገባም ብገባም በእግሬ ሳይሆን በአምቡላንስ ነበር የምመለሰዉ፡፡

ቤተመንግስቱን ማለቴ ሆቴሉን ከመልቀቄ በፊት ቀለል እንዲለኝ ወደ ሽንት ቤት አቅጣጫ አቀናሁ ፤ የምን ሽታ የምን ቆሻሻ አመጣህልኝ ጓዴ ፤ ለካ እንደዚህ በዉድ ዋጋ የተበላ ምግብ እና መጠጥ መበላቱ ብቻ ሳይሆን የሚራገፈዉም ለክብሩ በሚጠን እና እጅግ ፅዱ በሆነ ቦታ ነዉ፡፡ እዚህማ በፍፁም አልፀዳዳም እስኪ ያቺ መሽናት ክልክል ነዉ የምትል የሰፈሬ ማስታወቂያ ዛሬ ዉድ ነገር ይድረሳት ብዬ ተመልሼ ወጣሁ፡፡

ለዛሬዉ ከራሴ ጋር እየተሟገትኩና እየተገረምኩ በሰላም ቤቴ ገብቻለሁ ለሌላ ግዜ ግን እኔ አዉቃለሁ ፤ ያቺ የእናንተ ሰፈር እንቁራሪት ፤ ቤት የምትመጣዉ አስታወስካት ? በምን እንደሞተች ሰማህ ? በሬዉ ያንን የወንዝ ዉሀ ሲሸመጥጥ አየችዉ ፤ እሱን ካላከልኩ ብላ እሷም ሸምጥጥ ፤ በመጨረሻ እንደ ፊኛ ተወጥራ ፈነዳች እልሀለሁ ፤ አየህ ሁላችንም በአቅማችን የሚመጥነን ቦታ ልንገኝ ይገባል፡፡

ልብ በሉ እኔ ዛሬ በዚህ በክፍያ ትኬት ካርድ ለምሳ ብቻ ያወጣሁት ገንዘብ አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ለወር የማያገኘዉን ገንዘብ ነዉ፡፡ ስንቶቻችን ነን በዚህ አይነት የእለት ተእለት ኑሮ የምንኖረዉ ? እኛ ተርፎን ለፒዛ 350 ብር ለበርገር 170 ብር ፤ ለኮካ 50 ብር ስናወጣ ባዶ ሆዱን ተጠቅልሎ የሚያድር እና የሚያቃስት መኖሩን መዘንጋት የለብንም፡፡ እኛዉ ለእኛ ካልደረስንለት የእኛን ችግር እና እንቆቅልሽ ማንም አይፈታልንም፡፡ የመረዳዳት ባህላችን የበለጠ ማደግ ይኖርበታል፡፡ እስኪ ቱጃሮቻችን እና ዲያስፖራዎቻችን አንዳንዴ እንኳን ከራሳችሁ ወጣ ብላችሁ እንደ ጉንዳን የበዛዉን የዝቅተኛ ነዋሪ ህብረተሰብን አኗኗር ለመቀየር እና ሀሴት ለማግኘት የተቻላችሁን ሞክሩ፡፡

አሁን አሁን አብዛኛዉ ህዝብ ዉሀ ተቸግሮ ጥቂቶች ግን ገንዘብን እንደ ዉሀ ሲያፈሱት እያየን ነዉ፡፡ ኪሳችን ካልተገደበ ፤ ፍላጎታችን ካልተገደበ ፤ አፍስሰን አፍስሰን አንድ ቀን አደጋ ላይ መዉደቃችን አይቀርም ፤ አኗኗራችንም እዚህ እና እዛ ሆኖ ሀገራችን ላይ መኖር የማይቻልበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡

አንድ ወቅት የሰማሁት መረጃ ምን ይላል መሰላችሁ ፤ በአሜሪካ ሀገር የሚደፋዉ የምግብ ትራፊ ወይም በተለምዶ ቡሌ ተብሎ የሚጠራዉ ማለት ነዉ የአፍሪካን ዝቅተኛ ነዋሪ ህዝብ መመገብ ያስችላል፡፡

" አይ አንቺ ዓለም ላንዱ ሰቆቃ ላንዱ ድልቀቃ ! "

# 4.3 ግርምተ - ስም



በተለይ በቀደመዉ ጊዜ የልጆች ስም አወጣጥ ከሰዎች የእለት ተዕለት የህይወት አቅጣጫ ጋር የተንሰላሰለ ነበር፡፡ በወቅቱ ፎቶግራፍ እና ቪዲዮ ከአለመኖሩ ጋር ተያይዞ ይሁን አይሁን ምክንያቱን ባላዉቅም ፤ ወላጆች ትዝታዎቻቸዉን ፣ ያሳለፏቸዉን ጊዜዎች ፣ ችግሮቻቸዉን ፣ ህልማቸዉን ፣ ፅናታቸዉን ፣ ተስፋቸዉን አስፍረዉ እና ከትበዉ የሚያስቀምጡት በልጆቻቸዉ ስም ነበር፡፡

የአሁኑ ጊዜ ስያሜ አሰጣጥ ዉጥንቅጡ የወጣ ነዉ፡፡ የስም ትልቁ መስፈርት ሲጠራ ዉበት አለዉ ወይንም ዘመናዊ ይመስላል ወይ የሚለዉ አስተሳሰብ እያመዘነ መጥቷል ፡፡ ሀይማኖተኛ ሰዉ ከሆነ ደግሞ ወደ መፅሀፍ ቅዱስ ዞር ይልና ቃረም ቃረም አርጎ የሳበዉን ስም እንደ ታርጋ ለልጁ ይለጥፍለታል፡፡

ሁሉ ነገር ሽቅብ እየወጣ ባለበት በአሁኑ ጊዜ የስም እርዝማኔ መጠን ግን እየቀነሰ ነዉ፡፡ ባለረጃጅም ሆሄ ስሞች እየቀሩ ባለ ሁለት ወይንም ሶስት ሆሄ ስሞች እያጥለቀለቁን እንገኛለን፡፡

ከሰማኋቸዉ እና ግርምት ከሚፈጥሩብኝ ሀገር በቀል ስሞች የተወሰኑትን በምድብ ከፋፍዬ እስኪ ላጋራችሁ፡፡

## ምኞትን

ወላጆችችን ለልጆቻቸዉ ስያሜ ሲሰጡ የነበራቸዉን ምኞትን አንዳንዴም የወደፊት ፍላጎት ህልማቸዉን በልጆቻቸዉ ስያሜ ሲሰጡ ይታያል እነዚህም ስሞች ወላጆች በልጆቻቸዉ ተስፋ ዉስጥ የመኖራቸዉን ሚስጥር ያሳያል፡፡ እንደ ስናፍቅሽ ፣ ስመኘዉ እና ትንቢት የመሳሰሉት ስሞች ምኞታቸዉ እንደተሳካ ማሳያ ሲሆኑ እንደ ምትኬ ፣ ተስፋዬ ፣ ጤናዬ ፣ ነብዩ ፣ ኑርልኝ ያሉት ደግሞ ወደፊት በልጆቻቸዉ ላይ ያላቸዉን እምነት እና ተስፋ ከዚህም አለፍ ሲል ለልጆቻቸዉ ያላቸዉን ምኞት ያሳብቃሉ ፡፡ በሀሰት የታሰረ ፖለቲከኛ ሲፈታ የወላዳትን ልጁን ህሊና ብሎ የወደፊት ብሩህ ምኞቱን ይገልፅላታል ፡፡

ተገቢዉን ካሳ ሳይፈለዉ ቤቱን ያፈረሰበት ባለ ተስፋ ኮንዶሚኒየም ባያገኝም ልጅ ማግኘቱ ስለማይቀር ራሱን ካሳዬ ብሎ በተካዉ ልጁ ያፅናናል፡፡

## ሀይለኝነት

ሀይለኝነት እና የሚንተገተግ የጋለ ስሜት የተቀላቀሉባቸዉ ስሞችም አሉ፡፡ በተለይ እነዚህ ስሞች ፀብ ፀብ የሚሸታቸዉ ሲሆን ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን ያጠቃሉ ፡፡ ከእነዚህም ስሞች ዉስጥ ሀይለኛዉ ፣ ገስጥ ፣ ደባልቄ ፣ ጋርጠዉ ፣ ጥጋቡ ፣ በሀይሉ ፣ እሱ እንዳለ ፣ በግዱ ፣ ቀማቸዉ ፣ አሸብር ፣ አስጨናቂ ፣ እርገጤ ፣ ኢጋጨዉ አንዳንዶቹም ከዚህ አለፍ ብሎ ያላቸዉን የደም ጥማት ለልጃቸዉ ደመላሽ ብለዉ የብቀላን ዉህድ በስም መርፌ ይከትቡታል፡፡

በርግጥ ስሞች ናቸዉ እና በተጠሪዎች ላይ የሚፈጥሩት ስነልቦናዊ መነሳሳት እና ጫና ቢኖርም ልጆች የወጣላቸዉ ስም ተግባራቸዉን ይገልፃል ማለት ያስቸግራል፡፡ ቀማቸዉ ተብሎ ጭብጦዉን ተቀምቶ ሲመጣ ፣ አስጨናቂ ስንለዉ ጭንቀት ሲያናዉዘዉ ፣ ኢጋጨዉ ተብሎ ተገጭቶ ሲመጣ ፣ እርገጤ ተብሎ ፌደራል ፖሊስ ሲረግጥ … አይተናልና፡፡

## ገንዘብ

አንዳንዶቹ ወላጆች ልጆቻቸዉን ከገንዘብ አንፃር መግለፅ ምርጫቸዉ ሆኖ ይታያል ፤ አልማዝ አይቶ የማያዉቅ ሰዉ ልጁን አልማዝ ብሎ በእርሷ ይፅናናል ፤ ባለቤቱ ደግሞ ቀጣይዋን ልጅ ወርቂ ብላ ገበያ ሳትሄድ ፍራንካ ሳታወጣ ወርቋን ትሸምታለች፡፡ በየወሩ ደሞዝ ደረሰ አልደረሰ ብሎ የሚጨነቅ መንግስት ሰራተኛ የደሞዝ ተፅፅኖ ከኑሮ አልፎ የልጁን ስም ይቀማዋል ፡፡ የሰዉ ፍላጎቱ የተለያየ ነዉ እና አቅሙን የሚያዉቅ ድሀ ልጁን ድንቡሎ ብሎ ሲሰይም መንግስት ሰራተኛ ከሆነ ደግሞ ሺብሬ ይላል ከፍ ያለ ባለስልጣን ወይም ኢንቬስተር ከሆነ ደግሞ ሚሊዮን ብሎ ይቀጥላል ፤ እስካሁን ቢሊዬን የገባ ሰዉ የለም መሰለኝ ቢሊዮኔ የሚል ስም ለመስማት አልታደልኩም፡፡ ሌሎች የልጃቸዉ ባለፀጋነት ፍንትዉ ብሎ የታያቸዉ ቅዠት ሆኖ እንቅልፍ የነሳቸዉ ደግሞ ሀብታሙ ፣ ሲሳይ ወይም ፀጋዉ ሲሉ ያሞካሹታል፡፡ ኪሳራ ያስመረረዉ ነጋዴ ልጁን ትርፌ ብሎ በንግድ የከሰረዉን ያለ ምንም ቀረጥ በልጁ ስም ያካክሳል፡፡ የእለት ምግብ ፍጆታዉን መሙላት ተስኖት ከኑሮ ወለል በታች የሚኖር ምስኪን የሚያስበዉ ስለ ዕለት ቁርሱ ነዉ እና ስንቄ ብሎ አፅምሮቱን በልጁ ስም ይወጣል፡፡ ታዲያ ምን ዋጋ አለዉ አንዳንዱ ሀብታሙ ተብሎ ሀብታም ደጃፍ ላይ ሳይደርስ እተገረዘበት አልጋ ላይ ይገነዛል፡፡

## ባህሪያት የሚገልፁ

አንዳንድ ህፃናት በተወለዱበት ጊዜ የሚያሳዩት ፀባይ ወይንም አመል ለስያሜያቸዉ መጠሪያ ሆኖ ይቀራል፡፡ ከዚህም ባለፈ ወላጆች ለልጆቻቸዉን የሚመኙትን ባህሪ መጠሪያቸዉ አድርገዉ ያንፀባርቁታል፡፡ እንደፈለጉ ሲያንቆሳብሏት ኮሽ የማትል ህፃን ስሟ ትዕግስት ፣ ይታገሱ ፣ እንደልቤ ወይንም ጥሩ ነሽ ይሆናል ፡፡ ሲያጫዉቱት ግንባሩን የሚቋጥር እና ፈገግ የማይል ቆፍጣና ጨቅላ ኩራባቸዉ ይፀድቅለታል ፡፡ ያዙኝ ልቀቁኝ ባይ ፣ ታጋይ አልሞት ባይ ተጋዳይ ከሆነ ጫኔ ወይንም በልሁ አይቀርለትም፡፡ የዋህ የዕግዜር ልጅ ከሆነ አለበለዚያም ቤተሰቦቹ እንዲሆን ከተመኙለት ደግሰዉ ብለዉ ይሾሙታል፡፡ ሁሉን ቻይ ሆደ ሰፊ ከመሰላቸዉ ደገሞ ቻላቸዉ ይበየንለታል፡፡

## ምስጋና

ልጆች ለወላጆች ከብቸንነት ወደ ቤተሰብነት ፤ ከጨለማ ኑሮ ወደ ብርሀን እና ተስፋ ወደ ተሞላበት ኑሮ መሸጋገሪያ ናቸዉ ፡፡ በዚህም ምክንያት ወላጆች አምካቸዉን አጥብቀዉ ያመሰግናሉ ከዚህም አለፍ ብለዉ የልጆቻቸዉን ስያሜ በዛዉ

በምስጋናቸዉ አፅነተዉት ይቀራል፡፡ ለዚህም አንደ ተመስገን ፣ ችሮታዉ ፣ በእሱ ፍቃድ ፣ ስጦታዉ ፣ ረድኤት ፣ በረከት ያሉ ስሞች ማሳያ ይሆናሉ፡፡

ያዉ አንዳንድ ቤተሰብ ንግስናን ተመኝቶ ባይሳካለትም ፤ ራሱን በራሱ ለማንገስ ልጁን ይወልድና የተወለደዉንም አንቦቃቅላ ዘዉዴ ፤ ሴት ከሆነችም ያዉ ዘዉድ ነሽ ብሎ ሰይሞ አምላኩን ያመሰግናል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ሲወለድ ዙፋን …

## ከምግብ ጋር የሚያያዙ

እኔን ፈገግ ከሚያረጉኝ እና ከሚያስገርሙኝ የስም አይነቶች ዉስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከምግብ ጋር የሚያያዙ ስሞች ናቸዉ፡፡ ሰዎች ምን ያህል ለምግቦቻቸዉ ፍቅር እና አድናቆት ቢኖራቸዉ ነዉ አድናቆታቸዉ ከአድናቆትነት አልፎ የልጆቻቸዉን ስም የሚነጠቃቸዉ ?

ወደ ፍራፍሬ ተራ ስንገሰግስ ምንም እንኳን አሁን ትርንጎ ገበያ ላይ ብዙም ባይታይም ትርንጎ የሚባል ስም ግን ሞልቷል ፣ የሎሚ መዓዛ ሲያዉደን የሎሚ እሸትን አንዴት እንዘነጋታልን ፣ ብርቱካን ኪሎ ሀምሳ ብር መገባቱ ፍንትዉ ብሎ የታየዉ አርቆ አሳቢ አባት ልጁን በደህና ጊዜ ብርቱካን ብሏት ከብርቱካን ተራ ተሰዉሯል፡

ወደ እህል ተራ ከፍ ስንል ደግሞ እሸቱ ፣ ስንዴነሽ እና ምስር አይነት ስሞች አይጠፉም፡፡ ኧረ ሌሎችም እንደ ማሬ ፣ ወተት አይነት አስገራሚ ስሞችንም ኮምኩመናል፡፡

## ምስሰል

በተለይም በጎጃም አካባቢ ደግሞ ስም ከስምነቱ በተጨማሪ ተያያዥነት ያለዉ ትርጉም እንዲሰጥ ተደርጎ ነዉ የሚወጣዉ፡፡ ሰሙ ከስምነት አልፎ አረፍተነገር መሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ እንደ አዝመራዉ በቀለ ፣ ጠቢቡ ሰለሞን ፣ ንጉሱ ነገሰ ፣ ዝናቡ ዘነበ ፣ ሀይለኛዉ አየለ ፣ እሸቱ ደረሰ ፣ ፍቅር ይልቃል ያሉ ስሞች ብቻቸዉን መልዕክት ማስተላለፍ የሚችሉ የስያሜ አይነቶች ናቸዉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ስሞች እንዳሉ ሆነዉ እኔ በግሌ አንዳንድ ዘና የሚያደርጉ ስሞችም ገጥመዉኝ እና ፈገግ አርገዉኝ ያዉቃሉ ልክ እንደ እህል ዉሀ ፣ ሙጬ ፣ ቁልጮ ፣ ጨበር ፣ ለጥ ይበሉ ፣ ትንቧለል ፣ ሲደልል ፣ ግድየለዉ ፣ ትንቡሾ ፣ አይታከቱ ፣ መሸኛሽ ወርቅ ፣ ዳገቱ ፣ ሰንደቁ ፣ አንቲገን (Anti-GUN) እና ማስቲካ ያሉ ስሞች ይገኙበታል፡፡

ለካ የትዝታ ንጉሳችን ጋሽ ማህሙድ አህመድ ማን ብዬ ልሰይምሽ ብሎ ከራሱ ጋር ሙግት ዉስጥ የገባዉ ያለ ምክንያት አይደለም ?

**ማሳሰቢያ** - እነዚህ ስሞች በአማራዉ ክልል በተለይም በሸዋዉ አካባቢ የሚዘወተሩ እና ሁሉም የተዘረዘሩት ስሞች ሰዎች የሚጠቀሟዉ ስሞች እንጂ ፈጠራዎች እንዳልሆኑ በአፅንኦት እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡

" ስሙ የተፃፈ ካለ መከፋት አይቻልም … የተግባር እንጂ የስም ትልቅ እና ትንሽ የለዉምና ! "

# 4.4 ሁላችንም ሌቦች



ማክሰኞ ሀምሌ 17 2011 ዓ.ም ይሄን ቀን ደመቅ ካደረጉ ዜናዎች አንዱ የሙዚቃ ንግስታችን ድምፀ መረዋዋ አስቴር አወቀ 26ኛ የአልበም ስራዋ ለአድናቂዎቿ የምታበረክትበት ቀን ነበረ፡፡ 11 ሙዚቃዎችን ያካተተዉ ጨዋ የተሰኘዉ አልበሟ ዉስጥ 9ኙ ስራዎች ሙሉ ለሙሉ ግጥም እና ዜማቻቸዉ የእራሷ ሲሆኑ 2ለቱ ላይ ደግሞ የግጥም እና ዜማ ጠበብቱ የምናከብረዉ ይልማ ገብረዓብ አሻራዉን አሳርፎባቸዋል፡፡ እኔም ከመስሪያቤት ለምሳ በወጣሁበት ቅፅበት ሸገር ባንድ እግሯ ቆማለች፡፡ አዟሪዎች ሁሉ መፅሀፍቶቻቸዉን መቸርቸር ትተዉ የንግስቷን አልበም ይቸረችሩታል፡፡ ሊስትሮ የሚባል ነገር የለም ሁሉም በየመኪናዉ በየሰፈሩ በየጉራንጉሩ ይዞ ይርመሰመሳል፡፡ በጉጉት ሲጠብቅ የነበረ አድማጭም ቀለም እያደረገ መግዛቱን ተያይዞታል፡፡ አላስችልህ ያለዉ የመኪናዉን ቴፕ እያጎረሰ ይኮመኩማል፡፡ ብቻ ከተማዉ ቀዉጧል ፤ እዚህም እዚያም ጨዋ በጨዋ ሆኗል፡፡ የአስቴካ እንደ ምንጭ ዉሀ ኩልል ብሎ የሚወርድ ለዛ ያለዉ ዉብ ዘመን አይሽሬ ደምፅ ይንቆረቆራል ፤ ስቅርቅር እያለ አንጀት ድረስ የሚደርስ ልዩ ቅላፄ ፤ የተለየ ምት ብቻ እጅግ እፁብ ድንቅ ስራ፡፡

አመለ ጨዋ … ዲሪሪሪሪ … ሲገኝ የሚበጅ … ዲሪሪሪሪ …..

እንሰሳም ይለምዳል … ዲሪሪሪሪ … እንኳን የሰዉ ልጅ

.

.

.

አልወራረድም … ዲሪሪሪሪ … ከእንግዲህ በመልኩ … ዲሪሪሪሪ …

ጨዋነቱ እንጂ … ዲሪሪሪሪ … የወንድ ልጅ ልኩ

.

.

.

እየተደመምኩኝ ደስ ሲለኝም … አመለ ጨዋ …. ዉድድ … እያልኩኝ ተመልሼ ወደ ቢሮ አመራሁ፡፡ ቢሮ ገብቼም አብዛኛዉ ስራዬ ኢንተርኔት ላይ እንደመሆኑ በገባሁበት ቅፅበት የዩቱዩብ ገፆች ሁሉ የእርሷን ስራዎች በህገወጥ ለቀዉ እያስኮመኮሚቸዉ ነዉ፡፡ በደቂቃዎች ዉስጥ በአስርሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ኮምኩመዉታል፡፡ ግልፅ ብሎ ታየኝ መቼ ይሆን የሰዉ ልፋት የሚገባን ? እኛ ጥበብ ሞተች እያልን ፤ እዚሁ ደግሞ ጥበብን እየቀበርናት ነዉ፡፡ ታዲያ ምኑ ላይ ነዉ የሚገርመዉ ያላከበርናትን ጥበብ የማንም ስራ ፈት ባተሌ እየመጣ ቢፈነጭባት፡፡

ዛሬ የአስቴር ነገር ሆነና ግልፅ ብሎ ታየኝ ፤ ለካ ሁሌም ስንሰርቅ የኖርን ሙልጭ ያልን ሌቦች ነን፡፡ ምክንያቱም ሌባ ማለት ያልሰራበትን የሚቀማ ፤ ያልከፈለበትን ሰርቆም ይሆን የተሰረቀ የሚጠቀም ፤ ሰዎች የልፋታቸዉን ሳያገኙ የፈጠራ ዉጤታቸዉን በነፃ የሚኮመኩም ስለሆነ፡፡

ይሄ ሌብነታችን ብዙዎችን ተመፅዋች እና አመድ አፋሽ አድርጓል፡፡ ያከበሯት ጥበብ ሳታስከብራቸዉ እንድትቀር አድርጓል፡፡ አርቲስቶቻችን ታመዉ እንኳን እጃቸዉን ለምፅዋት የሚዘረጉ ፣ ተቸግረዉ የሚለመንላቸዉ ፣ ሰርተዉ ያጡ መናኛ ሲሆኑ አይተናል፡፡

ከህሊናህ የማይጠፉ የሀገርኛ ፊልም ጥራ ብባል በመጀመሪያ የምጠራዉ ፊልም ከሂወቴ የፊልም ሰንጠረዥ መጀመሪያ ላይ የተቀመጠዉ ላምባ የተሰኘዉ በኩላሊት ህመምተኞች ላይ ያተኮረዉ ፊልም ነዉ፡፡ ይሄ ፊልም ከእዉነት አንጀቴን ከሰረሰሩት እና የሰዉ ልጅ ምድራዊ ፈተናን ካሳዩኝ በተጨማሪም በጥንቃቄ ከተሰሩ ኢትዮጵያዊ ፊልሞች ለእኔ ግንባር ቀደሙ ነዉ፡፡ ሁል ጊዜ ስለ ኩላሊት ህመም ሲነሳ በአዕምሮየ ዉስጥ የሚመጣብኝ ገፅታ የፊልሙ መሪ ተዋናይት ናት፡፡ የፊልሙ ዳይሬክተር አንተነህ እና ሌሎችም ባለቤቶች የፊልሙን ገቢ በቅንነት ለኩላሊት ህሙማን ቢያበረክቱም ብዙም ሳይቆይ ነበረ ከሲኒማ ቤት ተሰርቆ የታሰበለትን ያህል ሳያበረክት በአጭሩ የተቀጨዉ፡፡ ከዚህ በላይ ምን ከንቱነት እና ሌብነት ይኖራል፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ዉስጥ ቁምነገር ያለበት ፤ የተለፋበት እና በጥንቃቄ የተሰራ ፊልም የለንም እያሉ ማሚረት ከንቱ ድካም

ነዉ፡፡ ያዉ ያንን የለመድነዉን እንቶፈንቶ የቃላት ጨዋታ እየሰማን እንሽካካለን፡፡ መጀመሪያ ሰዎችን ከመተቸታችን በፊት እኛ ሀላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል፡፡ አረጂናሉን እየገዛን ፣ ሲኒማ እየኮመኮምን ፣ የተጣመመዉን የጥበቡን ኢንደስትሪ ልናቃነዉ ይገባል፡፡

ከሁሉም የባሰ ሌብነት ያየሁበት ሌላዉ የጥበብ ዘርፍ ደግሞ የመፅሀፍት እና ህትመቱ ዘርፍ ነዉ፡፡ መፅሀፍት ቅጂ እና ሽያጭ ቁጥጥር የሌለበት እና በጥቂቶች እጅ ስር የዋለ የጥበብ ኢንደስትሪ ነዉ፡፡ በራሴዉ ዳቦ ልብ ልቡን አጣሁት እንደሚባለዉ ፀሀፊዉ (ደራሲዉ) የሚገባዉን ጥቅም የማያገኝበት እና ከደሙ ንፁህ የሆነበት ፣ አሳታሚዎች ፣ አከፋፋዮች እና ሻጮች ብር የሚቃረጡበት ቅጥ ያጣ ሂደት ነዉ ያለዉ፡፡

እንደ ይስማዕከ ወርቁ (ዴርቶጋዳ) ፤ አረቡ አብደላ (ኤክስትሪም ሲሪየስ) ያሉ ኢትዮጵያን ፀሀፊያን እና ደራሲያን እዉቅና ካገኙ በኋላ ያደረጉት የመጀመሪያ ስራቸዉ የራሳቸዉን ማተሚያቤት ማቋቋም ነበረ፡፡ ይሄ የሚያመለከተዉ የነበረባቸዉን የህትመት እሮሮና ብሶት የራሳቸዉን ህትመት ቤት በማቋቋም ነበር እልሀቸዉን የተወጡት፡፡ ያዉ እነሱም ማነህ ባለተራ በሚል በተራቸዉ በዝባዥ እንደማይሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

መፅሀፍት ያለፈቃድ እና አሳታሚዉ እዉቅና በገፍ ታትመዉ ለገበያ ይቀርባሉ እኛም እንሸምታለን በመጨረሻም የለፋበት ባለቤቱ አጨብጭቦ ሲቀመጥ ህገወጥ ቀማኛዎች ኪሳቸዉን አጭቀዉ ቤታቸዉ ይገባሉ፡፡ አመናችሁም አላመናችሁም 4ኪሎ መፅሀፍት መደብር ላይ 5 መፅሀፍትን እያንዳንዳቸዉን በ30 ብር ሁሉንም በአጠቃይ በ150 ብር ገዝቼ አዉቃለዉ፡፡ መፅሀፉ ላይ በተቀመጠዉ ዋጋ ቢሆን ኖሮ በትንሹ 500 ብር አወጣ ነበር ፤ እኔ ግን ሁሌም እንደምናደርገዉ ቅናሽ ሳገኝ ጠራርጌ ወስጃለዉ፡፡ ለዚያ ነዉ ሙልጭ ያልኩኝ ሌባ ነኝ የምለዉ ፤ 30 ብር እንኳን መፅሀፍት ሊገዛ ቀርቶ ለህትመት ከሚወጣዉ ወረቀት እምብዛም እንደማይበልጥ እያወቅኩኝ ለማንበብ ከነበረኝ ጉጉት እንፃር ሸምቼያለዉ፡፡ በዚሁ ከቀጠልን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፅሁፎችን በፌስቡክ መንደር ብቻ ማግኘታችን ፤ ጠበብት ፀሀፊዎችን ቀብረን የፌስቡክ ሳይማሩ ከታቢዎችን ማፍራታችን የማይቀር ሀቅ ነዉ፡፡

“ ለጥበብ ዋጋ እንስጥ ! ”

# 4.5 የፈሪ ፈሪ



እኛ ኢትዮጵያዉያን ስንባል ከአያቶቻችን እና አባቶቻችን ሲወርድ የመጣ የአልሸነፍ ባይነት ፣ ተጋዳይነት እና ልበ ሙሉነት ስነ-ልቦና ያለን ህዝቦች ነን፡፡ ታሪካችን ሁሉ ከደም እና ጀግንነት ጋር የተንሰላሰለ ነዉ፡፡ ለዚያም ይመስላል ስነ-ቃሎቻችን ፣ ግጥሞቻችን እና ቅኔዎቻችን ሁሉ ጀግናን የሚያኮፍሱ ፈሪን የሚያንኳስሱ የሆኑት፡፡ ምናልባት ወደፊት በአዲስ ፋሽን ተብሎ ካልመጣ በስተቀር አንዳለመታደል ሆኖ እስካሁን ድረስ ፈሪን ለማወደስ የተፃፈ ግጥም ወይም ፅሁፍ ጆሮዬም ለመስማት ፣ አይኔም ለማንበብ አልቻለም፡፡

እስኪ ቀደም ብሎ ማህበረሰቡ ይጠቀምባቸዉ የነበሩ ፈሪን አንኳሳሽ የተወሰኑ የግጥም ስንኞችን እንመልከት ፡-

**<u>ግጥም 1</u>**

ዉረድ እንዉረድ ፤ ተባባሉ እና

አስደበደቡት ፤ አፋፍ ቆሙና ፡፡

**<u>ግጥም 2</u>**

ፈሪ ፈራና ፤ ዋሻ ቢተኛ

ጆሮዉን በላዉ ፤ የአይጥ ቀበኛ ፡፡

## ግጥም 3

ቅልጥሙ ረጃጅም ፤ ለሱሪ ማጌጫ

ጣቶቹ ረጃጅም ፤ ለአልጫ መዋጫ

ወንዶቹ ሲመጡ ፤ ወደ ጓዳ ሩጫ ፡፡

## ግጥም 4

በያዘዉ ሽመል ፤ ቢሸነቁጠዉ

አሬራዉ ወጣ ፤ የቀላወጠዉ ፡፡

በሀገራችን ህዝብ ተወዳጅ ከሆኑት ኩራቶቻችን መካከል ቴዎድሮስ ካሳሁን ካዜማቸዉ ዜማዎች የአንዱ ግጥም ትዝ አለኝ ( ግጥሙ የራሱ ይሁን የህዝብ ግጥም እርግጠኛ አይደለሁም) -

ይወለድ እና ፤ እንከፍ እንከፉ

ጋን ይሸከማል ፤ ከነ ድፍድፉ

ይወለድ እና ፤ ጫማዉ ሰፋፊ

ሆኖ ይቀራል ፤ ጎመን ቀራፊ

እንግዲህ እነዚህ ዘና የሚያደርጉ ግጥሞች የሚያስተላልፉት ተመሳሳይ መልዕክት ፍርሀት እና ስንፍናን ማንኳሰስን ነዉ፡፡ እንግዲህ ቀደም ባለዉ ጊዜ የፍርሀት መገለጫ ከጦርነት ፣ ከድብድብ እና ከመሳሰሉት ጋር የተያያዘ መሆኑን ከግጥሞቹ እንረዳለን፡፡ የአገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ በጦርነት የተሞላ እና በጀብድ የተጠናቀረ ነዉ፡፡ በእነዚያ በፍልሚያ ወቅቶች እነዚህ እና መሰሎች ፈሪን የሚያንኳስሱ ግጥሞች የአገራችንን ህልዉና ለማስጠበቅ የአንበሳዉን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ያላበዉ ፈሪ ቢኖር እንኳን የሚደርስበትን ዘለፋ ለመቋቋም ስለሚከብደዉ ያለ ዉድ በግዱታዉ ለጦር አዉድማ ይሰለፋል፡፡

እንግዲህ ፍርሀት ትርጓሜዉ እንደ አንደምታዉ እና ዘመኑ እንደደረሰበት ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ በዚህ ባለንበት ጊዜ ፍርሀትን ለመግለፅ የተለያዩ መንገዶች እና ሁኔታ ቢኖሩም የሚከተሉት አይነት ፈሪዎች ይበዛሉ፡፡

ትክክለኛዉ የአስፋልት ቀና መንገድ ተነጥፎለት እያለ በአጭሩ የምታደርሰዉን አቋራጭ የኮረኮንች ጎዳና ተጠቅሞ ህልሙን ለማሳካት የሚሮጥ ፣ ከእዉነት ጋር አንገት ለአንገት ተያይዞ ድል ማድረግ ሲችል በሀሰት ጭንብል ለመደበቅ እና ተሹሎክሉኮ ለማግኘት የሚሞክር ፈሪ፡፡

ለቆመበት እና ላመነበት አላማዉ ሽንጡን ገትሮ መከራከር የማይችል ፤ አቋም የሌላዉ ወላዋይ ፡፡ ከበላይ አካል የወረደዉን መልዕክት እንደ 10ቱ ትዕዛዛት አሜን ብሎ ተቀብሎ ሌሎችንም ካልጋትኩ የሚል የህዝብ ተወካይ ካድሬ፡፡

እኔነኝ ያለ የንግድ ሰዉ ሆኖ የራሱን የተሻለ ስትራቴጂ ነድፎ ፣ የተቀላጠፈ አገልግሎት ሰጥቶ ተፎካካሪዎቹን እጃቸዉን ማስከንዳት ሲችል ከመንግስት ጋር ድብብቆሽ እየተጫወተ ፣ ጉቦ አየሸጎጠ እና ህዝብ እየበዘበዘ ለመክበር የሚዳዳ ቁማርተኛ ነጋዴ፡፡

ትምህርት ላይ ሆኖ የበለጠዉን ተማሪ የበለጠ ሰርቶ ለማሸነፍ ከመጣር ይልቅ በተለያዩ መንገዶች ጓደኛዉን አሰናክሎ መቅደም የሚፈልግ ተምሮ ያልተማረ ከንቱ ፡፡

አዉቃለሁ ባይ ፤ ህሊናዉን ሸጦ ለሆዱ የሚያድር ፣ በዲግሪ ላይ ዲግሪ ደርቦ ዶክተር ነኝ ፕሮፌሰር ነኝ ባይ ፣ ያልተፈጠረ ታሪክ ቀምሮ ፅፎ ቀለም ያስተማረዉን ማህበረሰብ ደም የሚያቃባ ተንከሲስ ፈሪ፡፡ ፊትለፊት ተጋፍጦ ማሸነፍ ያልቻለዉን በባሌም በቦሌም ብሎ የአዉራ ዶሮ ማዕረጉን መሸፈኛ አድሮጎ ወንድም ከወንድሙ የሚያባላ እርባና ቢስ ፡፡

በዉብ እና ለስሳሳ የሙዚቃ አልበም ሰርቶ አድናቂዉ ማስደመም ሲችል እከሌ አልበም አወጣ ሲባል የአልበሙን ምርቃት የሚያራዝም በስራዉ የማይተማመን ሙዚቀኛ ፡፡

በባህሉ በማንነቱ የሚያፍር ፤ ነጮች ያመጡትን ነገር ሁሉ አሜን ብሎ እንደወረደ የሚቀበል ተላላ፡፡ ሱሪ ዝቅ ሲያደርጉ ዝቅ የሚያደርግ ፣ ሲነቀሱ የሚነቅስ ፣ ባላቶሊ ሲቆረጡ የሚቆረጥ ፣ የጫት ቤት ፊታዉራሪ ፣ የዉስኪ ቤት አጋፋሪ ፣ የቤቲንግ ቤት ቆማሪ፡፡

ፈሪ ያላፈራዉን ሀብት እና ያለፋበትን አግበስብሶ ኮሽ ባለ ቁጥር ቀልቡ የሚርቀዉ ቀልበ ቢስ ፤ ያመነበት ዉሳኔ የሌለዉ እና ላላመነበት ዉሳኔ ራሱን በጥቅም አሳልፎ የሚሸጥ ፤ በአቋሙ የማይፀና ዝዋዥዌ ተጫዋች፡፡

ወይ የማይማር ፣ ወይ የማይሰራ ፣ ወይ የማያሰራ በየሰፈሩ ሲንጎዳጎድ የሚዉል ፣ ማጅራቱን ገትሮ ሲሰራ የዋለ ጀግና ልባምን ማታ ጠብቆ ማጅራቱን የሚመታ ዉሽልሽል፡

ሀሳቡን መግለፅ እየፈለገ ሀሳቡን ለመግለፅ እና ያሰበዉን ለማሳካት ጊዜ እስኪለወጥ የሚጠብቅ ፀሀፊ ፤ ከለዉጥ በኋላ በየመድረኩ ይሄንን ፅፌ ነበር ብሎ የደበቀዉን መጣጥፍ ከሸጎጠበት እያወጣ ለማቅረብ የሚሯሯጥ ገጣሚ ፡፡

በዉድ ሀገሩ እና በእናቱ የሚደራደር ተደራዳሪ ፣ ዘረኛ ሰላም አስከባሪ ፣ ህግ ማስከበር ያቃተዉ ቀማኛን የሚሸሽ ንፁህንን የሚገርፍ የህዝብ ጠበቃ ነኝ ባይ ፖሊስ፡፡

የጨበጠዉን የፍትህ መዶሻ ገንዘብ ወይንም ስልጣን ላለዉ ሰዉ አሳልፎ እየሰጠ እያስደለቀ ፍትህን የሚዛባ ፤ ንፁህንን መቀመቅ የሚያወርድ ልፍስፍስ የፍርድ ቤት ዳኛ፡፡

ፈሪ በራሱ አቅም የማይተማመን በሌሎች ሀብት ተጠልሎ መኖር የሚፈልግ መናኛ ነዉ፡፡ የፈሪ ፈሪ ስልጣኑን ተገን አድርጎ ተቃናቃኞቹን ለማምከን ቀን ከሌት የሚያሻጥር ትንቡሽቡሽ ነዉ፡፡

ሁሉም ከላይ የተመለከትናቸዉ ባለድርሻ አካላት ሀላፊነታቸዉን የማይወጡ አና የቆሙበት አላማ ያልተገለጠላቸዉ ፈሪዎች ናቸዉ፡፡

ፈሪ ማለት በአሁኑ ጊዜ አላማ የሌለዉ ፤ አላማ ቢኖረዉም ለቆመበት ዓላማ የማይቆም ፤ ህሊናዉን ለጥቅም አሳልፎ የሚሸጥ በአጭሩ -

የመምህር - አላዋቂ

የተማሪ - ኮራጅ

የዶክተር - ቸልተኛ

የጋዜጠኛ - ወገንተኛ

የፖለቲከኛ - ብሄርተኛ

የባለስልጣን - ጉልበተኛ

የዳኛ - ጉቦኛ

የጥበብ ሰዉ - ጉረኛ

የገበሬ - ሰነፍ

የዘበኛ - እንቅልፋም

የሹፌር - ሱሰኛ

የአናፂ - ምስማር ሰራቂ

የወታደር - ወኔ ቢስ

የፓርላማ - እንቅልፋም

የቤት አከራይ - ጨማሪ

የነጋዴ - ኪሎ አጭበርባሪ

የእንጀራ ሻጭ - ጀሶ ቀልቃይ ነዉ::

አለማችን ኡደቷን ትቅጥላለች ፤ ከማህፀኗ ብዙ ጀግናዎችን እንዳፈራች ሁሉ የትየለሌ ፈሪዎችንም ማፍላቷን ትቀጥላለች:: ላገሩ አጥንቱን ከአፈር ለመቀላቀል የወሰነ ኩሩ እንደሚፈጠር ሁሉ ድቅንድቅ የፈሪ ፈሪ ባንዳም መፈልፈሉ አይቀሬ ነዉ:: ድፍረት ወይንም ፍርሀት አብሮን የሚፈጠር ደዌ ሳይሆን በአስተዳደጋችን እና በአኗኗራችን የምናዳብረዉ የእኛነታችን ነፀብራቅ ነዉ::

“ አንቺማ ፈሪም አያምርብሽ ፤ ጅብ እንዳያስበላሽ ይቅርብሽ … ” አለ ኤልያስ ተባባል

# 5. ትኩረት

“ ዳሳ ስሙ እንሚያመለክተዉ ስያሜዉን ያገኘዉ በአካባቢዉ በሰፊዉ ከሚበቅለዉ የሳር ዝርያ ዳሳ ነዉ፡፡ ዳሳ በአይነቱ ረዘም ብሎ ከርደድ ያለ እና ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለዉ የሳር አይነት ነዉ፡፡

.

.

.

ከአጥቢ እንስሳት አንፃር ዳሳ በቁጥር ከ 50 እስከ 70 የሚደርሱ በሀገራችን ብቻ የሚገኙ እጅግ ዉብ የሆኑ ቀይ ቀበሮዎችን አቅፎ ይዟል፡፡ ሌላኛዉ የዳሳ እና የኢትዮጵያ መገለጫ ቀይ ደረቱን ግልብጥ እያደረገ የሚንጎማለለዉ ኩራተኛዉ ጭላዳ ዝንጀሮ ነዉ ፡፡ በዳሳ ከ1000 - 1400 የሚደርሱ የጭላዳ ዝንጀሮዎች ሲገኙ የሚኖሩት በተናጠል ሳይሆን በጋራ ነዉ፡፡ ”





“ በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! ”

# 5.1 የቀለም እናት - የቀለም አባት




አሁን ላይ ያለ ማንኛዉም ነገር እዚህ ለመድረስ መነሻ ወይም መጀመሪያ ቀደምት ነገር ያስፈልገዋል፡፡ የሰዉ ልጅ ወደዚህ ምድር ሲመጣ መነሻ ይዞ ነዉ የመጣዉ በእርግጥ መነሻዉ ላይ የሀሳብ አለመስማማት ቢኖርም ማለትም ሀይማኖታዊ ነን የሚሉት የሰዉ ልጅ በተፈጥሮ በፈጣሪ የተሰጠ ልዩ ፀጋ ነዉ ሲሉ ፤ ፊደል ቀማመስን የሚሉት ደግሞ የሰዉ ልጅ በዝግመታዊ ለዉጥ በሂደት የመጣ ነዉ ብለዉ ይሞግታሉ፡፡ ዞሮ ዞሮ ያም ሆነ ይህ ሁላችንም ከአባት እና ከእናት የመጣን መሆኑ ላይ ማንም የተቃዉሞ ሀሳብ የለዉም ፡፡ ከዚህ ተፈጥሮአዊ ግዴታ ዉጪ ማንኛዉም ፊደል ቆጠርኩ ወይም ተማርኩኝ የሚል ሰዉ ተጨማሪ አለማዊ የቀለም እናት እና አባት ይኖረዋል፡፡ ዛሬ ስለ እነዚህ የቀለም እናት እና አባቶቻችን የተወሰነ ነገር ለማለት አሰብኩኝ፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት ዘመናዊ ትምህርት ባልነበረበት ጊዜያት ቤተሰቦች ልጆቻቸዉን የእዉቀት ቸነፈር እንዳይገርፍባቸዉ ወደ የኔታ ይልኩ ነበር ከዚህም በተጨማሪ በየቤተ-እምነቶቻቸዉ ወስደዉ እዉቀትን እንዲቋደሱ ብሎም አገልገሎት እንዲሰጡ ያደርጉ ነበር፡፡ ከዚያም ከፍ ብለዉ በየአስኳላዉ ልጆቻቸዉን ለዘመናዊ ትምህርት ይልኩ ነበር፡ በነገራችን ላይ ይህ ቀደምት በሀገራችን ይሰጥ የነበረ ትምህርት ላይ ላዩን ሀይማኖታዊ ይምሰል እንጂ ዉስጡ ገባ ብለን ስናየዉ

አስደናቂ ነበር ፡፡ አሁን አለም ደረስኩበት የምትለዉን የፊዚክስ ህጎች ፣ የስነ-ክዋክብት መረጃዎች ፣ የህክምና ጥበቦች ፣ የጦርነት የዉጊያ ስልቶች ቀደምት አያቶቻችን በብራና ለይ ከትበዉት ስናገኝ በዚያን ጊዜ ያለምንም ሳታላይት ፣ ያለምንም ቴሌስኮፕ ፣ ያለምንም ማይክሮስኮፕ አያቶቻችን ርቀዉ መጓዝ እንደቻሉ መረዳት እንችላለን፡፡ ይሄንን ስናስብ ግን መነሻቸዉ እነዛ የፊደል አባቶቻቸዉ የኔታዎች መሆናቸዉን መዘንጋት የለብንም፡፡

እስኪ ከተለያዩ መለኪያዎች አንፃር የቀለም አባቶቻችን እና እናቶቻችንን ድሮ እና ዘንደሮን ለመቃኘት እንሞክር -

## ክብር

በጥንቱ የትምህርት ጊዜያት ትምህርቱን ይሰጡ የነበሩ የኔታዎች በተማሪዎቻቸዉ ዘንድ ከፈጣሪ ቀጥሎ ያሉ የምድር ገፀበረከቶች ተደርገዉ ይቆጠሩ ነበር ፤ የኔታ የኔ ጌታ የሚለዉ የተማሪዎች ምስጋና ምን ያህል በተማሪዎቻቸዉ እንደ ፈጣሪ ይታዩ እንደነበር ማሳያ ይሆነናል፡፡ ግዜዉ እየጨመረ ሲመጣ በተቃራኒዉ ለመምህራን ያለዉ እይታ እያሽቆለቆለ ይገኛል፡፡

በአለማዊ ትምህርት እንኳን በ70ዎቹ እና 80ዎቹ ተማሪዎች ቤታቸዉ ዉስጥ ለየት ያለ ነገር እንደ ማር ፣ እንቁላል ፣ ወይም ቅቤ ካለ ፍቅራቸዉን ለመግለፅ ይዘዉ ወደ መምህራቸዉ ቤት ነበር የሚፈተለኩት፡፡ ማህበረሰቡ ለመምህር የተለየ ቦታ ነበረዉ ፤ የሰርጉ ዘፈን ራሱ የእኛ ሙሽራ ሹራብ ሰሪ ወሰዳት አስተማሪ ነበር አሁን ወሰዳት ዲያስፖራ ሆኗል ፡፡

በቅርብ በእኛ ጊዜ እንኳን ስናየዉ ከ 1-4 ስንማር መምህር ክፍል ሲገባ ከመቀመጫችን ብድግ ብለን እንነሳለን በመቀጠልም ተቀመጡ ሳነባል አንኳንስ ቁጭ ልንል ቀርቶ ከቆምንበት ንቅንቅ ማለት አንችልም ነበር፡፡ ከ5-8 ስንማር ደግሞ ከመቀመጫ መነሳቱ ቀረና እንኳን ደህና መጡ መምህር ብቻ ሆነ ይባስ ብሎ ሁለተኛ ደረጃ ስንገባ ሁሉም ነገር ቀረና መምህርን ከክፍል ጓደኛ ነጥሎ ማየት ተሳነን፡፡ እንግዲህ አሁን ላይ ለመምህራኖቻችን ያለንን ክብር ለእናንተ ልተወዉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሚከበር መምህር ቢኖር ከታች መዋዕለ-ህፃናት ላይ ያሉት እነ ሚስ እና ሚስተር ብሎም በኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪ የሚሽቆጠቆጥላቸዉ ሌክቸረሮች ብቻና ብቻ ናቸዉ፡፡

## ጥቅም

በፊት አንድ አከራይ ድምፁን ከፍ አድርጎ እኔ ቤት ያለዉ ልጅ መምህር ነዉ ብሎ ይኩራራ ነበር አሉ ፤ አሁን ላይ ... ምን ይገርምሀል !... አንድ መምህር አስገብቼ የቤት ኪራዩን እንኳን በአግባቡ አይከፍለኝም ሆኗል ነገሩ፡፡

አባቴ መምህር ነዉ እና ስለድሮ ትዝታዎቹ እያወራኝ መጀመሪያ መምህርነት ተቀጥሮ በወር 180 ብር ነበር የሚከፈለዉ እና በወቅቱ ጥሩ ተከፋይ እንደነበር እና ቦታ እስከመግዛት የደረሰዉ በዚህ ደሞዝ እንደነበር ያወጋኛል ፡፡ አሁን ምንም እንኳን ደሞዙ እጥፍ በጥፍ ተባዝቶ በሺዎች ቢቆጠርም ከገንዘቡ የመግዛት አንፃር ብሎም ከሌሎች ሙያ አንፃር ተገቢዉን ክፍያ አንደማይከፈለዉ አያለሁ፡፡

አለማችን ላይ እንደ እና ቻይና ያሉ ትላልቅ አገራት ከፍተኛ ክፍያ የሚከፍሉት ለሁሉ ነገር መፈልፈያ ኢንኩቤተር ለሆኑት መምህራን ነዉ ፡፡ መምህራንን አስደሰትን ማለት የተሻሉ ተተኪዎች ለማፍራት የሚያስቸለንን አንድ እርምጃ ተራመድን ማለት ነዉ፡፡ መምህራን ከኢኮኖሚዉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ትኩረታቸዉን ዒላማቸዉን ትምህርት እና ትምህርት ላይ አንዲያነጣጥሩ ማድረግ ይገባል፡፡ ሁሌ ወቀሳ ብቻ ሳይሆን የተሰሩትንም ጥሩ ጎኖች ማሞገስ ከእኛ ከዜጎች የሚጠበቅ ነገር ነዉ፡፡ አሁን ላይ በተለያዩ ከተሞች መዲናችንን አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎችም ከተሞች ለመምህራኖች የተሻሉ ነገሮች

መደረግ እየተጀመረ ነዉ፡፡ ለምሳሌ በትራንስፖርት እና በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ይሄ ድርጊት መንግስትን የሚያስሞግስ እና ይበል የሚስብል ሲሆን ወደ ሌሎችም አካባቢዎች በሂደት ሊስፋፋ የሚገባ ነዉ፡፡

ባንድ ወቅት ጀርመን ሀገር የከፍያ ጥቅም ጥያቄ ያነሱ ሰራተኞች ወደ መራሂተ አንጌላ ሜርክል ይቀርቡና በዚህ ሀገር ከፍተኛ ክፍያ ለመምህራን እንደሆነ እና የእነሱም ክፍያ እንደ መምህራኖች ከፍ እንዲል ይማፀናሉ፡፡ የመራሂቷ ምላሽ አስገራሚ ነበር፡፡ እንድ ጥያቄ ጠየቁ እናንተን አሰልጥኖ ለክፍያ ያደረሳችሁ ማነዉ ? የሚል ነበር ሰራተኞቹም ሳያመነቱ መምህራኖቻችን አሉ፡፡ በመቀጠል መራሂቷም እኮ እንዴት ሆኖ ነዉ እናንተ ለዚህ ስራ ካበቋችሁ የቀለም አባቶቻችሁ እና እናቶቻችሁ በላይ ሊከፈላችሁ የሚችለዉ፡፡ ከተከፈላቸዉም የበለጠ የሚገባቸዉ እናንተን እዚህ ላደረሱት መምህራኖቻችሁ ነዉ የሚል ነበር፡፡

በእኛ ሀገር ነገሮች ሁሉ የተገላቢጦሽ ነዉ፡፡ ዛሬ ላይ ምንም እንኳን የስራ ዓለምን ከተቀላቀልኩ በጣም ጥቂት ወራት ብቻ ቢሆኑኝም የሚከፈለኝ ክፍያ ግን ለ30 ዓመታት አገልግሎት የሰጠዉ አባቴን ጨምሮ እኔን እዚህ ካደረሱኝ የቀለም አባቶቼ እና እናቶቼ የተሻለ ነዉ፡፡ በአዲሱ የደሞዝ ስኬል አንድ የንግድ ባንክ ጀማሪ ተቀጣሪ 16 ዓመት ሙሉ ያስተማሩት የቀለም አባቶቹን እና እናቶቹን በአንድ ጀንበር በደሞዝ አጥፎአቸዉ ቁጭ ይላል፡፡ ይሄ ልፋትን ዋጋ የሚሳጣ እና ለመምህራንም ቅስም ሰባሪ ነዉ፡፡ መምህሩ እያለ ደቀ መዝሙሩ ነግሷል፡፡ ለልፋታቸዉ ተገቢዉን መክፈል ካልቻልን ነገ ጥሩ ፍሬ የሚያፈሩ መምህሮችን ማጣታችን አይቀሬ ነዉ፡፡

## ለሙያዉ ያለዉ ፍቅር

በአሁኑ ሰዓት የአንድን ብላቴና ተማሪ ስለ ወደፊት ራዕዩ ብትጠይቀዉ ምናልባት ዶክተር ወይም ኢንጂነር ይልሀል ፤ አለበለዚያም ፓይለት ወይንም ሙዚቀኛ ካለህ በኋላ ነዉ አማራጭ ሲያጣ መምህር የሚልህ፡፡ ይህ ትልቅ አስደንጋጭ መልዕክት ነዉ ፤ በቶሎ ልንነቃ ይገባል ፤ ለሙያዉ ያለዉም አክብሮት በምን ያህል ደረጃ እየወረደ እንደመጣ ማወቅ እንችላለን፡፡

አብዛኞቹ መምህርን የመምህርነት ማተብን ከአንገታቸዉ ላለመፍታት ጠፍሮ የያዛቸዉ ለሙያዉ ያላቸዉ ፍቅር እና የሚያፈሯቸዉ ስኬታማ የሙያ ልጆቻቸዉ ናቸዉ ፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ከቀጠለ ግን ኑሮአቸዉ እና ተያያዥ ጉዳዮች ይሄንን የሙያ ፍቅር ጥላሸት እንዳይለዉሱት ያስፈራል፡፡

ከጓደኞቼ መካከል አንደ አባቱ መምህር የሆነ ልጅ ስለ አባቱ እያወጋኝ ነበር፡፡ አባቱ የመልቀቂያ ፈተና ወስዶ አሁን ዩኒቨርሲቲ በየመንደሩ ሳይሆን በጊዜዉ እንደ ቤተ መንግስት እንደሚቆጠረዉ አንድ ለእናቱ ወደሆነዉ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህክምና ይቀላቀላል፡፡ ወቅቱም ወላጆች ልጆቻቸዉ መምህር እንዲባሉላቸዉ ትልቅ ፍላጎት የነበራቸዉ ነበር እና ፤የእሱም የሌት ተቀን ህልም መምህርነት ነበረ በዚህም ልቡ አላስችል ብሎ ሲሸፍትበት ግቢ ዉስጥ አንዷት መምህርነት የደረሳትን ተማሪ ይቀይራታል፡፡ ነገር ግን አሁን ጊዜዉ የተገላቢጦሽ ሆነና እርሱ የሀይስኩል መምህር ሆኖ ሲቀር እሷ ጫፍ የነካች ዶክተር ሆናለች፡፡

እንግዲህ መምህርነት ሰዎች ከላይ ያየነዉን አይነት መስዋዕትነት የሚከፍሉለት እንቁ ሙያ ነዉ፡፡ አሁን ላይ እስኪ ማነዉ ኮምፒዉቴሽናል ሳይንስ ወይንም መምህርነት ደረሰኝ ብሎ እልል እያለ ሲያሽካካ የምታገኘዉ ፤ የትምህርት ማስረጃዉን እና ማመልከቻዉን ይዞ የቀይሩኝ አቤቱታዉን ለማስተጋባት ቢሮ ለቢሮ ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ለትምህርት ሚኒስቴር ፣ ፈተናዎች ኤጀንሲ ለፈተናዎች ኤጀንሲ ሲንኳትን ታገኘዋለህ እንጂ …

## ጥራት

አሁን ላይ ሳስበዉ የሚከብደኝ ነገር እዉነት አሁን ላይ ወደ መምህርነት እየገቡ ያሉ አብዛኞቹ መምህርን ለዚች ሀገር ቀጣይ ተስፋ የሚሆኑ ዜጎችን ለማፍራት ብቁ ናቸዉን ? የሚለዉ ጥያቄ ነዉ ፡፡ ቀደም ባለዉ ጊዜ ለመምህርነት የሚገባ ሰዉ ብቁ ከሆኑት ተማሪዎች ተመርጦ ለዚያዉም በሰርተፊኬት ነበር የሚጀምረዉ ፤ በመቀጠልም ዲፕሎማ ፤ ዲግሪ እና ማስተርስ እያለ ራሱን ብቁ ያደርግ ነበር፡፡ አሁን አሰረኛ ክፍል ከጨረሰ በኋላ ዉጤት ያልመጣለት ሰዉ አማራጭ ሲያጣ መምህርነትን መሸሸጊያ አድርጎታል፡፡ ካገኘ በመንግስት አለበለዚያም በክፍያ ዲፕሎማዉ ኸረ እንዲያዉም አልበቃ ብሎት ዲግሪዉን ጭኖ ከቸች ይላል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ምደባም ላይ እንደዛዉ ጥሩ ተማሪዎች ህክምናን ፣ ምህንድስናን ፣ ኮምፒዉተር ሳይንስን ከተቀላቀሉ በኋላ ነዉ የቀሩትን ለቅሞ ኮምፒዉቴሽናል ሳይንስ ብሎ ለመምህርትን ለማብቃት ተፍ ተፍ የሚባለዉ፡፡ ሲጀመር መምህሩ ብቁ ካለሆነ ብቁ የሆነ ዜጋን ለማፍራት ሩጫዉ እልህ አስጨራሽ ነዉ የሚሆንብን፡፡ በዚህ ከቀጠልን ነገሩ ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ ይሆን እና ጨዋታዉ የተገላቢጦሽ መሆኑ አይቀሬ ነዉ፡፡

አሁን ባለንበት ጊዜ በሀገሪቷ የመምህራን እና የትምህርት ተደራሽነት ከሁሉም ጊዜ በላይ አድጎ እና ተመንድጎ የሚገኝበት ወቅት ነዉ፡፡ ብዙ መምህራን ፣ ብዙ ተማሪዎች ፣ ብዙ የትምህርት ተቋማት ፣ ብዙ ትምህርት እድል ብቻ ብዙ ሁኔታዎች መመቻቸታቸዉ ግልፅ እና የሚያስመሰግን ነዉ፡፡ በዚያዉ ልክበእዉቀት የተሞሉ መምህራን ፣ በስነምግባር እና እዉቀት የታነፁ ተማሪዎች ፣ በህንፃ ሳይሆን በመፅሀፍት የተሞሉ ትምህርትቤቶች ቁጥርም አብሮ ማደግ እና መመንደግ ይኖርበታል፡፡

## እድገት

እኔ በሂወቴ ላይ ከማልዘነጋቸዉ ብዙ እንቁ መምህራን መካከል መሰናዶ ላይ የሂሳብ መምህራችን የነበረ አንድ ወንድማገኝ ሙሉጌታ የሚባል መምህር ነበረን፡፡ የመሰናዶ ትምህርት አልቆ ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ አንድ ህንዳዊት መምህር ነበረች (ስም መጥቀሱ ተገቢ ስላለሆነ ነዉ) መሰናዶ ላይ ያለዉን ተመሳሳይ ሂሳብ ትምህርት ደግማ አስተማረችን ፡፡ ምንም አንኳን በመካከላቸዉ የትምህርት ልዩነት ቢኖርም እና እሱ ዲግሪ ኖሮት እሷ ፒኤችዲ ብትኅናፀፍም እዉነት ለመናገር ለማወዳደር የሚከብድ ልዩነት ነበራቸዉ ፤ እርሱን ጨምሮ ብዙ ኢትዮጵያዊያን መምህሮች ከእሷ የተሻለ የማስተማር ክህሎት አላቸዉ ፤ ይሄን አይነት ልዩነት ሀገራችን ብዙ ወጪ አፍስሳ የምታመጣቸዉ የዉጪ ዜጎች ላይ መመልከቱ እየተለመደ የመጣ ነዉ፤ በተለይ ከህንድ መጥተዉ ዩኒቨርስቲዎቻችንን ያጥለቀለቁት ሰዎችን ማለቴ ነዉ፡፡

አስገራሚዉ ነገር የእርሷ ደሞዝ አይደለም ከወንድማገኝ ጋር ሊነፃፀር ቀርቶ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች ደሞዝ አንድ ጋር ቢደመር ሊደረስበት የማይችል ነዉ፡፡ ስለ እዉነት ለመናገር ይሄ ለሀገሪቷ ትልቅ ብክነት እና ዉርደት ነዉ፡፡ ለዜጎቿም ሀገራቸዉን እንደ ሌላ ሁለተኛ ሀገር እንዲቆጥሯት የሚያስገድዳቸዉ ትልቅ ስህተት ነዉ ፡፡ መምህራኖቿ ተገቢዉ የትምህርት እድገት እና ስልጠና እንዲያገኙ እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አሁን ካለባቸዉ የህንዳዊያን እና ሌሎች ሀገሮች ወረራ ነፃ አንዲወጡ ማድረግ ይገባል፡፡ ሀገራችንም ክፍያዋ እዚሁ የሀገሯን ዜጋ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል አለባት፡፡

# ትኩረት

አዲስ አበባ ዉስጥ ብዙ ግዜ ከምወዳቸዉ ቦታዎች አንዱ ወደሆነዉ ወመዘክር ስሄድ ሁሌ የሚያስገርመኝ አንድ ነገር ነበር፡፡ ከወመዘክር ወጥተን በስተቀኝ ስንጓዝ አሻግረን የተሰደሩትን ዘመናዊ ሰማይ ጠቀስ የባንኮች ህንፃዎችን በቅርብ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክን እጅግ ዉብ ህንፃ እንመለከታለን፡፡ ከሱ ፊት ለፊት አስፋልቱን አሻግረን ስንመለከት ደግሞ አንድ የጥንት ፎቅ ቤት የምትመስል ቤት ትታየናለች (*መጀመሪያ ላይ ያለዉ ፎቶ ነዉ)፡፡ ይቺ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ያያት ሰዉ ዙሪያዋን ከከበቧት ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች አንፃር ተዘንግታ ሳትፈርስ የቀረች የቀድሞ ይዞታ ነዉ የምትመስለዉ፡፡ ነገር ግን ጠጋ ብሎ ላያት በሯ ፊት ለፊት ሰንደቅ የሰቀለች የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፅህፈት ቤት ነች፡፡ ከተማችን ስንት ህንፃዎች እንደ ቁጥቋጦ ከየት መጡ ሳይባል እና ባለቤታቸዉ ሳይታወቅ እያፈራች ባለበት በዚህ ወቅት ለዚህ ፅህፈት ቤት ህንፃ መጥፋቱ የትኩረት ማነስ መኖሩን ያመላክታል፡፡

አለማችን አሁን ለደረሰችበት የላቀ ጊዜ የአንበሳዉን ድርሻ ልዉሰድ ያለ አካል ካለ ያለ ምንም ድርድር እና እሽቅድምድም ኒሻኑ የመምህራን ሊሆን እንደሚገባ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ፡፡ ከተማችን ላይ ምን አይን የሚያቁለጨልጩ ሰማይን የታከኩ የስነ-ህንፃ ዉጤቶች ብንመለከት ፣ ኮምፒዉተር መጥቶ ስራችንን ቢያቃልልን ፣ ትራንስፖርትን ተጠቅመን በደቂቃዎች ዉስጥ መገኛችን ብንቀያይር ፣ ስልኮችን ተጠቅመን አለምን አንድ መንደር ብናደርጋት ፣ ኩላሊታችን እና ዉስጥ እቃችንን እያስነቀልን ብናስተክል ፣ የተቀላጠፈ አገልግሎት ብናገኝ ፣ ልቦና ያለዉ ባለስልጣን ቢኖረን ፣ የሀገር ፍቅር ያለዉ ወታደር ባለቤት ብንሆን ፣ ለሀቅ የሚተጉ ጋዜጠኞች ቢኖሩን ፣ ልብ በሉ የእነዚህ ነገሮች ሁሉ የጀርባ አጥንታቸዉ እና ጠንካራ መሰረታቸዉ እነዛ ያለ ምንም ስስት ዘራቸዉን የዘሩብን የቀለም እናት እና አባቶቻችን ናቸዉ፡፡

እስኪ ሁላችንም አንድ ጊዜ ቆም ብለን እናስበዉ አሁን ላይ ላለንበት ማንነት ያደረሱን እነዛ ሳይወልዱ ያሳደጉንን ፣ በባዶ ቀፎ ጭንቅላታችን ዉስጥ ቀለማቸዉን ቀምመዉ ያንቆረቆሩብንን ፣ ስናጠፉ የቆነጠጡንን ፣ ፈተና ስንሳሳት እርር ድብን ያሉልንን ፣ መጥፎ ስንሰራ የመከሩንን ፣ ስንጣላ ያስታረቁንን ፣ ሲነስረን ደማችንን ያለመጠየፍ የጠረጉልንን ፣ እንባችንን ያበሱልን ፣ ስንታመም የጠየቁንን ፣ ስንቸገር ምሳ ብላ ብለዉ ፍራንክ የሸጎጡልንን ፣ ታሪክ እና ተረታቸዉን አዉርተዉ ያዝናኑንን ፣ ባጭሩ ሙሉ ባንሆንም ባዶ እንዳንሆን ያደረጉንን ሁሌም በዉስጣችን ታተመዉ የሚቀሩትን የአስኳላ እናት እና አባቶቻችንን ዞር ብለን እናስባቸዉ ፣ ክብር እንቸራቸዉ ፣ ቅድሚያ እንሰጣቸዉ ፣ ዉለታቸዉን አንርሳ፡፡

በመጨረሻም አንድ የህንዶችን ምሳሌ ጠቅሼ ልለፍ ፤ ህንዶች ፈጣሪህን እና መምህርህን አብረህ ብታገኛቸዉ ቀድመህ ሰላምታ ልትሰጠዉ የሚገባዉ ለመምህርህ ነዉ ፤ ምክንያቱም እሱ ነዉ እና የፈጣሪህን ታላቅነት ያስተማረህ በማለት ለመምህራኖቻቸዉ ያላቸዉን ክብር ይገልፃሉ፡፡

“ ክብር ለቀለም አባቶቻችን እና እናቶቻችን ይሁን ! ”

# 5.2 መንዝ ጓሳ



ኢቢኤስ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ የሚተላለፈዉን የኢቢኤስ አዲስ ነገር ፕሮግራም ዜና እያየሁ ነበር፡፡ ዜናዉ እንደዚህ ይላል - በአዉስትራሊያ የካንጋሮ ህጋዊ አደን ተፈቀደ ፤ እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ማንኛዉም አዉስትሪያላዊ ከዛሬ ጀምሮ የአደን መሳሪያ ይዞ በመዉጣት ካንጋሮ ማደን ይችላል ፡፡ ይህ የካንጋሮ አደን የተፈቀደበት ምክንያት ያልተለመደ ነበር ፤ በአሁኑ ጊዜ የተፈጥሮ ሀብት እና የእንሰሳት መመናመን በሚያሰጋበት ጊዜ የ20 ሚሊዬን ዜጎች ሀገር የሆነችዉ አዉስትራሊያ ግን የካንጋሮ ቁጥር ከህዝቤ ከእጥፍ በላይ በዝቶ 50 ሚሊዮን ደርሷል እናም ካንጋሮዎችን መቆጣጠር እና አደጋ እንዳይፈጥሩ መከላከል ተስኖኛል ትላለች፡፡

በዜናዉ ቪድዮ ላይ አንድ ካንጋሮ አንድን ዉሻ አንገቱን ጠፍንቆ ይዞ ደም በደም አድርጎት ይታያል በመጨረሻም መኪና ሲያሽከረክር የነበረ ተጓዥ ድርጊቱን አይቶ ከመኪናዉ በመዉረድ ካንጋሮዉን በቡጢ ጉንጬን ይለዋል ፤ ወዲያዉኑ ካንጋሮ ሆዬ የያዘዉን ዉሻ ይለቃል፡፡ እንግዲህ ይህን የመሰለዉ የካንጋሮዎች ዉንብድናቸዉ እና ብዛታቸዉ መንግስትን ህጋዊ አደን እንዲፈቅድ አስገድዶታል ፡፡ እኛ ሀገር የተገላቢጦሽ ነዉ ፤ የእኛ ብርቅዬዎች ጭላዳ ባቡን ፣ ቀይቀበሮ እና ዋልያ አይቤክስ ግን በተቃራኒዉ ዝርያቸዉ እየቀነሰ መምጣቱ ይነገራል፡፡ እስኪ ዛሬ ብርቅዬ አእዋፋት ፤ እፅዋት እና እንሰሳት መከማቻ ስለሆነ

ነገር ግን በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል እንደሚባለዉ ማንም ትኩረት ስላልሰጠዉ ፣ ጆሮ እና አይን ስለነፈግንዉ አንድ ቦታ እንነጋር፡፡

ከመዲናችን አዲስ አበባ በሰሜን በር አቅጣጫ ማለትም የደብረብርሀን መንገድ ይዘን ስንጓዝ ጣርማ በር ስንደርስ የደሴ መቀሌን መስመር በስተግራ ትተን በቀኝ በኩል ባለዉ ፒስታ መንገድ እንታጠፋለን ፤ ይህ ትኩረት አልባ እና ከጃንሆይ ጀምሮ ለረጅም ጊዜ በፒስታነት ያገለገለ መንገድ መቼ እንደሚሰራ ባናዉቅም እስከዚያዉ ግን እልህ አስጨራሽ እና አድካሚ ጉዞ ማድረግ ግዴታ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ 260 ኪሎ ሜትሮችን ከመዲናችን ከራቅን በኋላ ጓሳን እናገኛለን፡፡ ይህ አካባቢ በመንግስትም ሆነ በሌሎች ባለድርሻ አካላት ትኩረት በመነፈጉ ምክንያት የቅርብ ሩቅ ሆኖ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ ሳያዉቀዉ ተደብቆ ቆይቷል፡፡

ጓሳ ስሙ እንሚያመለክተዉ ስያሜዉን ያገኘዉ በአካባቢዉ በሰፊዉ ከሚበቅለዉ የሳር ዝርያ ጓሳ ነዉ፡፡ ጓሳ በአይነቱ ረዘም ብሎ ከርደድ ያለ እና ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለዉ የሳር አይነት ነዉ፡፡ መስህቡ በአጠቃላይ ከ 100 ስኩዬር ኪሎሜትር በላይ ስፋት ያለዉ ሲሆን ከባህር ጠለል በላይ በአማካይ 3500 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ጓሳ የሚተዳደረዉ በሰሜን ሸዋ ዞን መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ሲሆን የወረዳዉም ዋና ከተማ መሀልሜዳ ይባላል፡፡ ጓሳ ከምድር ጠለል በላይ ከፍ ብሎ ስለሚገኝ የመንዝን ጣት የሚያስቀረጥም የጦስኝ በግ ስጋ እና ለጋ ቾቤ እያጣጣሙ ካልተቀመጡ ቅዝቃዜዉ አጥንትን ሰርስሮ መግባቱ አይቀሬ ነዉ፡፡

ከአጥቢ እንሰሳት አንፃር ጓሳ በቁጥር ከ 50 እስከ 70 የሚደርሱ በሀገራችን ብቻ የሚገኙ እጅግ ዉብ የሆኑ ቀይ ቀበሮዎችን አቅፎ ይዟል፡፡ ሌላኛዉ የጓሳ እና የኢትዮጵያ መገለጫ ቀይ ደረቱን ግልብጥ እያደረገ የሚንጎማለለዉ ኩራተኛዉ ጭላዳ ዝንጀሮ ነዉ ፡፡ በጓሳ ከ1000 - 1400 የሚደርሱ የጭላዳ ዝንጀሮዎች ሲገኙ የሚኖሩት በተናጠል ሳይሆን በጋራ ነዉ፡፡ ልክ እንደ 1 ለ 5 አደረጃጀት አንድ የጭላዳ አባወራ እስከ 5 የሚደርሱ ሚስቶች እና እቁባቶች ይኖሩታል ፤ ከዚህም ተጨማሪ ከእነሱ የተገኙት የአብራክ ክፋዮቹ እና ሌሎችም የቤተሰቡ አባላት ሆነዉ ኑሮን በጋራ ይገፋሉ፡፡ ለቀይ ቀበሮዎች እንደ ምግብነት የሚያገለግሉ እንደ ፍልፈል እና የመሳሰሉ የተየለሌ የአይጥ ዝርያዎች እዚሁ ጓሳ ታጭቀዉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪ ሌሎች እንደ ጥንቸል ያሉ እና ሌሎች እንሰሳት ጓሳን ከትመዉ ኑሮን እየኖሩ ነዉ፡፡ ከእኛ የሚጠበቀዉ የእረፍት ቀኖቻችንን አመቻችተን ብቅ ብለን እነሱን መጎብኘት ብቻ ነዉ፡

እፅዋትን በጓሳ ስንመለከታቸዉ ጓሳ ዋናዉ የጓሳ መገለጫ የሳር አይነት ነዉ አብዛኛዉ የጓሳ ስፋት በዚህ የሳር ዝርያ የተሸፈነ ነዉ፡፡ ጅብራ ሌላዉ ዋነኛ የጓሳ መገለጫ እፅዋት ነዉ፡፡ አእዋፋት የጓሳ ሌሎቹ ገፅታዎች ናቸዉ ከ 110 በላይ የአእዋፍት ዝርያዎች በጓሳ ሲገኙ ይህ ማለት ከኢትዮጵያ አንፃር ስንመለከተዉ በሀገሪቷ ከሚገኙ 861 የወፍ ዝርያዎች 12 በመቶዉ የሚገኙት በዚሁ ቸል ባልነዉ እና ባልዘመርንለት ጓሳ ነዉ፡፡14 የሚሆኑ አእዋፍት የትኛዉም የአለም እና የሀገራችን ክፍል ብትዞሩ አታገኟቸዉም ከጓሳ በቀር ሌላዉ አስገራሚ ነገር በኢትዮጵያ ከሚገኙት ብርቅዬ አእዋፍት ዉስጥ 45 በመቶዉ የሚገኙት እዚህ ነዉ፡፡

ጓሳ የሚያስገርሙ እዉነታዎች አሉት የሀገሪቱ የዉሀ ቋት ነዉ ማለት እንችላለን፡፡ ለተለያዩ ወንዞች ምንጭ የሆነ አስደማሚ የዉሀ ቋት ነዉ ፡፡ ለታላቁ ወንዝ አባይን ጨምሮ ለሌሎች እንደ አዋሽ ላሉ ወንዞች ገባር የሆኑ ወንዞች መነሻቸዉ እና ምንጫቸዉ ጓሳ መሆንን ስንቶቻችን እናዉቃለን ፡፡ ጓሳ በተለይ በክረምት እና መስከረም አካባቢ የምንረግጠዉ ቦታ ሁሉ ዉሀ ያዘለ መሆኑ ምን ያህል የዉሀ ቋት መሆኑን በቀላሉ መረዳት እንችላለን፡፡

ጓሳ ልዩ የሆነ እና በሀገራችን ባልተለመደ መልኩ በህብረተሰቡ ከ 400 አመታት በላይ ቁሮ በተባለ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ሲጠበቅ እና እንክብካቤ ሲደረግለት የቆየ ቦታ ነዉ፡፡ ይህም ከሰሀራ በታች ከሚገኙ በዕድሜ ከገፉ ጥብቅ ቦታዎች አንዱ ያደርገዋል፡፡ በቁሮ ህግ መሰረት ማንኛዉም ማህበረሰብ የጓሳን አካባቢም ለእርሻም ሆነ ለግጦሽ መጠቀም አይችልም፡፡ በአጋጣሚ ማህበረሰቡ በጓሳ ክልል እንሰሳ እንኳን ይዞ ለማለፍ ይዞ ቢፈልግ የእንሰሳዉን አፍ በገመድ ወይም በደህና ጨርቅ አስሮ መሆን ይጠበቅበታል ይህ ካልሆነ ግን ከማህበረሰቡ ሸንጎ ከፍ ያለ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡እንደ ሁኔታዉ ቢለያይም በአብዛኛዉ በ 4 ዓመት አንድ ጊዜ የጓሳ ላይ ያለዉ ሳር በጣም ስለሚያድግ ማንኛዉም የሚፈልግ ማህበረሰብ መጥቶ የቻለዉን ያህል ጓሳ ይዞ መመለስ እንዲችል ፈቃድ ይሰጠዋል ፡፡ በዚህ ግዜም ቢሆን የአካባቢዉን ስነ-ምህዳር እና ድንቅዬ እንሰሳትን ለመጠበቅ ሲባል እንስሳት እንዲገቡ አይፈቀድላቸዉም ፡፡

እኛ እዚሁ ሆነን ምንም ሳናዉቀዉ እና ሳንረዳዉ በአካባቢዉ የዉጭ ሀገራት ሳይንቲስቶችን እና የጥናት ባለሙያዎችን ከከተሙ ሰነባብተዋል፡፡ እዉቅ በስነ-ምህዳር እና ተያያዥ ጉዳዮች የሚሰሩ ባለሙያዎች ጥሩ ቦታ ሆኖ አግኝተዉታል፡፡ በተለይ Frankfurt zoological society ከአዉሮፓ ህብረት ጋር በመሆን ሰፊ ጥናት እየሰራ ይገኛል፡፡ የሚያስደንቀዉ የአካባቢዉ ጭላዳ ዝንጀሮዎች እና ሌሎችም እንሰሶች ከእነዚህ አዉሮፓዉያን ተመራማሪዎች ጋር ልዩ የሆነ ተግባቦት አላቸዉ፡፡

ይህ በህብረተሰቡ እንደዚህ ሲጠበቅ እና እንክብካቤ ሲደረግለት የቆየ እንቁ ሀብታችን በሚመለከተዉ አካል ተገቢዉ ትኩረት እና ማስታወቂያ ተሰጥቶት ለሀገሪቱም ሆነ ለማህበረሰቡ መስጠት ያለበትን አገልግሎት እየሰጠ አይገኝም፡፡

ምንም እንኳን አመቱን ሙሉ ጓሳ አረንጓዴ እና እጅግ ዉብ ቢሆንም በመስከረም ወራት ለመጣ ሰዉ ዙሪያዉን ከተለያዩ ምንጮች የሚወጣ ኩልል ያለ ዜማ የሚመስል ድምፀት ፣ ህብረ ዝማሬ መሰለዉ የወፎቹ ድምፅ ፣ ጥጋብ የወጠረዉ የጭላዳ ዝንጀሮ ትግል እና ልፊያ ፣ የቀይ ቀበሮዎች አይጥን የማደን እና የአይጥ ከመበላት ለመዳን የሚደረግ እልህ አስጨራሽ የሞት ሽረት ፍትጊያ ፣ የጥንቸል ፈጣን ሩጫ ፣ ቀዝቃዛዉ እና ነፋሻማዉ የአካባቢዉ አየር ፤እየኮመኮሙ የፈጣሪዎን ስራ እያደነቁ ሁሌ ከወዳጅዎ እና ከቤተሰብዎ ጋር የሚዝናኑበት ቦታ እንዲሆን መመኘትዎ አይቀርም፡፡

ስለ ጓሳ የተወሰነዉን ብቻ እና ለማስተዋወቂያ ያህል ነዉ እንጂ እኔ የጠቀስኩት www.guassaarea.org በመጎብኘት የበለጠ መረጃ ማግኘት እና የተሻለ ትኩረት መስጠት ይቻላል፡፡ ስለ ጓሳ ስናነሳ ዶክተር ዘላለም ተፈራን በጓሳ ላይ በሰሩት መጠነ ሰፊ ስራ ሳያመሰግኑ ማለፍ ትልቅ ስህተት ነዉ፡፡

" ቀጣይ የጉብኝት መስመራችሁ ወደ ጓሳ ! "

# 5.3 ነገረ ዩኒቨርሲቲ



የሳምንቱን ትምህርት አገባድጄ አርብ ቀን ወደ ቤት እየተጓዝኩ ነዉ፡፡ በሚኒባሱ ዉስጥ ከጎኔ ነሸጥ ያረገዉ በእድሜ ብዙ የማንለያይ የሚመስለኝ ወጣት ተሰይሟል፡፡ ከተቀመጥኩ በኋላ ብዙም ትግስት አልሰጠኝም ወግ ጀመረ ፡፡ እንዴት ነዉ ነገሩ ወደ ቤት ዛሬ አርብ አይደለም እንዴ ኦቨር ነዉ እንጂ የምን ወደ ቤት ነዉ ብሎ ለትዕዛዝ የቀረበ ጥያቄ ሰነዘረ ፤ እኔም እህስ ብዬ በሩን ከፈትኩለት ፡፡ ለካስ ልጁ ዩኒቨርሲቲን የቀመሰ ነበር እና የጊቢ ታሪኩን ታሪክ ያስኮመኩመኝ ጀመር ፡፡ ያወራኝ ነገር ሁሉ ብዙ የተለየ አልነበረም የተለመደ (Default) የሆነዉን አብዛኛዉ የጊቢ ተማሪ የሚያሳልፈዉን አይነት ሂወት ነዉ የተረከልኝ፡፡ የተወሰኑ ደቂቃዎች ካወራን በኋላ የአዲስ-አዳማ ፍጥነት መንገድ ሳይታሰብ ጎሮ ላይ ቁጭ አድርጎን የወሬያችን መቋጫ ሆነ፡፡ ምንም እንኳን ልጁ ጎሮ ላይ ቢቀርም መገናኛ እስከደርስ የእኔ ሀሳብ በልጁ ጨዋታ ላይ ነበረ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ አሁን ባለንበት ስርዓት ዉስጥ እንደ ትልቅ ስራ ከሚነሱት መካከል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደ አሸን መፍላት ነዉ፡፡ ይህ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት ለሀገሪቷ ትልቅ እምርታ ነዉ ፤ ምንም እንኳን አንዳንዶች 100 መፅሀፍት የሌላቸዉ 50 ዩኒቨርሲቲዎችን ከመክፈት 10000 መፅሀፍት ያላቸዉን 10 ዩኒቨርሲቲዎችን መክፈት እና ጥራት ላይ ትኩረትን ማድረጉ የተሻለ ነዉ ብለዉ መብዛቱን ጥያቄ ዉስጥ ቢያስገቡትም፡፡

በእርግጥ በትክክል የተጠና ጥናት ማግኘት ባልችልም በሀገሪቷ ትምህርት ላይ የከፍተኛ ትምህርት እድል አግኝተዉ የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥራቸዉ ከአጠቃላይ አብረዋቸዉ ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ ሲማሩ ከነበሩ ተማሪዎች ዉስጥ ከ20% አይበልጥም፡፡ ሌላዉ ነጥብ እየጣለ ተንጠባጥቦ የቀረዉ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆን ተማሪ ይሄን የከፍተኛ ተምህርት እድል ማግኘት አይችልም ፡፡ የሌላዉን እድል ዘግተዉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዉስጥ ከገቡት 20 በመቶ ደግሞ በግምት ቢበዛ 15 በመቶ የሚሆነዉ ብቻ ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ ሆኖ ወይንም የራሱን ስራ ፈጥሮ የሚወጣዉ ፤ ሌላዉ 85 በመቶ ወይ ስራ አጋጥሞት ካልሆነም ስራ አጥ ሆኖ ይቀራል፡፡ ይሄ ወደ አጠቃላይ አሀዝ ስንቀይረዉ አገሪቱ ከምታፈራዉ የአንድ የትምህርት ዘመን ተማሪ ( ከ1ኛ ክፍል - ዩኒቨርሲቲ ደረጃ አንድ ጋር ተምሮ የሚጨርስ (Batch) ) ዉስጥ ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ የሚሆነዉ 10 በመቶ እንኳን ሊደርስ አይችልም፡፡

አንድ ተማሪ የዩኒቨርሲቲን መግቢያ ነጥብ አግኝቶ ሲገባ ሌላ አንድ ወንድሙ እድሉን በሱ በመነጠቁ የመማር ህልሙ ከስሞ የህይወቱን አቅጣጫ ለመቀየር ይገደዳል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዳችን ዩኒቨርሲቲ ላይ ስንገኝ ከራሳችን በተጨማሪ እድሉን ዘግተንበት የመጣነዉን ሰዉ ሀላፊነት ጭምር ተሸክመን ነዉ፡፡

እዚህ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ስንማር የሀገራችን ሀብት እየተጠቀምን መሆናችንን ልንዘነጋ አይገባም ፤ መንደር ላይ ቁጭ ብለዉ ፀሀይ የሚሞቁ ጓደኞቻችን እድል ዘግተን እንደመጣን መረዳት አለብን ፤ እየተበደረች በምትኖር ሀገር ዉስጥ ሆነን እኛ እዳ ከፋዮቿ ደግሞ ስንኩል ሆነን ስንቀር አገር አመድ አፋሽ ሆና ትቀራለች፡፡

በአሁኑ ጊዜ ዩኒቨርሲቲ ላይ መጥፎ እይታ እንዲኖር ያደረጉ ሁለት አይነት ጉልህ ችግሮች አሉ፡፡ የመጀመሪያዉ ከስነምግባር ጋር የተያያዘ ሲሆን ሌላዉ ከተጠመቅንበት የዘረኝነት አመለካከት ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡

ከስነምግባር አንፃር የሚነሳዉ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ወይንስ የሱስ መቅሰሚያ (UNIVERSITY PLACE OF EDUCATION OR PLACE OF ADDICTION?) የሚል ነዉ፡፡

እንዳየሁት ከሆነ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ህይወት ላይ ከባዱ ጊዜ የመጀመሪያ ዓመት ነዉ፡፡ የመጀመሪያ ዓመት ፈተናዎች መቋቋም እና ድል ማድረግ የቻለ ተማሪ ቀሪዎቹን ዓመታት በስኬት የማሳለፉ ነገር የተሻለ ይሆናል፡፡ የብዙ ተማሪዎች ሂወት የሚመሰቃቀለዉ ልክ ታስሮ እንደተፈታ እምቦሳ ከቤት ሲወጡ የነፃነት ብዛት መርገጫ እና መቀመጫ አሳጥቷቸዉ ራሳቸዉ መምራት ተስኗቸዉ ያየሁትን ልንካ ፣ ሁሉን ካልሞከርኩት ፣ ለምን ይቀርብኛል ማለት ሲጀምሩ እና ያለ ባትሪ በድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ መጓዝ ሲጀምሩ ነዉ፡፡

የተማሪዎች ሱስ በተለይ ከከተማ አከባቢ ከመጡ የከፍተኛ ትምህርት አባላት ዘነድ የተለመደ ነዉ፡፡ ጫት ፣ ሀሽሽ፣ ሲጋራ ፣ ጋንጃ ፣ መጠጡ ፣ ኧረ ምኑ ቅጡ፡፡ እነዚህ ሱሶች ድሮ የወንዶች ነበር አሁን በእኩልነት የተሰጣቸዉን መብት ተጠቅመዉ ይመስለኛል የሴቶች የሱሱ አባላት ቁጥራቸዉ የትየለሌ ነዉ፡፡ የሚገርመዉ የከተሜዉ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን እነሱን ተከትለዉ የሚተኑት ነቃን ባዮች ከየክፍለ ሀገር የሚመጡ ፤ አላማቸዉን የረሱ እናታቸዉ መቀነት ፈትታ የላከችዉን ፍራንካ ለሲጋራ የሚያዉሉ እርባና ቢሶች መኖራቸዉ ነዉ፡፡

ተማሪዎች በሱስ አለም ከተዘፈቁ በኋላ ወጪያቸዉን ለመሸፈን ስለሚቸገሩ ሱሱም ስለሚገፋፋቸዉ ወዳልተፈለገ የሂወት አቅጣጫ ያመራሉ፡፡ ወንዶች የኮምፒዉተር እና የስልክ ስርቆትን ሲያጧጡፉት ሴቶች ደግሞ ገላቸዉን ለመሸጥ ወደ ጎዳና ያማትራሉ፡፡ አንድ ስሙን መጥቀስ በማልፈልገዉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በተለምዶ ሴተኛ አዳሪ የምናለቸዉ የሂወት አቅጣጫ ወደ ግራ የዞረችባቸዉ ምስኪኖች ሀገር ብዙ የምትጠብቅባቸዉን ገና በአስራዎቹ እና ሀያዎቹ የሚገኙ ታዳጊ የዩኒቨርሲቲ ሴቶችን ስራችንን አስተጓጎሉብን በዚህም እንጀራ ማግኘት ተስኖናል ብለዉ ተደራጅተዉ ለዩኒቨርሲቲዉ ያስገቡትን ደብዳቤ ለማየት ችያለሁ፡፡ ወላጅ በእዉቀት ትሞላልኛለች ያላት ልጅ ሆዷ ሞልቶ ወደ ቤቷ ስመለስ ፤ ይባስ ብሎም የፈጣሪን ፀጋ ሜዳ ላይ ጥላ ሂወቱን እንዲያልፍ ስታደርግ ከማየት በላይ ምን መዓት ሊመጣ ይችላል፡፡

አንድ ወዳጄ የነገረኝ ነገር በጣም አስገርሞኝ ብሎም አስደንግጦኝ ነበር፡፡ በአንድ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ ደም በሚሰበሰብበት ወቅት ተማሪዎች ምርመራ ለማድረግ እና ደም ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም በመጨረሻም ደም ሰጥተዉ ምርመራዉ ከልገሳ በኋላ እንዲደረግ ተደርጎ ከ 65 በሙቶ በላይ የሚሆነዉ ደም ኤች አይ ቪ ኤድስን ጨምሮ በተለያዩ በሽታዎች ተበክሎ በመገኘቱ ከጥቅም ዉጪ ሆኖ እንደተደፋ ነገረኝ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አንዲት የዩኒቨርሲቲ ጓደኛዬ እንዳጫወተችኝ በተለይም አሁን ላይ ሀገራችን እያሰራችዉ ከሚገኙት ፕሮጀክቶች ጋር በተለይም የሰሜኑን የሀገራችን ክፍል

ከሚያገናኘዉ የባቡር መስመር ጋር ተያይዞ የእርሷንም ጓደኞች ጨምሮ ብዙ ታዳጊ የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች ህይወታቸዉ ላይመለስ እየተበሻቀጠ ይገኛል፡፡ ይህ አስደንጋጭም የደዉል ድምፅ ሊሆን የሚገባ መርዶ ነዉ ፤ ማህበረሰቡም ይሄንን ጠንቅቆ ያዉቃል ነገር ግን በምናገባኝ ስሜት በቸልተኝነት እያለፈዉ ይገኛል፡፡ ጤናማ ያለሆነ ወጣት ዜጋ ያላፈራች ሀገር የመጪ ተስፋዋ ላይ ቀይ መብራት ይበራል ፤ አፍነን ያቆየነዉ እድፍ የሁላችንንም ቤት ማንኳኳቱ አይቀሬ ነዉ ፡፡

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሁሉን የመሞከር እና የማወቅ እድሜ ላይ ከመገኘታችን አንፃር ለግሎባላይዜሽን የመጀመሪያዎች ተጋላጮች ነን ብዬ አስባለሁ፡፡ በዚህም ምዕራባዉያን የተቀበሏቸዉ እኛ ግን በፍፁም ልንቀበላቸዉ በማንችላቸዉ ፤ በሀይማኖትም ይሁን በማህበረሰባችን እጅግ ፀያፍ የሆኑ እንደ ተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት አይነት አስነዋሪ ድርጊቶች እነዚህን ለጋ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ሰለባ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነዉ አሁንም ሰም በማልጠቅስበት የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ዉስጥ በአንድ ሴሚስተር ዉስጥ ከ 4 በላይ ወንዶች ልጆች መደፈራቸዉን የሚሳይ አስደንጋጭ ሪፖርት መመልከት መቻላችን ምንያህል የአስተሳሰብ ዝቅጠት እንደሰፈነና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዓለማቸዉን እየሳቱ እንደሆነ ማሳያ ነዉ፡፡ መንግስትም ሆነ ማህበረሰቡ በሹክሹክታ ሲደብቅ እንጂ እንደዚህ አይነት ተግባራትን በግልፅ ተነጋግሮ መፍትሄ ሲሰጥ አይታይም፡፡

የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነህ/ሽ ከሰመመን ልትነቃ/ቂ ይገባል፡፡ ሀፍ ላይፍ ብለህ ሀፍ አልኮል እና እስክስታ ወርደህ ከዚህም አልፎ እየተደባደብክ ጥርስህን ነቅለህ ጭንቅላትህ ተፈተንክ የምትመጣ ፣ ጥናትሽ ትተሽ ልክ እንደ አደዋ ታሪክ ይመስል ከማንም ጋር ያደረግሽዉን ዉሎ ለጓደኞችሽ ስትተርኪ የምተዉይ ፣ ከለር ደይ ብለህ ቀለም ስትቃባ የምትዉል ፣ ዋተር ደይ ብለሽ ዉሀ መቆጠብ ሲገባሽ ዉሀ ስተደፊ የምትዉይ ፣ ፈተና የጨረስክ ለት ወደ መጠጥ ቤት የምታቀና ፣ ክላስ ሳትመጪ አስተማሪሽ ቢሮ የምተመላለሺ ቀልብ ግዢ ፤ ቀልብ ግዛ ፤ ከሰመመናችሁ ንቁ፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት አላማቸዉ ሳይገባቸዉ በመጣላቸዉ መንገድ ለሚተምሙት እንጂ እናንተ ቀን ከሌት የምታትሩት (ቀለሜዎች) ፣ ለዓላማችሁ ስትባዝኑ ሰገጤዎች የተባላችሁ ፣ ቴንሽን ይዟችሁ ከካፌ ትሪ ይዛችሁ የወጣችሁ ፣ ላይብራሪ ጠረንጴዛ ላይ እንቅልፍ የወሰዳችሁ ፣ ለምን እና እንዴት ብላችሁ ራሳችሁን የጠየቃችሁ ፣ የተሰጣችሁ አደራ እንቅልፍ የነሳችሁ ፣ የፍቅር ጓደኛ ባለመያዛችሁ ሲንግሉ መጠሪያችሁ ለሆነ ፣ ለእነ ድንግሉ ፣ እመኑኝ እናንተ ናችሁ የኢትዮጵያ ቀንዲሎች ፣ እመኑኝ እናነተ ናችሁ የኢትዮጵያ እንባ አባሾች ፣ የኢትዮጵያ እሾህ መንቀያ ወረንጦዎች፡፡

ሁለተኛዉ ከዩኒቨርሲቲ ጋር የተያያዘዉ መጥፎ እይታ ዓለም ተምሮ ካለፈበት እኛ ደግሞ እንደ ፋሽን እየተንቦጫረቅንበት ከምንገኘዉ የዘረኝነት አረንቋ ጋር ይያያዛል፡፡

ዩኒቨርሲቲ የዘረኝነት ጨዋታ መጫዎቻ ነፃ ሜዳ መሆኑ አሁን ላይ ግልፅ ሆኗል ፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ለመጋለብ እና በእነሱ ተፈናጠዉ የመጨረሻ ግባቸዉን ለማሳካት የቋመጡ ሀይሎች ይሄንን ትኩስ እና ወጣት ሀይል ላልተፈለገ ነገር ሲገፋፉት ይታያል፡፡ አሁን ላይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነኝ ሲባል መጀመሪያ በሰዉ አዕምሮ ላይ የሚመጣዉ ጥያቄ ትምህርት እንዴት ነዉ ሳይሆን ግቢ ሰላም ነዉ ሆኗል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዘረኝነት ቅርሻት መትፊያ ተመራጭ ቦታዎች መሆናቸዉ እጅግ አሳሳቢ ነዉ፡፡ ብር ያለዉ ወጣቶችን በጥቅም ገፋፍቶ ለእሳት ብሎም ለሞት የሚማግድበት ፣ ላይብረሪ እስኪርብቶ ይዞ የገባ ተማሪ ሲመለስ ስለት ይዞ በገባ ህሊና ቢስ ከንቱ ነፍሰ በላ ሂወቱን የሚያጣበት ፣ ልጆቻቸዉን በየትምህርት ተቋማቱ የላኩ ቤተሰቦች እንቅልፍ

ሳይዞርባቸዉ ዉለዉ አድረዉ የሚያነንቡበት ፣ በቡድን ተደራጅተዉ የቤት ስራ የማይሰሩ ተማሪዎች በቡድን ተረዳጅተዉ በዘረኝነት ተጨማልቀዉ ሴራ ሲጠነስሱ የሚዉሉበት ፣ ወንድም ወንድሙን የሚገድልበት የጦር አዉድማ ሆኗል፡፡

ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን እና እኔ እድለኛ ሆኜ በሚከባበሩ ፣ እጅግ በሰለጠኑ ፣ ከዩኒቨርሲቲያቸዉ ስም በላይ እጅግ በላቁ ፣ ራሳቸዉን ከሚያዉቁ ባለ ህልም ልባሞች ፣ ሁሌም በምኮራባቸዉ የአዲስ አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር በመማሬ ያለምንም ሰቆቃ እና ጭንቀት ትምህርቴን ለማጠናቀቅ በቅቻለዉ፡፡ ነገር ግን በተለይ በክልል ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ ጓደኞቼ ያለ ጥፋታቸዉ የስቃይን ገፈት ቀምሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ትምህርታቸዉን ሲያቋርጡ ፣ አንዳንዶቹ ከህንፃ ላይ ወድቀዉ ተሰብረዉ ሲመጡ ይባስ ብሎም አንድ መቀመጫ ላይ ተቀምጬ የተማርኩት የት ይደርሳል የተባለ ጓደኛዬ ደግሞ ምክንያቱ ሳይታወቅ ህይወቱ አልፎ ሲገኝ ፤ ከዚህ በላይ ምን ቅስም የሚሰብር ነገር አለ ? ሀገር ተስፋዋን ስትነጠቅ ከማየት በላይ ፣ ወላጅ ባዶ እጁን ሲቀር ከማየት በላይ …

ዩኒቨርሲቲ ላወቀበት የወደፊት የህይወቱን ሀዲድ የሚዘረጋበት ቦታ ነዉ፡፡ የዩኒቨርሲቲ ስሙን ስንመለከተዉ የትምህርት ማዕከል ይሁን እንጂ ወጣቶች የህይወት ፈለጋቸዉን የሚያንፀባርቁበት ስፍራ ነዉ፡፡ ለዚያም ነዉ አይኖች ሁሉ ወደዚህ ቦታ የሚያማትሩት፡፡ ዩኒቨርሲቲ የሀይማኖት እሽቅድምድም የሚከወንበት ፣ የግል እና የቡድን ቢዝነሶችን የሚጧጧፉበት ፣ አዳዲስ ሀሳቦች እና ፍልስፍናዎች የሚፈለፈሉበት ፣ የስልጣን ጥም ያለበትም ወደ ተማሪ ህብረት ጠጋ ብሎ የስልጣን ጥሙን የሚቆርጥበት ፣ ፖለቲካ እንደጉድ የሚፈተፈትበት ፣ ከሰዉ ጋረ በጋራ መኖር የምንማርበት ፣ራስን ማስተዳደር ሀላፊነት ከወላጆች ተቀብለን ራሳችንን የምናነግስበት ወይንም የምናወርድበት እጅግ ድንቅ ሚስጥራዊ ቦታ ነዉ፡፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የሆንን ወደ ኋላ ዞር ብለን የተሸከምነዉን የወላጅ እና የሀገር አደራ ተረድተን የወደፊቷ ኢትዮጵያ ጠንሳሾቿ ልንሆናት ይገባል፡፡ ስላልተገነዘብን ነዉ እንጂ ከሁሉም የሀገሪቷ ዜጎች ይልቅ እምቅ መግነጢሳዊ ሀይል ያለዉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች እጅ ነዉ፡፡ ንቅ የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት አባላት ናቸዉ ሁሌም ሀገሪቷን የሚዘዉሯት የመሬት ላራሹ አቀንቃኞቹም ሆኑ የእኛ ዘመን መሪዎች የነበሩት እነ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ይሁን ባህር ማዶም ተሻግረን እነ ቼጉቬራን ብንጠራ ህልማቸዉን እዉን ያደረጉት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቆይታቸዉ ነበር ፤ አለም ላይ መሪ የሚባሉት የንግድ ባለቤቶች እነ ቢልጌት እና ዙከንበርግ መነሻቸዉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነዉ፡፡ ስለዚህም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ወጣቶች ለሀገራቸዉ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ ማሳያ ነዉ፡፡

ምንም እንኳ የዩኒቨርሲቲ ገፅታ እና በሰዎች ዘንድ ያለዉ አመለካከት አሉታዊ ከሆነ እንደሰነባበተ ግልፅ እና ግልፅ ቢሆንም አሁንም ቢሆን ቁጥራቸዉ ይነስ እንጂ ትጉህ ፣ የእናታቸዉን አንገት ቀና የሚያደርጉ ፣ ዘረኝነትን የሚፀየፉ ፣ ራሳቸዉን ለህልማቸዉ የሚገዙ ኩሩ የኢትዮጵያ ልጆች በየትምህርት ተቋማቱ አሉ፡፡ እሙን ነዉ ዓለምን የቀየሯት ጥቂቶች ናቸዉ ፤ እነዚህም የቁርጥ ቀን ልጆች የኢትዮጵያን መፃኢ ተስፋ ብሩህ እንደሚያረጉት እተማመናለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ** -( እንደ እኛ ባለ ሀገር ዉስጥ ትክክለኛ ወቅታዊ ትንተና ማግኘት እጅግ ከባድ ነዉ ስለዚህ በሙቶኛ ስገልፅ የነበረዉ የተለያዩ ነገሮችን ከግምት ዉስጥ በማስገባት መሆኑን ተረዱልኝ)፡፡

" ከምንም በላይ ትኩረት ፤ ለነገ የሀገር ተረካቢዎች "

# 5.4 ሳይቃጠል በቅጠል



ታች ክፍል እያለን በህብረተሰብ ሳይንስ ትምህርታችን የሀረማያ ሀይቅ የሚባል አለ እየተባልን ተምረን ነበር ፤ ነገር ግን ይህ ትዉልድ የሀረማያን ሀይቅ ከኋላ አርጎ ሰልፊ ፎቶ ለመነሳት ፣ እስኪሰለቸዉ በሀረማያ ሀይቅ ለመንቦጫረቅ ፣ ከሀረማያ ሐይቅ አሣ አጥምዶ ለማጣጣም አልታደለም፡፡ ሀረማያ ሀይቅ ሜዳ ላይ ኳስ መጫወት እንጂ ዋና መዋኘት አይችልም ፤ ሀረማያ በደረሰበት በደል እና ያለ አግባብ አጠቃቀም ብሎም ትኩረት በመነፈጉ ቦታዉን ለቆ ጓዙን ሸክፎ ኮብልሷል፡፡ አንድ ወቅት ላይ የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የሀይቁን ህልዉና ለመመለስ እየጣረ እና እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ሰምቻለሁ ፤ ይበል የሚያስብል ጥሩ እንቅስቃሴ ነዉ፡፡ እኛን አሁን ላይ ሊያሳስበን የሚገባዉ ላለፈዉ ነገር እየተቆጩ የአዞ እምባ ማንባት ሳይሆን ሌሎች ሀይቆች እና ዉብ ተፈጥሮቻቸዉ እነ ሀረማያ በተጓዙበት ጎዳና እንዳይነጉዱ እና የታሪክ ተወቃሽ እንዳንሆን የሀላፊነታችንን መወጣት ነዉ፡፡

ሀረማያን አጥተነዋል እያልን ስናወራ ደግመን ደግሞ እነ ጣና ፤ አቢያታ ፣ ዝዋይ እና ሌሎች የስምጥ-ሸለቆ ሀይቆች እጣ ፈንታቸዉን እየተጠባበቁ ይገኛሉ፡፡ የሚጠፉት ሀይቆቻችን ብቻ አይደሉም እነዛ አይን የማያስከድኑ መልከ መልካም አእዋፍቶቻቸዉ ፣ ሽታቸዉን የማይጠገበዉ እፅዋቶቻቸዉ ፣ እንደፈለግን የምንንከባለልባቸዉ የሀይቅ ዳር አሸዋዎች ፣ በጀልባ ላይ እየተዟዟርን ሀሴት የምናገኝባቸዉ ታሪካዊ ቦታዎች ፣ ጣት የሚያስቆረጥሙ እያልን የምናጣጥማቸዉ አሳዎቻቸዉም ላይመለሱ ወደ ሌላኛዉ አለም መሸጋገራቸዉ አስፈሪ እና አስደንጋጭ ሀቅ ነዉ፡፡

እስኪ እነዛ ተከባብረዉ የሚኖሩ አዞ እና አእዋፋት አስቧቸዉ ፤ አዞዉም ከጥርሱ ላይ ስጋ የምታወጣለት ወፍ በህይወት አትኖርም ፣ ወፏም ከጥርሱ ላይ ስጋ እንድታነሳ የፈቀደላት ያ አዞ ላይገናኙ ይለያያሉ፡፡ ያአስፈሪ ግርማ ሞገስ ያለዉ ጉማሬን ጨምሮ ሌሎችም ላይገናኙ ተማምለዉ ይለያያሉ፡፡ አብዛኞች አእዋፍትም ኢትዮጵያን እየለቀቁ ወደ ጎረቤት ሀገር ኬንያ እየተሰደዱ ይገኛሉ፡፡ አሳዛኝ የሚያደርገዉ ግን የእነሱ መጥፋት እና መለያየት ምክንያቶች እኛ ሆነን እያለ ይባስ ብሎ ደግሞ ቸልተኞች መሆናችን ነዉ፡፡

ጣና ሀይቅ ከ 5 ሚሊዮን አመታት በፊት በእሳተ ገሞራ አማካይነት የተፈጠረ እንደሆነ ይገለፃል ፤ ህልዉናቸዉ ከሀይቁ ጋር የተያያዘ 7 ቋሚ እና ከ 40 በላይ አነስተኛ ወቅታዊ ወንዞች ይገኛሉ ፤ እንደ ጥናቶቹ ቢለያዩም በአማካይ 40 የሚደርሱ ደሴቶች በሀይቁ ላይ ሰፍረዋል ፤ ጣና ሀይቅ ከምድር ጠለል ከ1786 ሜትር በላይ ሲገኝ ፤ በአጠቃላይ ከ3000 ስኩዬር ኪሎሜትር በላይ ስፋት አለዉ፤ እስከ 14 ሜትር የሚደርስ ጥልቀት ሲኖረዉ አማካይ ጥልቀቱ ግን 9 ሜትር ነዉ ፤ ሀይቁ የኢትዮጵያ 50 በመቶ ንፁሳ ዉሃ ይዞታ ይሸፍናል ፤ ጣና በጣም ብዙ የአሳ ዝርያዎች መገኛም ነዉ አስገራሚ የሚያደርገዉ ደግሞ ከ 70 በመቶዉ በላይ ሀገር በቀል መሆናቸዉ ነዉ፡፡

ጣና ሀይቅ የአለማችን ረጅሙ ወንዝ እና ከ120 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ለሚጠቀምበት የብሉ-ናይል እናት ፣ በብዙ የሚቆጠሩ እኛነታችን ፣ ማንነታችን ፣ አለምን የመራንበትን ቀደምት ስልጣኔያችንን ባጠቃላይ ታሪካችንን የያዙ ገዳማትን እና ታሪካዊ ቦታዎችን በእቅፉ አቅፎ የያዘ ፣ ብዙ ያላወራንለት እና ያልሰበክንለት ነገር ግን ከምናስበዉ በላይ ብዙ ሚስጥሮችን በጓዳ ጎድጓዳዉ ሸሽጎ የያዘ የእኛነታችን ሚስጥር ጠባቂ ነዉ፡፡

አሁን ይህ የምናወራለት ጣናችን የጤና እክል እየገጠመዉ ይገኛል ፤ ድምፁን አጥፍቶ በሚያስገርም ፍጥነት አንድ በአካባቢዉ አጠራር እምቦጭ የተባለ እኩይ አረም እየተፈታተነዉ ይገኛል፡፡ ሰለሞን ክብረት በተባለ ባለሙያ በተፃፈ አንድ ፅሁፍ እንደሚገልፀዉ በ2014 እ.ኤ.አ እምቦጭ የሀይቁን 20000 ሄክታር ሸፍኖት እንደነበር እና በ2016 ደግሞ በእጥፍ አድጎ ተመንድጎ እንቦጭ የሀይቁን 40000 ሄክታር አጥለቅልቆታል፡፡ በ2017 ይሄ አሃዝ ወደ 50000 ሄክታር እያሻቀበ ይገኛል፡፡ በተቃራኒዉ የሀይቁ የአሳ ምርት በአመት ከ13000 ቶን በላይ የነበረ ሲሆን አሁን በእምቦጭ እና በተያያዥ ምክንያት ከ10000 ቶን በታች በአመት ሆኗል፡፡ በዚህም ከቀጠለ በጥቂት አመታት ዉስጥ ሀይቁ 75 በመቶ የአሳ ይዞታዉን በጥቂት አመታት ዉስጥ ያጣል፡፡

ጣና የእኛን እርዳታ ከመቼዉም ጊዜ በላይ ይፈልጋል ፤ እምቦጭን ለማስወገድ ስነህይወታዊ እና በሰዉ ሀይል የማስወገድ እርምጃዎች ይወሰዳል ፤ እንደ አቅራቢዉ ሰለሞን ክብረት ገለፃ ስነህይወታዊ እርምጃ የተሻለ እንደሆነ ይገልፃል ፤ በአሁኑ ጊዜ በሀይቁ ላይ ከ 162000 በላይ የአካባቢዉ ማህበረሰብ አረሙን በእጅ ነቀላ ለማጥፋት እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ብዙ አመታትን መዉሰዱ የማይቀር ነዉ፡፡ ለአብነት ያህል በቪክቶሪያ ሀይቅ ላይ ማለትም ዩጋንዳ ፣ ታንዛንያ እና ኬንያ ላይ የተነሰራፋዉን አረም ነቅሎ ለማስወገድ የኬንያዉ ብቻዉን ወደ 60000 ሄክታር ይጠጋል ፤ የአረም ማስወገጃ ማሽኑ በቀን 10 ሄክታር ብቻነዉ የማስወገድ አቅም ያለዉ ስለዚህ በአጠቃላይ 6000 ቀናት ወይም ከ16 አመታት በላይ ይፈጃል፡፡ ስለዚህ ስነ-ህይወታዊ እርምጃ መዉሰዱ ያዋጣል፡፡

እኛ ጋር ስንመጣ ስለ አባይ ስንት ዘፈን ፣ ስንት ግጥም ፣ ስንት ዘገባ ያዥደጎደ ትዉልድ እንቦጭን እንንቀል ብሎ አለማስተጋባቱ ግን ያስደንቃል፡፡ ቢገባን እኮ የእኛ እያልን የምናዜምለት ፣ የምናቅራራበት ፣ የምንሞትለት አባይ ሊኖር የሚችለዉ እናቱ እና መሸጋገሪያ ድልድዩ የሆነዉ ጣና ጤነኛ ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡ አለበለዚያ ያ ስንት ያሰብንለት ፣ የጨፈርንለት

፣ ያስካከንለት ፣ ቦንድ የገዛንለት ፣ ከግብፅ ጋር እልህ የተያያዝንበት የአባይ ግድብም የእምቦጭ ሰለባ ተጠቂ ሆኖ ያሰብነዉ ህልም መና እና ምኞት ሆኖ መቅረቱን ስንቶቻችን አስበንዉ እናዉቃለን ? ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ እና ከ 5 በላይ ግዙፍ ማሽነሪዎች ቢሰበሰቡም ወደተግባር ገብተዉ ጣናን መታደግ አልተቻላቸዉም፡፡ ይሄ ቸልተኝነት ጣናን ከ አለን ወደ ነበረን እንዳያሸጋግረዉ ያስፈራል፡፡

የእምቦጭ እና የጣና ጉዳይ የአማራ ክልል ወይም የአካባቢዉ ማህበረሰብ ጉዳይ ብቻ አይደለም የእኛ የኢትዮጵያዊያም ጭምር እንጂ ፤ ቢገባቸዉ የጣና ጦስ እየጨመረ ከመጣ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለግብፃዊያን እና ሱዳናዊያንም ስጋት ነበር፡፡ የሶሻል ሚዲያ እያነበብኩ ነበር እና ዜናዉ የኦሮሚያ ወጣቶች ተሰባስበዉ የእምቦጭ አረም ለመንቀል ከኦሮሚያ ክልል ወደ ባህርዳር እንደተጓዙ ይገልፃል፡፡ እዉነት ለመናገር ከእኛ ኩሩ ማንነት እና ስብዕና ካለን ኢትዮጵያዊያን የሚጠበቅ የሚያስመሰግን እና ሊጠናከር የሚገባዉ ስራ ነዉ የሰሩት፡፡ ጣና የእነሱም የመላዉ ኢትዮጵያዊያን እንቁ እና ዘመን አይሽሬ ሀብት ነዉ፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ማህበረሰብ ልክ እንደ ኦሮሚያ ወጣቶች ሁሉ የጣና ጉዳይ የእርሱ ጉዳይ ሊሆን ይገባል፡፡

አሁን ላይ ሆኜ ለመናገር ሚዲያዉ ስለ ስንት ነገር ሲያራግብ የጣና እንቦጭን እና የመሰሎቹን ነገር ጆሮ ዳባ ልበስ ማለቱ የሚያሳፍር እና የሚዲያዎቻችንን ትርጉም አልባነት የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይሄኔ ጣና ሀይቅ ላይ ግድብ ተሰራ ቢሆን ኖሮ ከጋዜጣ እስከ ቴሌቪዥን መቆሚያ መቀመጫ ነበር የምናጣዉ፡፡ ይሄ ጣና ሲታመም ሄዶ ያልጠየቀ ሚዲያ ሁሉ ጣና ሲሞት ስለ ጣና ለማዉራት ገፆች አይበቁትም ፤ ብዕሮቹም አይነጥፉም፡፡ ሳይቃጠል በቅጠል ያሉት አበዉ ለካ ወደዉ አይደለም፡፡

በዚህ ቸልተኛነታችን ከቀጠለ እኛ እድለኞች ነን የተወሰኑትንም ሀይቆቻችን እና ተፈጥሮ ቦታዎቻችንንም ቢሆን ለማየት ታድለናል ፤ መጪዉ ትዉልድ ግን እንደ ሀረማያ ፣ ጣና ፣ አቢያታ እና ዝዋይ የመሳሰሉ ሀይቆችን እና የተፈጥሮ ቦታዎች ለማየት በጥሩ ሁኔታ ጠብቀዉ እና ተንከባክበዉ ወዳቆዩት ሌሎች ሀገሮች ደርሶ መመለስ ይጠበቅበታል፡፡

“ ቅርሶቻችንን መጠበቅ ከእኛ ይጀምራል ! ”

# 6. ግርምት

“ ካስትሮ የሚል ስማቸዉ ሲነሳ ለኢትዮጲዉያን አዲስ አይደለም የክፉ ቀን ባለዉለታችን ናቸዉ፡፡

.

.

.

የተለያዩ የህክምና ባለሙያዎችን ፣ በሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያንም የትምህርት እድል እና ከ5000 በላይ ለሚሆኑ በኢትዮ-ሶማሊ ጦርነት ወላጅ አልባ ለሆኑ ዜጎች ነፃ የት/ት ዕድል ሰጥተዋል ፣ እንዲሁም ከሶማሊያ ጋር በነበረን ጦርነት ላይ ቁጥራቸዉ ቀላል የማይባል በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኩባዉያን ወታደሮችን በማሳተፍ የነበራቸዉ ጉልህ ሚና እና የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጉ እንደ ነበር ታሪክ አይዘነጋዉም ፡፡ የካራማራን ድል ስናስብ ኩባን መዘንጋት አይታሰብም፡፡ ”




“ በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! ”

# 6.1 ባለ 638 ነፍስ



ፊደል ካስትሮ ወይም በሙሉ ስማቸዉ ፊደል አላጃንድሮ ካስትሮ ሩዝ የኩባ ነፃ አዉጪ እንዲሁም በምዕራቡ ዓለም የመጀመሪያዉ ኮሚኒስት መስራች እና መሪ ነበሩ፡፡ ከ1959 እስከ 1976 በጠቅላይ ሚኒስቴርነት እንዲሁም ከ1976-2008 በፕሬዝዳንትነት ኩባን አገልግለዋል፡፡ ካስትሮ ኩባን ወደ 50 ዓመት ከገዙ በኋላ በ2008 ስልጣናቸዉን ለታናሽወንድማቸዉ ራዉል ካስትሮ አስረክበዋል፡፡ ምንም እንኳን በፖለቲካ ነፃነታቸዉ እና በሚከተሉት ኢኮኖሚ ስርዓት ወቀሳ ቢደርስባቸዉም ጤና አገልግሎት ፣ በትምህርት እና ግብርና ፣ በዘረኝነት ላይ ትልቅ ለዉጥ ማምጣታቸዉ የማይካድ ሀቅ ነዉ፡፡

ካስትሮ የሚል ስማቸዉ ሲነሳ ለኢትዮጲዉያን አዲስ አይደለም የክፉ ቀን ባለዉለታችን ናቸዉ፡፡ በ1978 ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል ፤ የካስትሮ ልጆች እየተባለ ሲጠራም እንሰማለን ምክንያቱም በደርግ ዘመነ መንግስት ከርዕዮተ ዓለም መመሳሰል ጋር ተያይዞ ከኢትዮጵያ ጋር ጥብቅ ወዳጅነት ነበራቸዉ፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ የህክምና ባለሙያዎችን ፣ በሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያንም የትምህርት እድል እና ከ5000 በላይ ለሚሆኑ በኢትዮ-ሶማሊ ጦርነት ወላጅ አልባ ለሆኑ ዜጎች ነፃ የት/ት ዕድል ሰጥተዋል ፣ እንዲሁም ከሶማሊያ ጋር በነበረን ጦርነት ላይ ቁጥራቸዉ ቀላል የማይባል በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኩባዉያን ወታደሮችን በማሳተፍ የነበራቸዉ ጉልህ ሚና እና የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጉ እንደ ነበር ታሪክ አይዘነጋዉም ፡፡ የካራማራን ድል ስናስብ ኩባን መዘንጋት አይታሰብም፡፡

ካስትሮ በህይወት በኖሩባቸዉ 90 ዓመታት ማለትም ከ1926 - 2016 ህይወታቸዉ እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትና ያለፈች ነበረች፡፡ ከፍተኛ የሆነ የአይበገሬነት መንፈስ ያለቸዉ እጅ መስጠት የማይሆንላቸዉ ነበሩ በዚህ ምክንያት እና በሚከተሉት ፖለቲካ ስልት ከማይጥማት እና የረጅም ጊዜ ጠላታቸዉ የሆነችዉ እና የሻከረ ግንኙነት የነበራት ሀያሏ አሜሪካ አስፈሪ እና ለመማን የሚከብዱ ጥቃቶችና ተንኮሎች ይደርሱባቸዉ ነበር ፤ በስልጣን ዘመናቸዉ አሜሪካ ብቻዋን በሲአይኤ አማካኝነት ከ 638 በላይ በደንብ የተጠኑ እና የታቀዱ የግድያ ሙከራ አድርጋባቸዋለች፡፡ እንግዲህ ሲአይኢን ከሚያክል ጥራት ያለዉ ፣ ልምድ ያለዉ ገዳይ ፣ አሜሪካዉያንን እንዲሁም አለምን ከሚቆጣጠር የደህንነት ድርጅት እንጂ ከቀበሌ ታጣቂ

የግድያ ሙከራ አይደለህም እኘህ ሰዉ ከሞት አፋፍ ያመለጡት ፤ ለዚያዉም ከ638 በላይ ጊዜ ፤ ከዚህም ነፍሳችን እስካልተፈረደባት ምንም ብንፈተን ከዚህ ዓለም እንደማንለይ መረዳት እንችላለን፡፡ በሀገራችን አንድ አባባል አለ የከፉ ሰዉ እና የድመት ነፍሳቸዉ 7 ነዉ ይላል ፤ የካስትሮ ግን ከ638 በላይ ነፍስ ነዉ ያላቸዉ ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ ዘና የሚያደርጉን እና ትምህርት የሚሠጡንን ገጠመኞቻቸዉን እና አንዳንድ የግድያ ሙከራዎችን እንመለከታለን ...

## ገጠመኝ

ካስተሮ በ1979 የአሜሪካ ጉዞአቸዉ አንድ ጥያቄ ቀረበላቸዉ ፤

ጋዜጠኛ - በቃ ይሄንን ሰደርያ ሁሌም እንደለበሱት ነዉ

ካስትሮ - የምን ሰደርያ

ጋዜጠኛ - ሀገር ያወቀዉን ነዋ የጥይት መከላከያ ሰደርያ

ካስትሮ - ወዲያዉኑ የሸሚዛቸዉን ቁልፍ ፈትተዉ ሰፊዉን ደረታቸዉን ለጋዜጠኛዉ እና ለካሜራዉ አሳዩት ከዚያም ከት ብለዉ ሳቁና እግዲህ እደምታዩኝ ነኝ እንኳንስ በሀገሬ እዚህም እናንተ ሀገር ኒዉዮርክ ያደረኩት የጥይት መከላለያ ሰደርያ የለም ይሄንን ስልህ ግን ባዶዬን ነኝ እያለኩህ አይደለም በእርግጥም ሰደርያ አለኝ ግን እናንተ እንደምታስቡት ሳይሆን የሞራል የጥይት መከላከያ ነዉ ያለኝ ብለዉ አፉን አስይዘዉ መለሱት ፡፡

## በዋና ልብስ

በ1963 በሲአይኤ ካስትሮን ለመግደል ያወጡት እቅድ ከካስትሮ የዋና ፍቅር ጋር በተያያዘ ነበር ፡፡ ካስትሮ ዋና ስለሚወዱ ለምን አደገኛ የሆነ የዋና ልብስ አናዘጋጅላቸዉም ብለዉ አሰቡ ፤ በቤተ-ሙከራ ከተቀመሙ መሳሪያዎች ልብሱ የመተንፈሻ መሳሪያም አብሮት ተዘጋጀ ፤ ልብሱም በፈንገስ የተሞላ እና በቀላሉ ለአደገኛ የቆዳ በሽታ እና ለመተንፈሻ አካላት አጋልጦ የሚገል ነበረ ፤ በመጨረሻም ልብሱ ከካስትሮ ጋር ለስምምነት ይደራደር በነበረዉ በአሜሪካዊ ጠበቃ ጀምስ ዶኖቫን አማካኝነት ለካስትሮ በስጦታ እንዲሠጥ ተስማሙ ፤ በመጨረሻም ጠበቃዉ አሳስቶ ሌላ የመዋኛ ልብስ ለካስትሮ ሰጥቶ ኖሮ እቅዱን አፈር በላዉ፡፡

## በፍቅር ጓደኛቸዉ

ማሪያ ሎሬንዝ በወቅቱ 1959 አካባቢ የካትስሮዉ ፍቅር አጋር ነበረች ፡፡ እርሷም ስትናገር ወቅቱ በሲአይኤ ተመልምላ የኩባዉን መሪ የመግደል ሀላፊነት የተሰጣት ሴት ነበረች፡፡ እርሷ በሲአይኤ ሁለት ቦቱሊዝም- ቶክሲን የተባሉ የተቀመሙ ኪኒኒዎችን ካስትሮ በሚጠጡት መጠጥ ዉስጥ እንድትጨምር ነበር ሴራዉ የተሴረዉ ፤ መድሀኒቶቹም ከካስትሮ ጋር ከተዋሀዱ በኋላ 30 ሰከንድ ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ካስትሮን ከዚህ አለም ያሰናብታቸዋል ማለት ነዉ ፤ ነገር ግን መደሀኒቶቹ በቀዝቃዛ እቃ ዉስጥ ከሚገባዉ በላይ ተቀምጠዉ ኖሮ መክነዉ ጥቅም አልባ በመሆናቸዉ የታቀደዉ ሳይሳካ ቀርቶ ሌላዉ የሲአይኤ ደባ ተኮላሸ፡፡

## በሲጋራ

ይሄኛዉ ደግሞ ስልጣን ከያዙ አንድ ዓመት በኋላ ነበር ፤ የስካትሮዉን የሲጋራ ከፍተኛ ተጠቃሚነት በማየት እርሳቸዉ በሚመርጡት የሲጋራ አይነት ተመርጦ የሲጋራዉ ካርቶን ሲአይኤ ባዘጋጃቻቸዉ ሲጋራዎች ተሞላ ፤ የተዘጋጁት ሲጋራዎች መርዛማ ስለነበሩ ከመካከላቸዉ ዉስጥ አንዷን አንድ ጊዜ እንኳን ከሳቧት ካስትሮ ወዲያዉኑ ነዉ ላይመለሱ የሚያሸልቡት ፤ ሲጋራዎቹ ለእርሳቸዉ ቅርብ ለሆነ ማንነቱ ግን ላልተገለፀ ሰዉ ተላለፉ ነገር ግን ምን እንደተፈጠረ በማይታወቅ ምክንያት ተድበስብሶ ቀረ፡፡

## <u>በብዕር</u>

ሲአይኤ በቴክኖሎጂ የተመነጠቀ እና የሚያስቀና ጥበብ ያለዉ ድርጅት ነዉ ሌላ እቅድ አወጣ ብዕር ማዘጋጀት ፤ ብዕሩ የተዘጋጀዉ ለመፃፊያነት ብቻ አልነበረም ከዚያ ይልቅ እጅግ የሚያስደንቁ ጥቃቅን የሆኑ እና በአይን ለመለየት የማይቻሉ መድሀኒት ወደ ቆዳ ዘልቆ ማስገባት የሚያስችሉ መርፌዎች (hypodermic needles) ነበሩት ፤ ስለዚህ በቀላሉ ካስትሮ ብዕሩን ሲጠቀሙ እርሳቸዉ ምንም ሳይታወቃቸዉ እና ሳይረዱት መርዛማ መድሀኒት ሰዉነታቸዉን ሰርስሮ እና ዘልቆ መግባት ይችላል፡፡ ወዲያዉኑ በኩባ ለካስትሮ ቅርብ ለሆኑ የስራ ሀላፊ ተሰጥቶ በእርሳቸዉ አማካኝነት የካስትሮን ፍፃሜ ለማብሰር ተዶለተ ፤ የተዶለተዉንም እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ ሀላፊዉ በህዳር 22 1963 ተላልፎ ተሰጠ ፤ ባጋጣሚ የዛን እለት ሲአይኤ የሰዉ መሪ ለመግደል ሲሯሯጥ በወቅቱ የአሜሪካ መሪ የነበሩት ጆን ኬኔዲ በሰዉ ተገድለዉ ይችን ዓለም ተሰናበቷት ፤ የታሰበዉ ቀርቶ ያልታሰበዉ ተከሰተ ፤ እንዲህ ነዉ እንግዲህ የራሷ እያረረባት የሰዉ ታማስላለች ማለት ፤ በዚህ እና በተለያዩ ምክንያቶች ብዕሩ ወደ ኩባ ከመሄድ ተረፈ ፤ ካስትሮም ያቺ የድመት ነፍሳቸዉ አልገኝ አለች፡፡

## <u>ማፍያ</u>

ሲአይኤ ነገሮች ሲከሽፉበት በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ ልፍስፍስ አይደለም ፤ የካስትሮን ፍፃሜ ለማቅረብ ኤፍቢአይ ከሚፈልጋቸዉ ዋና 10 ዝርዝር ከገቡ 2 የወንበዴ ማፍያ አለቆች ከነበሩት ሳም ጋንሺያ እና ሳንቶስ ትራፊካንት ጋር መደራደር ጀመረ ፡፡ በወቅቱም ድርጅቱ ስራዉን ከፈፀሙለት 150000 ዶላር ወይም በአሁኑ ምንዛሬ ከ1.25 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለመክፈል ተስማማ፡፡ በመጨረሻም ሳም ጋንሺያ ከጥይት ይልቅ ኪኒኒ መድሀኒቶች አስተማማኝ ስለሆኑ እንዲቀርቡለት ሀሳብ አቅርቦ በሲአይኤ 6 በጣም ገዳይ ኪኒኒዎች ተዘጋጁ በመጨረሻም ወደ ካስትሮ ለማድረስ ለእሳቸዉ ቅርብ ለሆነ ሰዉ ተላልፎ ተሰጠ ፤ ነገር ግን ሳይሳካ ተድበስብሶ ቀረ፡፡

የሚያስገርም ነዉ የሲአይኤ ጥረቱ ብዙ ነበር ካስትሮን ብቻ ሳይሆን ያንን እንደ ዓርማ የሚቆጥሩትን ዠርጋጋ ፂማቸዉን ከፊታቸዉ ገፅ ላይ ለመጥፋት ተሯሩጦ ነበር፡፡

ፊደል ካስትሮ ኩባን የምታክል ሀገር ይዘዉ አሜሪካንን የምታክል ሀያል ሀገር ያርበተበተ ሀሞተ-ኮስታራዉ ፣ እስከ ጥግ ድረስ በራሱ የሚተማመነዉ ፣ አንደበተ - ርቱዑ ፣ የነፃነት አባት ፣ አይበገሬዉ ፣ ሞት የማይደፍረዉ እየተባሉ የሚጠሩት ካስትሮ በህዳር 25 2016 በ90 ዓመታቸዉ ለሞት እጃቸዉን አስረከቡ፡፡ (*አቆጣጠሮቹ በሙሉ እኤአ ናቸዉ)

" ሞት የታወረች ናት … ቀንህ ካልደረሰ ፈልጋ አታገኝህም ! "

# 6.2 የኮንትራት ኑሮ



አብዛኞቻችን በተለይ በወጣትነት እድሜ ላይ የምንገኝ ልጆች እግርኳስ መከታተል የዕለት ከዕለት ተግባራችን አካል ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ወጣት ወንድ ልጅ የአዉሮፓ ሀገራት ሊግ የማይከታተል ፣ የተጨዋቾችን ሙሉ ስም ፣ ሀገራቸዉን ፣ ክለባቸዉን ፣ የፀጉር ስታይላቸዉን ፣ ምናምናቸዉን … ያልሸመደደ እንደ ፋራ እየተቆጠረ ያለበት ጊዜ ላይ ነዉ ያለነዉ፡፡ እራሳችንን ከዚህ ለመሰወር ግማሾቻችን ቢጥመንም ባይጥመንም ከጓደኞቻችን ጋር ኳስ ሄደን ለማየት መሯሯጡን ስራዬ ብለን ይዘነዋል፡፡ እዚህ ስንት እከክ እና ችግር እያለብን የሌላ ሰዉ እከክ ያሳስበናል ፣ የሜሲ ጉዳት ሲያስለቅሰን ፣ የሱዋሬዝ ንክሻ ሲያደማን ፣ የኮስታ ቀይ ካርድ ጨጓራችንን ሲልጠዉ ይታያል፡፡

እንግዲህ አብዛኞቻችን ለእግር ኳስ ቅርብ ነን ብዬ አሰብኩ ፤ እነዛ እኛ መለያቸዉን የምናመልክላቸዉ እና ጥርስ እስከመዋለቅ ብሎም እስከ ሞት መስዋት የምንከፍልላቸዉ ክለቦች ለእኛ የተሻለ እግርኳስ ለማሳየት ብሎም ለራሳቸዉ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ፤ እራሳቸዉን ለማጠናከር በክረምት እና በጥር ወር የዝዉዉር መስኮት ላይ ኮከብ ተጨዋቾችን ኮንትራት ለማስፈረም ከገበያ ገበያ ፣ ከሀገር ሀገር ፣ ከክለብ ክለብ ፣ ከዚህ እዚያ ሲማስሱ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ በተቃራኒዉም ብቃታቸዉ የወረደ ተጨዋቾችን ለገበያ ሲያቀርቡ እና ኮንትራታቸዉን ሲሰርዙ እናያለን፡፡ የእኛም ሀገር ሚዲያዎች ቁጭ ብለዉ ስራ ፈተዉ ኔይማር የአለም ሪከርድ በሆነ ዋጋ ፒኤስጂን ተቀላቀለ ፣ ኤዲን ሀዛርድ በማድሪድ እይታ ዉስጥ ከገባ ሰነባብቷል ፣ ጁቬንቱስ ለክርስቲያኖ ሮናልዶ ኮንትራት አቀረበለት ፣ እከሌ ክለብ አልባ ሆኗል እያሉ ጆሮዎቻችንን ማደናቆር ፣ ዓይናችንን ማደንገዝ ተክነዉበታል ፣ ለነገሩ ለገቢም አሪፍ ነዉ አሉ በዚህ ሰሞን ብዙ ጋዜጦች እና መፅሄቶች እንደሚሰበሰቡ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡

ይሄ የክለቦች ኮንትራት የሚል አባዜ ከእግርኳስ ዉጪ በሂወታችንም ዉስጥ ተጠናዉቶን ይታያል፡፡ እኔ እንደማስበዉ በእርግጥ ሰዎች ነን እና በዚህ አለም ስንኖር ይሄ ኮንትራት መኖር የለበትም አይደለም ነገር ግን ይሄ ነገር ቅርፁን እና ይዘቱን እየቀየረ ከመጣ ቆይቷል፡፡ በተለያዩ ሁኔታዎች አሁን ያለንበት አለም ስናያት ከቋሚ ነገር ይልቅ ሁሉ ነገር ልክ እንደ ኳስ ዝዉዉር በኮንትራት ሆኗል፡፡ እስኪ የተወሰኑትን የኮንትራት አይነቶች አንያቸዉ -

## ጤና

ቀደም ባለዉ ጊዜ ጤንነት ላይ የተለያዩ እንከን ሲያጋጥሙን በባህላዊ ህክምና ብሎም በሀይማኖታችን ነበር የምንፈወሰዉ ፤ ይህም ካተልሳካ ወደ የማይቀረዉ ማረፊያችን እንጓዛለን ፤ አሁን ግን ላይ እያየነዉ ያለዉ ነገር ምንድን ነዉ ? ሰዉ በጠና ሆስፒታል ሄዶ ድኖ መመለሱ የእግዜር ቸርነት እንዳለ ሆኖ ባለዉ ኮንትራት ላይ እየተወሰነ መጥቷል ፤ ኩላሊት ስትሮክ ፣ ልብ ፣ ካንሰር ፣ ብቻ ብዙ ብዙ አለብህ ይባልና ኮንትራቱን ፈርመህ ዉጪ ሄደህ ካልታከምክ ከዚህ ጊዜ በኋላ ከዚች ዓለም ጋር ያለህ ኮንትራት ያበቃል ብለዉ የምንሞትበትን ቀን አስልተዉ ይነግሩናል፡፡ ብዙዎች እህት እና ወንድቻችን በኢኮኖሚ እና በተለያዩ ችግሮች ያቺን ኮንትራት መፈረም አቅቷቸዉ በኮንትራት እየኖሩ መሆናቸዉን መዘንጋት የለብንም ፤ ባገኘነዉ አጋጣሚ ከጎናቸዉ ልንቆም ይገባል፡፡

## ጓደኝነት

ኮንትራት ከሚታይባቸዉ አንዱ እና ዋነኛዉ ጓደኝነት ነዉ፡፡ ማንን ጓደኛ ላድርግ ገንዘብ አለዉ/አላት ? መልከመልካም ነዉ/ናት ? ጎበዝ ነዉ/ናት ? ስታይሉ ይመቸኛል/ትመቸኛለች ? አራዳ ነዉ/ነች ? ቁምነገረኛ ነዉ/ናት ? ተብሎ በመስፈርቱ ይመረጥ እና የጓደኝነት ኮንትራት ይፈረማል ከቆይታ በኋላ ገንዘቡም እንደ ጉም ተኖ ሲጠፋ ፣ ቁንጅናዉም እንደ ቅጠል ሲረግፍ ፣ ጉብዝናዉም ትምህርት ሲያበቃ ፣ ስታይሉም ሌላ የተሻለ ስታይል ሲገኝ ፣ አራዳዉም ሰገጤ ሲሆን ፣ ቁምነገረኛ የተባለዉም ቱሪናፋ ሆኖ ሲገኝ የኮንትራት ዉሉ ፍፃሜ ይሆን እና ልክ እንደ ከለቡ ወደ አዲስ ጓደኛ ምልመላ ገበያ ላይ ሲወጣ ማየት የተለመደ ነዉ፡፡

## ትዳር

ትዳር የኮንትራት ሲሆን ማየት የተለመደ ነገር ነዉ ፤ አሁን ግን በሚገርም ሁኔታ ፍቺ ልክ እንደ አንድ ባህል እየተለመደ መጥቷል፡፡ አንድ በህግ ዙሪያ የወጣ ሪፖርት በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ፍርድ ቤትን ካጨናነቁ ጉዳዮች ፍቺ ከግንባር ቀደሞቹ ዉስጥ መሆኑ ይገለፃል፡፡ መጀመሪያ ላይ እኔ ልሙትልሽ/ልሙትልህ ተብሎ ኮንትራት ይፈረማል በኋላም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ዉሀ ቀጠነ ፣ ማነዉ የደወለዉ ፣ የት አመሸህ/አመሸሽ ፣ የሚባሉ ነገሮች ይመጡ እና የኮንትራቱ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ይሄ የትዳር ኮንትራት በዓይነቱ አደገኛ ኮንትራት ፣ ቤተሰብን ብሎም ሀገርን አደጋ ላይ የሚጥል ፣ በቤተሰብ ፍቅር ማደግ እና ለሀገር መጥቀም ያለባቸዉን ልጆች ለህብረተሰቡ ብሎም ለሀገር ሸክም የሚሆኑ እና አደጋ የሚፈጥሩ ዜጋዎችን የሚፈጥር ነዉ፡፡

## ስልጣን

ስልጣን የኮንትራት ነዉ ፤ ስልጣን የተሰጠዉ አካል ወይም ግለሰብ የያዘዉ መቀመጫ የኮንትራት መሆኑን ልብ ሊለዉ ይገባል፡፡ ለህብረተሰቡ መከታ ይሆናል ሲባል ለሀያላን ሀገር ሎሌ ከሆነ ፣ ሀገርን ያሳድጋል የተባለ ራሱን ካሳደገ ፣ መንገድ ይገነባል የተባለ ፒስታ አንጥፎ በአስፋልት ካወራረደ ፣ ሆስፒታል ይሰራል ተብሎ ክሊኒክ ከሰራ ፣ ተገቢዉን ታክስ ያስከፍላል ሲባል የሚዘርፍ ከሆነ ፣ የተገልጋይ እሮሮ ለማየት ካልፈለገ ለመስማት ከደነቆረ ፣ ቆጣሪ ተክሎ መብራት ከነፈገ ፣ መስመር አስገብቶ ዉሀ ከሌለዉ ፣ ያለ መፅሀፍ እና መምህር ትምህርት ቤት ገነባሁ ካለ ፣ እንደ ሾላ ፍሬ ዱብ ማለቱ የማይቀር ሀቅ ነዉ ፤ ምክንያቱም ይቺ ዓለም በኮንትራት የተተበተበች ናት ፡፡

## <u>ስራ</u>

ይሄ የተለመደ እና መደበኛ የኮንትራት አይነት ነዉ ፡፡ አንድ ሰዉ ስራ ለመቀጠር ወይም ኮንትራት ለመፈረም መስፈርቶቹን ማሟላት ይኖርበታል ፤ ኮንትራቱን ለማስቀጠል የገባዉን ቃል ማሟለት እና መተግበር ይኖርበታል፡፡ እነደ ዉሀ በሳምንቱ እንደ መብራት በሶስት ቀን ከመጣ ፣ በሰዓት መገኘት ሲገባዉ አንበሳ ባስ ከጠበቀ ፣ የያዘዉ ዲግሪ የአዉራ ዶሮ ዲግሪ ከሆነ ፣ ተገልጋይ አክባሪ መሆን ሲገባዉ ተገልጋይ አብጠርጣሪ ከሆነ ፣ በአጭር ጊዜ ይሄኛዉን ኮንትራት ተነፍጎ ሌላ ኮንትራት ፍለጋ ማስታወቂያ ቦርድ ለገሀር ለለገሀር ፣ አራት ኪሎ ለአራት ኪሎ ፣ ደላላ ለደላላ መንከራተቱ አይቀርም፡፡

እናንተስ ምን አይነት ኮንትራት ፈርማችሁ ታዉቃላችሁ ? አስፈርማቸሁስ ? ሌላም የኮንትራት ዓይነት ካለ ጨምሩበት ፤ ኮንትራት ስንፈርምም ሆነ ስናስፈርም በደንብ እናስብበ፡፡ ነጮቹ **sleep on it!** ይሉታል ፡፡

“ ጓዴ ፤ ዴግሞ ለኮንትራት ኑሮ … ዴግ ዴጉን ተመኝ ! ”

# 6.3 ሂወት IN THE አአሳቴዩ



ሂወት ሂወት የምትሆነዉ ፤ የሰዉ ልጅ የኑሮን ኡደት ሲሽከረከራት የተለያዩ ደረጃዎችን ሲወጣ እና ሲወርድ ነዉ፡፡ እነሆ እኔም የሂወቴ አንዱ አካል በሆነዉ የትምህርት ጉዞዬ የ12ኛ ክፍልን ካጠናቀኩኝ በኋላ የወደ ፊቷ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ መፀነሻ ይሆናል ተብሎ ታስቦ በ 2003 ዓ.ም ለተመሰረተዉ አዲስአበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በ2008 የመጀመሪያዎቹ ተፈታኞች በአጠቃላይ ደግሞ ለ5ኛ ጊዜ የሚቀበላቸዉ ተማሪዎቹ መካከል አንዱ አድርገዉ እድል እና ጥረት አንድ ጋር ተረዳድተዉ ከዩኒቨርሲቲዉ ደጃፍ ላይ ወረወሩኝ፡፡

አአሳቴዩ ምንም እንኳን ከከተማ ትንሽ ራቅ ያለ ቢሆንም ብዙዎች በዚህ እና በሌላ ምክንያት ቦታዉን ቢያማርሩም እኔ በግሌ ግን በተለየ መልኩ ለተማሪዎች ቀልብን ሰብስቦ ለመማር ምቹ ቦታ መሆኑን አምናለሁ፡፡ እጅግ ፀጥ ያለ ከራስ ጋር ለመመሰጥ እና አትኮሮትን ለመሰብሰብ የሚያስችል እንቅስቃሴም ማድረግ ለሚፈልግ እጅግ ሰፊ ቦታ ያለዉ ግቢ ነዉ፡፡

አአሳቴዩን ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የሚታዩ የዶርም እጥረቶች አይታዩበትም፡፡ ሌላ ዩኒቨርሲቲ በተለይ ፍሬሽ ማን ሲሆን እስከ 40 ተማሪ አንድ ጋር መኖር ፈታኙ ነገር ነዉ፡፡ አአሳቴዩ መንግስት የትምህርት ኮምፒዉተሮችን ከማሟላት ይልቅ ብዙ ቅርፅ የለሽ ህንፃዎችን የሚያሰራበት እና የሚያስኮለኩልበት ወቅት ስለሆነ ከፍሬሽ ማን ጀምሮ ቢበዛ 4 ሰዉ ነዉ አንድ ዶርም ዉስጥ፡፡ ለብቻቸዉ 1 ዶርም ከዚያም በላይ አንድ ሰዉ 2 እና ከዚያ በላይ ዶርም ለብቻዉ ሲኖረዉም ተመልክተናል፡፡ እንደዚህም ሆኖ እጅግ ብዙ ህንፃዎች ገብቼ እስከ የምመርቀበት ቀን ድረስ አገልግሎት እንደማይሰጡ እና ተሰርተዉ እንደተቀመጡ ታዝቤያለሁ፡፡

ከቶ ልረሳቸዉ ከማልችላቸዉ ቦታዎች ዋነኛዉ ላይብረሪ ነዉ ፡፡ በጊቢ ዉስጥ እያለሁ ከላይብራሪ የቀረሁበትን ቀን አላስታዉም፡፡ የበጋዉ አልበቃ ብሎኝ ሁለት ክረምቶችን ከጊቢ አልወጣሁም በዚህም ጊዜ መጠለያዬ ላይብረሪ ነበር ፤ አይደለም ለስራ ፊልም እንኳን ለማየት እና ቻት ለማድረግ ከቀልቤ የምሆነዉ ላይብራሪ ዉስጥ ነበረ ፤ ብዙ ግዜ በቀን በአማካይ ከ10 ሰዓት በላይ የምቆይበት ቦታ ነዉ፡፡ አስታዉሳለሁ በክፍላችን በሚወጣዉ ቶፕ 10 ከተለያዩ አስቂኝ ዘርፎች ዉስጥ እኔና ጓደኛዬ ሌላኛዉ ብሩክ ከላይብራሪ ባለመጥፋታችን የላይብራሪ ኮከብ ሰቃዩች የሚል ተቀፅላ ተሰጥቶን ነበረ፡፡ ብዙ ተማሪች ላይብራሪ የሚገቡት ለፈተና ቀን ብቻ ስለሆነ ላይብረሪን ከልባቸዉ ይጠሉታል፡፡ አንዳንዶቹማ በተለይ በማጠቃለያ ፈተና ዝግጅት ጊዜ ከወንበር ላይ ይወድቃሉ ባስ ሲልም በተለይ ሴቶች ራሳቸዉን ስተዉ የሚወድቁም አጋጥመዉኛል፡፡ ላይብራሪን ሳነሳ ሳላመሰግነዉ የማላልፈዉ ሰዉ ሰዎችን ለመርዳት የማያደርገዉ ነገር ስለሌለዉ የቀለም አስተማሪዬም በተጨማሪም ስብዕና የተማርኩበት የቅርብ ጓደኛዬን የላይብራሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ቸሬ ለማን ነዉ፡፡

በነገራችን ላይ አአሳቴዩ ከታዘብኩት ነገር ላይብራሪ የሚገባዉ ለማንበብ ብቻ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ፡፡ አንድ ከሌላ ዩኒቨርሲቲ የመጣ ጓደኛችን ተማሪ ለኢንተርንሺፕ መጥቶ ቆይ እዚህ ጊቢ ተፈትኖ ነዉ የሚገባዉ ያላችሁኝ በእዉቀት ብቻ ነዉ ወይንስ በመልክም ጭምር ነዉ ሲል የቀለደበት እና አአሳቴዩ ዉስጥ እጅግ ብዙ ቆንጆ ኢትዮጵያን የሚመስሉ እንስቶች እንዳሉ የገለፀበት ቀልድ አስታዉሳለሁ፡፡ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሰዉ ከማንበብ ዉጪ አይኑን ያረፈባት ቸካይ ላይ አይኑን ለማማተር ሳይፈልግ ከወረቀት ጋር እንሚታገል ታዝቤያለሁ፡፡ አንዳንዱማ በዛዉ ወረቀቱን እንደታቀፈ ልጅቷን ረስቶ በእንቅልፍ ጭልጥ ይላል ፤ ሲነቃ ልጅቷ ወጥታ ብቻዉን ተቀምጦ ያገኘዋል ፤ በንዴት ጠንጼዛዉን እየደለቀ ያቋረጠዉን እንቅልፍ ዶርሙ ሄዶ ይቀጥለዋል፡፡

ከጊቢ ትዉስታ ዉስጥ ሌላዉና ዋነኛዉ የካፍቴሪያ ትዝታ ነዉ፡፡ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ካፌ የተሟላ ባይሆንም ከ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ሲወዳደር መካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተገንዝቤያለሁ ፤ ሌሎች ቦታዎችን የማየት ዕድሉ ሰለነበረኝና ስለሰማሁ ማለቴ ነዉ፡፡ ኪሳችን ሞላ ያለ ቀን ክብነሽ እና መምህራን ካፌ ትተናት ብንኮበልልም የማትቀየመን የአአሳቴዩ ካፌ የመኖር ህልዉናችን እና ሚስጥራችን ነበረች፡፡ ካፌ እንደየሰው የተለያየ አመለካከት አለዉ ፣ ግማሹ ሰቃይ ነዉ ( የምግብ ፍቅር አለበት ) ፣ ግማሹ ሆዳም ነዉ( ሲበላ ጅብ ያስቀናል) ፣ የዜግነት ግዴታዉን ለመወጣት የሚበላም አለ (ፍላጎት የሌለዉ) ፣ ከነጭራሹም የማይመጣ ሞልቷል፡፡

አንድ ጓደኛችን ነበር ሲበዛ የምግብ ፍቅር አለበት ፤ በጣም ተመጋቢ ነዉ፡፡ እሱ ሲኖር የሚተገበር አንድ ህግ ነበር ህጉ “ ቀድሞ የጨረሰ ሌላዉን ያጫርሳል ” የሚል ነበር ፤ አቤት ራሳችንን ከ ድንገተኛ ጥቃት ለመከላከል ብለን የምንጎርሰዉ አጎራረስ ምግብ በዞረበት ዞረን የማናዉቅ ነበር የሚመስለዉ ፤ ያዉ የተረታ እና የተረፈዉ ካለ ጓደኛችን እያነሳ ወደ ገደሉ ይልከለታል፡፡ አስታዉሳለሁ ስራ በጀመርኩት ወቅት ከሌላ የጊቢ ጓደኛዬ ጋር እንደለመድነዉ ምግብ ስንበላ አንዱን አብሮን የነበረ የመስሪያቤት ጓደኛዬን ከጨዋታ ዉጪ አደረግነዉ፡፡ እኛም ልጁ ከጨዋታ ዉጪ ሆኖ ብዙ እንዳልበላ የገባን ምግቡ ካለቀ በኋላ ነበረ፡፡ በድርጊታችንም የተበሳጨዉ የስራ ጓደኛዬ GUYS BE PROFFESSIONAL ብሎ አሳፍሮን ነበረ፡፡ እግዜር ይይልሽ የአአስቱ ካፌ እንቺ ነሽ ያሰደብሽን፡፡

ካፌ የፈተና ሰሞን የመዝናኛ ቦታ ጭምርም ነዉ፡፡ በቴንሽን ተናዉዞ ሰሀን ይዞ ወደ ዉጪ የሚነጉድ ፣ ሰሀን ይዞ የመጣ መስሎት ኩባያ ላይ እንጀራ እና ወጥ ጨምሩልኝ የሚል ፣ እንጀራ አስደርጎ ወጥ የሚረሳ ፣ በአንዱ በር ገብቶ ሳይበላ በሌላኛዉ በር ይዞ ተመልሶ የሚወጣ ኧረ ስንቱ፡፡

ሌላዉ የካፌያችን ገፅታ ምን መሰላችሁ ካፌ ዉስጥ ምግብ ብቻ አይደለም የሚበላዉ ሰዉም ይበላል፡፡ ለምሳሌ - ያንን ልጅ ተመልከተዉ ተመልከተዉ ስሀኗን እኮ ወለወላት የህዳሴዉ ጅብ ብየዋለሁ ፣ እቺኛዋን ደግሞ አየሃት እንጀራ ለመጀመሪያ ጊዜ የምትቀምስ ነዉ የምትመስለዉ እኮ ፣ የማስታዉሰዉ ቀኑ ዜርፎር ነበርና እንዱ እስቲኪኒ አቀብለኝ ሲል ሰምቸዉ ነገሩ ግራ ገብቶኝ ዞር ስል ለካ ቀጭን ልጅ ከፊታቸዉ ተቀምጣ ጓደኛዉና እሱ ልጅቷን እየበሉ (እየፎገሩ) ነበር ፡፡ አይ ሀሜት ... ቢረሳ ቢረሳ እንዴት ካፌ ይረሳል፡፡

ተረሳህ ወይ ፤ ተረሳሽ ወይ .....

የዜር ፎር ቀን ያለ የሰቀላ ሰልፍ ፤

እንጀራ ነዉ ተብለን እንጀራ መሰል ነገር የበላንበት ቀን፤

ስጋ አይሉት ፕላስቲክ ያላመጥንበት ፤

ከጆግ መለስ ባለ ኩባያ ሻይ ያንደቀደቀንበት ፤

ሳንከፍል በሞቴ ተባብለን የተገባበዝንበት ፤

ሸክም እንጂ ጉርሻ የማይመስል ጉርሻ የተጎራረስንበት ፤

ጠጠር እንደ ቆሎ የቆረጠምንበት ፤

እንቁላል በኪሳችን ሰርቀን የቀሸብንበት ፤

ዉሀ ሊያመጣ የሄደ ሲመለስ ምግቡ ድምጥማጡ ጠፍቶ ዉሀዉን የሚጠጣበት ፤

በርበሬ ተወዶ በበርበሬ የተቃጠልንበት ፤

ጠቅሰን ያስጨለፍንበት ፤

ሸርተቴ ይዞን የተራወጥንበት ፤

አዳልጦን የወደቅንበት ...

ከተማሪ የማይጠበቅ ግን የብዙ ተማሪ ቅስምን ከሰበሩ ድርጊቶች አንዱ የኮምፒዉተር ፣ ቦርሳ እና ስልክ ስርቆት ነዉ፡፡ ጥቂት ሌቦች ግቢዉን ያንቀጠቅጡት ነበር፡፡ እኔን ጨምሮ የዚህን ገፈት ያለቀመሰ አለ ብዬ አላስብም፡፡ በተለይ በፈተና ሰሞን ባንድ ጊዜ እስከ 6 ላፕቶፖች የሚሰረቁበት ወቅት ነበረ፡፡ ላይብራሪ እና ዶርም ደግሞ የቀማኛዎቹ ተማሪዎች ተመራጭ ቦታዎች ናቸዉ፡፡ አስገራሚም ስርቆቶች አሉ ፤ አስታዉሳለሁ ጓኛዬ እንደ ደከመዉ ለእረፍት ጆሮዉ ላይ ከስልኩ ሙዚቃ ከፍቶ ኤርፎኑን ሰክቶ እየኮመኮመ ያሸልበዋል፡፡ ከሰመመኑ ሲነሳ ያለ ሙዚቃ እና ስልክ ባዶ ጆሮዉ ላይ የተንጠለጠለ ኤረፎኑን ብቻ አግኝቶታል፡፡

በሳቅ እና በደስታ የተሞላ የዶርም ክፍል ዉስጥ ሂወት፡፡ ከምንም በላይ ያጣሁት ነገር ቢኖር የሚመስለኝ ያን በለዛ እና በሳቅ የተሞላ የዶርም ህይወት ነዉ፡፡ ሁላችንም በተመሳሳይ የእድሜ ደረጃ ስለምንገኝ በተረኛዉ ላይ ሙድ መያዝ ፣ ምግብ ደብቆ ያስቀመጠ ካለ በልቶ ጠብቆ ሲመጣ ኩም ማድረግ ፣ አንዱ ብር ካለዉ ያ ብር የሁሉም የጋራ ይሆናል ህይወት ሁሉ የጋራ የሆነችበት ብቸኛ ቦታ ነዉ፡፡ ሁሌም ሳቅ ፤ ከፍቶን እንኳን ሳንስቅ ዉለን አድረን አናዉቅም፡፡

በአብዛኛዉ ዩኒቨርሲቲ ላይ የሚገኝ እድሜዉ በወጣትነት ላይ እንደመገኘቱ በተለይ ከተቃራኒ ፆታ ጋር መላከፍ (በቃላት መሸንቆጥ) የተለመደ ነዉ፡፡ በአንዳንድ የኒቨርሲቲዎች እንዲየዉም ከመልከፍ ባለፈ ሴቶች ከመሸ አይወጡም ከወጡም ጥፊ ቀምሰዉ ባስ ሲልም ስልካቸዉን ለቀማኛ ሰዉተዉ ነዉ የሚመለሱት፡፡ በነበረኝ ቆይታ አአሳቴዩ አንዲት ሴት ልጅ ብቻዋን በፈለጋት ሰዓት ወጥታ የምትንቀሳቀስበት እና እንደፈለጋት ብትሆን ዞር ብሎ የሚያያት ሰዉ የሌለበት ሁኔታ መኖሩን ተመልክቻለሁ፡፡ በተቃራኒዉ ብዙ ሴቶች የሚለክፍ ወንድ የለም እያሉ እንደሚያሙ በሹክሹክታም ቢሆን ሰምተናል ... በነገራችን ላይ አአሳቴዩ የበግም ይሁን የፍየል ተራ የሌለዉ ብቸኛዉ ዩኒቨርሲቲ ሳይሆን ይቀራል ብላችሁ ነዉ፡፡

ሌላኛዉ ከአሳሳቴዩ ተማሪዎች ከሪፖርት ዉጪ የሚደግፋቸዉ አካል ባይኖርም ከግል በተጨማሪ በቡድን ህልማቸዉን ለማሳካት ተፍ ተፍ የሚሉበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ብዙ የቴክኖሎጂ ክለቦች ያለ ምንም ድጋፍ በግቢዉ ዉስጥ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ከዚያም ዉስጥ ከጓደኞቼ ጋር የመሰረትነዉ ለኢትዮጲያዉን ነፃ ትምህርት ለመስጠት ያቋቋምነዉ ኩራዝ-ቴክ ለእኔ ትልቁ የግቢ ስጦታዬ ነዉ፡፡ ያለ ምንም ክፍያ ፣ ወጪችን ከኪሳቸዉ አየሸፈኑ ህልማቸዉን ለማሳካት ደፋ ቀና የሚሉ ታዳጊዎች ፣ እንቅልፍ የለሽ አንዳንዴም በረሀብ የተሞሉ ምሽቶች ፣ ቁርጠኝነት ፣ እልኸኝነት ፣ አልሸነፍ ባይነት ፣ የሀገር ፍቅር ፣ የተሻለ ነገር የመስራት ፅኑ ፍላጎት በቲማችን ዉስጥ በየቀኑ የሚታዩ ነገሮች ነበሩ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሁላችሁንም ትላንት የነበራችሁ ዛሬም ያላችሁ የኩራዝ-ቴክ ቤተሰቦች ምንያህል እንደምንዋደድ ብታዉቁትም ዛሬ በትዉስታዬም ድጋሜ እጅግ እንደምወዳችሁ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ ፅድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ ነዉና ነገሩ የዩኒቨርሲቲዉ አካል መደገፍ እንኳን ባይችል ህልማቸዉን ለማሳካት እንቅፋት ባይሆንባቸዉ እመኛለሁ፡፡

እድሜ ለዩኒቨርሲቲዉ ባለዉለታ ሁሌም አአሳቴዩ ሲባል አዕምሮአችንን ላይ ድቅን ስለሚልብን የብዙዎችን ጫና ተቋቁሞ ህልሙን ለማሳካት ለሚሯሯጠዉ ታታሪዉ በረከት ደባይ ይሁንና ለተማሪዎች ተምሳሌት እና ራዕይ ሲባል ታዋቂ ሰዎች ሁሌም እየተገኙ ተሞክሯዉን ያካፍሉ ነበረ፡፡ ከሀይሌ እስከ ዶ/ር ኢለኒ ፣ ከጎሳዬ አስከ ሮፍናን ፣ ከጃኖ ባንድ እስከ ፀደኒያ ፣ ከብሩክ የሺጥላ እስከ ኮሜዲያን እሸቱ ፣ ከሳሚ ዳን እስከ እሱባለዉ ፤ ከጌታነህ እስከ ሎዛ ... የአአሳቴዩን መሬት ያልረገጠ የለም ፤ የሁሉንም የዉድቀት ታሪክ የስኬት ሚስጢር ለጥንካሬያችን ምግብ ቢሆነን ብለን ኮምኩመናል ፡፡

በግሌ ከነበሩኝ ቆይታዎች የነበረኝ ቆይታዎች ከአአሳቴዩ ልዘነጋቸዉ እና ልፍቃቸዉ ከማልችላቸዉ ትዉስታዎች እንቁ ከሆኑ ተማሪዎች እና ጓደኞቼ ባሻገር ከመምህሮቼ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ነበር፡፡ አንደ የትምህርት ክፍሉ እና እንደ ግለሰቡ ለየቅል ቢሆንም በእኔ በኩል ግን ሁሉን ነገራቸዉን ሳይሰስቱ የሰጡኝ ዉለታቸዉን ልመልስላቸዉ የማልችላቸዉ ምንግዜም ከህሊናዬ ሊጠፉ የማይችሉ ፣ ቁጭ ብድግ በሉልኝ ፣ አንቆሳብሉኝ የማይሉ ቅን መምህሮች ነበሩኝ፡፡ ከእነዚህ መምህሮቼ ጋር ከአብዛኞቹ ጋር አሁንም ከአአሳቴዩ ከወጣሁ በኋላ ሁሌም የማገኛቸዉ እና የተለያዩ ስራዎችን አብረን የምንሰራ የማከብራቸዉ ወንድም እና እህቶቼ ሆነናል፡፡

ጊቢ በነበርኩበት ጊዜ ምናልባት የኔን ለየት የሚያደረገዉ እንደ አብዛኞቹ ሌሎች ጓደኞቼ ለወሬ ማሞቂያ የሚሆኑ እንኳን ትዉስታዎች አልነበሩኝም፡፡ ምናልባት በነበረኝ ቆይታ እጅግ በብዙ ነገሮች እና ስራዎች መወጠሬ አዉቄም ይሁን

ሳላዉቅ እንደዚህ አይነት ሂወት ሳላሳልፍ ከጊቢ ለመዉጣቴ እንደ ምክንያት ይሆናል፡፡ የምቀርባቸዉ እና እዉነተኛ ብዙ የሴት የቅርብ ጓደኞች ቢኖሩኝም የሴት ፍቅር ጓደኛ ሳይኖረኝ ነዉ ግቢን የለቀቅኩት፡፡ እጅግ ብዙ ካልቸር ደይ ፣ ከለር ደይ ፣ አሸር ፣ ዋተር ደይ ፣ ቢኖሩም እንደ እድል አንዱ ላይ እንኳን ተገኝቼ አላዉቅም፡፡ ብዙዎች የሚቀርቡኝ አንድ ቀን ምናልባት ሊቆጨኝ እንደሚችል ቢያወጉኝም ፣ እስካሁን አልቆጨኝም ፣ የወደፊቱን … በነገራችን ላይ በግቢ ዉስጥ ያለዉን የፍቅር ግንኙነት ከሚቃወሙት እና በትምህርትም እንደሚያደክም ከሚያምኑት ወገን ሆኜ አይደለም፡፡ እዉተኛ እና ረጅም ርቀት የተጓዘ ግንኙነት ያላቸዉ እና በትምህርትም ቢሆን ከስኬት ጫፍ የደረሱ ጓደኞች ስላሉኝ በስርዓት እና በእምነት ላይ የተመሰረተ ጥምረትን እደግፋለሁ፡፡

በአሳሳቴዩ በነበርኩበት ወቅት እጅግ የምጠላዉ ነገር ቢኖር ቢሮ መሄድ ነበረ፡፡ ምንም አይነት ጉዳይ በአንድ ጊዜ እንደማያልቅ የተማርኩበት አሰልቺ ቢሮክራሲ ያለዉ ተቋም ነዉ፡፡ አአሳቴዩ ምንም አንኳን ሳላመሰግናቸዉ የማላልፈዉ ወጣት ቅን እና ሁሉም የሚወዳቸዉ እንደ ዶ/ር ምስራቅ ፣ ዶ/ር ቢኒያም እና ዶ/ር በለጠ ***(የግለሰቦችን ሰም መጥራት ተገቢ ባይሆንም ቀና ሰዎች ስለሆኑ ምናልባት ለሌሎች አርአያ ቢሆኑ ብዬ አስቤ ነዉ)*** አይነት ቅን አመራሮች ቢኖሩትም ያለዉ የተወሳሰበ የአሰራር የቢሮክራሲ ግን ያሰቡትን እንዳያሳኩ ሲጎትታቸዉ ይታያል፡፡

እዉነት እዉነት ነዉ ፤ አዉቃለሁ በተለይ በአመራር ላይ ያሉ ሰዎች እንደሚከፋቸዉ እና በፍፁም እንደማይቀበሉት ነገር ግን እዉነተኛ ለዉጥ ለማምጣት ምንም ቢኮመጥጠንም እንደ ኮሶ ልንሸመጥጠዉ የግድ ይለናል፡፡ አአሳቴዩ ተማሪዎቹ እና የዩኒቨርሲቲዉ አመራር ወይንም መንግስት እጅግ የተራራቀ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸዉ፡፡ አአሳቴዩ ርቀዉ የሄዱ እና የነገሱ ተማሪዎችን ሰብስቦ ይዞ መንገስ የተሳነዉ ዩኒቨርሲቲ ነዉ፡፡

አለምክንያት አይደለም አአሳቴዩ ተማሪዎችን የምወዳቸዉ፡፡ በነበርኩባቸዉ ዓመታት ዉስጥ ረብሻ እና አመፅ የተከሰተዉ አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ፤ እጅግ ሰላማዊ ግቢ ነበረ፡፡ ብዙዎች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሆነን ሳንረብሽ ልንወጣ ነዉ እያሉ የሚቀልዱበት ጊቢ ነበር፡፡ ይሄም በታህሳስ 2011 ዓም አካባቢ ሲሆን ለ 2 ሳምንታት የዘለቀ ዓመፅ ነበር፡፡ ለየት የሚያደርገዉ አመፁ እንደ ሌሎቹ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በብሄር ፤ በዘር በተማሪዎች መካከል የተከሰተ አልነበረም፡፡ የአመፁ መነሻ በዩኒቨርሲቲዉ ለተማሪዎች ተገብቶ የነበረ የትምህርት እድል ፣ የስራ እድል ፣ ማበረታቻ ሽልማቶች ቃል አለመፈፀሙ ነበረ ፡፡ በዚህም ጊዜ ትምህርት ቢቋረጥም የሰዉ ልጅ ሊጎዳ ቀርቶ መስታዎት ሳይሰበር የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች ድምፃቸዉን ከማሰማታቸዉ የተለየ ያደረጉት ምንም ነገር የለም ይሄም እጅግ አስታዋይ መሆናቸዉን የሚያንፀባርቅ ነዉ፡፡

የዩኒቨርሲቲዉ ከፍተኛ አመራር አሁንም ቢሆን አለም ካለችበት ሁኔታ ጋር አብሮ የሚራመድ ነዉ በቴክኖሎጂ የተቃኘ አስተሳሰብ አለዉ ብዬ አላምንም፡፡ ስለሆነም ለዉዷ ዩኒቨርሲቲያችን የነገን ብሩህ ተስፋ እዉን የሚያደርጋት ከቴክኖሎጂ ጋር አብሮ ሊራመድ እና የተማሪችን ነባራዊ አስተሳሰብ ተረድቶ ከተማሪዎች ጎን ሊቆም የሚችል አዲስ አመራር እንደሚያስፈልጋት አምናለሁ፡፡

ያዉ ነገሩ ከስንዴ ዉስጥ እንክርዳድ አይጠፍም ነዉ እና የአአሳቴዩ ተማሪዎች በሙሉ ምሉዕ ናቸዉ እያልኩ እንዳልሆነ ትረዱኛላችሁ፡፡ ከሌሎች ጊቢዎች ጋር ሲነፃፀር ቁጥሩ ይነስ እንጂ ቦዘኔ እና ሱሰኛ ተማሪዎችም እንዳሉ የአደባባይ ሚስጢር ነዉ፡፡ ነገር ግን የአአሳቴዩ ተማሪዎች በፍቅር ለመኖር ፤ ያለብሄር ግጭት ተቻችሎ መቆየትን ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ ሁሌም የምኮራባቸዉ ተማሪዎች ናቸዉ፡፡

የምወዳት አአሳቴዩ ምንም እንኳን ካንድ ጊዜም በላይ ሁለቴ ተጨማሪ የነፃ የትምህርት አድሎችን ብታቀርብልኝም የሂወት ጉዞዬ ወደ ግራ ሆነና ሳይገጣጠም ቀርቶ እየወደድኳት ልለያት ወሰንኩኝ፡፡

“ የአአሳቴዩ ቤተሰቦቼ ዉስጤ ናችሁ ፤ በሚያግባባን ቋንቋ ብዬ ነዉ ! ”

# 7. ቅምሻ

" እቱ ተሳስቼ ፤ ባንቆሳብልሽ

ከምሬ ቆልዬ ፤ ከላይ ብክብሽ

.

.

.

ቦታሽን ታዉቂያለሽ ፤ አንቺ ግን ወረድሽ ፡፡ "




" በቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት ፤ ከኢትዮጵያዉያን ለኢትዮጵያዉያን ! "

# 7.1 ከራዲዮኔ

ከራዲዮን ናት ፤ ያቺ የዋኋ ወፍ
ሰዎችን ፈዉሳ ፤ እሷ የምትረግፍ፡፡
ከራዲዮኔ ነሽ ፤ እማ አንቺ ለእኔ
ከፅንሰት ጀምሮ ፤ አለሽኝ ከጎኔ፡፡



እማ...
እኔ ለወደቅኩት ፤ አንቺ ደንግጠሻል
እኔ ለደማሁት ፤ አንቺ አልቅሰሻል
እኔን ለማሳደግ ፤ እራስሽን አጥተሻል
ዉበትሽን ሰጥተሽኝ ፤ አንቺ ጎስቁለሻል
ምን ቃላት ምን ተግባር ፤ አንቺን ይገልፅሻል
ኑሪ ለዘላለም ፤ ክብር ይገባሻል
ከራዲዮኔ ነሽ ፤ መጠሪያሽ ያንስሻል ፡፡

ስቃዬ ስቃይሽ ፤ ደስታዬ ደስታሽ
እኔን ሰዉ አርገሻል ፤ ራስሽን አራቁተሽ
መከፈል ቢያቅተኝም ፤ ቢበዛ ዉለታሽ
ከአይኔ ላይ አትጠፊም ፤ ሲነጋና ሲመሽ
ኑሪልኝ እማዬ ፤ ከራዲዮኔ ነሽ፡፡

ማን አለ እንዳንቺ ፤ የሚያነብ የልቤን
በእይታ ብቻ ፤ የሚያዉቅልኝ ዉስጤን
ሁሌም ያኮራኛል ፤ ካንቺ መፈጠሬ
ቁልፉ አንቺ ጋር ነዉ ፤ የእኔነት ሚስጥሬ
በፍቅር ላይ ፍቅር ፤ ደርበሽ አልብሰሽ
ሞቆኝ አድጌያለዉ ፤ ምስጋና ይድረስሽ
ቃላቶች ያጥሩኛል ፤ ምን ብየ ልግለፅሽ
ሁሌ እወድሻለሁ ፤ ከራዲዮኔ ነሽ፡፡

የከት ጃኖዬ

የክብር ካባዬ

የጠዋት ወጋገን ፤ የማታ ጀንበሬ

ከራዲዮኔ ነሽ ፤ ባንቺ ነዉ መኖሬ

ከራዲዮኔ ነሽ ፤ ላንቺ ነዉ መኖሬ፡፡

“ ክብር እነሱነታቸዉን ሳይሰስቱ ለእኛነታችን ለቸሩን ዉድ እናቶቻችን ! ”

# 7.2 ልናገረዉማ



ልናገረዉ እንጂ ፤ ልናገረዉማ

ነገር ዉስጤ ገብቶ ፤ ከእኔ ካልተስማማ

የምን መደበቅ ነዉ ፤ የምን ማስመሰል

ዉሸትን አምቆ ፤ መትከን መብሰልሰል

ሀሜት ማከማቻ ፤ ጉድጓድ መቆፈር

ነገርን አክርሮ ፤ ቂምን መቋጠር

አዉጥቼ አዉርጄ ፤ እዉነቱን ፈልጌ

አምሼ ወቅጬ ፤ በደንብ ፈትጌ

ነገር ዉስጤ ገብቶ ፤ ከእኔ ካልተስማማ

ልናገረዉ እንጂ ፤ ልናገረዉማ ፡፡



" አሜን ብለህ ከሚከነክንህ ... ተናገረዉማ ... ነፃ ትወጣለህ ! "

# 7.3 የህልሜ ኑዛዜ

በራፌ ቢንኳኳ ፤ ነቃሁኝ ከእንቅልፌ
በሩንም ከፈትኩት ፤ እያዛጋሁ ከአፌ ፡፡

ከፊት ለፊት ሆኜ ፤ እያየሁ በአርምሞ
ህልሜን አገኘሁት ፤ ከደጃፌ ቆሞ፡፡

ወዲያዉ ተከለፍልፌ ፤ ልይዘዉ ስሞክር
አትጠጋኝ ብሎ ፤ አደረገኝ ገፍተር
ሁሉ ግራ ገብቶኝ ፤ ስዞር ስደናበር
ድምፁን ጮክ ፤ አድርጎ ጀመረ ንግግር፡፡

ስማኝማ ብሩክ ፤ ስማኝ አንድ ጊዜ
አዉጥቼ ልንገርህ ፤ የልቤን ኑዛዜ
ቀን ከሌት ከሰራህ ፤ በርትተህ ከተጋህ
ሁሌም ሳትዘነጋኝ ፤ እኔን ተከትለህ
አትጠራጠረኝ ጊዜዉ ሲደርስልህ ፤ እጄን ትይዛለህ፡፡



አለበለዚያማ .....

ተኝተህ አልመህ ፤ ስትነቃ ረስተኸኝ
ከሆነ ነገሩ ፤ አሁን እንዳየኸኝ
ዛሬ ይበቃሀል ፤ መቼም አታገኘኝ
ብሎኝ ተሰወረ ፤ እዛዉ እንደቆምኩኝ፡፡

" ገራሚ ህልም ... ልባም ተመልካች ካላገኘ ... መለስተኛ ቅዠት ነዉ ! "

# 7.4 እቱ ተሳስቼ

እቱ ተሳስቼ ፤ ባንቆሳብልሽ

ከምሬ ቆልዬ ፤ ከላይ ብክብሽ

ያለ ስምሽ ስም ፤ ያለ ዝናሽ ዝና

ያለ የሌለሽን ፤ ባሞግስ ቁንጅና

ካንቺ ዉጪ ሌላ ፤ የሌለ መስሎሽ

ኩራት ተያያዘሽ ፤ ቀና ደፋ እያልሽ

እዚህ እዚያ ስትይ ፤ ወጥ እየረገጥሽ

ከቆጥ ስታወርጂ ፤ ከብብት ጥለሽ

እቱ ተሳስቼ ፤ ከላይ ብክብሽ

ቦታሽን ታዉቂያለሽ ፤ አንቺ ግን ወረድሽ ፡፡



" ክብርን ክብር ለሚገባቸዉ ብቻ ... የምን ማሽቃበጥ ነዉ ! "

# 7.5 መች እጠላሻለሁ

ፀባይሽ ቢያስቸግር ፤ ቢሆን አሜኬላ
የጠቀመሽ ቀርቶ ፤ የጎዳሽ ቢበላ
ብልህ እንዳልነበርሽ ፤ ብትሆኚም ተላላ
መች እጠላሻለሁ ፤ አላይ ከአንቺ ሌላ ፡፡



ዉበትሽ ቢረግፍ ፤ ብታጪም አለኝታ
ሆዳም ቢበዛብሽ ፤ ቢረሳ ዉለታ
ብታረዝ ብጠማ ፤ ብገረፍ ብመታ
መች እጠላሻለሁ ፤ አንቺ የኔ ከርታታ ፡፡

ብርሀንሽ ጠፍቶ ፤ ቢበዛ ጨለማሽ
ትዉልድ ቢሆንብሽ ፤ የእናቱን ጡት ነካሽ
በዉሸት ፈጠራ ፤ ሰዎች ሁሉ ቢያሙሽ
መች እጠላሻለሁ ፤ አለሁኝ ከጎንሽ ፡፡

ቀዳሚ እንዳልነበርሽ ፤ ብትሆኚ መጨረሻ
ሌላ እንዳልረዳሽ ፤ ብትማፀኚ ጉርሻ
ሀዘንሽ ቢበዛ ፤ ሆነሻል አልቃሻ
መች እጠላሻለሁ ፤ እኔ የአንቺ መካሻ ፡፡

ቤተሰብሽ ብዙ ፤ እንዳልነበር ሙሉ
ሁሉም ተበታትኗል ፤ ጠፍቶበታል ዉሉ
እቃዉን ሸክፎ ፤ ትቶሽ ቢነጉድ
መች እጠላሻለሁ ፤ አንቺ የኔ ዉድ ፡፡

መች እጠላሻለሁ ፤ መቼም አልጠላሽም
አንቺ እንደማትረሺኝ ፤ እኔም አልከዳሽም ፡፡

" ማን እንደ እናት ፤ ማን እንደ ሀገር ... !"

# 7.6 ሳናዉቅ አዉቀንልሽ

**ከትላንት በስቲያ**

ቢሰማ  ችግርሽ ፤ ቢሰማ ማጣትሽ

ለመግባት ብንፈልግ ፤ አንቺን ልንረዳሽ

ቁልፉ ጠፍቶብናል ፤ የጓዳ ማጀትሽ፡፡

**ትላንት**

ፈልገን ፈልገን ፤ ቁልፉን አግኝተናል

ግን መግባቱ አቅቶን ፤ ከደጃፍ ቆመናል፡፡

ቁልፉን ለመፈለግ፤ ብንተባበርም

ቀድሞ ለመግባት ግን ፤ መስማማት አልቻልንም፡፡

የእኔ እብስ አባዜ፤ ቢጠናወተን

በየወገናችን ፤ ቡድን ተቧድነን

አንዱን ስናወርደዉ ፤ ሌላ ስናወጣ

አንዱን ስንሸልም ፤ ሌላ ስንቀጣ

ጉልበቱ የራደዉ ፤ እጁን እየሰጠ

አልሸነፍ ያለዉ ፤ ልቡ እንደወጠጠ

አንድ ጋር የሆንነዉ ፤ ድሉን አግኝተናል

ከደጃፍ የቀሩት ፤ ሰላም ነስተዉናል፡፡



**ዛሬ**

ለነገሩ ......

እኛስ የገባነዉ ፤ መች ተስማማንልሽ

በእኔ ልወቅልህ ፤ በእኔ ልወቅልሽ

ተምረን ተመርቀን ፤ ሳናዉቅ አዉቀንልሽ

ሁሉም ተናጋሪ ፤ ጠፍቶ የሚሰማሽ

ጠናብሽ ህመምሽ ፤ መች ይሆን መዳኛሽ፡፡

# 7.7 አየዋለሁኝ

ሀሳብ ሀሳብን ፤ ጥሎ ሲሸረዉ

ካርድ ጠብመንጃን ፤ ሲያሽቀነጥረዉ

ዝምድና ወድቆ ፤ ከህሎት ሲልቀዉ

ብሄረኝነት ፤ ገደል ሲገባ

በሰላም ወጥተን ፤ ሰላም ስንገባ

የራበዉ በልቶ ፤ ፊቱ ሲፈካ

ጨለማዉ ነግቶ ፤ ብርሀን ሲተካ

እዉነት ስትነግስ ፤ ሚዛን ሲደፋ

ሀገሬዉ ሁሉ ፤ ሆዱ ሲሰፋ

ህሊና ቆሞ ፤ ልኬት ሲለካ

ወንድም ወንድሙን ፤ ሲሾም ሲተካ

የእናታችን ፤ ክብሯ ሲመለስ

ቅንነት ሞልቶ ፤ ደግነት ሲፈስ

ጊዜዉ ቢረዝም ፤ ቢርቅም ከቶ

ህሊና ያጣዉ ፤ ህሊና ገዝቶ

አየዋለሁኝ ፤ ድህነት ሞቶ

አየዋለሁኝ ፤ ከንቱነት ጠፍቶ

አየዋለሁኝ ፤ ወገኔ ኮርቶ

አየዋለሁኝ ፤ አንድነት በርቶ ፡፡



" ጊዜን ጊዜ ሲሸረዉ ፤ የማናየዉ የማንሰማዉ ነገር ይኖር ይሆን ? "

# 7.8 ከመምጣት አልቀርም

የዳሽን ተራራ ፤ ልቤን ቢያደክመኝም
የጓሳ ቁር እጄን ፤ ቢቆራርጠኝም
የሶፍ ዑመር ዋሻ ፤ ዉበቱ ቢያፈዝም
የኤርታሌን ሙቀት ፤ መቋቋም ቢከብድም
አባይን መሻገር ፤ ጉልበትን ቢያርድም
ምን መንገድ ቢያስፈራ ፤ እንደ ሊማሊሞ
ከመምጣት አልቀርም ፤ ልቤ በአንቺ ታሞ፡፡

ፋሲልን ሳይጠግብ ፤ ላሊበላን አይቶ
አክሱም ደረስ ብሎ ፤ አልነጃሺም ወጥቶ
ከታች ወረድ ብሎ ፤ ኮንሶንም ጎብኝቶ
መሄድ እንኳን ቢከብድ ፤ ይሄን ሁሉ ትቶ
ከመምጣት አልቀርም ፤ ቀኑ ቢመሽ ነግቶ ፡፡

የሀረር ጅብ መጥቶ ፤ ካፊ ላይ ቢቀማኝ
ጭላዳ ዝንጀሮ ፤ ደረቱን ገልብጦ ቢንጎማለልብኝ
ዋልያ ተኩራርቶ ፤ ቀንዱ ቢያስፈራኝም
ቀይ ቀበሮ ሸሽታ ፤ ዉበቷን አንዳላይ ብትከለክለኝም
ያ የሜዳ አህያ ፤ ዘሎ ቢረግጠኝም
መንፈሴ ጠንካራ ፤ ዉስጤም ፅኑ ነዉ
ከመምጣት አልቀርም ፤ ልቤን እመኘዉ፡፡

እስኪ ምኑን ይዤ ፤ ምኑን ልተወዉ
የሄድኩበት ሁሉ ፤ በጣም ደግ ነዉ
ከኦሮሞዉ ገንፎ ፤ ትግሬ ጥህሎዉን
ከደቡቤ ቆጮ ፤ አማራዉ ጠላዉን
ይዞልኝ ቢመጣ ፤ መምረጡ ተስኖኝ



ሁሉንም ከትቼ ፤ ቁንጣን ቢይዘኝም

እግሬ ግን ጀምሯል ፤ መንገዳገዱን

ቁልቁለትቱን ወርዶ ፤ ወጥቶ አቀበቱን

ምን መንገድ ቢያስፈራ ፤ እንደ ሊማሊሞ

ከመምጣት አልቀርም ፤ ልቤ በአንቺ ታሞ፡፡

" ምን መንገድ ቢያስፈራ ፤ እንደ ሊማሊሞ … ! "

# 7.9 ካሸካከምህ

ስማኝማ ወንድም ፤ ስማኝ ልምከርህ
ኑሮን አታማርረዉ ፤ ምንም ቢከብድህ
ችግሩ ይሆናል  ካሸካከምህ፡፡



ሁሉም ጫና አለበት ፤ የኑሮ ፈተና
ይዞት የሚዞረዉ ፤ ብሎ ደፋ ቀና፡፡
በእርግጥ ይለያያል ፤ የኑሮ ክብደቱ
እንደ ፍላጎቱ ፤ እንደ እየ ትልምቱ፡፡

ያተ ግን ከታየህ ፤ እጅጉኑ ገዝፎ
የሚጥልህ ከሆነ ፤ ጉልበት አዝለፍልፎ
ለይተህ እወቀዉ ፤ መጀመሪያ አቅምህን
ከዚያም  አስተካክለዉ ፤ አሸካከምህን፡፡
ብለኸዉ ብለኸዉ ፤ ካልሆነ ነገሩ
ሳይሻል አይቀርም ፤ ፈትቶ መቋጠሩ፡፡

" አንተም ከከበደህ ፤ አዉርደህ ተሸከም ወንድሜ ! "

# 7.10 በግማሽ ልደመር

ተደመር ተብዬ ፤ ስለመን ስንተት
ነገሩ አስቆኝ ፤ ስስቅ ስዘባበት
ከቁብም ሳልቆጠረዉ ፤ ስዞር ስቀናጣ
መደመር አምርሮ ፤ አይኑን ገልጦ መጣ፡፡



ስንት አይነት ዳንኪራ ፤ እንዳልወረድንበት
አደባባይ ሁሉ ፤ ሰልፍ ቢበዛበት
አፋን እንዳልዘጋሁ ፤ ስንቱን ጋዜጠኛ
ዛሬ አፍ አዉጥቶ ፤ አለኝ አላስተኛ
መቆም መቀመጡ ፤ በቅጡ ቢሳነኝ
ከሰዉ ተማክሬ ፤ ልደመር ወሰንኩኝ፡፡

ተዉ እንጂ ....

ኧረ እንዴትስ ሆኖ ፤ እንዴት ልደመር
መቀነሱ እኮ ነዉ ፤ ስንት ዓመት ለፍቼ ያገኘሁት ብር
መናዱ አይቀርም ፤ የነበረኝ ሁሉ ያየጥንቱ ክብር
ሰዎች ይንቁኛል ፤ በድሮ ስራዬ በጎሳ በዘር
ይህ ሁሉ አስፈርቶኝ ፤ ቆምኩ እንጂ ከበር
እኔ መች አስጠላኝ ፤ ከእናንተ ጋር ሆኖ አብሮ መደመር ፡፡

እኔን ስትጠይቁ ፤ እኔን ስትፈልጉ
ብሸሸዉ ብደበቅ ፤በየሸንተረሩ በየጥጋጥጉ
አልቻልኩም መሰወር ፤ ከእናንተ እይታ
ይሄዉ መጥቻለሁ ፤ ቢበዛ አቤቱታ፡፡

ሰዎች መላ አጣሁኝ ፤ መፍትሄ ስጡኝ
የማደርገዉ ጠፋኝ ፤ ግራ እየገባኝ
ጠዋት ተነስቼ ፤ እየተደመርኩኝ
ከሰዓት በኋላ ፤ እቀነሳለሁኝ ፡፡

እንዲሁ እንደባተትኩ ፤ ሜዳ ላይ እንዳልቀር
ከስልጣኔም ሳልወርድ ፤ ከሀብቴም ሳልከስር
ይቅር ብላችሁኝ ፤ አርጋችሁ ትብብር
ሰዎች ፍቀዱልኝ ፤ በግማሽ ልደመር፡፡

“ በቃ ስንደመር እና ስንቀነስ እየተጣፋ ዜሮ ላይ ቁጭ ሆነ ነገሩ ! ”

# 7.11 ይድረስ ለአፍሪካ ፖለቲካ

እንዴት ቀኑን ዉለሽ ፤ እንዴትስ አድረሻል

ማንንስ አዉርደሽ ፤ ማንን አዉጥተሻል

አየሁኝ ሰማሁኝ ፤ በጠና ታመሻል

ማገገም አልቻልሽም ፤ መካሪ አጥተሻል፡፡

ምርጫ ካርድ አድለሽ

ኮሮጆ ቀይረሽ

ስታገባድጂ ፤ ድራማ ከዉነሽ

ዝሆኖችሽ ታግለዉ ፤ ከነጭፍሮቻቸዉ

አቅም ያነሰዉን ፤ ደቁሰዉ ገንድሰዉ

የወረደዉ ወጥቶ ፤ የወጣዉ ወርዶብሽ

ጥይት ተተኩሶ ፤ ቦንብ ፈነድቶብሽ

የልጆችሽን ደም ፤ በጆግ ጨልጠሻል

አጥንታቸዉንም ፤ ጨርሰሽ ግጠሻል

አየሁኝ ሰማሁኝ ፤ በጠና ታመሻል

ልጠጋሽ ብፈልግ ፤ ፀባይሽ ገፍቶኛል

ፈጣሪ ይሁንሽ ፤ እኔስ እርቄያለዉ

አደብ ስትገዢ ፤ እጠይቅሻለሁ፡፡




" አይ አፍሪካ እና ምርጫ ፤ ከምናስመስል ቢቀርብንስ ? "

# 7.12 ድግሱ

ሰዎች ተመራረጡ

ገንዘብ ከባንክ አወጡ ፡፡

አስቤዛዉ ተሸማመተ

ስጋዉ ተበላለተ

ቀይ ወጡም ተወጠወጠ

ቁርጡም ተቆራረጠ

ሽሮዉ ተንደከደከ

አልጫዉ ተንተከተከ

እንጀራዉም ተጋገረ

በላይ በላዩ ተነባበረ

ጠላዉ ተጠማመቀ

ዝግጅቱም ተጠናቀቀ፡፡




ድግሱም ተጀመረ

የሰዉ መዓት ተከመረ

አዘጋጆቹም ተደናገጡ

እንጀራዉ በዝቶ ፤ አለቀ ወጡ

ወዲያዉ በድንገት ፤ ተጠርተዉ ወጡ ፡፡

አጀንዳ ተይዞ ፤ ጉዳዩ ሲጣራ

እነ አግበስብሰዉ ፤ እነ ሞት አይፈራ

አዘጋጅ ነን ብለዉ ፤ ድግሱን ደግሰዉ

ከገዙት ሸቀጥ ላይ ፤ ቆንጥረዉ ቆንጥረዉ

ይሄን አርገዉ እንኳን ፤ አልበቃ ቢላቸዉ

ቀይ ወጡን ፡ ስጋዉን ፤ ለእነርሱ አስቀርተዉ

ለመጣዉ ሰዉ ሁሉ ፤ አልጫ አበሏቸዉ ፡፡

" እጅዎትን ይታጠቡ ፤ ርቀትዎን ይጠብቁ ፤ ከሙስና ራስዎን ይከላከሉ ! "

# 7.13 ድብብቆሽ



ስጠራሽ ሳትሰሚ ፤ ጠርተሽኝ ሳልሰማሽ

ፈልገሽ ጠፍቼሽ ፤ ፈልጌ እያጣሁሽ

ሳትጠሊኝ ጠልተሽኝ ፤ ሳልጠላሽ ጠልቼሽ

አስሬ ስፈታሽ ፤ ሳስታዉስ ስረሳሽ

አገኘሁሽ ብዬ ፤ ጨብጬ ስለቅሽ

አልሜ ተኩሼ ፤ ለጥቂት ስስትሽ

ስቀርብሽ ርቀሽ ፤ ስትቀርቢኝ ርቄሽ

የእኔ እና አንቺ ነገር

ሆነ ድብብቆሽ፡፡

" አኩኩሉ … ነግቷል ፤ ጨዋታዉ ፈረሰ … ዳቦዉ ተቆረሰ ! "

# ዋቢ መዛግብት

1. ዝጎራ - በዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ
2. የሀበሻ ጀብዱ - በአዶልፍ ፓርለሳክ ተፅፎ በተጫነ ጆብሬ መኮንን የተተረጎመ
3. You Can win – በሺ.ቭ ኬራ
4. ተጨማሪ ገላጭ ምስሎችን ከPixbay እና freepik ተጠቅመናል፡፡
5. እና ሌሎችም ...

“ ሠናይ ሠናዩን ያሰማን ፤ ሰላም ለኢትዮጵያ ! ”